# የተከፋፈለ ልብ

# ማ ው ጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| የአበራ ሃሳብ | 5 |
| የተከፋፈለ ልብ | 65 |
| በልሁ ቺስታው | 82 |
| መና የቀረ ህይወት | 97 |
| በሽተኛው | 116 |
| የሱራፌል እጣ | 135 |
| የመጀመሪያው መሰናክል | 158 |

# የአበራ ሃሳብ

ታዴዎስ ምትኩ ከዋናው አውራ ጎዳና ተገንጥላ እንደ እባብ እየተጥመለመለች ወደ መንደሩ የምትወስደውን መንገድ ተከትሎ በችኮላ ተራመደና ከአንዲት ቤት አጠገብ ሲደርስ ፣ ግራና ቀኝ ደግሞም ወደ ኋላ ገልመጥ ገልመጥ ብሎ ተመለከተ ። በአካባቢው የሚታይ ሰው አልነበረም ። በመንደሩ ላይ በሚያፏጨው የጥቅምት ነፋስ ውስጥ የከተማው ቱማታ ከሩቅ ይሰማል ።

ታዴዎስ ከትንሿ ቤት በራፍ ሲደርስ በሩን ደጋግሞ አንኳኳው ። በጣም ቸኩሏል ። ካልመሸ በስተቀር እዚያ አካባቢ አይታይም ። ቤቱ ከጭቃ የተሰራ ሆኖ፣ ከውጪ በኩል ግድግዳው እሸዋ ግርፍ ነው ። ከፊት ለፊት ያሉት ሁለቱ ተካፋች መስኮቶች ተዘግተዋል ። ከበሩ ግራና ቀኝ ደረጃው ላይ የጠወለጉ ሃረጎች፣ ባአሮጌ ቆርቆሮ ከተሰራው የእበባ መያዣ ውስጥ ሆነው፣ እንገቶቻቸውን ዘንበል ዘንበል አድርገው በትካዜ የቆሙ ይመስላሉ ።

ታዴዎስ እንደ ተለመደው በሩን ደጋግሞ ሲያን ኳኳው ፣ ከተዘጋው ቤት ውስጥ እየቀረበ የሚመጣ የሰው ኮቴ ተሰማና በሩ በዝግታ ተከፈተ ። አበራ ነበር የከ ፈተው ። ታዴዎስ ቀጭንና ረጅም ሰውነቱን ገርበብ ባለው በር አሾልኮ ጥልቅ አለና በሩ ተመልሶ ተከረቸመ ።

ቁመቱ አጠር ያለ ሆኖ ፣ በደንብ የተገነባ ሰውነት ያለው ነው—አበራ ። ያለፈው ጊዜና የስቆቃ ህይወቱ

ማረሻ ጥልቅና ረጃጅም በሆኑ መስመሮች ፡ ዱካውን መዝግቦ ያለፈበት ግንባሩ ሰፊ ነው ። ጭንቅላቱ ተለቅ ያለ ሆኖ ፡ ከፊት ለፊቱ በኩል በራው ዘልቆ የገባ ነው ። የደፈረሱት አይኖቹ ቅዶች ጠባቦች ቢሆኑም ፡ ትኩር ብለው ሲመለከቱ የሚረብሹ አይነቶች ናቸው ። ብዙ ያዩ አይኖች ። ክፉና ደጉ ሁሉ እላያቸው ላይ የታተመ ባቸው የሚመስሉ አይኖች. . .አጭርና ወፍራም አንገት ፡ ሰፊ ትከሻ ፡ ገልበጥ ያለ ሰፊ ደረት. . .ዘወትር ከሚለብ ሰው ካኪ ኮትና ሱሪ ጋር ሲመለከቱት ፡ አበራ በቅርቡ ወደ ከተማ የመጣ ገጠሬ እንጂ የከተማ ሰው አይመስልም ።

ያን ጊዜ ጫማ አያደርግም ነበር ። ለምን ጫማ እንደማያደርግ ሲጠየቅ መልሱ ያው ነበር ። "ሰራተኛው ህዝብ ቀን በሃሩር ፡ ሌት ደግሞ በቁር እየተንገላታ ለመ ዝባሪ ጌቶች ይገብራል ። በሩቅ ለሚያየው ፡ ነገር ግን ለማይጠቀምበት ምርት ፡ ላቡን ያንጠፈጥፋል ። ሀብቱን ጉልበቱንና ሞራሉን ገብሮ ጨርሷል ። በልቶ ያልጠገበ ፡ ጠጥቶ ያልረካ ፡ ለብሶ ያላማረበት በሚሊዮን የሚቆጠር ወገ ባለበት ሀገር የእኔ ጫማ መድንቀር ማንጥል ጌጥ ነው ። ማማሹን ተላጭታ ማማሹን ተሰርታ እንደሚባ ለው ተረት ነው. . ."

እንዳንዴ ደግሞ እንዲህ ይሉታል—ጓደኞቹ ።

"አበራ . . .ፈረንጆች እኮ በደንብ የሚለብስና ጫማ የሚያደርግ ሰው ነው የሚወዱት. . ."

"የቶቹ ፈረንጆች?" አበራ ይጠይቃል ።

"አሰሪዎቹ ።"

"የእነሱ ፍቅር በእፍንጫዬ ይውጣ ። ከመቼ ጀምሮ ነው ደግሞ ጌታ ሎሌውን የወደደው?"

"የማህበር መሪ ሆነህ እንዴት. . ."

"ሳይሰሩ በሰው ጉልበት የሚሽቀረቀሩትን እየኮ ነንን እንዴት ይሆናል? ሁላችንም ጫማ ማድረግ ስን ችል ያን ጊዜ እኔም አደርጋለሁ . . .አብረን እናጌጣ ለን. . ." የዋህነት አይደለም ።

ይሄው ነበር የዘወትር መልሱ ። ጫማ አጥቶ አል ነበረም ። ለይስሙላም አይደለም ። እምነቱ እምቢ አለው ። በቃ ።

አበራ በሩን መልሶ ዘግቶ ፣ እንደ ተቆነጠጠ ልጅ በሚያለቅሰው አሮጌው ጣውላ ላይ በእርጋታ ተራመደና ከቤቱ በአንደኛው ማእዘን በኩል ከቆመው ጠረጴዛ አጠገብ ሲደርስ ወንበሩን ስቦ ተቀመጠ ። ታዴዎስም ሰላምታ ከሰጠው በኋላ ተከትሎት ሄደና ከጠረጴዛው አጠገብ ግድግዳውን ተደግፎ ቆሞ ፣ አንዲት ሲጋራ ከቅጠለ ወርቅ ፓኬት ውስጥ መዞ አወጣና አቀጣጠለ ። መልከም ሰልካካ ፊቱ ላይ አሁንም የብስጭት ስሜት እንደ ታተመበት ነበር ። አገጩ ላይ የሶስት ቀን ፂም አቀምቅሟል ።

ከአንድ ጠረጴዛና ከሶስት ወንበሮች በስተቀር ቤቱ ውስጥ ሌላ እቃ የለም ። ከቤቱ ጣሪያ መሃል በቀጭን የኤሌክትሪክ ሽቦ ጫፍ ላይ የተንጠለጠለችው ባለ አርባ ሻማ አምፑል ፣ በጉም እንደ ተሸፈነች ፀሀይ ቤቱ ውስጥ የደበዘዘ ብርሃን ፈንጥቃበታለች ።

"ተቀመጥ ታዴዎስ . . .ይቅርታ አንድ ጊዜ ይቺን ያብዳቤ አርቅቄ ልጨርስ . . .ለጥጥ ፋብሪካ ሰዎች ፣ ድሬዳዋ የሚላክ ነው. . ." አለ አበራ ፣ ጠረጴዛው ላይ አጎንብሶ በችኮላ እየፃፈ ።

ታዴዎስ ቸኩሏል ። ከሲጋራው አከታትሎ ይስብ ለታል ። ወና ወና በሚሸተው የቤቱ አየር ውስጥ ፣ የሲ

ጋራው ጭስ እንደ ክር እየተጥመለመለ በቀጭኑ ወደ ጣሪያው ይንዛል ።

"ጊዜ የሚሰጥ አይደለም ፣ አበራ" አለ ታደዎስ ። አበራን በሰያፍ እያየው ። አበራ ከሚፅፍበት ወረቀት ላይ አይኖቹን መለሰና ታደዎስን ትኩር ብሎ ተመለከተው ።

"ክትትሉ እንደ ቀጠለ ነው" አለ ታደዎስ ። "የማህበሩ መቋቋም የጊ ግር ውስጥ እሳት ነው የሆነባ ቸው ። የሆነ ያልሆነውን እያስወሩ ነው ። በአዲሱ ማህ በር ውስጥ የእነሱን ሰዎች ሳያስገቡ አልቀሩም ። በተ ለይ ጉልማ ቀን ቀን ከሰራተኛው ጋር ተደባልቆ እንደ ሚውልና ሲመሽ ግን ከእነዚያ አውሬዎች ጋር እንደ ሚዶልት ታውቋል ። ከፈለክ ማስረጃ አለኝ ። ያም ሆነ ይህ ፣ በተለይ አንተ ላይ ስላተኮሩ ፣ እስኪ ለማንኛውም ጠንቀቅ በል ። ጉልማ ግን . . .የፈለከውን በለኝ እንጂ የወጣለት ይሁዳ መሆኑን ደርሰንበታል ። አብሯቸው እያሰረ ነው ።"

አበራ አይኖቹን ደበልጥ አጥብቦ ታደዎስን ተመ ለከተው ። መንጋጋው ይንቃንቃል ። ይሄው ነው አበራ ። አንድ ነገር በጥልቅ ሲያሳስበው ጥርሶቹን ደጋግሞ ይነክሳቸዋል ። በዚህን ጊዜ ነበር መንጋጋው የሚንቃነ ቀው ። የሚያስበው ነገር ከመንጋጋው ጋር ሃይለኛ በሆነ የስሜት አውታር የተቆራኘ ይመስላል ።

"እንዴት ማወቅ ቻልክ?" አለ አበራ ፣ በመጨረሻ እያንዳንዱ ቃል ላይ እየረገጠ ። ወፍራም ነው ድምፁ ።

"እነሱ እንደሚከታተሉን እኛም እንከታተላቸዋ ለን ። ታስታውስ እንደሆነ ባለፈው ጊዜ ስለ መረጃ አስፈላጊነት ተነጋግረን ነበር ። እና በተባባልነው መሰ

ረት ጠንክር ጠንክር ያሉትን የእኛን ሰዎች በተለያየ አቅጣጫ አሰማርተናል ። የጉልማን እንቅስቃሴ በትሰይ ነው የምንከታተለው” አለ ታዴዎስ ፡ ወንበሩን ስቦ ጠረጴዛው ላይ በክንዱ እየተደገፈ ።

“ማነው ያየው ? የት ነው የታየው ? ምን ሲያደርግ?” አበራ አከታትሎ ጠየቀ ፡ ሲፅፍበት የነበረውን ኖአር ድንጎት ጠረጴዛው ላይ ወርውሮ ። ፎሽ ነው አበራ ፣ ለአንድ ነገር አንድ ጥያቄ በፍፁም አያረካውም ። እን ዴት? ለምን? መቼ? . . ሁሉን ማወቅ ይፈልጋል ።

“ታይቷል . . .በተደጋጋሚ ታይቷል” አለ ታዴ ዎስ ፣ ያለቀቸውን ሲጋራ ለመጨረሻ ጊዜ ምጥጥ አድ ርጎ ጭሱን ከሳበው በኋላ ፡ በረጅሙ ተንፍሶ መልሶ እያስወጣው ።

“ሲኖራ ቤት . . .ሲኖራ ቤት ሆኗል አሉ ፡ መኖሪ ያውም መደለቻውም ። ታውቀው የለም የዚያችን አር መን ቤት? አሁን በቅርብ እንኳን ከሙሴ ቫስኪንና ከእኛ እሰሪ ጋር ሲጠጣ ነበር አሉ ። ሁልጊዜ አዚያው ናቸው አሉ ። እና ፣ እንደምታውቀው ለመገናኛት አይደ ለም የሚገናኙት ። በግልፅ ሲያሴሩ ነበር ማለት ነው ። የተቋቋመውን ማህበር ለማፍረስ ፣ ሌሎች እንዳይመሰ ረቱ ለማድረግ ፣ ከስራ ለማባረር ፣ ለማስፈራራትና ለማ ሳሰር . . .ማን ያውቃል ከዚህም የከፋ ድግስ አዘጋጅ ተው ይሆናል” አለ ታዴዎስ ፡ ወለሉ ላይ የጣላትን የሲጋራ ቁራጭ በጫማው ጫፍ እሸት እያደረገ ።

አበራ አይኖቹን ፊት ለፊቱ ካለው ፡ ግራጫ ቀለም ከተቀባው ከቤቱ ግድግዳ ላይ ተክሎ ታዴዎስን ያዳ ምጠዋል ።

ለትንሽ ጊዜ በቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሰፈነ ።

"ታዲያ ምን መደረግ አለበት ትላለህ?" አለ አበራ፣ መልስ የሚፈልገትን አይኖቼን ወደ ታደዎስ መልሶ ።

"ጉልማ ይሁዳውና እሱን መሰሎች ሁሉ ፣ ከአመራሩ ሳይውል ሳያድር የሚወገዱበት ዘዴ መፈለግ አለበት ። አለበለዚያ በስንት መከራ የተቋቋመው ማህበር እድሜው አጭር ይሆናል ። እነ ጉልማ ከአሰሪዎቹ የባሱ መርዘኞች ናቸው ። ሁለት እራስ ያላቸው እባቦች፤ ምንም ከማድረግ አይመለሱም ። በስልጣን ጥምና በሚያገኙት ጉርሻ ሰክረዋል ። አላማቸው በቅርቡ የሚቋቋመውን ኮንፈደሬሽን ለመቆጣጠር ነው ። እቅዳቸውን ማክሸፍ አለብን ። ሳይቀድሙን መቅደም አለብን ። እስስቶች ፤ እባቦች ። ጉልማ. . .ሴሎችም ። አበራ ፣ ያለንበት ጊዜ በጣም አስጊ ነው ፤ ወሳኝ ነው ። መውደቅ ወይም መጣል ። ይሄ ነው አማራጩ. . ."

"በቅርቡ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ይወጣል ይባላል ። የማይቀር ነው ። ፈቀዱም አልፈቀዱ ማህበሩን ከማቋቋም የሚያግደን ሃይል የለም ፣ በግድም በውድም ። እነሱም ቢሆኑ ከሁኑ ተርበድብደዋል ። ዛሬ እንዲህ የሆኑ ነገና ከነገ ወዲያ ምን ሊሆኑ ነው ። ገና ፣ ገና ምን ተይዞ ጉዞ ፤ ብዙ ትግል ይጠብቀናል ። ብዙ ታሪክ ይጠብቀናል ። ገና ብዙ ክፉና ደግ ጊዜ ከፊታችን ተደቅኗል ። እና ፣ ታደዎስ . እንዳልከው ለይሁዳዎች እንዘይድላቸዋለን ። ግዴለም ። ክንዳችንን ሳንንተራስ . . ብንሞትስ ፤ ሞት ምንድነው? ሞት ስራችንን አያሸንፈውም ። ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ይባላል ። ከነስማችን ነው የምንሞተው ። አሁን ስለ ሞት ማሰቢያ ጊዜ አይደለም ። ገና ብዙ ስራ ይጠብቀናል. . .ስመሆኑ ጉልማ ከነሙሴ ቫስኪን ጋር. . .ሲኖራ ቤት? ይገርማል!. . ."

አበራ እንደገና ማሰቡን ቀጠለ ፤ መንጋጋው ይኑቃ
ነቃል ። “የጉልማ ነገር እውነት ከሆነ አደገኛ ነው”
ይላል አበራ በሃሳቡ ። “በአንድ እራስ ሁለት ምላስ ።
አባቦች ናቸው ። ታዴዎስ እውነቱን ነው ። ቀን ሰው
ሌሊት አውሬ ። እንደዚህ ነው ጉሊማ ። ብቻውን አይ
ደለም ማለት ነው ጉልማ ፤ ብቻውን አይደለም ። የተደ
በቁ ወኪሎችም መኖር አለባቸው ። ስንት ምስጢር
ባክኗል ማለት ነው ። እየወሰደ ያቀብላቸዋል ፡ ለገንዙብ—
ለገንዘብ እራስን መሸጥ—ህሊናችን መሸጥ—ሰራተኛውን
መሸጥ ።”

“እንደምታውቀው ጉልማ ብቻውን አይደለም”
አለ ታዴዎስ ፡ የአበራን ሃሳብ አቋርጦ ፡ “ብቻውን አይ
ደለም ። ለጊዜው ሁሉንም ባናውቃቸው አሰሪዎቹ አብ
ረውት ናቸው ። ከማህበሩ ውስጥና ውጪም ወኪሎች
አያጡም ። በአሰሪዎች ጀርባ የመንግስት ተወካዮች
አሉ ። ከታህሳስ ወዲህ እነሱም የቆሰለ አውሬ ነው የሆ
ኑት ። ይህንንም ያንንም መንካከሳቸው አልቀረም ።
የታህሳስ ሁኔታ ሁሉን እንዲፈሩ ፡ ሁሉን እንዲጠረጥሩ
አድርጓቸዋል ። ተማሪውን ፡ ወታደሩን ፡ ሰራተኛውን ።
የሞተ ሰው ለምን ሰቀሉ? ወታደሩን ለማስፈራራት
ነበር ። “ሬሳ ሰቃዮች” እያለ አለም ሲዛበትባቸው ምንም
አልመሰላቸውም ። እንዳልከው ሞት አይቀርም ። ግን
የማይሞት ሞት መሞት አለብን ። ሁሉም ነገር እያደር
መጥራቱ አይቀርም ። ለማንኛውም አንተ ራስህን ጠብቅ ።
ሰው ከሰው የማይተማመንበት ጊዜ ነው ። የጥርጣሬና
የፍርሃት ጊዜ ነው ። ለመኖር ሲባል መጠርጠር ግዴታ
ነው ። አንተን ግን እስካሁን ኢላማ ሳያገቡህ አይቀ
ርም…” አለና ታዴዎስ ፡ ሌላ ሲጋራ አውጥቶ አቀጣጠለ ።

"ልክ ነህ ታዴዎስ" አለ አበራ ፣ ድንገት ከተቀመጠበት ወንበር ተነስቶ ክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ ። ሁለት እጆቹን ኪሱ ውስጥ ጨምሮ መሬት መሬቱን ይመለከታል ። "መጠንቀቁ ይበጃል ። ለእኛ ሞት አይደለም የምንጨነቀው ። እኛ ብንሞትም የቀረውን ስራ ሌሎች ይሰሩታል ። በጅምሩ እንዳይቀጭ ግን መጠንቀቅ አለብን ። አጠቃላይ ማህበሩ ተቋቁሞ፡ ስራው ሁሉ መልክ መልክ ከያዘ በኋላ ብንሞት አይቆጭም ። አሁን ግን ሁሉ ነገር እንደ ተዝረከረከ ነው ። ይህች ቤት እንኳን ከታወቀች ምን ያህል ጉዳት እንደ ሚከተል ታውቀዋለህ ። ከዛሬ ጀምሮ የምስጢር መረጃ ሁሉ ሌላ ቦታ መደበቅ ይኖርበታል ። የብዙ ሰው ህይወት አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል ። እንዳልከው እርስ በእርስ መተማመኑ እስቸጋሪ እየሆነ ሄዷል ። ግን ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርምና ገና ለገና እነሱ አሰፍ ስፈዋል ብለን አንዲት ጋት እንኳን ወደ ኋላ አንልም ።"

አበራ በዝግታ እየተራመደ ከቤቱ መሃል ሲደርስ፡ ከአናቱ በላይ ከተንጠለጠለችው አምፑል ስር ቆመ ። ከሌላው የቤቱ ክፍል ሁሉ አበራ የቆመበት ቦታ የበለጠ ብርሃን አግኝቷል ። ታዴዎስ ከተቀመጠበት ሆኖ አበራን በአይኑ ይከተለዋል ።

"ና ወደዚህ ታዴዎስ. . ." አለ አበራ ድንገት ፣ በዚያው ጠንካራ ድምፅ ። ታዴዎስ ከተቀመጠበት ተነሳና አበራ አጠገብ ቆመ ።

"ታዴዎስ" አለ አበራ ፣ እንደገና ። ታዴዎስ ቀና ብሎ አበራን ተመለከተው ። ሁለቱም መልክ ላይ ብርሃን ፍንትው ብሎበታል ። "ታዴዎስ. . .በዚህ ፀማያስ ተማምን ውቅት ለመጨረሻ ጊዜ ቃል ኪዳን እንግባ ።

እኔ በቃል ኪዳን አምናለሁ ። ከሰው እንድበት በሚወጣው ቃል አምናለሁ ። ቃሉን ጠበቀም አልጠበቀም በኋላ የሚታይ ነገር ነው ። ለጊዜውም ቢሆን እመነኝ አምንሃለሁ መባባሉ ወኔ ይሰጣል ፤ ያደፋፍራል ፤ ያስተማምናል . . . ላልከዳህ ላትከዳኝ ፤ ሰራተኛውን ላንከዳው፤ ከእሱ ቀድመን የሚመጣውን ሁሉ ልንመክት . . . ወኅሁን አሻግረን ፡ ባህሩን አቋርጠን ፡ ከረሃብ እስር እስፈትተን ፡ እንደ ውሻ ሳይሆን እንደ ሰው ወደ ሚኖርበት ወደብ ልናደርሰው. . . ቃል ኪዳን እንግባ ። ይህ ካልሆነ ግን ተንበርክከን ሳይሆን ቆመን ልንሞት ቃል እንግባ...”

በሁለቱ ሰዎች መካከል ለጥቂት ሴኮንዶች ፀጥታ ሰፈነ ። ተራ ፀጥታ አልነበረም ። ሁለቱም ቃል ኪዳኑን ያሰላስሉ ነበር ። በምን አይነት ሃይለ ቃል ፡ ቃል ኪዳናቸውን ያፅኑ? ይሄ ነበር ያስጨነቃቸው ።

“አንተ አንጋፋ ነህ አበራ. . . አንተ ቃሉን ንገረኝ። እኔ ከአንተ እየተቀበልኩ እደግመዋለሁ” አለ ታዴዎስ ፡ አበራን ቀና ብሎ እየተመለከተው ።

እላመነታም ። አበራ ግንባሩን አኮሳትሮ ፡ የቀኝ እጁን ቁልቁል እንደ ዘረጋ ቡጢውን ጨብጦ ቃሉን ተወጣው ።

“ሰራተኛውን ብከዳ ፡ የሚያምኑኝን ጓደኞቼን ብከዳ፡ በሰራተኛው ለመጣ ነገር እንዲት ጋት እንኳን ወደ ኋላ ብል ፡ በጊዜያዊ ጥቅም ብደለል. . . እውነት ትክዳኝ ። ህይወቴ በሙሉ እንደዚህ ምሽት የጨለመ ይሁን ፤ ቀኑ ይጨልምብኝ ! ”

ታዴዎስ የራሱን ቃላት ጨምሮ ቃል ኪዳኑን ደገመው ። ድምፃቸው በዘይት ቤት ውስጥ ተራ በተራ አስተጋባ ። ማንም ምስክር አልነበረም ። ከእናታቸው በላይ የምትበራዋ ብርሃን ብቻ ነበረች — ምስክራቸው ።

አበራ ቀና ብሎ ታደሰን ተመለከተውና ፈገግ ብሎ እጁን ዘረጋ ። ጥርሶቹ ችርችም ብለው የበቀሉና ያልበሰዙ ነበሩ ። ታደሰም ፈገግ ብሎ እጁን ዘረጋ ። ፈገግ ሲል አገጩ፡ መሃል ሰርጎድ ይልና መልኩ ይበልጥ ደስ ይላል ። ከዚያም ተጨባበጡ ። አካባቢው በጨለማና በፀጥታ እንደ ተዋጠ ነው ። ትንሽ ቆይተው ፡ መጀመሪያ ታደሰ ከቤቱ ወጥቶ ሄደ ። ከዚያም ጥቂት ቆይቶ አበራ ተከተለውና ሁለቱ ሰዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች ከድድቅ ጨለማው ውስጥ ገብተው ተሰወሩ ።

በዋናው አውራ መንገድ አድርጎ ወደ መኖሪያ ቤቱ የምትወስደውን የእግር መንገድ ተከትሎ ፡ እቤቱ አካባቢ እስኪደርስ ድረስ ብዙ ነገር ያስብ ነበር ። ታደሰ የነገረውን ሁሉ መልሶ መላልሶ ያሰላስላል ። ስለ ይሁዳው ጉልማ ያስባል ። ስለ ማህበሩ ያስባል ። ስለ ታደሰ ያስባል ። ስለ ቃልኪዳኑ ያስባል ። እስካሁን ስለ ተሰራው፡ ወደ ፊት ስለሚሰራው ያስባል ።

"ወሳኝ ጊዜ ላይ ነው የደረስነው" ይላል በሃሳቡ ። "ቢሆንም የመጣው ይመጣል እንጂ ወደ ኋላ ማለት የለም ። አዎን ፡ ሳይቀድሙን መቅደም አለብን ። ሌሎች ማህበሮች መቋቋም አለባቸው ። እናም ፡ የምስጢር ቤታችን መታወቅ የለበትም ። ብዙ መረጃዎች አሉበት ። አባሎችን የሚመለከት ፣ ማህበሩን የሚመለከት . . . እንደ ተሰበሰብን ቢያፍስንስ ፣ አደጋ ነው . . . "

ከዚያም ወደ ቤቱ እየቀረበ ሲሄድ ሃሳቡ ወደዚያው ተመለሰ ።

"ብዙነሽ እንዴት ሆና ይሆን?" አለ አበራ ፣ በሃሳቡ ። "አራስ ነች ። ስስተኛው ልጅ ። ይሁን እስቢ ካለነሱ ምን ተስፋ አለን ። አዎን ፡ ተስፋችን ናቸው—

ልጆቻችን ። እንደ ምንም ብለን ካሳደግናቸው አንድ ቀን በተራቸው እነሱም እኛን ይተኩን ይሆናል—ማን ያውቃል ። እኛ ብንሞትም ልጆቻችን አሉ ። የወለደ ሰው አይሞትም ፤ ስሙ አይሞትም ፤ ስራው አይሞትም . . . .”

እንደገና ሃሳቡ ወደ ሌላ አቅጣጫ አመራ ።

“አዎን ፤ ዘለአለም በሃብታሞች ፍላጎት እየተመራን ነው—የምንኖረው ። ስልጣን ወይንም ሀብት ባላቸው ሰዎች ፍላጎት እየተመራን ፤ በእነሱ ፍላጎት እንቀጠራለን ፤ እንባረራለን ፤ እንራባለን ። ልጆቻችን ይራባሉ . . . አሁን እንዲያው በሀገሩ ላይ ያለነው ሰራተኞች ሁሉ ፤ የየእቅማችንን ገንዘብ አዋጥተን ትልቅ የልማት ድርጅት ብናቋቁምስ ? አዎን ፤ ያለ አግባብ የሚባረሩት ወንድሞቻችን ከዚያ ሊቀጠሩ ይችሉ ነበር ። ልጆቻቸውም ከመራብና ከመቸገር ይድኑ ነበር ። ወላጆቻቸው ቢሞቱም እኛ እናሳድጋቸው ነበር . . . ”

“አዎን ፤ እንደዚህ አይነት ማህበር ያስፈልገናል ። እናቋቁማለን ። እሺ ፤ ሰሞኑን ምን ምን መስራት አለብን? አዎን ፤ ተጨማሪ ማህበሮች ማቋቋም . . . መዋጮ መሰብሰብ አለበት ። ታደዎስ እንዳለው የአሰሪዎችን ወኪሎች ለይተን ማወቅ አለብን ። ዋናው ማህበር ውስጥ አምልጠው መግባት የለባቸውም ። በፍፁም! አለበለዚያ እስከ ወዲያኛው ስንወቀስበት እንኖራለን . . . ይህ መሆን የለበትም—በምንም አይነት መሆን የለበትም . . . ”

በኮረኮንቹ መንገድ ላይ እየተደነቃቀፈ ወደ ቤቱ ቀና ደፋ ይላል ። ጨለማው አይን ቢወጉ አያሳይም ። ወደ ቤቱ ከምታስገባው መታጠፊያ መንገድ ላይ አንዲት መኪና ጨለማ ውስጥ ቆማለች ። የመኪናዋ የፊት መብራቶች ድንገት በሩ ።

"እሱ ነው . . . እየመጣ ነው" አለ ፤ ከሹፌሩ ጎን የተቀመጠው ሰውዬ ። ከዚያም የመኪናዋ የኋላ በር ተከፈተና ሁለት ሰዎች ዱብ ዱብ ብለው ወረዱ ። ምን እንደሚመስሉ ፤ ማን እንደሆኑ አይለዩም ። እየሮጠ አበራ አጠገብ ከደረሰ በኋላ ፤ አንደኛው ሰውዬ የያዘውን የእጅ ባትሪ ድንገት ቿ አድርጎ አበራ ፊት ላይ አበራበት ። አበራ ፊቱን በሁለት እጆቹ ሸፍኖ ወደ ፊቱ ሲሮጥ ፤ አንደኛው ሰውዬ ከፊቱ ቀደመና ፤ "ቁም! እንዳትነቃነቅ! ትበላሽህ!" አለ ። ወዲያውም የሽጉጡን መጠበቂያ አላቀቀና አፈሙዙን አበራ ሆድ ላይ አስደገፈው ።

ወደ ፊትም ወደ ኋላም መሄድ አልቻለም ። ሰዎቹንም መለየት አልቻለም ። የእጅ ባትሪው ብርሃን አሁንም ፊቱ ላይ ነው ። ምንም አልተናገረም ። እንደዚህ ዓይስበው ይሆናል ብሎ አልገመተም ነበር ። በአካባቢው ያሉት ውሾች ይጮሃሉ ። ወዲያው አጅበው ጨለማ ውስጥ ቆማ ወደ ምትጠብቀው መኪና ወሰዱት ። ድርጊቱ ሁለት ደቂቃዎች አልፈጀም ነበር ።

አበራ ከመሃል ፤ ሁለቱ ሰዎች ከግራና ከቀኝ አጅበውት ተቀምጠዋል ። የሽጉጡ አፈሙዝ ጎኑን ሲወጋው ይሰማዋል ። የመኪናዋ የውስጥ መብራት ጠፍቷል ። ሁሉም ዝም ብለዋል ። የመቃብር ያህል ዝምታ ።

መኪናዋ ከመቅፅበት ተንሳችና ጨለማውን በፊት መብራቶቿ እየቀደደች ፤ በኮረኮንቹ መንገድ ላይና ታች እየነጠረች ከዋናው አውራ ጎዳና ገብታ ነጎደች!

— 2 —

"እንዳልኳችሁ አደገኛ ሰው ነው ። ብዙ ግዜ አብረን ሰርተናል ። እንደ እጁ መዳፍ ነው—የማውቀው" አለ ጉልማ ፣ በእጁ የያዘውን ብርጭቆ ወደ አፉ ብሎ የቀረውን ውስኪ በአንድ ትንፋሽ ከጨለጠ በኋላ ። ከዚያም በሃሳቡ የሚታየውን ሰው በእርግጫ ይመታ ይመስል ፣ ቀጭንና ረጅም ቅልጥሙን በአየር ላይ አወናጭፎ ግራ እግሩ ላይ ደረበው ። የጉልበቱ መጋጠሚያ ተንቋጨ ። የንስር ምንቃር የሚመስለውን አፍንጫውን ፣ በረጃጅሙ አጥንታም ጣቶቹ አሸት አሸት አደረገና ሚጥሚጣ በሚመስሉት ትናንሽና ቀንጭቃጫ አይኖቹ ፣ ባዶውን ብርጭቆ ትኩር ብሎ ተመለከተው ። እንደ ሾተል የሳሱት ከንፈሮቹ ፣ ጭንቅላቱ ውስጥ እንደ ጉንዳን የሚርመሰመሰውን ሃሳብ ከራስ ቅሉ ወጥቶ ወደ ውጪ እንዳይፈስ የሚያግዱት ይመስል ከርችም ብለዋል ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ስለ አበራ አሰበ ። ያ የሚጠላውና የሚፈራው መልክ በአይኑ ህሊናው ታየው—ባለፈው ስብሰባ አብረው አንድ ክፍል ውስጥ እንደ ተቀመጡ ። ከዚያም የአበራ ድምፅ ጆሮው ውስጥ ጮኸበት ፣ "...አንዲት ጋት እንኳን ወደ ኋላ አንመለስም! የመጣው ቢመጣ...አንዲት ጋት ፣ አንዲት...አንዲት!" ከሩቅ እንደሚሰማ የገደል ማሚቱ ድምፅ ነበር ።

ጉልማ የአበራን ምስል ከህሊናው ሰሌዳ ላይ ለማጥፋት ይመስል ፣ አይኖቹን ጭፍን ክድን አደረገና በረጅሙ ተነፈሰ ። ከዚያም ፣ "በቅርቡ ይለይልናል!" አለ በሃሳቡ ፣ "ወይ እኔ ወይ እሱ...ይለይልናል!" ከዚያም አይኖቹን አጠገቡ ወደ ተቀመጡት ሰዎች መለሳቸው ።

የሻምበል አጥላባቸው ሰውነት ሊፈርስ የደረሰ ጎታ ይመስላል ። በሰውነቱ ልክ የተሰራ ከሚመስለው ፎቴ ወንበር ውስጥ በጀርባው ተለጥጦ ፣ አንድ ጊዜ በረጅሙ ስቦ መልሶ በሚያወጣው የሲጋራ ጢስ ቀለ በት እየሰራ ወደ ጣሪያው ይወረውረውና የጢሱ ቀለበት ሽቅብ ሄዶ ሄዶ አየር ውስጥ ሲበተን ፣ አይኖቹን በልጥጦ ያየዋል ። እንደገና ጠባብና ወፍራም የጢስ ቀለበቶችን ያስወጣል ። ጥቂቶቹ ከጣሪያው ደርሰው ይጋጩና ይበ ተናሉ ። አጥላባቸው ደስ ይለዋል ።

ሙሴ በጎሲያንም ቢሆን የግንድ ጉማጅ የሚያክ ለውን ቡናማ ሲጋራ ፣ በመቃ የተነፋ በሚመስሉት ጣቶቹ ይዞ ፣ በሌላው እጁ መዳፍ ፣ ስስ ሆኖ እንደ ሲጋራ ወረ ቀት የሚያብረቀርቀውን ቡናማ ፀጉሩን አሁንም አሁ ንም ወደ ኋላ ይዳምጠዋል ።

ጉልማ ከተደገፈበት ፎቴ ወንበር ቀና አለና ከወ ገቡ ለሁለት ታጥፎ ፣ የውስኪውን ጠርሙስ አንገት ጨመደደና ከጠረጴዛ ላይ አንስቶ በሃይል ሲዘቀዝቀው ከብርጭቆው ከንፈር ጋር ተላተመና መጠጡ ተንቆረቆረ። ከዚያም ቀጭን ሻይ የሚመስለውን ፈሳሽ የያዘውን ብርጭቆ ትክ ብሎ በፍቅር አይን ተመለከተው ።

"እና ፣ እንዳልኳችሁ አደገኛ ነው ። ለብዙ ጊዜ አውቀዋለሁ ። ተፈጥሮው እራሱ ደስ አይልም ። ሁሉ ነገሩ ለብጥብጥ የተሰራ ነው የሚመስለው ። ተው ቢሉት የሚሰማ አይነት አይደለም ። ሃብታም በአይኔ አልይ ባይ ነው ። አቅም ቢኖረውማ በቃ. . .የሚሰራበትን ድርጅት እንኳን ከባለቤቱ ነጥቆ ለሰራተኞች ከመስጠት አይመ ለስም ። ምቀኝነት ነው እንዳይባል ፣ ለራሱ ምንም አይፈ ልግም ። ጫማ እንኳን ማድረግ የማይፈልግ ሰው ምን

ትሉታላችሁ ። እራሱን እየጣለ ፡ ለሌላው እሚጨነቅ የሚል ሰው ምን ይባላል? እንደዚህ አይነት ሰው አደገኛ ነው ። ለምንም ለማንም አይተኛም ። ማህበር የሚባል አማርኛ ከጥንቱ ከጠዋቱ ያመነጨው እሱው እራሱ ነው ። ቃጫ ፋብሪካን እንደዚያ ሲያጦክ ቆየ ። አሁን ደግሞ የሙሴ ቫስኪንን ቤት እያረበሸ ነው!!”

“አዲሱ አዋጅስ? . . እ . . ምን ይላል? ምናልባት በዚያ በኩል መፍትሄ ይገኝ እንደሆን. . .” ሙሴ በጎሲያን ፡ ጉልማን አቋረጠና ጠየቀ ። ጉልማ ጥያቄውን አላስጨረሰውም ። የፈረንጁ ሃሳብ ወዴት እንደሚሄድ አስቀድሞ የተረዳ ይመስላል ። እሱም በተራው ሙሴ በጎሲያንን አቋረጠና መናገር ቀጠለ ።

“የአሰሪና የሰራተኛ አዋጅ ቢታወጅም እንዳልኳችሁ አንቀፅ 22 አ. . . አዎን ፡ አንቀፅ 22 ነው. . . ማህበራቱ በፖለቲካ ስራ እንዳይካፈሉ ይከለክላል ። ግን እነአበራ ይህንን እሺ ብለው የሚቀበሉ ይመስላችኋል? በፍፁም አይቀበሉም! ሙሴ ቫስኪን የሚሉት እንደገባኝ ፡ አዋጁ ይገድባቸዋል ነው. . . እነሱ ግን አዋጁን ከቁም ነገር አይቆጥሩትም ። የእነሱ ሃሳብ ትልቅ ነው፤ ልባቸው ትልቅ ነው. . .እኔ በደንብ አውቃቸዋለሁ ።”

“እሺ, ልትግባቡ አትችሉም ማለት ነው? ማግባባት አይቻልም? ለምሳሌ ገንዘብ ብንሰጠው ። ወይም ጉርሻ ፤ ወይም. . .የፈለገውን ። የፈለገውን እናደርግለታለን ።”

ጉልማ ሙሴ በጎሲያንን እንደገና አቋረጠውና በአይኑ ከገረመመው በኋላ ድምፁን ከፍ አድርጎ ቀጠለ ።

“ማህበሩ ለሁለት ተከፍሏል ። በምንም አይነት ልንግባባ አንችልም ። እነሱ የተነሱት ማህበር ለማቋ

ቋም ሳይሆን መንግስት ለመገልበጥ ነው!” አለና ጉልማ፣ አጥላባቸውን በአይኑ ጥግ ተመለከተው ። ከዚያም ንግግሩን ቀጠለ ፣ ጠንከር አድርጎ ።

“አበራ ሲናገር እኔ እራሴ በጆሮዬ ሰምቼዋለሁ ። የተከበረውን ዘውድ ሲዘልፍ ፣ የተንቃንቀ ጥርስ ነው አለ ። እስኪ ተመልከቱት ፣ ዘውድን የሚያክል ትልቅ ነገር በተንቃንቀ ጥርስ እያስመሰለ መዝለፉን ። ስራተኛው የዋህ ነው ። ወደ ጥፋት የሚመሩት እነ አበራ ናቸው ። አበራና መሰሎቹ በጊዜ ከተለቀሙ. . .በቃ ሰላም ነው ። የሚጠረጠሩትንም ማባረር ነው ። እስኪ እነ አበራ ከረሃብ እንደሚያድኗቸው እናያለን ። እስኪ እነሱ ስራ ይሰጧቸው እንደሆን እናያለን ። እና ፣ የተወሰደው እርምጃ ትክክል ነው ። ወደፊትም በየድርጅቱ መቀጠል አለበት ። በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ይጠጣል. . .” አለና ጉልማ ፣ ሁሉቱን ሰዎች ተራ በተራ ከተመለከተ በኋላ ፣ ብርጭቆውን አንስቶ ከመጠጡ ተጎነጨለት ።

አጥላባቸው ከተቀመጠበት ድንገት ቀና ብሎ የሲጋራውን አመድ መተርኮሻው ላይ አራገፈው ።

“እሺ ፣ ለምሳሌ በእኔ ድርጅት ውስጥ ያሉትን እንዴት ማወቅ ይቻላል?” ሙሴ በጎሲያን ፀጉሩን ወደ ኋላው እየላገ ጠየቀ ። ከዚያም ሁለቱን ሰዎች ተራ በተራ ተመለከታቸው ፣ ከሲጋራ የሚወጣው ሰማያዊ ጢስ እንዳይገባበት አይኖቹን አጥብቦ ።

“ቀላል ነው. . .ማወቅ ይቻላል” አለ ጉልማ ፣ ወንበሩ ውስጥ ተመቻችቶ እየተቀመጠ ። “እስካሁን የምናውቃቸው አሉ ።”

ወደ እንጨት መሰንጠቂያው ፋብሪካ የምትወስደው ቀይ አሸዋ የፈሰሰባት ቀጭን መንገድ ላይ ፣ አንዳ

ንድ ሰዎች ወዲህና ወዲያ ይላሉ ። መንገዱ ዳር ካለ ችው ባለ አንድ ፎቅ የድንጋይ ቤት ውስጥ ፣ የሚጠጡ ሰዎች ድምፅ ውጪ ድረስ ይሰማል ። አልፎ አልፎ ሳቅ ይፈነዳል ። የጣሊያንኛ ቃላት በሰዎች ንግግር ጣልቃ እየገቡ ይሰማሉ ። ሲኞራ ያንን አጭርና አርበ ሰፊ ሰውነታቸውን ፣ እንደ ዳክዬ ግራና ቀኝ እያወዛወዙ በተቃጠለ ዘይት በተወለወለው ወለል ላይ ወዲያና ወዲህ ሞንደል ሞንደል ይላሉ ።

ክትልቁ ቤት ጀርባ እና ጉልማ ዘወትር የሚሰበሰቡበት ትንሺ ክፍል ለጥቂት ጊዜ በፀጥታ እንደ ተዋጠች ቆየች ። ሶስቱም ሰዎች በሃሳብ ተውጠዋል ። አጥ ላባቸው በመጨረሻ ፀጥታውን ሰበረው ።

“እሺ ጥሩ ነው. . .ያልካቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ትሰጠኛለህ ።”

“ከዚያስ?” አለ ሙሴ ቦጎሲያን ተሽቀዳድሞ ።

“ከዚያ በኋላ ያለው የእኔ ስራ ነው” አለ አጥላ ባቸው ፤ ሙሴ ቦጎሲያንን እያየ በሙሉ ልብ ሳቅ ብሎ ። የፊት ጥርሶቹ በልዘዋል ። ሙሴ ቦጎሲያን ጭንቅላቱን በአምንታ ነቀነቀ ።

“አዎን ፣ ከዚያ በኋላ የአንተ ስራ ነው” አለ ጉልማ፣ አጥላባቸውን እያየው ፤ “ጥቂት በጥባጮች ካሉ ባህሩ በሙሉ ይደፈርሳል ። የካቻምናውን ግርግር ማስታወስ ይበቃል ። ‘እባብን መቅጨት ከእንቁላሉ ጋር ነው’ ይባ ላል ። ቀንደኞቹም ቲፎዞዎቹም የስራቸውን ማግኘት አለባቸው ። ይሄ የእኔ ወይም የሙሴ ቦጎሲያን ወይንም የሻምበል ጉዳይ ብቻ አይደለም ። ሁላችንንም ይመለከተ ናል ። በዘውዱ ላይ ፣ በሃገር ላይ የሚመጣ ነገር ሁላች

ንንም ይመለከተናል” አለና ጉልማ ፣ ሁለቱን ሰዎች በሚንቀዠቀዡ አይኖቹ ተራ በተራ አያቸው ።

ከዚያም አይኖቹን ሙሴ ቦንሲያን ላይ ተክሎ ንግግሩን ቀጠለ ።

“ሙሴ ቦንሲያን . . .ንጉሱ ለውጪ ሃገር ሰዎች ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት እርስዎም ቢሆኑ ያውቁታል ። ያን ጊዜ ቤተ መንግስት ተጠርተሁ ያነጋገርዎት ጊዜ አይተውታል ። እናንተም እንደዚሁ ሃብት አግኝታ ችሁ ፣ ተከብራችሁና ታፍራችሁ በሃገራችን የምትኖሩት ዘውዱ ስላለ ነው ። በዚያች በቀውጢ ሰአት እንዴት እንደሆንን ሁላችንም እናስታውሳለን ። የውጪ ሰዎች ቅር እንዳይላቸው ፣ ሲተቀጠሩት ብልጫ ደሞወዝ ይከ ፈላቸው ፣ ለአሰሪዎችም የስራ ግብር ይቀንስላቸው ብለው ያዘዙት እራሳቸው ናቸው ። አይደለም እንዴ?” አለ ጉልማ ፣ ሙሴ ቦንሲያንን እየተመለከተ ። ፈረንጁ መስ ማማቱን በአንገቱ ንቅናቄ ገለፀ ።

“የአበራን ነገር እንዳልኳችሁ ለእኔ ተውት ። ሲሆን በማግባባት ያወጣታል ፤ አለበለዚያ በተማር ነው ዘዴ እንጠቀማለን” አለ አጥላባቸው ፣ ጣልቃ ገብቶ። ከዚያም ፈገግ አለ ። በኩራት ፈገግ ሲል እንደ ቁወለ ወለ ብርጭቆ የሚያበራው የፊቱ ስጋ ተወጣጠረና ይበልጥ አብለጨለጨ ።

“እምን ፣ እሱን እንግዲህ እናንተ ታውቁበታላ ችሁ” አለ ጉልማ ፡ ፊቱን ወደ አጥላባቸው አዞሮ ፈገግ እያለ ።

“ለምርመራ ክፍሉ ሃላፊ ትእዛዝ ሰጥቼ ነው የመ ጣሁት ። አሁኑኑ ሂጄ ሁኔታው ምን ላይ እንደ ደረሰ

አጣራለሁ" አለ አጥላባቸው ፤ እንደገና በኩራት ፈገግ ብሎ ።

ወዲያው ሲኞራ በሩን ከፍተው ገቡ ።

"ማዶና ሳንታ ማሪያ! ጥያችሁ ጠፋሁ አይደል? አሎራ!..ጠጡ እንጂ ፤ ምን ይምጣ?" አሉ ሲኞራ ፤ አንዴ ሰዎቹን አንዴ ደግሞ ባዶውን የውስኪ ጠር ሙስ እየተመለከቱ ።

ጉልማ ወደ ሽንት ቤት ሄደ ። አጥላባቸውም ተከ ትሎት ወጣ ። ጉልማ የሽንት ቤቱን በር ከፍቶ ገባ ። አጥላባቸው ከውጪ ቆሟል ።

"ስማ ጉልማ" አለ አጥላባቸው ።

"እ?" አለ ጉልማ ፤ ሽንቱን እያፈሰሰ ።

"ይህ ፈረንጅ ገንዘቡን እንዴት አደረገው?"

"ዝም ብሏል ።"

"ለምን አባቱ ነው ዝም የሚለው?"

"እኔ እንጃ!"

"እምቢ ካለ . . ምናባቱ በሃያ አራት ሰአት ነው ከሃገር የምናስወጣው!"

"እንዴትና?"

"ቀላል ነው ። አንድ ምክንያት መፍጠር ይቻላል ። ድርጅቱን ለመግዛት ያማከሩኝ ስንት የቤተ መንግስት ሰዎች አሉ መሰለህ ።"

"ይከፍላል ፤ እከፍላለሁ ብሏል" አለ ጉልማ ።

"አሎራ!" አሉ ፤ ሲኞራ እየሳቁ ። ሙሴ ቦንሲያን የድፍን መቶ ብር ኖት ከኪስ ቦርሳው አውጥቶ ከፈለ ።

“ግራሲ” አሉ ሲኞራ ፡ ገንዘቡን ሳቅ እያሉ እየተቀበሉ ። ሲስቁ አይኖቻቸው ይበልጥ ይጠቡና ዘወትር ቀይ ቀለም ሽው የሚያደርጉበት የታችኛው ከንፈራቸው ወደጎን ይለጠጣል ፡ ከዚያም ፀጉራቸውን ዳበስ ዳበስ ያደርጉታል — ትመል ሆኖባቸው ። የተመልካቹን አይን ወደ ፀጉራቸው የሚጋብዙ ነው የሚመስሉት ። ከድሮው መልካቸው የቀራቸው ያው ፀጉራቸው ነው— በቀለም የሚታገዘው ፀጉራቸው ። በተረፈ ያው ዳሌያቸውና በተራመዱ ቁጥር የእግሮቻቸውን እንቅስቃሴ እየጠበቀ ላይ ታች የሚለው መቀመጫቸው ነበር ።

“ተጫወቱ እንጂ ምን ላምጣ? ጊዜው ገና ነው” አሉ ሲኞራ ፡ በጣሊያንኛ ።

“ብዙ ተጫወትን ፤ አመሰግናለሁ!” ሙሴ ቦጎሲያን በጣሊያንኛ መለሰላቸው ።

“የሚበላ ነገር ላምጣላችሁ?”

“አመሰግናለሁ ፤ የእራት ሰአት ደርሷል ።”

“መሄዳችሁ ነው?”

“አዎን ፤ መሄዳችን ነው ።”

“ነገ አትመጡም?”

“እንመጣለን ፤ አንቀርም ።”

“ሲኞራ” አለ ሙሴ ቦጎሲያን ትንሽ ቆይቶ ።

“አቤት!” አሉ ሲኞራ ፡ ፈገግ ብለው ።

“ዛሬ በጣም አምሮብታል ።”

“አመሰግናለሁ ሲኞር ቦጎሲያን ።”

“ተስማማዎት ታዲያ?”

“ምኑ?”

“ሃበሻው ።”

“ኦ ማዶና ሳንታ ማሪያ! ሃበሾች ፍቅር ይችላሉ” አሉና ሲኞራ ፣ ጉልማን ሲያስታውሱ ጉንጮቻቸው ቀላ ቀላ አሉ ።

የሲኞራ ባል ፣ ሚቼ ሲኞር ሉዊጂ ፣ በህይወት ሲኖሩም ሲትዮዋ የአበሻ ወንድ መስረቅ ልማዳቸው ነበር ። የጀመሩት በገዛ ወጥ ቤታቸው ነው ። መርጊያ ይባላል ። ታዲያ አንድ ቀን መርጊያ ለምሳ የሚዘጋጀውን የምግብ አይነት ለመጠየቅ ከእመቤቲቱ መኝታ ቤት ሲገባ በሩ ተከፍቶ ሲኞራ ፊታቸውን ወደ አሊጋው አዙረው ጫማቸውን ለማድረግ ጎንበስ ብለዋል ። እንኳን በውስጥ ሱሪ ፣ ቀሚስ ለብሰውም ቢሆን የማረብሹ አይነት ነበሩ ። እጅሬ መርጊያ እንዲህ ያለውን አጋጣሚ ሲጠብቅ ቆይቶ ኖሮ ፣ የመጣው ይምጣ ይልና እፈፍ ያደርጋቸዋል ። ሲኞራም አልከለከሉት ።

ከዚያ በኋላ የአበሻ ወንድ ጣማቸው ። ባላቸው ወጣ ሲሉ መርጊያ ይተኳል ። እዚያው መኝታ ቤት ነበር ሲኞር ሉዊጂ የያዙት ። ከስራ ይባረራል ። ሲኞራ ግን አመል ሆኖባቸው ይቀራል ። በመሃሉ ባላቸው ያርፋሉ ። መጠጥ ቤቱ ይከፈታል ። ከዚያ በኋላማ እንደ ልባቸው ሆኑ ። የሚፈልጉትን ወንድ በአይኑ ያውቃሉ ። ጉልማ አይናቸው ከገባ ቆይቷል ። ቤታቸው ቤቱ ሆኗል ። እንደ ፈለገው ይበላል ፣ ይጠጣል ። ጉልማ ለሚሰጣቸው ደስታ ሲኞራም ወሮታውን ከመክፈል ወደ ኋላ ያሉበት ጊዜ የለም ። ‘የኪስ ገንዘብ’ እንደ ፈለገው ይሰጡታል ።

“ሃበሾች እኮ መጥላትም ያውቃሉ ፣ ሲጠሉ ደግሞ መጥፎ ናቸው” አለ ሙሴ ቦጎሲያን ። ተያዩና ተሳሳቁ ።

"እኔ እንኳን እስካሁን የሚጠላኝ አበሻ አልገጠመኝም ፤ አበሾች አይጠሉኝም ።"

"አርመኖችስ?" አለ ሙሴ ቦኀሲያን ፣ ነገሩን ወደ እራሱ እየመለሰ ።

"አርመኖች ቆንጆዎች ናቸው. . .ፍቅር ላይ ግን እንደ አበሾች አይሆኑም ። ኢ.ኪ.ኪ.ኪ.ኪ.! . ."

"ቤቃ እርሶ አበሻ ብቻ ነው የሚወዱት ማለት ነው?"

"አይ ፣ ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ ። አሞሬ ሚዮ ።" እንደገና ተሳሳቁ ።

"ሙሴ ቦኀሲያን" አሉ ሲኞራ ፣ ትንሽ ዝም ብለው ቆይተው ።

"ወይ!"

"መቼ ነው ሃገራችን የምንሄደው?"

"እኔ ሃገር የለኝም. . .ሃገሬ ይኸው ነው ። እርሶስ?"

"እኔም የትም አልሄድም ። እርሶም እንደ እኔ ይቺን ሃገር ይወዷታል?"

"በጣም. . . በጣም እወዳታለሁ" አለ ሙሴ ቦኀሲያን ፣ ወንበሩ ውስጥ ተስተካክሎ እየተቀመጠ ፣ "አቢሲኒያ ቆንጆ ሃገር ነች ። ኑሮ ርካሽ ነው ። ሰራተኛ ርካሽ ነው ። ባለስልጣኖቹ ብቻ ገንዘብ ይወዳሉ ። ገንዘብ መስጠት ። ቤቃ ከዚያ በኋላ ችግር የለም ። ያልተበላች ሃገር ነች ። ወደ ፊት ብዙ እድል አለን. . ."

"ሙሴ ቦኀሲያን ።"

"ወይ!"

"ለመሆኑ ከመጡ ስንት ጊዜ ሆኖት?"

"ከመጡ? ምን ከመጡ ይሉኛል! እኔ እኮ እዚሁ ተወልጄ ነው ያደግሁት!"

"እሺ ፣ እርስዎ በጣም ሀብታም ኖት ፣ አይደለም?"

"ሚሊዮኔር አይደለሁም ፤ ግን በቂ ገንዘብ አለኝ ።"

"ታዲያ ለእኔ ምን ያደርጉልኛል?"

"አ! ለእርሶማ ጉልማ አለ ።"

"ጉልማ ምንም የለው. . .ፍቅር ብቻ ነው ።"

"ሻምበልስ?"

"ሻምበል አለኝታ ነው ።"

"እኔስ?"

"እርሶ ገንዘብ ነው ።"

"ማንን ይመርጣሉ?"

"ሁላችሁንም ፤ አ.ኪ.ኪ.ኪ.ኪ.!!"

"ሶስታችንንም?"

"ምናለበት!"

"ሲኞራ ፣ እኔ ልንገሮትና. . .ሶስቱንም መውደድ አይቻልም ። ሶስቱንም ማግኘት አይቻልም ። አንዱን መምረጥ አለቦት ።"

ጉልማና አጥላባቸው በሩን ከፍተው ገቡ ። ሶስቱም ሰዎች ጥቅ ብሏቸዋል ። አጥላባቸውና ፈረንጁ ለጉልማ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ በቤቱ ጀርባ ወጥተው ከደጅ ወደምትጠብቃቸው ሚሊቼንቶ መኪና ውስጥ ገቡ ። ጉልማም ወደ ሲኞራ መኝታ ቤት ሄደ ።

# — 3 —

ከተማው ፅልመት ለብሷል ። የፖሊስ ጣቢያው አካባቢ ወፍ እንኳን ዝር አይልበትም ። ከሌሊቱ ስምንት ሰአት አካባቢ ነው ። አበራ ቃል መቀበያው ክፍል ውስጥ ተቀምጧል ።

አንድ ጠረጴዛ ፤ ሁለት ወንበሮች ፤ አንድ ስልክ ፤ የሲጋራ መተርኮሻ ፤ ያልተጻፈባቸው ወረቀቶች ፤ ይኸ ብቻ ነበር ክፍሉ ውስጥ ያለው ሉቃ ። ከቤቱ ጣሪያ መሃል ቁልቁል ከተንጠለጠለው የኤሌክትሪክ ሽቦ ጫፍ ላይ፥ አንዲት አልፑል በተከፈተው መስኮት በኩል በሚገባ ነፋስ እየተገፋች ትወዛወዛለች ። ቤቱ ኦና ኦና ይሸታል ።

"ታጨሳለህ ? . . . ይኸው ሲጋራ . . . "አለ ከጠረጴዛው ጀርባ የተቀመጠው ሰው ፤ ከኮት ኪሱ ውስጥ ያወጣውን የሲጋራ ፓኬት ፊት ለፊት ለተቀመጠው ለአበራ እያቀረበለት ።

"አላጨስም !" አለ አበራ ፤ እራሱን ነቅንቆ ። ክንዶቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ ፊት ለፊት የተቀመጠውን ጠያቂ ያየዋል ።

"እሺ አታጨስም . . . ጥሩ ነው ። ታዲያ ምን ይምጣልህ? ቡና ፤ ሻይ ?" ሰውየው እንደገና ጠየቀ—በምፀት ፈገግታ ። አበራ አልመለሰለትም ።

ጠያቂው ሲጋራውን አቀጣጠለና ጭሱን ወደ ውጪ ሲወረውረው በመስኮት የሚገባው ነፋስ ክፍሉ ውስጥ በታተነው ። አሁንም ፈገግ እንዳለ ነበር ።

"እሺ አበራ" አለ ሰውየው ፤ በሲጋራው ጫፍ መተርኮሻውን መታመታ እያደረገ ። "ምናለበት ይኸ ሁሉ

ነገር ቢቀርብህና እራስህም ችግር ላይ ወድቀህ ቤተሰ ብህን ጭምር ችግር ላይ ባትጥል . . . ምን ለመሆን ነው፣ እስኪ አስብበት . . . ”

አበራ አልመለሰለትም ። ወንበሩ ላይ ተስተካክሎ ተቀመጠና ጠያቂውን ተመለከተው ። መልከ መልካም ፥ ከሰላሳ አምስት አመት የማይበልጠውና የሲቢል ልብስ የለበሰ ሰው ነው ። ጠያቂው ንግግሩም ሆነ እንቅስቃ ሴው ረጋ ያለና የተመጠነ ነው ። ከአበራ መልስ የሚጠ ብቅ ይመስላል ።

“ከእሱ በፊት እስኪ እኔ ልጠይቅህ . . . ለመሆኑ ለምን ታሰርኩ? ለምን ተያዝኩ? ሁለት ቀን ሙሉ ብር ሃን ሳላይ ፥ ያለ እህልና ውሃ አንድ ክፍል ውስጥ ለብ ቻዬ ለምን ታሰርኩ?” አበራ ድንገተ እንባረቀ ።

“እሱ ቀላል ነው” አለ ጠያቂው ፥ እንደገና በም ፀት ፈገግ ብሎ ። “ለምጠይቅህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ከሰጠኸኝና . . . ማለትም ከተባበርከ አሁኑኑ ወደ ቤትህ ትሄዳለህ ። ለመሆኑ አብርሃምን ታውቀዋለህ ? እስኪ በዚህ እንጀምር ። ”

“አብርሃም ማን ?”
“አብርሃም ወንድሙ ። ”
“አዎን ፥ አውቀዋለሁ ፤ የስራ ባልደረባዬ ነው ። ”
“አሁን የት ነው ያለው ?”
“እኔ እንጃ!”
“መቼ ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ያየኸው ?”
“አላስታውስም ። ”

“እሺ ተወው ። እሱ ለጊዜው ጠፍቷል ። ይገኛል፤ የትም አይሄድ ግዴለም ። ለመሆኑ ማህበራችሁ እንዴት ነው ?”

“የቱ ማህበር?”
“ያቋቋማችሁት ።”
“ጥሩ ነው ።”
“ለመሆኑ ምን ይሰራላችኋል?”
“ምኑ ?”
“ማህበሩ ።”

“መረዳጃ ማህበር ነው ። ስንቸገር ፥ ከስራ ስንባረር ፥ ስንሞት . . . . ይረዳናል ።”

“ታዲያ ለእሱ እድር አለ አይደል ?”

“እድር የሞተ ለመቅበር . . . ከሞት በኋላ ለመረዳዳት ነው። የእኛ ማህበር ግን በቁም ለመጠቃቀም ነው።”
“እሺ ጥሩ ነው . . ታዲያ መሪነቱን ወደድከው?”
“የምኑን መሪነት?”
“የማህበሩን ።”

“ብወድም ባልወድም የግድ መቀበል አለብኝ ፤ እንዴ መርጠውኛል . . . .በኪራም በሊማም . . . ”

“ታዲያ የተመረጥከው ለማወክ ነው?” አለ ጠያቂው ፥ ድንገት ግንፍል ብሎ ። መልኩ ተለዋወጠና አበራን በሚቁረጠረጡ አይኖቹ ትክ ብሎ ተመለከተው ።

“ለመበጥበጥ አይደለም . . . ለመብታችን እንድንሟገት ነው” አለ አበራ ፥ እንደ ወትሮው ፍርጥም ብሎ።

“መብታችሁን ማን ገፈፋችሁ? ከማን ጋር ነው የምትሟገቱት?” አለ ጠያቂው ፥ ድንገት አምልጦት የወጣውን ቁጣውን መልሶ ለመዋጥ እየታገለ ።

“ዱታዎቹ ናቸው . . . ከባለቤቶቹ ጋር ነው የምንሟገተው ።”

"ለምን ዘውዱን ትዳፈራለህ ?"

"አልደፈርኩም ። ደፈርክ ከተባልኩ ቅጣቴን ልቀበል ፤ እኔ ግን እውነቱን ነው የተናገርኩት ።"

"ምኑ ነው እውነቱ ?"

"የታወቀ ነው ። አንዱ እያመረተ ውጤቱን ሳይሰራ ለሚበላ ያስረክባል ። ሰራተኛው እንደ እንስሳ ተቆጥሮ ከማእድ ላይ ተቆርሳ ከምንም ችግር የማታወጣ ደሞዝ ትጣልለታለች . . . ይኸን ብያለሁ ፤ አልዋሸም ። የሚያስቀጣ ከሆነም እቀጣበታለሁ ። የሚያሳዝነው ግን ነፃነት አለ በሚባልበት ሃገር ፣ ከስራ ወጥቼ ወደ ቤቴ ስሄድ በማላውቃቸው ሰዎች በጨለማ መታፈኔ ነው . . ."

"ቅጣቱን ለጊዜው ተወውና ለመሆኑ የት ነው በምስጢር የምትሰበሰቡት?"

"በሚስጥር አንሰበሰብም ። ያው ስራ ቦታ እንገናኛለን ፤ እንነጋገራለን ።"

"ምንድነው የምትነጋገሩት?"

"ስለ ማህበሩ ።"

"ምን?"

"በቃ ስለ ማህበሩ መጠናከር ፤ ስለ መዋጮ ፤ እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው አባሎች . . ."

"ባለፈው ጊዜ ፣ ከስራ የወጣህ ጊዜ የደረሰብህን ችግር ታስታውሳለህ?"

"አዎን ፣ ታዲያ ምን ላደርግ እችላለሁ? አስወጡኝ ብዬ አልወጣሁ. . ."

"ቤተሰብህ አልተቸገረም? አሁንስ ሚስትህ ወልዳ አራስ ቤት ተኝታለች አይደለም? እሷስ አትቸገርም?"

“ተጣምገረናል . . . ትቸገራለች . . . ትዲያ ምን ይደረ ጋል? ሁለት ወደ አይሆንም ። ከሁለቱ አንዱን አማራጭ መያዝ የግድ ነው ።”

“አንዱ አማራጭ ማነው?”
“ሰራተኛው ።”
“ሌላውስ?”
“አሰሪዎቹ ።”

“ስማ አቶ አበራ ፣ እኔ ልንገርህ . . . ምን በወጣኝ ብለህ እጅህን እዚህ እሳት ውስጥ ትከታለህ? አንተ የሰንት ልጆች አባት ነህ! . . . ብትሞት ወይ ብትታሰር ልጆችህ ያለ አሳዳጊ የትም እንደሚቀሩ አታውቅም? ደግሞም መንግስት ለሰላማዊ ሰዎች እንጂ ለሌረኞች ፣ ለአድመኞችና ለበጥባጮች ምህረት የለውም ። የኪዎም ናውን ታህሳስ ረሳኸው? እስካሁን የሰራኸው ሁሉ በስ ህተት ስለሆን ይቅርታ ይደረግልሃል ፣ ትፈታለህ ። ወይ ስራህ ትመለሳለህ ። ደምወዝም ቢሆን ይጨመርልሃል ። ግን ከዚህ ከማህበር ውስጥ እጅህን አውጣ ። እኔ የምመ ክርህ ይኸንን ነው ። ሃሳብህን አሁኑኑ ለውጥ ። በኋላ ይቆጭሃል እ?” አለ ጠያቂው ፣ በዶረቱ ጠረጴዛው ላይ ተደግፎና አንገቱን ወደ አበራ አስግጎ ።

ለጥቂት ሴኮንዶች ቤቱ ውስጥ ፀጥታ ሆነ ።

“በስህተት አይደለም ፣ ባለማወቅ አይደለም ፣ አውቄ ነው የሰራሁት!” አለ አበራ ፣ ድንገት ግንፍል ብሎ ። “የስራተኛው መብት ይከበር ፣ መረዳጃ ማህበር እናቋ ቁም ፣ የልፋታችን ተመጣጣኝ ዋጋ ይከፈለን ማለት ምን ወንጀል ነው? ምን አጥፍቼ ነው ይቅርታ የሚደ ረግልኝ? ደግሞም በሰራተኛው የምለውጠው ምንም ነገር የለም . . . የተናገሩት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፋ

ይላል የሃገራችን ሰው ። የሰራተኛውን ቃል በጆሮዝ አልሸጥም ፤ አለውጥም. . .ልጆቼም ቢሆኑ ስኔ ካላቸው ያድጋሉ ፤ አለዚያም እንደ ፍጥርጥራቸው ይሆናሉ ። ለጊዜያዊ ጥቅም ብዬ ከሞት በኋላ ለሚመጣ ወቀሳ አልዳርጋቸውም ። ከሞቱ በኋላ ከመወቀስ በህይወት ሳሉ ንፁህ ህሊናን ጠብቆ እንዳጡ፣ እንደ ነጡ መኖር ይሻላል ።”

የዚህን ጊዜ የጠያቂው ሰውነት በንዴት ሞገድ ተመታ ። እንደገና ለትንሽ ጊዜ ፀጥታ ሆነ ። የሰውዬው ፊት ከሰል መሰለ ። የታችኛውን ከንፈሩን በጥርሶቹ ነከስ አደረገና ልውጣ እያለ የሚተናነቀውን ንዴት ለማስቀረት ይመስል ደጋግሞ ምራቁን ዋጠ ።

ከዚያም እንደ ምንም ብሎ ወደ ቀድሞው ሁኔታው ተመለሰና እንደገና በምፀት ፈገግ አለ ።

“እሺ ጥሩ . . .” አለ ጠያቂው፣ የግድ ፈገግ ብሎ ። “ከኮሌጅ ተማሪዎች ጋር ለምንድነው የምትገናኘው?”

“አልተገናኘሁም” አለ አበራ ። “እነሱ ጋ ምን አደረሰኝ? እኔ አልተማርኩ ፤ ዕውቀት የለኝ. ከነሱ ጋር በምን አቅሜና ችሎታዬ ነው የምነጋገረው?”

“ነ ሺ ስንት ማህበር አላችሁ?”

“አንድ ።”

“ሌላስ?”

“በቃ!”

“እሺ አብርሃም ያለበትን አላውቅም ብለሃል ፤ ይሁን ። ሽኩር የት ነው ያለው ?”

"ሽኩር የሚባል ጓደኛ የለኝም ።"
"እውነቱን ብትናገር ይሻልሃል!"
"እውነቱ ይኸው ነው ።"

በጠያቂው ቆንጆ መልክ ላይ ሲያንገዋብብ የነበረው ፈገግታ ድንገት ድርግም አለና ወዲያውኑ የተቆጣ አውሬ መስሎ ቁጭ አለ ። በሲጋራ ላይ ሲጋራ ይለኩሳል ።

"ስማ አበራ ፤ ስለ አንተ የህይወት ታሪክ ፣ ስለ ምትሰራው ስራ ፣ ስለ እቅዳችሁ ሳይቀር አንድ በአንድ እናውቃለን ። ከኮሌጅ ተማሪዎች መገናኘትህን እንኳን ከደሃል ። እንደምትገናኙ ግን እናውቃለን ።"

ጠያቂው ከመቀመጫው ተነስቶ ክፍሉ ውስጥ ይንጎራደድ ጀመር ። አበራ በአይኑ ይከተለዋል ።

"የተማረው ነገር እንኳን ቀላል ነው ። ለልጅ ልምጭ ይበቃዋል ። እሳቸው ግን አንዳንዴ ሰው የሚላቸውን አይሰሙም ። ተው ፤ የድሃ ልጅ አታስተምሩ ፤ ለድሃ ልጅ ሹመት አትስጡ ሲባሉ እሺ አይሉም ። እነሆ እኔ እንደ እኔ ከሆነ አሁንም በዚች ሃገር ላይ ትልቅ ችግር እያንገዋበበ ነው ። ንጉሱ ብዙ ታሪክ ያውቃሉ ። ብዙ አንብበዋል ። ለምን ችላ እንደሚሉ ግን አይገባኝም ።" ጠያቂው ድንገት ፊቱን ወደ አበራ አዞረና ፣ "እሺ ፤ አሁን ወደ ክፍልህ መሄድ ትችላለህ" አለና ሲጋራውን መተርኮሻው ላይ ደፈጠጠው ።

አበራ ከተቀመጠበት ተነስቶ አንገቱን ቀና አደረገና ፊት ለፊቱ እየተመለከተ በሩን ከፍቶ ወጣ ።

ወዲያውም ጠያቂው የስልኩን መነጋገሪያ አነሳና በሚንቀጠቀጡ ጣቶቹ ቁጥሩን ደወለ ። አጥላባቸው ጋ ነበር የደወለው ።

"ሃሎ. . .ሻምበል አጥላባቸውን ነበር ።"

"እኔ ነኝ ፤ ማን ልበል?"

"ከጥያቄው ክፍል ፤ ተረኛ መኮንን ።"

"እሁ. . .መቶ አለቃ ፤ እሺ እንዴት አደረክ? ተናገረ?"

"ምንም ነገር ማግኘት አልተቻለም ፤ ምንም ፍንጭ አልሰጠም!"

"በቃ በሌላ ዘዴ ተጠቀሙ!"

"እሺ ጌታዬ!" አለና ጠያቂው መነጋገሪያውን መልሶ ከቦታው ካስቀመጠ በኋላ የታችኛውን ከንፈሩን በጥር ሶቹ እንደ ነከሰ አበራ ወደ ታሰረበት ክፍል ሁለት ጓደኞቹን ይዞ እየተጣደፈ ሄደ ።

— 4 —

ታዴዎስ የጓደኛውን መጥፋት እንደ ሰማ ነበር አበራ መኖሪያ ቤት የሄደው ። ብዙነሽ እራስ ልጅዋን እቅፋ አልጋ ላይ ተክዛ ተቀምጣለች ። ህፃኑ አይኖቹን ጨፍኖ በትናንሽ ቀይ ከንፈሮቹ የያዘውን ጡት ሳብ ሳብ ያደርጋል ። ሁለቱ ልጆች ከእንጨት ሳጥኑ ላይ ተቀምጠዋል ። የጎረቤት ሰዎች እዚህና እዚያ ፊንጠር ፊንጠር ብለው ተቀምጠው ይተክዛሉ ።

"እንዴት ነው ታዲያ ይኸን ሰውዬ የት ወሰዱት ይባላል?" አለች ብዙነሽ ፣ ታዴዎስን ቀና ብላ እያየ ችው ። "ያ ማነው እሱ. . .ጉልማ ነው ማነው የምት ሉት? እሱ ነው ቅድም መጥቶ የነገረኝ ። እኔማ እንዲ ያው ወይ መኪና ገጨው ወይንስ መንገድ ላይ ማጅራት መቺ ጉድ አደረገው ብዬ ነበር ።"

"ማን. . .ጉልማ. . .እ? መጥቶ ነበር እሌሽ? እሺ, ልጄ ፣ ምን አለ?" አለ ታዴዎስ ፣ ከተቀመጠበት ቦታ ድንገት ተነስቶ ።

"እሱማ አይዞሽ አታስቢ ፤ ስለ ማህበሩ ጉዳይ ሊያነጋግሩት ነው የጠሩት ፤ ይመጣል አለኝ ።እንግዲህ እንደ አፉ ያድርገው እንጂ ሌላ ምን ይባላል. . ." አለች ብዙነሽ ፣ እንገቷን ዘንበል አድርጋ የታቀፈችውን ልጅ እያየች ።

"እንዴት አወቀ. . .ማለቴ መያዙን?"

"ተይዞ ነው እንዴ?" አለች ብዙነሽ ፣ድንግጥ ብላ ።

"እሺ, የሄደበትን እንዴት አወቀ?" አለ ታዴዎስ ፣ እራሱን እያረመ ።

"እሱማ ጓደኛው አይደል? ሁለቱም ተመርጠ ዋል አሉ ። ወይ አብረው ሲሄዱ ይሆናል የኔውን ሰውዬ የያዙት. . .ወይ ሰው ነግሮት ይሆናል ። እረ መጥቶ መና ገሩም እግዜር ይስጠው" አለች ብዙነሽ ፣ መሬት መሬ ቱን እየተመለከተች ።

"እ. . . ይመጣል አታስቢ አለሽ? መምጣቱን እን ዴት አወቀ? ያቆዩት ይልቀቁት እንዴት ያውቃል?" አለ ታዴዎስ ፣ አንድ ቦታ እንደ ቆመ ።

"ነገሩን ያውቅ እንደሆን? እኔማ ምናባቴን አውቃ ለሁ ። ግን እንዲያው ሲናገር ደህና ሰው ይመስላል ፤ የሆዱን ማን ያውቃል" አለች ብዙነሽ ።

"እምም. . ." አለና ታዴዎስ ፣ የታችኛውን ከንፈ ሩን በጥርሶቹ ነካከሰ ።

"ምነው?" አለች ብዙነሽ ፣ የታዴዎስን መረበሽ ተመልክታ ።

"አይ እንዲሁ ነው. . .ሌላ ምንም አላለሽ?"

"አይ ፣ እሱ እንኳን ያለው እውነቱን ነው ። 'ምክ ሪው ፣ ይቅርብህ በይው ፣ እሱ አንድ ነገር ቢሆን ልጆ ቹን ማን ያሳድጋቸዋል?' አለኝ ። እውነቱን ነው እሱስ ። እኔም ሁልጊዜ የምለው ይኸንኑ ነበር ።"

"እምም. . .እሺ ፣ በይ ልሂድ አሁንም ። መስሪያ ቤት ሄጄ ሁኔታውን አጣራለሁ ። ወደ ማታ ብቅ እላ ለሁ" አለ ታዴዎስ ።

"ለመሆኑ የት ይሆን ያለው?"

"ማን ያውቃል ብለሽ ነው ።"

"አንተም እንግዲህ ጠንቀቅ በል ። መቼም ጓደ ኛው መሆንህን ሳያውቁ አይቀሩም ።"

"ታዲያ ቢያውቁስ? ማወቃቸውማ አይቀርም. . . ታዲያ አሁን አበራ ተይዞ እኔ ልሸሽ ነው ወይንስ ልደበቅ ነው?" አለ ታዴዎስ ፣ ድንገት ግንፍል ብሎ ።

"እኔማ ከጠዋቱም ይቅርብህ ብዬው ነበር" አለች ብዙነሽ ፣ ተክዛ ።

"ታዲያ ምን አጠፋ አሁን? ጓደኞቹ መረጡት ። ሌሎቹ ደግሞ ይዘው አሰሩት ። እሱ ምን ያድርግ ታዲያ? እስኪ አንቺው ፍረጂው ።"

"የሆነስ ሆንና እንዲያው ስንቅ እንኳን ማን ያቀ ብለዋል? እኔም ይኸው ገና ከአራስ ቤት አልወጣሁም ።

እንዲያው በረሃብ መሞቱ አይደለም ታዲያ?” አለች ብዙነሽ ።

ቤቱ ውስጥ የተቀመጡት ሰዎች በዝምታ ያዳም ጣሉ ። ታዴዎስ ከተቀመጠበት ድንገት ተነስቶ ብዙ ነሽ ወደ ተቀመጠችበት አልጋ ተጠጋና ፣ “በዚህ እስኪ ለእለቱ ልጆቹን ሸንግዪበት” አለና በእጁ ጨብጦ የያዘውን አምስት ብር ከብርድ ልብሱ ላይ አስቀም ጦላት መልስ ሳይጠብቅ እየተቻኮለ ከቤቱ ወጥቶ ሄደ ።

— 5 —

ታዴዎስ በቀጥታ ወደ ስራው ነበር የሄደው ። እንደ ደረሰ የስራ ልብሱን ለብሶ የሚሰራበትን ማሺን አንቀሳቀሰው ። ሃሳቡ ተረብሿል ። “አገኙት . . . በመጨ ረሻ አገኙት ። ሳይታሰብ አገኙት ። አሁን ዋናው ነገር የሚፈታበትን መንገድ መፈለግ ነው ። ቶሎ ካልተፈታ በቃ. . .እነዚህ ከሃዲዎች የልብ ልብ ያገኙና የቀሩት ንም ያስለቅሚቸዋል ። ዋናውን ማህበር በእጃቸው ለማስገባት ነው ጥረታቸው ። ማህበሩን ለባእዳን ጥቅም ማስከበሪያ ለማድረግ. . .ከሃዲዎች ፣ ይሁዳዎች ፣ የፈረ ንጅ ወኪሎች. . .” ይላል ታዴዎስ በሃሳቡ ።

ወሬው ወዳያው ነበር ፋብሪካው ውስጥ የተዳረ ሰው ። ቀኑን ሙሉ ሌላ ወሬ አልነበረም ። በሁኔታው ያዘኑት ብዙዎች ናቸው ። ምንም ያልመሰላቸውም ነበሩ ። እነ ጉልማ አካባቢ ግን ደስታ ነበር ።

ታዴዎስ ከእራሱ ጋር መነጋገሩን አላቆመም ።

“አበራን ማስፈታት አለብን ። እንደ ምንም ብለን ማስፈታት አለብን” ይላል ታዴዎስ በሃሳቡ ። “እሱ

ካልተፈታ በቃ ሌሎቹም እየፈሩ ወደ ኋላ ይላሉ ። እሱው ነበር የድሃው ወገን ። አዎን ፣ እሱው ነበር የማህበሩ አለኝታ ። እሱው በለፋለት ማህበር አሁን የጉልማ አይነት ይሁዳዎች ሊፈነጩበት? በፍፁም መሆን የለበትም ። እንደ ምንም ብለን ማስላቀቅ አለብን. . .”

ጉልማ ከጠዋት ጀምሮ ከአንዱ የስራ ክፍል ወደ ሌላው እየተዘዋወረ ስለ አበራ ሁኔታ የሆነ ያልሆነውን ሲቀባጥር ነበር የቆየው ። እውነቱ መታወቅ የለበትም ።

ጉልማ እነ ታደዎስ ክፍል ሲገባ ሰራተኞቹ በሙሉ ስራቸው ላይ አቀርቅረው ነበር ።

“እንደ ምን አረፈዳችሁ?” አለ ጉልማ ፣ ክፍሉ ውስጥ እንደ ገባ ። የማሺኑ ጩኸት ድምፁን ውጦ አስቀረው ።

“እንደ ምን አረፈዳችሁ?” አለ ፣ እንደገና ጮክ ብሎ ። የሰሙት ቀና ቀና ብለው በጭንቅላታቸው ሰላምታ ሰጡት ። ከዚያም ጉልማ ታደዎስ ወደሚሰራበት ቦታ ሄደ ።

“ደህና አረፈድክ?” አለ ጉልማ ፣ ታደዎስን እያየው ። ታደዎስ አልመለሰለትም ። አቀርቅሮ ስራውን ይሰራል ። ወደ ክፍሉ ሲገባም ሆነ ወደ እሱ ሲመጣ አይቶታል ። ጉልማ ጠጋ አለና የታደዎስን ትከሻ በእጁ መታ መታ አደረገው ። ታደዎስ ቀና ብሎ ጉልማን በቀዘቀዘ አይን አየው ።

“እ . . .ስራ ስራዬን እያየሁ. . .እ. . .አላየሁህም” አለ ታደዎስ ፣ ጉልማን ቀና ብሎ አይቶት ከመቅፅበት አይኖቹን ወደ ማሺኑ እየመለሰ ። እንደገና ዝም አለ ።

"ምነው ምን ሆንክ?" አለ ጉልማ ፤ በፈዝ ፈገግ ብሎ ።

"ምን ሆንኩ?. . .ምንም አልሆንኩ" አለ ታዴዎስ፤ ማሺኑ ላይ ጎንበስ እንዳለ ። ድምፁ የብስጭት ቃና ነበረው ።

"እኔ እንጃ. . .የከፋህ ትመስላለህ. . .ምነው ቤተሰብ ደህና አይደሉም እንዴ?" አለ ጉልማ ፤ ከአንገት በላይ ።

"ምን ይከፋኛል. . .ሁላችንም ደህና ነን" አለ ታዴዎስ ፤ ንዴት እየተናነቀው ።

"ታዴዎስ. . .እ. . .ምንድነው የሚወራው እባክህ. . .አበራን ያዙት አሉ?" አለ ጉልማ ፤ ትንሽ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ ፊቱን አጨፍግጎ ።

"አዎን ፤ ያዙት አሉ" አለ ታዴዎስ ፤ ቀዝቀዝ ብሎ አይኖቹን ከማሺኑ ላይ አልነቀለም ። "እህ. . .ሳታውቀው ቀርተህ ነው የምትጠይቀኝ ይሁዳ. . .ለብዙነሽ ማነው የነገራት?" ይላል በሃሳቡ ።

"እሱ ብቻ ምን አደረገ? ለምን ሁላችንንም አይዙንም? እሱ ብቻ አይደለም ተመራጭ ።"

"ምን አውቃለሁ እንግዲህ? የሚሆነውን ማየት ነዋ!" አለ ታዴዎስ ።

"እናንተን ማን ይይዛል. . ." ይላል በሃሳቡ ደግሞ ።

"መሃከላችን ጠቋሚዎች አሉ ማለት ነው" አለ ጉልማ ፤ ለይስሙላ የተናደደ መስሎ ።

"ይኖራሉ. . .የት ይጠፋሉ. . .ማን ያውቃል?" አለ ታዴዎስ ፤ ስራውን እየሰራ ። በሃሳቡ ደግሞ ፤ "አንተ

ትሆናለህ ጠቋሚው . . . አንተ መሆን አሰብህ ፤ ይሁዳ! ያልታወቀብህ መስሎሃል?" ይላል ።

"እስኪ . . . እ . . . ማን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ ከመሃከላችን?" ጉልማ እንደገና ጠየቀው ።

"እኔ እንጃ! ማን ያውቃቸዋል ብለህ ነው ፤ አይታወቁም ።" ታዴዎስ መለሰለት ።

'አንተ ራስህ ነህ ፤ አንተ ራስህ . . . ሌባ! አንተ ፤ አንተ ይሁዳ ፤ አውቅሃለሁ . . .' አለ በሃሳቡ ፤ ንዴቱ ፈንቅሎት ሊወጣ ደረቱን እየታገለው ።

በጀርባው ትኩስ ላብ ኮለል እያለ ሲወርድ ይሰማዋል ። እንቀው ፤ እንቀው ፤ አንገቱን ጨምድደህ ማሺኑ ውስጥ ጨምረው ፤ ቀረጣጥፈው . . . የሚል ስሜት ህሊናውን ረብሾታል ። ስሜቱን እንደ ምንም ውጦ ዝም አለ ። የፊቱን መለዋወጥ ፤ የእጁን መንቀጥቀጥና በጀርባው ስር በቀጭኑ የሚወርደውን ላብ ማን ጉልማ ልብ ብሎታል ።

"እስኪ በኋላ እንነጋገርበታለን . . . ሰራተኛው ሁሉ በሁኔታው አዝኗል" አለ ጉልማ ።

"ያሳዝናል . . . ማን ምን ማድረግ ይቻላል? ዝም ብሎ ማየት ነው ፤ መጨረሻውን" አለ ታዴዎስ ፤ አሁንም የጉልማን አይን ላለማየት ፊቱን ወደ ማሺኑ እንዳዞረ ። "አዛኝ ቂቤ አንጓች . . . አንተን ብሎ ለአበራ ተቆርቋሪ! ይሁዳ ፤ እስስት ነህ" ይላል በሃሳቡ ።

"እንዴት ዝም ብለን እናያለን?" በማለት ጉልማ ጠየቀ ።

"ሞኝህን ፈልግ ፤ ሊታናግረኝ ነው አይዱል? ከእኔ ምንም አታገኝም ። ሰላይ ይሁዳ ፤ እስስት!" አለና በሃ ሳቡ ። "ታዴዎ ምን ማድረግ ይቻላል?" ሲል ጠየቀው ።

"እንዲፈታ መጠየቅ ነዋ!" አለ ጉልማ ፣ የተቆረ ቆረ በሚመስል ድምፅ ።

"እንግዲህ እናንተ ጠይቁዋ!"

"እንዴትን?" አለ ጉልማ የተቆጣ መስሎ ።

"ተመራጮቹ እናንተው ናችሁ ፤ እናንተው ብትጠ ይቁ ይሻላል" አለ ታዴዎስ ጉልማን ቀና ብሎ እይቶት ።

"አንተ ደግሞ እንዴት እንደዚህ ትላለህ? ሁላች ሁም መርዳት አለባችሁ ። ይኸ የማህበሩ ብቻ ሃላፊነት አይደለም" አለ ጉልማ ፣ እየተቆጣ ።

"እናንተው ስትጠይቁ ነዋ እኛ የምንረዳው!"

"እንዴት እንዲህ ትላለህ ? አበራ የቅርብ ጓደኛህ አልነበረም እንዴ? መረዳዳት እኮ በዚህ በዚህ ጊዜ ነው" አለ ጉልማ ፣ ድምፁን ከቁጣ ወደ ሃዘን ለውጦ ።

"ከእናንተ አይቀርበኝም" አለ ታዴዎስ ፣ ሊናገር ያሰበውን ሃይለ ቃል ከአፉ እየመለሰ ። "ለእኔ የስራ ባልደረባዬ ነው ። ይልቁኑ እናንተ አይደላችሁም እንዴ አብራችሁ ተመርጣችሁ የምትሰሩት?"

"ያም ሆነ ይህ ሰውዬው ያሳዝናል ። የልጆች አባት ነው ። እኔን ያሳሰበኝ የልጆቹ በረሃብ መሞት ነው ። እንዲፈታ መጠየቅ አለብን" አለ ጉልማ ።

"ልጆቹ ድሮስ ቢሆን መቼ ጠግበው በልተው ያውቃሉ?" አለ ታዴዎስ ። ቀና ብሎ ጉልማን እየውና

ፈገግ አለ ። ንዴት የተቀላቀለው መራራ ፈገግታ ። "ለልጆቹ ብታስቡ አይደል ያስያዛችሁትን?" አለ ታዴዎስ ፣ በሃሳቡ ።

"እስኪ በነገሩ ሁላችሁም አስቡበት" አለ ጉልማ ፣ ለመሄድ እየተሰናዳ ።

"እናንተ አስቡበት እንጂ. . . እኛማ ተራ ሰዎች ነን" አለ ታዴዎስ ፣ ጮክ ብሎ ። በአካባቢው የነበሩት ሰራተኞች ቀና ቀና አሉና ሁለቱን ሰዎች ተራ በተራ ተመለከቷቸው ። ጉልማ ከክፍሉ ወጥቶ ሄደ ።

"መናጢ ይሁዳ ፤ ባንተ ቤት አልታወቀብህም!" አለ ታዴዎስ ፣ እንደገና ጮክ ብሎ ። ድምፁን ግን ማሺኑ ውጦ አስቀረው።

መዋጮው በምስጢር ነበር የሚሰበሰበው ። ታዴዎስ ነበር የእርዳታውን ገንዘብ በድብቅ የሚሰበስበው ።

"ለመሆኑ የት ነው የታሰረው?" አለ አንዱ ሰራተኛ መዋጮውን አንድ ብር ለታዴዎስ ከሰጠ በኋላ ።

"ማን ያውቃል?" አለ ታዴዎስ ።

"ይፈቱት ይሆን ?"

"ምናልባት ፤ እኛ ከተባበርን ።"

"አዎን፣መተባበር አለብን...ለመሆኑ ልጆች አሉት?"
"አዎን ።"
"ስንት ?"
"ሶስት ።"

"አምስት ሰው ነው የታሰረው በለኛ!" አለ ሰራተኛው ፣ በመገረም ።

"እንዴት ?" አለ ታዴዎስ ፣ ቀና ብሎ ኢያየው ።

"ሶስት ልጆች ፣ ሚስቱ ፣ እሱ እራሱ ፣ ታዲያ ምን ትላለህ? አምስት አይደሉም ?"

"ልክ ነህ ፤ አምስት ናቸው ማለት ነው" አለ ታዴዎስ ።

"እሱስ አንደኛውን የለየለት የመንግሥት እስረኛ ነው ። ልጆቹና ሚስቱ ግን የቁም እስረኞች ናቸው ፤ የረሃብ እስረኞች ። ረሃብን አውቃለሁ ። ረሃብ የከፋ እስር ቤት ነው ። ስራ አጥቼ ተርቤ አውቃለሁ ። ልጆቼ ሲራቡ ምንም ማድረግ አቅቶኝ በአይኔ በብረቱ አይቻቸዋለሁ ። አዎን ፣ አበራን ማስፈታት አለብን ! ልጆቹን ከረሃብ እስር ማስፈታት አለብን ። ነግ በኔ ነው" አለ ሰውየው ፣ የሃዘን ስሜት ጉሮሮውን እየተናነቀው ።

"አዎን ፣ የተቻለንን ማድረግ አለብን ። ለጓደኞችህም ንገራቸው" አለ ታዴዎስ ።

"ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንደሚባለው ነው" አለ ሰውዬው ።

"ልክ ነህ ፤ ሁላችሁም በርቱ እንግዲህ" አለ ታዴዎስ ።

ይሄ በሆነ በሁለተኛው ወር ሚያዝያ ላይ ጠቅላላ ማህበሩ በህግ ታውቆ ነባር ። የአሰሪዎቹ ወገን ከአዲሱ ማህበር ጋር ገና ከጠዋቱ መጋፈጥ አልፈለጉም ። መጀመሪያ ማባበል ፤ አለበለዚያ በሃይል መጠቀም ፤ ይሄው ነበር ዘዴው ። በመሃሉ አበራ ተፈታ ።

ለጊዜው ቢፈታ ምንም አይደለም ። ካስፈለገ ቀስ ብሎ እንደገና ማሰር ይቻላል ። ፀባዩን ካሳመረ አሳመረ፤

አለበለዚያ . . . የጉልማም ሃሳብ ይኸው ነበር ። የእስረዎቹም የነ አጥላባቸውም ሃሳብ ተመሳሳይ ነበር ። በእንዲህ ያለ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበር — አበራ የተፈታው ።

በስራ አመራር ኮሚቴው ስብሰባ ላይ በነብር እንግድነት ተገኝቶ ነበር ። የጥቂት ወራት እስር ምንም ለውጥ አላመጣበትም ። ለእመታትም ቢታሰር የሚለወጥ አይነት ሰው አልነበረም ። በአካልም በመንፈስም በቀላሉ የሚሰበር አይነት ሰው አይደለም ። በመፈታቱ ግን ደስ ብሎት ነበር ።

"እስኪ አንድ ጊዜ እንደማመጥ" አለ የስብሰባው አስተባባሪ ፡ ከተቀመጠበት ተነስቶ ። "የቅርብ ጓደኛችን ፡ ወንድማችን ፡ የትግል አባታችን እንጋፋው የጥንቱ የጥዋቱ አበራ ፡ ለጠላቶቻችን ተንኮልና ጥላቻ ሳይበገር በሰዎች ፈቃድ ሳይሆን በእውነት ረዳትነት ከእስር በመውጣቱ የተሰማንን ደስታ በጭብጨባ እንግለፅ!"

ወዲያው የተሰበሰቡባት ትንሽ ክፍል በጭብጨባ ተናጋች ። ተናጋሪው ጭብጨባው ጋብ እስኪል ጠበቀና ቀጠለ ።

"አዎ ፡ አበራ እውነተኛ የሰራተኛው አጋር ነው ። የድሃ ወገን ስለሆነ ለድሃ ይቆረቆራል ። ሰው ሁሉ እኩል መሆን አለበት እያለ ከድሮ ጀምሮ የሚከራከር ፤ ማህበር እናቋቁም ብሎ መጀመሪያ ሃሳቡን ያፈለቀ . . . ከዚያም በዚሁ ምክንያት ብዙ ፍዳና መከራ የደረሰበት . . . እንደ ወርቅ በእሳት የተፈተነ ሰው ነው!"

እንደገና ተጨበጨበ ። አበራ አፈር ብሎ በእግሩ ወለሉን መታ መታ ያደርጋል ። ጉልማ አንድ ጊዜ ትግሮቹን ያነባብርና እንደገና ይነጣጥላቸዋል ። ደግሞ

እንዶገና ያነባብራቸዋል ። የእጁን ጣቶች ያንቋቋል ። ወንበሩ ላይ ይቁነጠነጣል ።

"ወንድሞቼ!" አለ ተናገረው እንዶገና ። "አበራ የጥንቱን እንጂ የዘመኑን ትምህርት አልተማረም ። ግን ሃሳቡን ስናየው እንዲያው ሲፈጥረው ልበ ብርሃን መሆኑን እናያለን ። የአበራን ታሪክ ሁላችንም በደንብ የምናውቀው ነው ። አሁን መደጋገሙ ማሰልቸት ይሆናል ። በአጭሩ ለማለት የምፈልገው . . . አዲስ የተቋቋመው ማህበራችን ማለትም የኢትዮጵያ ሰራተኞች አንድነት ማህበር ስራ አመራር ኮሚቴ ባደረገው ዝግ ስብሰባ አቶ አበራ የማህበሩ የክብር ፕሬዚዳንት እንዲሆን በድምፅ ብልጫ ወስኗል ።"

ቀሪው ንግግር በጭብጨባው ተዋጠ ። አበራ ከተቀመጠበት ሲነሳ ጭብጨባው ቆመና የተሰበሰቡት ሰዎች አይኖች በሙሉ ወደ እሱው አተኮሩ ።

"ወንድሞቼ" አለ አበራ በትህትና ። "በፊት ከስራ ስባረር ፣ ከዚያም በኋላ እስር ቤት እያለሁ እኔንና ቤተሰቤን በመደገፍ. . .ደግሞም ከእስር እንድፈታና ወደ ስራዬ እንድመለስ ሳደረጋችሁልኝ እርዳታ ሁሉ ከልቤ አመሰግናችኋለሁ ። አሁን ደግሞ የማህበሩ የክብር ፕሬዚዳንት እንድትሆን ብላችኋል ። ከሰራሁት ስራ ጋር ሲወዳደር የሚበዛብኝ ክብር ነው ። ቢሆንም ቃላችሁን ለማክበር እቀበለዋለሁ ። አሁን የተመረጡት ወንድሞቻችን ከዚህ በፊት ከእኔ ቢበልጥ እንጂ ከእኔ የማያንስ ትግል ሲያደርጉ ቆይተዋል ። መመረጣቸው ትክክል ነው ። እንደምታውቁት እያንዳንዳችሁን በእድሜ ብበልጥም ብዙዎቻችሁ ግን በትምህርት ትበልጡኛላችሁ ። ሰራተኛው ደግሞ የሚፈልገው የተማሩና መልሰው የሚያስተምሩትን ፣ በችሎታቸው የሚመሩትን ነው ።"

"በትግል ዘዴም ቢሆን ከእኔ የምትሻሉ ሞልታች ኋል ። በምንም አይነት እኔ ከእናንተ አልበልጥም ። እኔም እድሜዬ ያስተማረኝን እናንተም በትምህርት ያገ ኛችሁትን አንድ ላይ አድርገን ለሃገራችን እንስራ ። ስልጣኑን ከእናንተ አልቀበልም ። ስልጣኑን ለእናንተው ትቼ ከእናንተው ጋር ትግሉን ለመቀጠል ወደኋላ እንደማልል ግን እንደገና ቃል ኪዳን እገባለሁ ። ዞሮ ዞሮ ስልጣኑ የሰራተኛው ነው ። እኛ ተወካዮች እንጂ ባለ ስልጣኖች አይደለንም ። እኛ ነገ ጠዋት አላፊዎች ነን ። ሰራተኛው ግን ዘወትር ይኖራል ። ትናንትም ፤ ዛሬም ፤ ነገም ይኖራል!"

— 7 —

አበራ ከተፈታ በኋላ አራት ወራት ያህል አለፉ ። ቀላል ጊዜ አልነበረም ። አድራሻቸው የማይታወቅ ደብ ዳቤዎች በተደጋጋሚ ይደርሱት ነበር ። "...ከአንድም ሁለት ሶስት ጊዜ ብትሞክር አሻፈረኝ ብለሃል ... ስትለቀቅ የተነገረህን ቃል አላከበርክም ። አሁንም ቢሆን ብትጠነቀቅ ይሻልሃል ። አለበለዚያ ይቆጭ ሃል..." እነዚህን የመሳሰሉ ቃላት ነበር የሚላኩለት ።

ማን እንደሚደውል አይታወቅም ። የስልክ ጥሪዎች ይደረጉለታል ።

"ሃሎ...አቶ አበራ ነህ?"
"አዎን ፤ እኔ ነኝ ።"
"በቃ እምቢ አልክ አይደል? አስቸገርክ አይደል?"
"ምኑን? ምን አደረኩ?"
"ደብዳቤውን አነበብከው?"
"የቱን ደብዳቤ?"

"ትናንት የደረሰህን!"
"እዎን ።"
"ታዲያ አታርፍም ማለት ነው?"
"ምን አደረኩ?"

"ታውቀዋለህ ። ኋላ ግን ይፀፅትሃል ። ምናልባትም ለፀፀት ጊዜ አታገኝም ይሆናል . . ብታስብበት ይሻ ላል. . ."

ከዚያም ስልኩ ይዘጋል ። እንደገና በነጋታው ይደ ወላል ። ምልልሱ ያው ነበር ። እሱም ቢሆን ለምዶት ነበር ፤ ማስፈራራቱን ፡ ማስጠንቀቂያውን. . .ማንኛው ንም ነገር ። ጉሱ ግን ያፈዝባቸው ነበር ። ስራውን ግን ቀጥሏል ።

በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ ሌሎች ማህበርች ተቋቋሙ ። የማህበረተኛው ቁጥር እየበረከተ ሄደ ። የም ስጢሩም የግልፁም እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ነበር ።

ነሀሴ ወር ላይ ነበር የመጨረሻው ውሳኔ ለእንጉ ልማ የደረሳቸው ። ቀኑ እሁድ ነበር ። ጉልማ እስከዚያን ጉለት አጋጥሞት የማያውቅ ቀጠሮ ነበረው ፤ ሲኖራ ቤት ። እዚያው ወዳጁ ቤት ነበረ ያደረው ። ሌሊቱን ግን አልተኛም ነበር ። ጭንቀት ። የረጅም ጊዜ መሰረ ጥረቱ ውጤት ለማስገኘት መቃረቡን አጥላባቸው ማታ ደውሎ ነግሮት ነበር ። ነገሩ እውነት አልመሰለህ እያለው ሲጨንቀው ፤ ሲጠበው ፤ ሲበጠብጠው ነበር ያደረው ።

ጠዋት አጥላባቸው ቁርስ ላይ ነበር የደረሰው ። ጉልማ አጥላባቸውን ፊት ለፊት አግኝቶ ከእቶ ለመስ ማት ነበር የጓጓው ።

"እና ሻምበል ፥ ማታ በስልክ የነገርከኝ ነገር . . በቃ ተወሰኗል ማለት ነው?" አለ ጉልማ ፥ አንድ እግሩን

በሌላው ላይ እየደረበና መልሶ እየለያየ ። አስሩንም ጣቶቹን ተራ በተራ እንቋቋቸው ። በተከፈተው መስኮት በኩል የሚታየው ዝናም ያረገዘ ሰማይ ነው ። የተከፋ እሁድ ነበር ።

"አዎን፡ ተወስኗል. . .ግን ነገሩ ተፈፃሚ እስኪሆን ድረስ በከፍተኛ ምስጢር መጠበቅ ይኖርበታል" አለ አጥላባቸው ፡ ፎቴው ውስጥ ጢያም ብሎ ሞልቶ በሲጋራ ላይ ሲጋራ እያቦነነ ።

"በፊትም ቢሆን ለሙከራ ያህል ነበር የተለቀቀው" አለ አጥላባቸው ። እንደገና ፡ "ከተለቀቀ ጀምሮ ረቂቅ ክትትል ተደርጓል ። ሰጪዎው ግን አልተመለሰም ። የሚመልስም አይኑት ሰው አይያለም ። እንዲያውም እንደ ተከታተልነው ከሆነ እየባሰበት መጥቷል ። እነሱ የያዙት አላማ ሌላ ነው ። በማህበሩ ስም የሚሰራው ስራ ሌላ እንዲሆን ደርሰንበታል. . ."

"እኔ አላልኩህም? ደረሳችሁበት አይደለም?" አለ ጉልማ ፡ ፍንድቅድቅ ብሎ ።

"አዎን ፡ ትክክል ነበርክ. . .ለሌላ አላማ መሆኑን ደርሰንበታል ። እንዲያውም የውጪ እጅ ሳይኖርበት እንደማይቀር ይጠረጠራል. . .የኮምኒዩስቶች እጅ. . . በዩኒቨርስቲ ያሉት ቀንደኛ አዋቂዎች በነገሩ ሳይገቡበት አልቀሩም—እና ንጉሱም ጆሮ ነገሩ ደርሶ በጣም ተቆጥተዋል አሉ. . ." አለ አጥላባቸው ፡ ወፍራምና ቀይ ፊቱ ፍም እየመሰለ ።

"እንዴት ነው ታዲያ? መቼ ነው? ማለቴ. . ." ጉልማ አመነታ ፡ ሊጠይቅ ያሰበው ነገር ድንገት ጠፋበት።

"ቀኑ እንኳን እንዳልኩህ ምስጢር ነው. . .ነገሩ ግን አልቆለታል" አለ አጥላባቸው ፡ ፍርጥም ብሎ ።

ሁለቱም ሰዎች ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ቆዩ ።

"አንድ ጥያቄ. . ." አለ አጥላባቸው ፣ ድንገት ፀጥታውን በሚያንቃጭል ድምፅ ሰብሮ ። "ውሳኔው ሲፈፀም. . .ማለቴ እርምጃው ሲወሰድ ምን አይነት ሁኔታ የሚከተል ይመስልሃል? በሰራተኛው አካባቢ ማለቴ ነው ። እንዲሁ ለመነጋገር ያህል ነው እንጂ ውሳኔው ይለወጣል ማለት አይደለም!" አጥላባቸው ፣ ጉልማን ትክ ብሎ ይመለከተዋል ። አይኖቹ ቶሎ ቶሎ ክፍት ክድን ይላሉ ።

"ምንም! ምንም አይነት ሁኔታ አይፈጠርም!" አለ ጉልማ ፣ መቀመጫው ውስጥ እየተቁነጠነጠ ። "ካታምና እንዚያ ከሃዲዎች በየቦታው ቅጣታቸውን ሲቀበሉ ምን የተፈጠረ ነገር አለ? ምንም አልተፈፀመም! የሰውን እልልታ አታስታውሰውም?. . .ሰውዬው አደባባዩ ላይ ሲንጠለጠል? አሁንም ቢሆን ሰራተኛው እልል ነው የሚለው ። የመረቀዘ ቁስል ተቆርጦ ሲወድቅ እንደዔት ነው. . . በሽተኛው ወዲያው አይደል እፎይ የሚለው? እንደዚያ ማለት ነው. . .ግልግል ነው ። ለሌላውም ትምህርት ይሆናል ። ከዚያ በኋላ ንቅንቅ የሚል ሰው አይኖርም!"

"ቆይ ቆይ ቆይ. . .አንድ የረሳሁት ነገር. . ." አለ አጥላባቸው ፣ ጉልማን አቋርጦት ። "ታዴዎስን ታውቀዋለህ አይደል? ታዴዎስ ማን ነበር? ቆይ. . ."

"ታዴዎስ ማን?" አለ ጉልማ ፣ በችኮላ ።

"ቆይ እስኪ የአባቱን ስም ዘንጋሁት. . ." አለና አጥላባትው ከደረት ኪሱ ውስጥ የብዙ ሰዎች ስም የተፃፈበትን ማስታወሻ አውጥቶ አይኖቹን ወረቀቱ

ላይ እንከባለላቸው ። ከዚያም አይኖቹን ጉድጓዶቻቸው ውስጥ አሽከረከረና ቀና አለ ።

"እ . . .አዎን ታዶዎስ. . .ታዶዎስ ምትኩ" አለ አጥላባቸው ፣ ጉልማን በሚጠይቁ አይኖቹ ትኩ ብሎ እያየው ።

"አ . . .ታዶዎስ የኛው!. . .እሱንማ በደንብ አውቀዋለሁ ። እኔ ደግሞ ሌላ ሰው መስሎኝ. . .ታዶዎስ ምትኩ አ!. . .የጭቃ እሾህ. . .እምም!" አለ ጉልማ ፣ እራሱን እየነቀነቀ ።

"ለመሆኑ እንዴት ያለ ሰው ነው? ብዙ ጊዜ ልጠይቅህ እፈልግና ምን እንደሆነ አላውቅም እረሳዋለሁ" አለ አጥላባቸው ።

"ታዶዎስ. . .አዎን ፣ መጀመሪያ ነገር እንዳልኩህ. . .ምን ልበልህ ፤ ምን እንደሚሰራ ምን እንደሚያስብ አታውቅበትም ። ልዝብ ሰይጣን ቢጤ ነው ። እንደ መልኩ አይደለም ። እና ፣ በተረፈ የአበራ የቅርብ ጓደኛው ነው ። እሱ ግን ጠይቄው ክዶኛል ። የስራ ጓደኛዬ ነው ነው የሚለው ። ከእሱ ጋር የዋለ ምን ጤነኛ ይሆናል ። 'ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝና. . .' የሚባል የፈረንጆች ምሳሌ አለ አይደል?"

"እንደሱ አይደለም ። እኔ የምፈልገው ተጨባጭ ማስረጃ ነው! እና በግልፅ ለመናገር ሰዎቻችን ሰሞኑን አበራ መኖሪያ ቤት አካባቢ ተሰማርተው ነበር. . . እና ፣ አበራ ቤት ሲገባም ሲወጣም በተደጋጋሚ የታየው እሱው መሆኑ ሪፖርት ስለ ደረሰኝ ነው ለማጣራት የጠየኩህ ። በተጨማሪም ሌላ መረጃ ካለ ሊጠቅመን ይችላል ። እርምጃ ከመውሰዱ በፊት እንደዚህ

አይነት ነገሮች ተጣርተው ጥንቃቄ መደረግ አለበት” አለ አጥላባቸው ፣ ፍርጥም ብሎ ። “በታዴዎስና በአበራ መካከል ከግል ወዳጅነት ሌላ ምን ይኖራል ብለህ ትጠራጠራለህ?”

“ይገርምሃል እኮ. . .አዲስ ስራ ነው የምትሰጠኝ ። እንዴት እስከ ዛሬ እንዳላሰብኩበት ለራሴም ገርሞ ኛል ። እንዳልኩህ ሰውዬው ልዝብ ሰይጣን ቢጤ ነው ። . . .አይግረምህ እንጂ ሁል ጊዜ ሳስበው ከአበራ ጀርባ ይኸንን ሁሉ ነገር የሚያመነጨው ታዴዎስ እንደሆነ ሆኖ ነው የሚሰማኝ ። ታዴዎስ ተምሯል ። በዚያ ላይ የሚቀርቡት ሰዎች በጣም ብልጥ ነው ሲሉ ሰምቻ ለሁ ። ደግሞም. . .እንዲያው ሳየው ቢቃ. . .አንድ ነገር እንደሚሰራ ይሰማኛል ፤ ግን ለምን እንደሆነ እንጃ. . . እዘነጋጥለሁ ። አሁን መቼ እለት እንኳ ያ ቀልቤሳ የነ ገረኝን ነገር እንዴት እንዴ ዘነጋሁት አሁን ነው ትዝ የሚለኝ ‘ማዶና!’ ትላለች ሲኖሩ. . . እንደዚህ እንደኔ ሲገርማት እኮ ነው!” አለ ጉልማ ፣ እየተገረመ ።

“ምንድነው የነገረህ?. . .ቀልቤሳ ነው ማነው ያል ከው ሰውዬ?” አለ አጥላባቸው ፣ ፍሬ ነገሩን ለመስማት እየጓጓ ።

“ይኸውልህ ፤ አበራ የታሰረ ጊዜ እርዳታ እንዲሰ በሰብለት ሲያስተባብር የነበረው እሱው ነበር አሉ ። አንድ በል ። ሁለተኛ ደግሞ የስራ ማቆም አድማ እና ድርግ ይል ነበር አሉ ። ሶስተኛ. . .”

“ታዲያ ያን ጊዜ እንዴት ሳትነግረኝ ቀረህ?” አጥላባቸው አቋርጦት እንባረቀበት ። ከዚያም ድምፁን ዝቅ አድርጎ ቀጠለ ። “ከዚህ የበለጠ ምን ማስረጃ ትፈልጋለህ? ፋብሪካውን በእሳት ካጋዩት ወይንም

ባለቤቱን ካልገደሉት ወንጀለኝነታቸው አይረጋገጥም ማለት ነው?”

“ይገርምሃል. . .እውነትህን ነው ። ምን እንዳሬዘ ዘኝ ግን አላውቅም ። ዘነጋሁት ። ደግሞም በሃሳብ ላይ ሃሳብ እየተደራረበብኝ በቃ. . .እውነት ግን እንደዬት ሳል ነግርህ እንደ ቀረሁ ለእኔም ይገርመኛል ። ሰውዬውን ግን ሁልጊዜ እጠረጥረዋለሁ” አለ ጉልማ ፣ እራሱን ለማረም እየሞከረ ።

አጥላባቸው በፊገዝ ሳቅ ብሎ የጎሪጥ አየው ። ጉልማ ደበልጥ ተረበሸ ።

“ምነው ሻምበል?. . .ምን መሰለህ ፣ የእኔ ግምት ነው. . .በጣም እጠረጥረዋለሁ” አለ ጉልማ ፣ በሚለማ መጡ አይኖቹ አጥላባቸውን እያየው ።

አጥላባቸው እንደገና ሳቅና መለሰለት ።

“የሁለታችንም ግምት አንድ መሆኑ ነው ያሳቀኝ” አለ ፣ ያሳቀውን ምክንያት ለጉልማ ላለመናገር ሌላ ዘዴ እየፈለገ ።

“እንዳየሁህ አንድ ትልቅ ተሰጥኦ አለህ—መጠር ጠር ። ሁሉን ነገር መጠርጠር ፣ መጠራጠር ። ይኸ ነው ትልቁ ችሎታ ። ማኪያቬሊ የሚባል ፈላስፋም ይኸንኑ ነው ያለው ። ስለ እሱ ሰምተህ ታውቃለህ? አዎ ፣ መጠ ርጠር የታላላቅ ሰዎች ዋናው መለያ ፀባይ ነው ብሏል ። ማኪያቬሊ. . .” አለና አጥላባቸው እንደገና ሳቀ ።

“ብዙ ጊዜኮ የሁለታችን ግምት ይመሳሰላል. . . ለዚህ ነው መሰለኝ ነገሩ ሁሉ የሚሳካልን ።” ጉልማ ፈገግ ብሎ መለሰለት ።

"ለማንኛውም ፣ እንግዲህ እንዳልኩህ ስሞኑን ሁሉም ነገር እልባት ያገኛል ። በነገራችን ላይ . . .ስለ ታዴዎስ የጠየኩህ እንደዚሁ አይደለም ። ለጥንቃቄ ያህል እሱም ዛሬ ተይዟል ። አሁን ግን መሄድ አለብኝ ። ስለ ሁኔታው ለማንም እንዳይነገር ። ፈረንጆቹም ቢሆኑ እንዳያውቁት ። ወደ ማታ ተመልሼ እመጣለሁ ። እ፤ እስኪ ስለ ገንዘቡ ጉዳይ ያንን ሰላቶ እንደገና አስታው ሰው. . ." አለና አጥላባቸው ከተቀመጠበት ተነሳ ። ከዚያም በተከፈተው መስኮት በኩል ወደ ውጪ ተመ ልክቶ የዝናቡን ማባራት ካረጋገጠ በኋላ ወጥቶ ሄደ ።

ጉልማ በረጅሙ ተንፍሶ ከተቀመጠበት ተነሳና ቆመ ። አጥላባቸው ሲሄድ ለምን ሰላምታ እንዳልሰጠው ጥቂት አሰላሰለና እንደገና በቁሙ ፎቴው ውስጥ ወደቀ ። ከዚያም ቅልጥሞቹን አነባበረና እንደገና ነጣጠላቸው ። አንድ ስድስት የሚሆኑት ጣቶቹን አንቋቋቸውና በተከ ፈተው መስኮት በኩል ውጪ ውጪውን ተመለከተ ። ወዲያውም የአጥላባቸውን መኪና ተነስታ ስትሄድ አዳመጣት ።

"የራሳቸው ጉዳይ ነው. . .ከእንግዲህ ወዲያ እንዳ ፈለጉ ያድርጓቸው. . .ዋናው ነገር መውገዳቸው ነው. . . እኔ ምንቸገረኝ ፤ እኔ አልወሰንኩ. . .እንግዲህ ስራቸው ያውጣቸው" አለ ጉልማ ፡ በሃሳቡ ። ለረጅም ጊዜ በጉጉት ሲጠብቁት የነበረ ነገር ሊፈፀም አንድ ቀን ሲቀረው የሚሰማው አይነት ጭንቀት ያዘው ። ጉልማ ሳያስበው ከተቀመጠበት ተነሳና ረጅም ሰውነቱን እየ ጎተተ ወደ ሲኞራ መኝታ ቤት ሄደ ። ሲኞራ አልጋው ላይ ተቀምጠው የእግሮቻቸውን ጥፍሮች ቀለም ይቀ ባሉ ። ጉልማ አጠገባቸው ተቀመጠ ። ሲኞራ የጥፍር ቀለሙን አልጋው አጠገብ ካለው ኮመዲኖ ላይ አስቀ

መጡና ክንዶቻቸውን ጉልማ አንገት ላይ ጠምጥመው፣ “ደስ አይልም፣ አምሬ ሚዮ!” አሉት ።

“ልቀቂኝ እባክሽን!” አለና ጉልማ ያቅፉትን የሲኞራን ክንዶች ከአንገቱ ላይ ካላቀቀ በኋላ አልጋው ላይ በጀርባው ተጋደመና አይኖቹን ጨፈናቸው ። ሃሳብ እንጂ መኝታ አልነበረም. . .

— 8 —

ነሀሴ 28 ቀን 1955 ። ቀኑን ሙሉ ሲዘንብ ነበር የዋለው ። አበራ ከስራ እንደ ተመለሰ በዝናብ የበሰበሰ ውን ልብሱን አውልቆ ሽቦ ላይ ካሰጣ በኋላ አሮጌ ልብስ ቀይሮ ከአግዳሚው ወንበር ላይ አረፍ ብሎ ነበር ። ከዚያም በሻይ ጀበናው ውሃ ሞላና ከሰል ምድጃው ላይ ጣደው ። ያከፋል ። ትንሽ ቆይቶ የቤቱ በር በሃይል ይን ኳኳ ጀመር ።

ከምሽቱ በግምት አንድ ሰአት ቢሆን ነው ። ዝናቡ እንደገና በሃይል መውረድ ጀመረ ። የቤቱ በር አሁንም ይንኳኳል ። ነገሩ አላማረውም ። ተጠራጠረና ዝም ብሎ ማዳመጡን መረጠ ። ብዙነሽ እራሱን ልጅ እቅፉ ተኝታለች ። መንኳኳቱ ሲበረታና ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁለቱ ልጆቹ መፍራታቸውን ሲያዩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጠየቀ ፤ “ማነው? ማነው የሚያንኳኳው?” መልስ የለም ። መንኳኳቱ ለጥቂት ጊዜ አቋረጠና እንደ ገና ቀጠለ ።

ከሰል ምድጃው ላይ ሻይ ፡ ጀበናው ውስጥ ይንተከ ተከል ። በመጀመሪያ በሩ ሲንኳኳ ከዝናቡ ሸሽቶ ለመ ጠለል የመጣ ሰው ነበር የመሰለው ። አበራ ወደ በሩ

ተጠግቶ በቀዳዳ ውጪውን ሲመለከት ነበር ሌላ ነገር መሆኑን የተረዳው ። ሁለት ሰዎች በሩ ላይ ቆመው ይንሾካሾካሉ ። ምን እንደሚባባሉ ግን አልሰማም ። እንደገና ጆሮውን በሩ ላይ ለጠፈና አዳመጠ ። "ቆይ አትቸኩስ!" ይህን ቃል ነበር የሰማው ።

አበራ እየሮጠ ሄዶ የአልጋውን ትራስ ከገለጠ በኋላ በእጁ እየዳበሰ መፈለግ ጀመረ ። ከዚያም ፍራሹን በረቀሰውና የሚፈልገውን አገኘ ። ካርታው ውስጥ የቀሩትን ጥይቶች ተመለከተ ። ሁለት ብቻ ነበሩ ። ሁለት ብቻ ። እራሱን ነቀነቀ ። ከዚያም ታደሰምስን አስታወሰ ። ተጨማሪ ጥይቶች እንዲወስድ ነግሮት ነበር—በዚያን ሰሞን ።

ሽጉጡን ካቀባበለ በኋላ ሁለቱን ልጆች አልጋው ስር አስገባና አስተኛቻቸው ። ብዙነሽን ግን ሊቀሰቅሳት አልፈለገም ። ጧ ካለ የድካም እንቅልፍ ውስጥ ነበረች ፤ የእራስ እንቅልፍ ።

በሩ እንደገና ተንኳኳ ። አበራ አልጠየቀም ። ሽጉጡን ወደ በሩ ደግኖ ቆሟል ።

"ክፈት! በሰላም በሩን ክፈት!" አለ አንድ የተረበሸ ድምፅ ከውጪ ። አበራ አልመለሰም ። ሁሉ ነገር ገብቶታል ። ምን እንደሚፈልጉ ፤ ማን እንደሆኑ ገብቶታል ።

"ጎበዝ" አለ አበራ በሃሳቡ ፤ "እንግዲህ አሟሟታችንን ማሳመር አለብን!" አጠገቡ ማንም ሰው የለም። በሃሳቡ ለሚታዩት ሰዎች የሚያስተላልፈው የመጨረሻው መልእክት ነበር ። የተኩሱ ድምፅ ነበር ከሃሳቡ የመለሰው ።

ወደ አባሬ ቤት ከሚያመጣው ኮረኮንች መንገድ ላይ አንዲት መኪና ጨለማው ውስጥ ቆማለች ። በውስጧም መልካቸው የማይታይ ሰዎች መሳሪያዎቻቸውን በተጠንቀቅ እንደ ያዙ ተቀምጠዋል ። ቤቱም ተከቧል ። ዝናቡ እንደገና በሃይል መጣል ጀመረ ።

የእጅ መትረየስ ነበር የተተኮሰው ። ዝናቡ ግን ድምፁን በከፊል ውጦታል ።

በመናኛ ጣውላ የተሰራው የቤቱ በር መሃል ለመ ሃል ወንፊት ሆኗል ።

ደግሞ ደጋግሞ ተተኮሰ ። አሊጋ ስር የነበሩት ልጆች በሃይል ጮሁ ። ብዙነሽ ባንንችና ክተኛችበት ተነሳች ። ወዲያውም የመንደሩ ውሾች በሃይል መጮህ ጀመሩ ።

"ስማ! አበሬ! በሰላም እጅህን ብትሰጥ ይሻል ሃል!" ያው የተረበሸ ድምፅ እንደገና ተጣራ ። አበሬ አልመለሰለትም ። አሁን ሁሉ ነገር ገብቶታል ። ምን እንደሚፈልጉ ገብቶታል ።

ቅድም ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ ነበረች ብዙነሽ ። እናም ፡ ሲያቃዠት ነበር ። ከወንዝ ዳር የቆመች ይመስላታል ። ደሮ ፤ ድሮ ሃገር ቤት የምታውቀው ጅረት ነው ። ሶስት ሰዎች ናቸው ፤ እሷ አበሬና ሌላ አንድ የማታውቀው ሰው ። አበሬ የወንዙን ጥልቀት ለመፈተሽ አንድ እግሩን ጅረቱ ውስጥ ይጨምራል ። ብዙነሽ ከዳር ሆና በሲጋት ትመለከተዋለች ። ከዚያም ፤ 'ነይ አይዞሽ እንሻገረዋለን' ይላትና ከንዷን ይዞ ወንዙ ውስጥ ይገባሉ ። ብዙነሽን ያሻግርና ሁለተኛውን ሰው ለመውሰድ ሲመለስ መሃል እንደ ደረስ ድንገት

የውሃ ሙላት እየገስገሰ ፣ እየዘለለና አረፋ እየደፈቀ ይመጣል ። አበራ ከደራሹ ውሃ ለማምለጥ ወንዙ ውስጥ እየተንቦጫረቀ ይሮጣል ። ዳር ለመድረስ በግምት አንድ አስር እርምጃ ሲቀረው ፣ ጐርፉ እግሩን ይጠልፈውና ውሃው ውስጥ ይወድቃል ። ከዚያ በኋላ አበራ አይታ ይም ። ብዙነሽ ከዳር ሆና ትጮሃለች ። ወንዙ ዳር ዳር እየሮጠች ትጮሃለች ። 'አበራ! አበራ! ወሰደው! ወሰደው! ውሃ በላው! ለሰው ብሎ ነው! ሰው አሻግራ ለሁ ብሎ ነው! ያገር ያለህ! ኡ! ኡ! ኡ!'

ተኩሱና የልጆቹ ጩኸት ነበር ከቅዠቷ የመለሳት ።

አበራ አንድ ጥይት በበሩ አቅጣጫ ተኮሰ ። የጥ ይቷ ድምፅ በውሾቹ ጩኸትና በዝናቡ ተውጦ ቀረ ። እንደገና የመትረየስ ተኩስ እንደ ፈንድሻ ተንጣጣ ።

"አበራ! ስማ! በሰላም እጅህን ስጥ ፤ አታመል ጥም!" ያው የተረበሸ ድምፅ እንደገና ተጣራ ። "ፈሪ ዎች! ለአንድ ሰው ይሄ ሁሉ?" አለ አበራ—በሃሳቡ ። ከዚያም ሁለተኛውን ጥይት በተሰነጣጠቀው በር ላይ ተኮሰ ። በሩ ወንፊት ሆኗል ። ብዙነሽ ከአልጋው ላይ ዘላ ወረደች ። ልጆቹ ከአልጋው ስር ወጡ ። ቤቱ በጩ ኸት ተደበላለቀ ። ወዲያውም ተኩሱ ቆመ ። የመን ደሩም ውሾች መጮሃቸውን አቆሙ ።

ሽጉጡ ከተዝለፈለፈው እጁ አምልጦ መሬት ወደቀ ። ከዚያም ሆዱን በሁለት እጆቹ ይዞ እየተንገዳ ገደ ወደ በሩ ተጠጋ ። በተሰነጣጠቀው በር በኩል ሲያ ካፋ ይታያል ። የሰው ኮቴ በጭቃው ላይ ሲንቦጫረቅ ይሰማል ።

ወዲያውም እጁ ላይ ለስስ ያለ ውሃ የሚመስል እርጥበት ተሰማው ። ጎንበስ ብሎ እጆቹ ያረፉበትን ቦታ

ተመለከተ ። ደሙ በጣቶቹ መካከል እያለፈ መሬት ላይ ይንጠባጠባል ። ከዚያም በጉልበቱ መሬት ላይ ወደቀና እንደ ተቆረጠ ዛፍ በደረቱ ተደፋ ። ደሙ በቀሚሱ እየወረደ ደፉ ዘንድ ሲደርስ ትንሽ ኩሬ ሰርቶ ረግቶ ቆሟል።

በሃይል ይተነፍሳል ። በደረቱ ከተደፋበት ጥርሱን ነክሶ እንደ ምንም ወደ ጎኑ ዘንበል ብሎ ጭንቅላቱን መሬት ላይ ካጋደመ በኋላ በበሩ ስንጥቅ ውጪውን ይመለከት ጀመር ። የሚነጋ እንጂ እየጨለመ የሚሄድ አልመሰለውም ። ጎህ ሲቀድ የሚታየው አይነት ብርሃን ነበር ። የብዙንሽ ጩኸት ከሩቅ የሚሰማ የገደል ማሚቶ መስሎ ህሊናው ውስጥ ያስተጋባል ። ከዚያም እጁን በግድ ዘረጋና በጣቶቹ መሬቱን ቧጠጠ ። ሽጉጡን ነበር የሚፈልገው ። አስታወሰ ፤ ሁለት ጊዜ መተኮሱን ። ወዲያውም መፈለጉን ተወው ።

አሁንም ያካፋል ። አበራ ከተኛበት በታ ሆኖ ውጪ ውጪውን ይመለከታል ። ትዝ አለው ። ልክ እንደዚህ ካፊያ በሆነ ቀን ነበር ፤ ከሃያ አምስት አመታት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ከተማ የመጣው ። እንዴት እንደመጣ አስታወሰ ። የመጣበት መንገድ ትዝ አለው ። አባቱ ሲሸኙት የተናገሩት ትዝ አለው ። “አበራ ፤ ይኸ ሁሉን እምቢ ማለት ምንም አይሰራልህም ። አሁን ልጅ ነህ ፤ ኋላ ግን ታዩዋለህ ፤ አያዋጣህም ። መስለህ ማደር ነው ። ከተማው እንደ ባላገር አይደለም ። እዚያ ባይተዋር ነህ ፤ ብቻህን ነህ ፤ የድሃ ልጅ አንገቱን ደፍቶ ነው የሚኖረው ። ሁሉን እሺ ብሎ ነው የሚኖረው ። ሰውም ያዝንለታል. . .” ብለውት ነበር—አባቱ ። ሌላም ብዙ ብዙ ነገር ብለውታል ። አሁን ግን ይኸ ብቻ ነበር ትዝ ያለው ። “ብቻዬን ሆኜስ አላውቅም. . .” አለ አበራ በሃሳቡ ።

እንደገና ሃሳቡ ወደ ቤቱ ተመለሰ ። ያቃስታል ።

“ውሃ! አንድ ብርጭቆ ውሃ!” እያለ የሚጮህ ይመስለዋል ። አፉ ግን አይንቀሳቀስም ። ውሃ መጠጣት ፈልጎ ነበር ። ይኸንን ሆዱ ውስጥ እንደ እሳት ገሞራ የሚቃጠለውን ነገር ማብረጃ . . . አንድ ብርጭቆ ውሃ ። ከዚያ በኋላ ሰላማዊ መኝታ ፤ ይኸን ነበር የተመኘው ። ከሩቅ ጅብ ሲጮህ የሚሰማ መሰለው ። “ገና በቀን. . . የቀን ጅብ” አለ በሃሳቡ ። “ቢቃ መጨረሻዬ መሆኑ ነው. . .ብለው ብለው በመጨረሻ አገኙኝ. . .አዎን ፤ ቀደሙኝ. . .ታዴዎስ ጥይቱን ውሰድ እንዳለኝ ብወስድ ኖሮ. . .ግን ምን ያደርጋል ። እነሱ ብዙ ናቸው! መትረየስ ፤ ለአንድ ሰው መትረየስ. . .”

“ብዙነሽ እንዴት ሆና ይሆን? እንዴት ትሆን ይሆን? አራስ ነች. . .ሶስት ልጆች. . .ምንም የላትም እኮ ፤ ምስኪን. . .ያው ገጠር ዘመዶቿ ጋ ትመለስ ይሆናል. . .ልጆቹ እዚያው እንደ ምንም እረኛም ፤ ኮኩል አራሽም ፤ አሽከርም ሆነው ያድጋሉ. . .እዚህ ከተማ ገላዋን ሽጣ እንኳን ልታሳድጋቸው አትችልም . . . በወሊድ የተጎሳቆለ ሰውነት. . .ማን ይፈልገዋል. . . ማንም አይፈልገውም. . .”

ከዚያም ብዙነሽን እንዴት እንዳገኛት ትዝ አለው ። ያኔ ፈረንጅ ቤት ስትሰራ ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነበረች ። ሰውነቷ እንኳን ገና አድጎ አላበቃም ነበር ። እንዴት እንደ ተዋወቁ አስታወሰ ። እሱም ገና ሙሉ ጎረምሳ ነበር ። ከስራ ሲመለስና ወደ ስራ ሲሄድ ብዙነሽ ተቀጥራ በምትሰራበት ቤት በኩል ነበር የሚመላለሰው ። ሁልጊዜ ያያታል ። ወይ ግቢው ውስጥ አለበለዚያም በር ላይ ያያታል ። ታየዋለች ። በሌላ መንገድ መሄድ

ያስጠላዋል ። ምን እንዲሆን ሳያውቀው ወደ ስራ ለመሄድ ሲሰናዳ እዚያ መንገድ ላይ ስለሚያያት ልጅ ያስባል ። ግራ ይገባዋል ። ከምትሰራበት ቤት አጠገብ ካለው ጎረቤት ይሄድና ስለ ልጅቷ ያጣራል ። እሷም ለካ ከተማው ውስጥ ዘመድ አዝማድ አልነበራትም ። እንደ ታጨች ነበር ከትውልድ ሃገሯ ጠፍታ የመጣችው ። ትንሽ ቆይቶም ባለ ሱቁን ሽምግልና ይልካል ። ማን መሆኑን ስታውቅ አላመነታችም ነበር ። ለካ ከዚያ ዘወትር ልነቅሽ እያለ ከሚያስቸግራት የገቢው ዘበኛ የሚያላቅቃት ሰው ነበር የምትፈልገው ። የመጀመሪያውን ልጅ ስትወልድ በደንብ አልታረሰችም ነበር ። ሰውነቷ እንደተጎዳ ቀረ ። ልጅ ሲደጋገም ከስራ ወጣች ። አበራ ሲታሰር ሲፈታ ኑሮ አላመች አለ . . .

“አዎን ፣ ገላዋን ቸርችራ እንኳን ልጆቹን ማሳደግ አትችልም” አለ አበራ ፣ በሃሳቡ ፣ ከወደቀበት ሆኖ እያቃሰተ ። ትኩስ ላብ መላ ሰውነቱን አዝፍቆታል ። “በፍፁም አትችልም ። ማን ይፈልጋታል? ካለኔ ማን ይፈልጋታል? ልጆቹንስ ቢሆን ማን ይፈልጋቸዋል? አባት የሌላቸው ልጆች ማን ይወዳል? እሷም ሃዘኑን አትችለውም. . .

“ያ ታዴዎስ የት ይሆን? እሱንም አግኝተውት ይሆን? ያንን ቤት አግኝተውት ይሆን ?”

“ብቻ እንኳን ማህበሩ ተቋቋመ! ካሁን ወዲያ ሊያፈርሱት አይችሉም! እርግጠኛ ነኝ! የቀረውን ስራ ሌሎች ይሰሩታል ። በእርግጥ ይሰሩታል! ይሰሩታል. . . ይሰሩ . . ይሰ. . .ይ. . .”

ህዳር 1967 ። ከሰአት በኋላ ነበር ። አንድ ሰውዬ የትልቁን ወህኒ ቤት በር አልፎ ሽቅብ ወደ ሜክሲኮ አደባባይ የሚወስደውን አውራ መንገድ ተከትሎ ይጓ ዛል። ቀጭንና ረጅም ሰው ነው ። ተጠቅልሎ በገመድ የታሰረ ብርድ ልብስ ጎኑ ላይ አስደግፎ በአንድ ክንዱ አቅፎ ይዞአል ። የጭንቅላቱ ፀጉር ከጆሮ ግንዱ ስር ሽበት ጣል ጣል አድርጎበታል ። ያጎፈረው ፂሙ እን ዲሁ መሸበት ጀምሯል ። ጉንጩ በጥፊ እንደ ተመታ ከሁለት ፊት ተሰርጉዶ ግራና ቀኝ አጥንቱ አፍጥ ጧል ። አይኖቹ ስርና ግንባሩ ላይ ረጃጅም መስመሮች ቢስመሩበትም የድሮ መልከ መልካምነቱ ጨርሶ አል ተደመሰሰም ። የጊዜው መርዘምና ያሳለፋቸው የመከራ አመታት አሁንም በአይኖቹ ላይ የሚበራውን ውስጣዊ ሃይል ጨርሰው አላደበዘዙትም ።

ግራና ቀኝ አካባቢውን በተራቡ አይኖቹ እየቃኘ ሽቅብ ደሩ ደሩ ይላል ።

ሜክሲኮ አደባባይ አጠገብ ካለችው ቡና ቤት በራፍ አጠገብ መሬቱ ላይ የብዙ ሰዎች ፎቶግራፎች ተደርድረዋል ። አጠገባቸውም አንድ ልጅ ቆሞ አላፊ አግዳሚውን በሚያግባቡ አይኖቹ እየተመለከተ እንዲ ገዙት ይጠይቃል ።

"ምንድነው አንተ ይሄ?" አለ ሰውዬው ፥ ቆም ብሎ ፎቶግራፎቹን እያየ ።

"የሚሸጥ ነው" አለ ልጁ ።

"ማነው የሰጠህ?" አለ ሰውዬው ፥ እየተጠራጠረ ።

"ተማሪዎች. . .ተማሪዎች ናቸው ።"

ሰውዬው ፎቶግራፎቹ ላይ ጎንበስ አለና እንደገና መሬት ላይ በርከክ አለ ።

"ምንድናቸው ታዲያ እነዚህ. . . ታውቃቸዋለህ?" አለ ሰውዬው ። ልጁም አጠገቡ በርከክ አለ ።

"ይሄ ተማሪ ነበር. . .ይሄ ወታደር ነበር. . .ይቺ ኛዋም ፀጉሯን ያጎፈረችው ተማሪ ነበረች. . .እኚህ ደግሞ አርበኛ ነበሩ አሉ. . .ይሄ ደግሞ ሰራተኛ ነበር. . ." አለ ልጁ ፣ የሰዎቹን ማንነት በቃሉ እንዳስጠኑት ሁሉ አንድ በአንድ ፎቶግራፎቹን በጣቱ እየጠቆመ ።

ወዲያውም የሰውዬው አይኖች ከዶጋኑ እንዳመለጠ ቀስት ድንገት ተወረወሩና ከመጨረሻው ፎቶግ ራፍ ላይ ተተከሉ ። ልቡ በአንድ በማይታይ ሃይል ለሁ ለት የተሰየፈ ይመስል ከተቀመጠበት ቦታ ውሃ ሆኖ ቀረ ። ከዚያም ፎቶግራፉን በሚንቀጠቀጡት ጣቶቹ አነሳና ወደ አይኖቹ አስጠግቶ ትክ ብሎ አየው ። የዚህን ጊዜ እንባው ድንገት አይኖቹ ላይ ተከለበሰና ምራቁን ደጋግሞዋጠ ።

ከፎቶግራፉ ግርጌ ተፅፎበታል ፣ "አበራ ፣ የመጀመ ሪያው የሰራተኞች መሪ ። በወደቀው መንግስት በግፍ የተገደለ" ይላል ፅሁፉ ።

"እ. . .እሱን ሰውዬ ያውቁታል እንዴ ጋሼ?" አለ ልጁ ፣ በሰውዬው ሁኔታ ተገርሞ ። አልመለሰለትም ። ለአስራ ሁለት አመታት ልቡ ውስጥ ተዳፍኖ የነበረው እሳት እንደገና ሲግም ተሰማውና መላ ሰውነቱ ሲቆ ጣጠረው ባልቻለ ስሜት ነዘረ ።

“ስ. . .ስንት ነው የሚሸጠው?”

“አንድ ብር ብቻ ነው” አለ ልጁ ።

ሰውዬው ገንዘቡን ከፈለና ፎቶግራፉን ይዞ ለብቻው እየተነጋገረ ሄደ ። “አበራ. . .አበራ. . .እውን ስምህና ስራህ ታውቀ?. . .የድሃው አጋር ፤ ጀግና እኮ ነበርክ. . .አበራ. . .እውነተኛ ጀግና. . .አዎን ፣ አንተን እንጂ ሃሳብህን መግደል አልቻሉም. . .” ከአስራ ሁለት አመታት በኋላ ልክ አበራን በአካል አግኝቶት የሚያነጋግረው ነበር የመሰለው ።

“አበራ. . .” ይላል ሰውዬው አሁንም አሁንም ። “አበራ. . .ሞትን ያሸነፈ ጀግና!”

ታዴዎስ የአበራን ፎቶግራፉ አሁንም አሁንም እየተመለከተና ብቻውን እየተነጋገረ ሃዘኑን ዋጥ አድርጎ እግሩ ወደ ወሰደው አቅጣጫ ይጓዝ ጀመር ። በመንገዱ ደሴት ላይ በተተከሉት የጥድ ዛፎች መካከል የቀለጠ ወርቅ መስሎ እየነጠረ የሚያልፈውን ጨረር ሲመለከቱት ግን ፣ ያን እለት ምንም ፀሃይ ባልጠለቀች ያስኝ ነበር ። ሁሉም ነገር እንደሊያ እንደ ፀሃይ ብርሃን እንደ ተዋበ ትንሽ ቢቆይ ፤ እናም ፣ ሰዎች ሁሉ ያንን እያዩ ለአፍታ እንኳን በምድር ላይ ያለውን ክፋትና ሰቆቃ የሚቋቋሙበት ሃይልና ተስፋ አግኝተው ደስ ባላቸው የሚያስኝ ነበር ።

ታዴዎስ ፣ ከአስራ ሁለት አመታት በኋላ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያች መንገድ ላይ በነፃነት ተጓዘ ። ወዴት እንደሚሄድ ለጊዜው አላወቀም ። ዝም ብሎ ወደ ጀንበር መውጫ ፊቱን አዞረና ጉዞውን ቀጠለ ። ወደ ኋላ እንጂ ወደ ትናንትናው እንደማይመለስ ግን በልቡ ሳይሰማው አልቀረም ።

# የተከፋፈለ ልብ

አስር ጊዜ ሰአቷን ትመለከታለች ። መንገዱን ስታቋርጥ ድንገት አንድ መኪና አጠገቧ ደረሰና ፤ ‘ሲጢጢጢጢጢ . . .ጥ’ ብሎ አስፋልቱ ላይ ተንሸራትቶ ቆመ ። ሊገጫት ለጥቂት . . .እሴኔ ግን አልቆመችም ። መንገዱን በትክክል አርምጃ ተሻገረች ፤ መሬት መሬቱን እያየች ።

“ቤትየ ፡ ዛሬ ከሞት ጋር ቀጠሮ ይዘሻል መሰለኝ . . . ህይወትሽን ከጠላሻት እኮ እራስሽን ማጥፊያ ሌላ የተሻለ ዘዴ አለ ። አታስቢ ፡ ልጆቹ እንደሆኑ በእድላቸው ያድጋሉ . . .” አለ የመኪናው ሹፌር ፡ በመስኮት አንገቱን ብቅ አድርጎ ። ከዚያም መኪናውን አስነስቶ ሸመጠጠ ።

ቀና ብላ እንኳን አልተመለከተችም ። ከመንገዱ ግራና ቀኝ በሁኔታው ተደናግጠው የቆሙትን ሰዎች አላየቻቸውም ። ምን እንደሚሉም አልሰማች ። ሃሳቧ በማታው ረብሻና በዛሬው ቀጠሮ መካከል ይዋልላል ። ቡና ቤቱ ውስጥ ገብታ ከበሩ አጠገብ ካለው ባዶ቟ታ ወንበሩን ስባ ተቀመጠችና በረጅሙ ተነፈሰች ።

ከአራስ ቤት ከወጣች ወዲህ እየሳሳ የመጣውን ፀጉሯን አሳጥራ ተስተካክላዋለች ። ወትሮም ጎላ ጎላ ያሉት አይኖቿ ስትከሳ ጊዜ ይበልጥ የተለቁ መስለው ወጣ ወጣ ካሉት ከጉንጮቿ አጥንቶች በላይ ቅዝዝ ብለው ይንከባለላሉ ። ከንፈሮቿ ደረቅ ብለው እንደ ብር ቱካን እምቡጥ ተፈነካከተዋል ። የፊቷ ቆዳ ገርጥቷል ።

ለዘጠኝ አስር ጉዳይ ሆኗል ። በዘጠኝ ሰአት ነበር ቀጠሮዋ ። አሁንም ሰአቷን ደጋግማ ታያለች ። ሞቃት የበጋ ቀን ነበር ። ያዘዘችውን ኮካ ኮላ አንድ ጊዜ እን ኳን ፉት አላለችም ። ብቻ በመስታወቱ አሻግራ ውጪ ውጪውን ትመለከታለች ። "ይመጣ ይሆን? ብንያም. . . ይመጣ ይሆን?" አለች ፣ በሃሳቧ ።

በጣም ተረብሻለች ። ከዚያም በሃሳቧ ወደ ኋላ ተመለሰች ። አስራ አንደኛ ክፍል ሆና ነበር ከብንያም ጋር የተዋወቀችው ። አንድ ብስራት የሚባል ልጅ ነበር ያስተዋወቃት ። ትዝ አላት ፣ በመጀመሪያ እይታ ነበር ብንያም የወደዳት ። እሷም እንደዚያው ። ሲፈጥረውም አይናፋር ብጤ ነበር ። ትዝ አላት—ያን እለት መኝታ ቤቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈራ ሲቸር የሳማት ።

በአንድ እጁ ይዞት የነበረውን ሲጋራ ረስቶት ፣ ፀጉሯን ከኋላ እንዳቃጠላት አስታወሰች ። "ይኸውልህ ያንተ ማስታወሻ. . ." ትለው ነበር ፣ ዘወትር አብረው ከዋሉ በኋላ ወደ ቤቷ ለመሄድ ፀጉሯን ስታበጣጥር ። ታዲያ ብንያም ትዝ ባላት ቁጥር በሲጋራው እሳት ተቃጥለው ያጠሩትን የፀጉሯን ዘለላዎች በጣቶቿ እየ ነካካች ትተክዝ ነበር ። የብንያምን አይናፋርነት ትወ ድለት ነበር ። "ብንያምዬኮ በጣም ያሳዝነኛል. . . ለምንድነው የሚወዱት ሰው የሚያሳዝነው?" እያለች ዘወትር እራሷን ትጠይቃለች ። የምትመልሰውም እራ ሷው ነች ። "ፍቅር ነው በቃ ፣ ፍቅር ነው ። ፍቅር ምን የማያደርገው ነገር አለ?"

አሁን ዘጠኝ ሰአት ሆኗል ። እሴኒ እንደገና ሰአ ቷን ተመለከተች ። ከዚያም እንደገና ውጪ ውጪውን ታይ ጀመር ። ከዚያም ወደ ሃሳቧ ተመለሰች ።

እንዴት እንደ ተለያዩ ደግሞ ትዝ አላት ። እንዴት ከአሁኑ ባሏ ጋር እንደ ተገናኙ አስታወሰች ። ዘወትር ከትምህርት ቤት ስትወጣ በመኪናቸው እየተከተሉ የሚያስቸግሯት ሰውዬ ፡ የተላኩት ሽማግሌዎች ፡ የሟች እናቷ ግፊት ፡ የቤተ ዘመዱ መረባረብ ፡ ገንዘብ ያለው ባል ለግብቷ አሮጊት እናቷን ለመርዳት የነበራት ህልም. . .ሁሉም ትዝ አሏት ።

"ምን ቸገረኝ ፡ ለጊዜው ባገባውስ? ለእናቴ ስል፣ ባገባውስ? በሃብቱ እጠቀማለሁ ፡ እናቴን እጠቅማለሁ እማርበታለሁ ። ከብንያም ጋር ያለኝን ግንኙነት በምስጢር እደርገዋለሁ ። ማን ያውቅብኛል? ልጅም አልፈልግም ። አልወልድም ። ከዚህ ከሽማግሌ. . .በፍፁም አልወልድም ። ሁሉን ነገር ካመቻቸሁ በኋላ ቀስ ብዬ እፈታውና ብንያምን አገባለሁ ።"

ያን ጊዜ የምታስበው ሁሉ ትዝ አላት ። ከእርሷ በስተቀር ማንም የማያውቀው ምስጢር ነበር ።

ዘጠኝ ሰአት ከአምስት ደቂቃ ሆኗል ። አሁንም ሃሳቧ ወደ ብንያም እየተመለሰ እምቢ አላት ። ካገባች በኋላም ቢሆን ብንያም ልቧ ውስጥ የጫረው እሳት ሳይጠፋ አመድ እንደ ለበሰ ነበር የቆየው ። ታዲያ ትዳሯ ወደ ቁም ቅዠት እየተለወጠ በሄደ ቁጥር ፡ ኑሮዋ የብረት ወጥመድ እየሆነ ሲመጣባት ፡ ዘወትር በሃሳቧ የሚያንሾካብበው ያው መኪረኛው ብንያም ነበር ። ልቧ በትዝታው ረመጥ ይግል ይግልና ሲቃሉጥ ሲደርስ ተደብቃ በእንባ ታጥበውና ትንሽ እፎይ ትላለች ። ብንያምን እንደገና ለማግኘት ምን ያላደረገችው ነገር አለ? ከቤቷ እየተደበቀች ወጥታ እሱኑ ፍለጋ ስንት ቦታ ረግጣለች? መጀመሪያ ቀን የደወለችለት እለት በስልኩ

ውስጥ ያፈሰሰችውስ እንባ? ጓደኛዋ ሰርግ ላይ ያገኘችው እለት እንደዬት ነበር የሆነችው? እሱም ትዝ አላት ።

እንደገና ሰአቷን ተመለከተች ። ዘጠኝ ሰአት ከአስር ይላል ። አሩብ ሰአት ለመጠበቅ ወሰነችና ውጪ ውጪውን መመልከቷን ቀጠለች ። አሁን ደግሞ የጓደኛዋ ሰርግ ትዝ አላት ። የራሄል ሰርግ ። እዚያ ነበር ከብዙ ጊዜ በኋላ ብንያምን ያየችው ። አይኖቿን አላመነቻቸውም ነበር ።

"ብንያም!" አለች እሌኒ ድንገት ከሰዎች መሃል አይታው ። ሳታስበው ነበር ቃሉ ከአፏ የወጣው ። ብንያም በዚያው ድሮ በምታውቀው እርጋታው ወደ እሷ ቀረብ አለና ፡ "ሰላም እሌኒ . . .ደህና ነሽ? በሃገሩ አለሽ እንዴ?" አለና ጨበጣት ። እሷ ግን ከባለቤቷ ጋር መሆኗን እንኳን ልብ አላለችውም ነበር ። አብረዋት ያሉትንም ሰውዬ ጨበጣቸው ። ከሰማውና ካየው ሁኔታ ባለቤቷ መሆናቸውን በግምት አውቋል ።

ትንሽ ወፈር ከማለቱ በስተቀር ያው የድሮው ብንያም ነው ። ያም ድሮ የምትወደው አይናፋርነቱም እንዳልለቀቀው ከሰላምታ አሰጣጡ አውቃዋለች ።

ረጅም ቁመት ፡ ደልዳላ ሰውነት ፡ ጉድጓዶቻቸው ውስጥ ገባ ብለው ረግተው የተቀመጡና ገና ሲታዩ የሚወደዱ አይነት አይኖች ፡ እራሱ ላይ የተዝለፈለፈው ፀጉሩ ፡ ጥቅጥቅ ብሎ ግራና ቀኝ ጉንጮቹ ላይ የሚወርደው ፂሙ ፡ ጥንክር ግጥም ያሉ ከንፈሮቹ . . .ያው ነው ብንያም ፤ አልተለወጠም ። እሌኒ ከመጠን በላይ ያረጀች መስሏ ተሰማት ። በተለይ ጡቶቿ ። እነዚያ ከወለደች በኋላ ከመጠን በላይ ያደጉት ጡቶቿ ለራሷም ቢሆን ያስጠሏታል ። ሌላው ቀርቶ እራሷም ብት

ሆን ድሮ ጡቶቿን ትወዳቸው ነበር ። እነዚያ ቀጥ ብለው ጥጥር ያሉ ጡቶች ፡ የሸሚዟን ቁልፎች በጣጥሰው ለመውጣት የሚታገሉ የሚመስሉ ጡቶች. . .አሁን በአናት ጡቶች ተተክተዋል ። ጡቶቿ ነበሩ ይበልጥ ያረጀች የሚያስመስሏት ።

ግብዣውም ላይ ቢሆን አይኖቿ ከብንያም ላይ አልተነቀሉም ነበር ። ልቧ ውስጥ ተዳፍኖ የነበረው እሳት እንደገና መጋም ጀመረ ። እና ፡ ትኩር ብላ ስታየው የድሮው ሁሉ ትናንት የሆነ ያህል ትዝ ብሏት ነበር ። ባለቤቷ አጠገቧ አልነበሩም ። ብንያም ወደ ውጪ ሲወጣ ጠብቃ ነበር ከተቀመጠችበት ቦታ ሹልክ ብላ የተከተለችው ።

‟ቢኒ ደህና ነህ ታዲያ?. . .አቤት ስንት ዘመን ሆነን ከተለያየን! በቃ. . .ያ ሁሉ ነገር ቅርት ቅርት ሆነ ፣ እ?” ብላው ነበር እሌኒ ፡ ከስሩ ቆማ ወደ ላይ እያየችው ።

‟ምን ታደርጊዋለሽ እሌኒ ፣ ይኸው ነው የህይወት ነገር. . .ግን አንቺ እንደምን ነሽ? ደህና ነሽ?”

‟ደህናም ነኝ. . .ደህናም አይደለሁም!” ብላው ነበር ፡ ድንገት ጉሮሮዋ እየደረቀና እንደ ህፃን ልጅ ሆዷን ባር ባር እያላት ።

‟ባለቤትሽስ?. . .እ. . .ትዳርስ ፡ ጥሩ ነው?”

‟አንተስ አላገባህም?” አለችው እሌኒ ፡ ጥያቄውን በጥያቄ መልሳ ።

‟ስለ ባለቤቴ አታንሳ ፣ እርሳው! ትዳሬ በጣም በጣም አስቀያሚ ነው ፣ አያስደስተኝም ። ግን ወድጄ

አላደረኩትም ። የህይወቴ ትልቁ ስህተት ነበር. . .” ልትለው ፈልጋ ነበር ። ለጊዜው ከአፍዋ አልወጣ ብሎ እምቢ አላት ።

“አላገባሁም” አለ ብንያም ።

“አላገባሁም?” አለች እሌኒ ፤ በብንያም አለማግባት የተደሰተች ይመስል ድንገት ፈገግ ብላ ።

“አንቺ ነበርሽ. . .በቃ ሌላ ሰው ነጠቀኝ ። ሌላ ለማግባት ግን ገና አላሰብኩም ። እንዳንቺ ቆራጥ አይደለሁም” አለ ብንያም ፤ እየቀለደ ። የእሌኒ ልብ ግን ያረግድ ነበር ።

“ስታገባ ትጠራኛለህ አይደል?” አለች እሌኒ ፤ በግድ ፈገግ ብላ ።

“አንቺ እንደ ጠራሽኝ. . .” አለ ብንያም ። የእሌኒ ፊት ቅጭም አለ ።

“እሱን ተወው ቢኒ. . .በሞቴ እርሳው እባክህ. . . አሁን ሁሉን ነገር ብነግርህ አታምነኝም ። ይልቁንስ ቢኒ ፤ የት ላግኝህ? ብዙ ነምነግርህ ነገር አለ ፤ እውነት አሁንም ብቻህን ነህ? አላገባህም?”

“ለምን?”

“እንደዚሁ በቃ!”

“አሁን ሂጂ በቃ. . .ባለቤትሽ ያዩሽ እንዳይሆን. . .”

“እባክህ ዝም በል ፤ ቢኒ. . .ታሾፍብኛለህ አይደል ፤ ቢኒ? ግን ቢኒ ፤ እውነቱን ነው. . .እ. . .አንድ ቀን ብቻ ባገኝህስ? ካሁን ወዲያ ወንድሜ ነህ አይደል? እኔም እህትህ አይደለሁ? እየው. . .ስንት ጊዜ ላገኝህ ያልገባ

ሁቡት ቀዳዳ አልነበረም ። የደወልኩልህ እለት ትዝ ይልሃል? የሰራሁት ያሳፍረኛል. . .ግን አሁን እህትና ወንድም እንሆንም? ይኸውልህ በጣም ብቸኛና የመን ፈስ እረፍት ያጣሁ ሴት ሆኜልሃለሁ ። እንደ. . .እንደ ማን ልበልህ. . . እንደ ማዳም ቦቫሪ. . . 'ማዳም ቦቫሪን' ያኔ አውሰኸኝ አንብቤው እንደ ነበር ትዝ ይልሃል? እማማም እኮ ሞተች! አልሰማህም እንዴ ብንያም?" አለችና አይኖቿ ላይ ድንገት ከንብል ያለውን እንባ ውጣ አስቀረችው ።

"መቼ ሞቱ?" አለ ብንያም ደንግጦ ፡ "ሙች አል ሰማሁም! ምን ሆነው ነው ግን?"

"ታማ ነው. . .አሁንማ አመት አለፋት" አለች እሌኒ በተሰባበረ ድምፅ ።

"ታዲያ. . .ታዲያ ለምን ፈለግሺኝ?" አለ ብን ያም ፡ ትንሽ ተክዞ ከቆየ በኋላ ። "ግን እኮ እሌኒ ጥሩ አይሆንም ፡ አንቺ ባለትዳር ነሽ ፤ እና. . ."

"ገባኝ ብንያም. . .እሱን ለጊዜው ተወው ። ምን መሰለህ ፡ ትንሽ የማዋይህ ነገር አለኝ ። ትንሽ ጭንቀት አለብኝ ። ለሰው ባዋየው ቀለል እንደሚል ልኘ አውቃ ለሁ ። ግን ለማን ልንገረው? መፍትሄ ካላገኘሁ እኔ እንጃ. . .ወደ ፊት መኖር የምችል አይመስለኝም. . . ቢሆ ፡ በወንድምነት እሺ በለኝ ። እሺ?" አለች እሌኒ ፤ እንባ እየተናነቃት ። እንድትደውልለት ቀጠሮ ሰጥቷት ነበር የተለያዩት ።

ድንኳኑ ውስጥ ከነበረው መቀመጫዋ ስትመለስ ፡ ባለቤቷን ተመልሰው ነበር ያገኘችው ። ለጊዜው ምንም አልተናገሯትም ነበር ። ማታ ግን ቂም ስቅሏን ሲያሳ

ይዋጉት ነበር የደሩት ። ሞቅ ብሏቸው ነበር ። እና ፡ ቀን ሰላምታ የሰጠችው ሰውዬ ማን እንደሆነ እንድትና ገር ፡ ከጓሱ ወጣቷ የት ቆይታ እንደ መጣች እውነቱን እንድታወጣ ጠይቀዋት ነበር ። ከዚያም የመኝታ ቤቱን በር ዘግተው በክርን ፡ በእርግጫ ፡ በቡጢ ፡ በጉሮሮ በጺ ኖቻቸው ጨምድደው ፡ አፏን በመዳፋቸው እያፈኑ ፡ መሬት ወርዳ ከተኛችበት ሲደበድቧት . . .እንዳይነጋ የለም ነጋ ።

ፊትም ቢሆን ይከፋት ነበር ። በተለይ ባለቤቷ ከድሮዋ ሚስታቸው የወለዳቸውን ልጆች ካመቀች በኋላ ግን ፡ እንደ እብድ ነበር ያደረጋት ። እሱን እራስ ቤት ተኝታ ስንት ቀን ውጪ አድረዋል? ታዲያ ይህ ንን ሁሉ ስታስብ እንጀቷ ብው ብሎ ይቃጠላል ። አንዳንዴ እንዲያው ብር ብላ ከቤቷ ወጥታ ውጪ ላገኘችው ለመጀመሪያው ሰው የሆዷን ዝክዝክ አድርጋ ነግራው ከዚህ ሲኦል እንዲያወጣት እግሩ ላይ ወድቃ ለመለመን ይዳዳታል ። ወይም ደግሞ አንዱ ወደ ት ፡ ከዚያ ኑሮ አላቆ ልጅዋንም ቢሆን ትታ ፡ ወደ ሌላ ሩቅ ቦታ ወስዶት አዲስ ኑሮ ለመጀመር ትመኛለች ። የቀን ህልም. . .

ከራሄል ሰርግ ወዲህ ከብንያም ጋር አንድ ሁለት ጊዜ ተገናኝተው ነበር ። ቤቱንም አሳይቷታል ፡ በእሷ ው ጥያቄ ። የደረሰባትን ሁሉ አንድ ሳይቀር ልቅም አድርጋ ነግራው ስቅስቅ ብላ አልቅሳበታለች ። ቢቻል ኖሮ በቀን በቀን ልታገኘው ትፈልጋለች ። ብንያም ሁል ጊዜ በቀጠራት ሰአት ነበር የሚመጣው ። ያን እለት ግን የቀጠሮው ሰአት ቢያልፍም እሱን ሳታገኘው ተመልሳ ወደ ቤቷ መሄድ አልፈለገችም ።

እሌኒ እንደገና ሰአቷን ተመለከተች ። ዘጠኝ ሰአት ከሃያ ሆኖ ነበር ። ከዚያም እስከ ትኩል ጠብቃው ለመ ሄድ ወሰና አጠገቧ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን ጠር ሙስ አንስታ ተጎንጨችለትና በረጅሙ ተነፈሰች ።

እንደገና ስለ ብንያም ታስብ ጀመር ። በመጨረሻ የተገናኙ እለት የተናገረውን አስታወሰች ።

"ምን ይሰራል እሌኒ . . . ሳንቲ ጥሩ አይደለም ። ታውቂዋለሽ . . . ያገባች ሴት ለባሏ ታማኝ መሆን አለ ባት ። ለህሊናሽም ቢሆን ጥሩ አይደለም ። እንደዉ ሆኗል። የሆነውን መቀበል መቻል አለብሽ ። "

"እሱ ለእኔ መቼ ታማኝ ነው?"

"ቢሆንም ፡ ወንድ ቢያጠፋም ምንም አይባልም ። ሴት ላይ ግን ሁሉ ነገር ይገንባታል ። ምን ታደርጊዋለሽ . . . ባህሉ ነው ። "

"እሺ ግዴለም ውጪ ይሂድ ፤ ግን ለምን ያንገላ ታኛል ? . . . ለምን መጀመሪያ ልጅ የለኝም አለ? ለምን አታለለኝ ?"

"ይኸው ነው . . . እኛ ወንዶች የፈለግነውን እስ ክናገኝ ድረስ እንዋሻለን ፤ ያገኘነው ሲሰለችን ግን የመ ጣው ቢመጣ ግድ የለንም ። የሰው ተፈጥሮ ነው ፤ ምን ታደርጊዋለሽ ?"

"በቃ አልወደውም እኮ ነው የምልህ! ምን ልበ ልህ . . . በፊት ሲያገባኝም በቃ ፡ አታሎኝ ነው ። ሃብታም ነው ፡ እናትሽን ይረዳልሻል ስላሉኝ ነው ። እውነት መስ ሎኝ ነበር ። ታውቃለህ ፡ እናቴ ምን ያህል ችግረኛ እንደ ነበረች ። ታዲያ እሷም ብዙ አልቆየች ፡ ሞተች ። ሳትሞ

ትም ቢሆን ምንም አላደረገላትም ። ወይ ለእናቴ ወይ ለእራሴ አልሆንኩም ። አሁን ደግሞ መሄጃ የላትም ብሎ ይጫወትብኛል !"

"ቢቃ ቻይው እሌኒ ። ምን ያደርጋል ብስጭት ? ህይወት እንደዚሁ ነች ። ሳታስቢው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ትጨምርሻለች ። ከዚያ በኋላ መውጣቱ እንቆቅልሽ ይሆናል ። ልትውጪውም ልትተፊውም የማ. ቸግርሽ ኑሮ ውስጥ ትከትሻለች ። ህይወት አንዳንድ ጊዜ ጨካኝ ናት ፤ ታደላለች ። ህይወት እራሷ ወደ ተሻለ አቅጣጫ እስከምትወስድሽ በትእግስት መጠበቅ ነው ። ያለው አማራጭ . . . እንዴ የሆነውን መቀበል መቻል አለብሽ፡ እሌኒ . . . ጊዜ የማይለወጠው ነገር የለም ። ጊዜ መድሃኒት ነው . . . "

"ትእግስቴ ሁሉ አልቋል ብንያም ። አንዳንዴ ምርር ሲለኝ ብር ብለሽ የትም ሂጂ ሂጂ ይለኛል ። ግን የት መሄድ እችላለሁ ? ብንያም እስኪ አስበው ። አንድ አይዞሽ የሚለኝ ሰው የለም ። ይህን ያህል ምን በደል ኩትና ነው አምላኬ እንደዚህ የሚያሰቃየኝ ?"

እሌኒ ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች ። ብንያም አጠገቧ ተቀምጦ ያፅናናታል ። እሷ ግን ሌላ ነገር ነበር የምትፈልገው ። እንዲያቅፋት ነበር የፈለገችው ። ከንዶቹ መሃል አድርጎት ፡ "አይዞሽ እሌኒ ፡ እኔ አለሁልሽ . . . " እንዲላት ነበር የፈለገችው ። አንድ ሃይል በተአምር ይኼንን የተመኘችውን እንዲያደርግላት አሰበች ። ከቤቱም መውጣት አልፈለገችም ነበር ።

"ቢቃ ምናባቱ ፡ እዚሁ ተቀመጪ ። ሻንጣሽን ቀስ ብለሽ ታመጪዋለሽ ፤ ወይም ተይው ይቅር ። ልጅቷንም በቃ ተያት ፤ አባቷ ያሳድጋት . . . እኔና አንቺ አብረን

እንኖራለን ፣ ሌላ ልጅ ትወልጃለሽ . . . .” እንዳላት ተመ
ኝች ። አቅፎ ተሸክሞ አልጋ ላይ አውጥቷት ፣ እንደ ድሯ
ቸው ላንዳፍታም ቢሆን እፎይ ብላ ፣ ቤቷ እንደ አውሬ
ጥርሱን አግጥጦ የሚጠብቃትን ኑሮ ለሴኮንድ ወይንም
ለደቂቃ ለመርሳት ነበር የተመኘችው ።

ብንያም ግን ምንም አላላትም ። በጣም የቀዘቀዘባት
ሆኖ ነበር የተሰማት ። እንደ ፈለገችው አልሆንላትም
ነበር ። የዚህን ጊዜ ነበር ያላትን ሁሉ ሃይል ሰብስባ ፣
“ብ...ብንያም ...ም...ምነው ችላ አልከኝ?” ያለችውና
በእንባ የታጠበውን ፊቷን ወደ እሱ መልሳ ሚጥሚጣ
የመሰሉትን አይኖቿን በልመና ያንከባለለችበት ።

“እሌኒ ፣ ነገርኩሽ እኮ . . . ለአንቺም ላኔም ጥሩ
አይሆንም ። ካሁን ወዲያ ወንድምነቱ ይሻላል ። እንደ
ዚሁ በሩቁ ብንጠያየቅ . . . እንደ እህትና እንደ ወን
ድምነት ?”

“እሺ ብንያም ፣ ለድሮው ፍቅራችን ስትል እንኳን
. . . በቃ አንድ ጊዜ እሳከ እቀፈኝና በቃ . . . አይዞሽ
በለኝ ። አንተም እንደ ሌላው ትጨክንብኛለህ ?...ብቸኛ
እኮ ነኝ ቢኒ ፤ አላሳዝንህም ፣ እ ?”

ትኩር ብሎ አያት ። እውነትም ታሳዝናለች። ትንሽ
ሴኮንዶች ዝም ተባባሉ ። ከዚያም ክንዶቹን ዘረጋና አቀ
ፋት ። ቀና ብላ አየችው ። ሁለት የእንባ ጠብታዎች ሽፋ
ሎቿ ላይ ተንጠለጠሉና አይኖቿን ስትጨፍናቸው እንደ
ብረት ምጣድ ከጋመው ጉንጮቿ ላይ ወደቁ ። አንገቱን
ጉንቅ አድርጋ አቀፈችው ። “ቢ . . . ቢኒ . . . እ . . .እኔኮ
እ . . . አሁንም ቢሆን እ . . . እወድሃለሁ ። ሙት ! ሙት
እወድሃለሁ . . . ድሮም አሳስተውኝ ነው ፤ ተሳስቼ ነው

የተለየሁህ . . . የህይወቴ ትልቁ ስህተት ነው ። ቢሆንም አርመዋለሁ ። እንደገና ደስተኞች እንሆናለን ቢኒ . . .”

ይኸን ነበር ያለችው ፣ ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙ እለት ።

እናም ፣ ያን እለት በቀጠሮው ሰአት አግኝታው ፣ ማታ የደረሰባትን በደል ነግራው ፣ እንደ ወትሮዋ እል ቅሳ ፣ እቀፈኝ ብላውና እቅፏት ፣ በደሏን ብንያም በሚ ሰጣት ደስታ አካክሳ ለመመለስ ነበርና ያሰበችው ።

ሳታስበው ለአስር አሩብ ጉዳይ ሆኖ ነበር ። ሰአ ቷን እንደገና አየችው ። ከዚያም ቡና ቤቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ሰአት ተመለከተች ። የሰአቱ ኦጆች ሶስት ሰአት ላይ እንደ ቆሙ ናቸው ። መቼ እንደ ተበላሸና እንደ ቆመ አይታወቅም ። የሷም ህይወት እንደ ግድ ግዳው ሰአት አንድ ቦታ የቆመ መሰላት ። ወደ ፊት ወይንም ወደ ኋላ የማይሄድ ህይወት ። ለሶስት አመ ታት ያልተለወጠ ህይወት . . .

ስለ ቤቷ ስታስብ አስጠላት ። ወዲያውም የኮካ ኮላ ውን ሂሳብ ከፍላ ወጣች ።

የሄደችበት ታክሲ ከመንገዱ ዳር ነበር የጣላት ። ብንያም ቤት ደርሳ የግቢውን በር አንኳኳች ። ከውስጥ የሚመጣ የሰዎች ጫጫታና የሙዚቃ ድምፅ ሰማች ። ለወትሮው ጭር ያለ ነበር–ግቢው ። ደጋግማ አንኳኳች። የማታውቀው ሰው ነበር በሩን የከፈተላት ።

“ሰላም . . . ብንያም ይኖራል ?” ካለች በኋላ ሰው የውን ቀና ብላ አየችው ።

“አለ . . . ግቢ . . . አለ ፣ ውስጥ ነው ።” ተስተናጋው ገባች ።

በረንዳው ላይ ሰዎች ተሰብስበዋል ። የቢራ ጠርሙሶችና መጠጥ የተሞሉ መለኪያዎች ፤ ጠረጴዛዎቹ ላይ ተቀምጠዋል ። ሁካታ ፤ ሳቅ ፤ ሙዚቃ ይሰማል ። ሳሎኑ ውስጥ ደግሞ ብዙ ሰዎች እጅብ ብለው ይደንሳሉ ። ክፍሉ በሲጋራ ጭስና በመጠጥ ሽታ ታፍኗል ። በጣም ይወብቃል ።

ከግቢው በር ላይ የተቀበላት ሰውዬ ሳሎን አስገባትና ከአንድ ጥግ ቦታ ባዶ ወንበር አሳያት ። ምን እንደ ምትወስድ አልጠየቃትም ። ጓዳ ገብቶ የቢራውን ጠርሙስ አመጣና ከፍቶ ከብርጭቆ ጋር አስቀመጠው ። ከዚያም ፤ "ተጫዋቺ ብንያም ይመጣል . . ." አላትና ወደ ውጪ ሄደ ።

እሌኒ ብዙ አሰበች ። ተጠራጠረች ። ብንያም ምንም ምንም አልነገራትም ነበር ። ታሰባለች ፡ "አገባ እንዴ ? ወይንስ ሌላ ነገር ነው ? እንዴት አልነገረኝም ?" ባይታ ወርነት ተሰማት ። የብንያም መቆየት ደግሞ ጥርጣሬዋን አባባሰው ። ሰአቷን ተመለከተች ። አስር ተኩል ሆኗል ። መኖሪያ ቤቷ ድንገት ትዝ አላትና መመለሷን ስታስበው ይበልጥ አስጠላት ። ባሏን ስታስታውስ ደግሞ ትና ንት ማታ ያሏት ነገር ጆሮዋ ውስጥ ደወለባት ። "አንቺ የድሃ ልጅ . . .እድሜ ለእኔ በይ ። ከድህነት አወጣሁሽ . . . አይተሽ የማታውቂውን አሳየሁሽ . . ." ብለዋት ነበር ። በብንያም አለመምጣት ደግሞ ይበልጥ ተናደደች ።

ከሶስተኛውም ቢራ በኋላ ብቸኝነት ጥርስ አውጥቶ ያኝካት ነበር ። ብዙ መጠጣት ፈለገች ። ብዙ የመጠጣትና የመስከር እና እንደምታያቸው ሰዎች የመሆን ፤ ከሃሳብና ከትካዜ ነፃ የመሆን ፍላጎት ድንገት ተሰረፀባት ።

ሰው ሁሉ ሰክሮ ነበር ። ሴትና ወንዱ ጥንድ ጥንድ እየሆነ ለዛ ባጣ ሁኔታ ሳሎኑ ውስጥ ይንተታሉ ። ማጓሯ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይዘናናል ።

ኢሌኒ እንደምታያቸው ሰዎች ሁሉ ለጊዜውም ቢሆን ነፃ ለመሆንና ጭንቀቷን ለመርሳት ፈለገች ። ባል ማግ ባቷን ለጊዜውም ቢሆን ለመዘንጋት ፥ መውለዷንም ቢሆን እንዳልሆነ አድርጋ ለማሰብ ተመኘች ። የማት ፈልገው ነገር ሁሉ እንዳልሆነ ሆኖ እንዲሰማት ነበር የፈለገችው ። እናም ፥ በድፍረት ፥ "ብንያምስ? . . . ብን ያም የታለ ?" ብላ ጮሃ ለመጠየቅ ፈለገች ። ስሜቷን ለማጠንከር ጭምር ነበር ደጋግማ የጠጣችው ። በመጨ ረሻም ድፍረቱን አገኘች ።

"ስ . . . ስማ የኔ ወንድም ፥ ምንድነው ይሄ ሁሉ ድግስ? ብንያምስ ? የታለ ብንያም ?" አለች ኢሌኒ ፥ ድን ገት ከመቀመጫዋ ተነስታ አጠገቧ ያገኘችውን ሰው በቀሉት አይኖቿ እየተመለከተች ።

"እስካሁን አላወቅሽም እንዴ ?" አለ ሰውዬው ፥ በማሾፍ መልክ ።

"ምኑን ?"

"ለምን እንደ ተደገሰ? . . . ለመሆኑ ምን ብለሽ ነው የመጣሽው ?"

"ከብንያም ጋር ቀጠሮ ነበረኝ . . . ሲቀር ጊዜ በቃ ፥ ዝም ብዬ መጣሁ ። ስመጣ . . ."

"አልነገረሽም ነበር ታዲያ እሱ ?"

"አገባ እንዴ?" አለች ኢሌኒ ደንግጣ ። "አግብቶ ኗው ፥ አውቄአለሁ ። ለዚሁ ነው የሚሸሸው ። ምን እስፈ

ራው ? እኔም ተደብቄው አግብቻለሁ ። ብድሩን መለሰ ማለት ነው ፣ በቃ ። እኔና እሱ ካሁን ወዲያ እህትና ወን ድም ነን . . . ኖኖ . . . እህትና ወንድም ሳይሆን . . . እወ ደዋለሁ . . . . ቢያገባም እወደዋለሁ . . . . የልቤን የምነ ግረው ለእሱ ብቻ ነው . . . የሚያዝንልኝ እሱ ብቻ ነው . . . ዛሬ ከዚህ ቤት አልሄድም ፤ ይገባሃል ? . . . አልሄ ድም ! የሱን ነገር መተው አልችልም ። ልቤ ተከፋፍሎ ብኝ እየተሰቃየሁ ነው ። ለምንድነው እንደ ፊልኩ መሆን የማልችለው ? ንገረኝ እስኪ . . . አልሰክርኩም . . . ግን ለምንድነው ፣ እ ?”

“ተዪ ቀይ ፤ አላገባም ።”

“ታዲያ ምንድነው ይሄ ሁሉ ድግስ ?”

“ፈርዌል ነው ።”

“የምን ፈርዌል ነው?”

“ብንያም ወደ ውጪ ሊሄድ ነው ።”

“ለምን ?”

“ለትምህርት ።”

“ትምህርቱን ጨርሶ የለም ?”

“ለሁለተኛ ዲግሪው ነው ።”

“አይመጣም በቃ ?” አለች እሴኒ ደንግጣ ።

“ይመለሳል ፤ ሁለት አመት ብቻ ነው የሚቆየው ።”

“ጥራልኝ እሱን . . . ለምን ይሸሸኛል ታዲያ ? . . . እንኳን ውጪ መሄድ ቢያገባ እንኳን ምንም አይደለም። እኔም ያልሆነ ሰው አግብቼ ነው እንደዚህ የምሆነው ። እንደዚህ የምሰቃየው ። እሱም ብሎኛል ፡ የተከፋፈለች ልብ ደስታ አታገኝም ብሎኛል ። ግን ዘለአለም ልቤ ሲያ ለቅስ ይኑር እንጂ አልተወውም ።”

“ሰው ለመሸኘት ሄዶ ነው ፤ ይመጣል ።”

“እንተ . . . ለምንድነው ያልነገርከኝ ፡ እ! ደግሞ ቀጥረኸኝ ትጠፋለህ ? አሁን ባልመጣ እኮ በቃ ፡ ገዞም ብለኸኝ ልትሄድ ነበር አይደል ?” አለች እሌኒ ገና ስታየው ሮጣ የብንያምን ክንድ በሁለት እጅዋ ጨምድዳ ከያዘች በኋላ ።

“ፊርቼሽ ነው እሌኒ. . .ያ የነገርሺኝ ነገር ሁሉ. . . በቃ ፡ እንደዚህ ስታምኚኝና የልብሽን ስትነግሪኝ ጥዬሽ መሄዴ አሳዝኖኝ ነው ። ድንገት ነው የተነገረኝ” አለ ብንያም ፡ በሃዘን እያየት ።

“በቃ ተወው. . .ሁለት አመት ነው አይደል? ትመጣለህ አይደል? እንኳን ደስ አለህ! ና ልሳምህ” አለችና ተንጠራርታ ጉንጮቹን ሳመቻቸው ።

ከዚያም ወደ ጓደኛው ዞር ብላ ፡ “ታውቃለህ . . . የድሮ ቦይ ፍሬንዴ ነው. . .ከሶስት አመት በኋላ ተገናኘን. . .ታዲያ አሁንም ሲከፋኝ የሚያፅናናኝ እሱ ብቻ ነው ። ካለሱ ማንም የለኝም ። በጣም ይከፋኛል ፤ በጣም በጣም. . .”

ከዚያም ወደ ብንያም ዞረችና ፡ “ቢኒ. . .ትናንት ማታ ምን እንዳለኝ ታውቃለህ ፡ ያ ሰውዬ? ፡ ‘አንቺ የድሃ ልጅ. . .እድሜ ለእኔ በይ አሳለፍኩልሽ. . .’ አለኝ እኮ. . .ታዲያ ከዚህ ሰው ጋር ነው ቻይና ኑሪ የምትለኝ?” አለችና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ።

“በቃ ተይው እሌኒ. . .ምን ነበር የተባባልነው? ካሁኑ ረሳሺው? መጠንከር አለብሽ ። ተስፋ አድርጊ ። አንድ ቀን ህይወትሽ ይለወጣል. . .በተረፈ ነገ ነይና እንጫወታለን ። አሁን መሽቷል ፡ ወደ ቤት ሂጂ. . .”

እሌኒ ሰአቷን ተመለከተች ። አንድ ሰአት አካባቢ ሆኖ ነበር ። "ጊዜው እንዴት ይሮጣል. . ." አለች በሃሳቧ ። ከብንያም ቤት ስትወጣ መሽቶ ነበር ።

ከታክሲው ወርዳ ወደ ቤቷ ስትሄድ እያሰበች ነበር።

"ሁለት አመት አይደለ. . .ቀላል ነው ። ነገ ጠዋት ይደርሳል ። መጠንከር አለብሽ አለኝ አይደል? አዎን ፣ መጠንከር ይኖርብኛል ። ጠንክሬ እጠብቀዋለሁ ። ተስፋ አድርጊ አለኝ አይደል? አዎን ፣ ተስፋ አደርጋለሁ. . . ከለሱ ማን ተስፋ አለኝ?. . .ብንያምዬ ሲመለስ ቤቶ ፣ የእኔ ይሆናል ። የእኔ ብቻ. . .ከዚያ በኋላ በቃ. . .ልቤ አይከፋፈልም ። አንድ ቦታ ይረጋል ። ሰላም አገኛለሁ... እስከዚያ ግን በቃ ምንጊዜም ያስጉኛ አልሆንም..."

የዕጌረዳ ሽታ በነፋሻው የበጋ ምሽት ውስጥ ከሩቅ ይጣቀሳል። በጨረቃ የደመቀው ምሽት ደስ ይላል። ነፍሳት ሁሉ በያሉበት ሆነው በየቋንቋቸው የምሽቱን መምጣት እያበሰሩ ህይወትን በፀጋ እየተቀበሉ ነበር ። የእሌኒ ልብ ብቻ ነበር እረፍት ፣ እፎይታና እርጋታ ያጣው ።

# በልሁ ቺስታው

ከአስራ ሁለት ወይም ከአስራ ሶስት አመት አይበልጠውም—በልሁ ። እጥር ፍርጥም ያለ ነው ። ፉንጋ ፊቱ ላይ እንዚያ ብልጣ ብልጥ አይኖቹ እረፍት የላቸውም ። በሆነ ባልሆነው ብልጭ እያሉ ደስተኛ የሚያስመስሉት የበለዘ ጥርሶቹ ብቻ ናቸው ። የቡና ዘንዘና የሚመስሉትና መጅ ያወጡት እግሮቹ ፤ እኛ መከረኛ አሳዳጊው አሮጊት ከሞቱና የሚላስ የሚቀመስ ከጠፋ ብዙ ቦታ መርገጣቸው አይቀርም ። ወላጅ እና ቱን አያውቅም ። አባቱ ወህኒ ቤት ነው ። "በሌብነት ነው" ይላል—የመንደሩ ሰው ሲያወራ ።

"እማማ ሞቱ ማለት ነው?" ያን ጉለት ከዚያች ዛኒጋባ ቤት ውስጥ ገናኘቱና በጣት የሚቆጠሩ የሚቿ ጓደኞች እየሆኑ አሮጊት ለቀስተኞች ጉድ ጉድ ሲሉ በልሁ አንዷን ሴትዮ ጠየቃቸው ።

"ሞቱ በቃ. . .እረፋት ልጄ. . .ሞተው ነው" በማ ለት ሴትዮዋ ፤ ልውጣ እያለ የሚታገላቸውን እንባ እየዋጡ መለሱለት ።

"ሞቱ. . .ሞቱ ፤ በቃ እማማ ሞቱ. . ." በልሁ ለብ ቻው እያጉተመተመ ወደ ውጪ እየሮጠ ሄደ ።

ከትንሿ ሱቅ አጠገብ የመንደሩ ልጆች ተሰብስ በው ቆመዋል ። በልሁን ሲያዩት ሁሉም ዝም አሉ ። እሱ ግን እየሮጠ ሄደና አጠገባቸው ቆመ ። ከዚያም

በነዚያ ትናንሽ አይኖቹ አንድ በአንድ ተመለከታቸው ። እነሱም መልሰው ያዩታል ።

"እማማኮ ሞቱ!" አለ በልሁ ፥ ጥርሱን ብልጭ እያደረገ ።

ልጆቹም ሳቁ ።

"እናውቃለን ። ዳጌሮ ጠዋት የእድር ጥሩምባ ሲነፋ ሰምተናል. . ." አለ አንዱ ልጅ ።

"ታዲያ ይሙቱዋ! አሮጊት ናቸው. . .ምን ቸገረህ?" ሌላው ለጠቀ ።

በልሁ የተናገረውን ልጅ ቀና ብሎ አየው ።

". . .ታዲያ ማን ያበላኛል? በቃኮ ካሁን ወዲያ ቺስታ ነኝ ማለት ነው" አለ በልሁ ።

ልጆቹ እንደገና ሳቁበት ።

"ቺስታ!. . .ቺስታ! እውነትም ቺስታ!. . .በልሁ ቺስታ!"

ልጆቹ እንደገና ሳቁበት ።

'ቺስታ' በዚያው የቅፅል ስሙ ሆኖ ቀረ ።

የመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት እንኳን ደህና ነበሩ ፤ ለክፉም አልሰጠው ። ሳልስቱ እስኪያልፍ ወጣ ገባ እያለ ለሐዘን ከሚመጣው የመንደር እንጀራ ፍርፋሪ ውንም ቢሆን ሲቀራርም ቆይቶ ነበር ። በአራተኛው ቀን ግን ከቤቱ ወጥቶ ሄደ ። ወደ አቃቂ ከምትፈሰው ትንሿ ወንዝ ላይ የተሰራችውን የእንጨት ድልድይ፣ ከታሰረችበት እንደ ተፈታች እምቦሳ እመር እያለ

አለፈና ከወዲያ ማዶ ካለው ከዶክተር ማርኮ ቤት አጠገብ ሲደርስ ቆመና አካባቢውን በአይኖቹ ይቃኝ ጀመር።

የዶክተር ማርኮ ቪላ በኩራት ተገሽሮ ከወንዚ ማዶ ረባዳው መሬት ላይ የዛገ የቆርቆሮ ክዳናቸውን ብቻ ለሰማዩ እያሳዩ በሃፍረት የተደበቁ የሚመስሉትን ያረጁ ትርኪ ምርኪ ቤቶች ቁልቁል የሚመለከት ይመስላል ። እናም ፣ በእብንበረድና በመስታወት የተገጠገጠውን ደረቱን ወደዚያው አዞሮ ፣ “እንዚያ እዚያ ማዶ ያሉት ቤቶች እውን የሰዎች መኖሪያ ናቸው?” እያለ የሚጠይቅ ይመስል ነበር ።

በሩ ላይ መኪናዎች ተደርድረዋል ። የግቢውም የብረት በር እፉን ከፍቶ የሚያዛጋ ይመስላል ። የውድ ምግብ ሽታና የለስላሳ ሙዚቃ ጣእመ ዜማ በክረምቱ አየር ውስጥ ተበትኗል ። በልሁ ሁኔታውን ሁሉ ተረድቶታል ። ብዙ ጊዜ ቅዳሜ ቀን ከዚያ ቤት የምሳ ግብዣ እንደሚኖር ያውቃል ። ትንሿ ሆዱ ውስጥ ወስፋቱ መጮህ ጀመረ ።

የግቢውን በር ሲያልፍ ማንም አላየውም ነበር ። ዘውትር የስልክ እንጨት መስሎ ቆመጡን እንደ ያዘ በውርርድ ከግቢው በር ላይ የማይጠፋው ቶላ ዘበኛውያን እለት ምን እንደ በላው አይታወቅም ፣ በአካባቢውም አልነበረም ። በልሁ በቀጥታ ከቤቱ ጀርባ ካለው ኩሺና ነበር የሄደው ። የቤቱ ሰራተኞች እንድንም ሳይቀሩ ከዋናው ቤት ውስጥ ሽር ጉድ ይላሉ ። የመንደሩ አውደልዳይ ውሾች ብቻ ነበሩ ግቢውን የሚዞሩት ። ከቤቱ አጠገብ ከሚገኘው ዛፍ ላይ ከታች ከቄራ የመጡ አሞሮች ሰፍረውበታል ።

ቶላ ዘበኛው አሞሮቹን ለማባረርና ከግቢው በር ላይ መግባት ፈርተው እጅብ ብለው የቆሙትን ተልከ

ስካሽ ውሾች ለመዋምታት ነበር— በኋላ በር የወጣው ። ወደ ተከፈተው ኩሽና ሲመለከት ደፉ ላይ ተቀምጠው ምላሳቸውን እየጎለጎሉ የሚያፋሽጉትን ድመቶች አያቸው ። ቶላ ድመቶቹን በእርግጫ እያለ ካባረረ በኋላ ወደ ውስጥ ሲመለከት በድንጋጤ አይኖቹ ተጎልጉለ ውና አፉን ከፍቶ ከቆመበት ተቸንክሮ ቀረ ።

በልሁ ከኩሺናው ወለል ላይ ሁለት እግሮቹን አንፈራጦ ተቀምጦ ፣ በትልቅ ትሪ ከተቀመጠው እንጀራ ላይ በየአይነቱ ወጥ አድርጎ ያለ ምንም ሃሳብ እየጠቀ ለለ ይጎርሳል ።

"ኢንዴ!" አለ ቶላ ፣ ራሱን በሁለት እጆቹ ይዞ ፣ "ዴሞ ማን ቴሳራሉ እንቴ?"

በልሁ ምንም ሳይረበሽ ቶላን ቀና ብሎ አየና ፣ "እበላለኋ!. . .ሌላ ምን አደረኩ?. . .በላሁ እንጂ!. . ." አለ ፣ በአፉ የያዘው ምግብ እያነላተፈው ።

"ማን ፈቅዶ ኖ የሚትበላ?" አለ ቶላ ፣ በልሁን ለመያዝም የቤቷን እመቤት ለመጥራትም እየዳዳው ።

"እትዬ አስቴር ናቸዋ! እትዬ አስቴር ናቸው የሰጡኝ" አለ በልሁ ፣ መውጫውን በር እየተመለከተ ። ወይዘሮ አስቴር የዶክተር ማርኮ ባለቤት ናቸው ።

ወይዘሮ አስቴር ከዋናው ቤት ሲወጡ ፣ ቶላ ደግሞ እሳቸውን ሲጠራ ፊቱን ሲያዞር አንድ ሆነ ። በዚህን ጊዜ ነበር በልሁ ሹልክ ብሎ ከኩሺናው የወጣው ። ወይዘሮ አስቴር አይተውታል ። በተቀደደችው ቁምጣ ሱሪው ቂጡ ብቅ ብላለች ። በአጫጭር እግሮቹ እመር እመር ብሎ በግቢው ላይ እንደ ድመት እየቧጠጠ ከወጣ በኋላ መሬት ላይ ዘሎ ወርዶ ተሰወረ ።

ከዚያም እግሬ አውጪኝ ብሎ ከትንሿ አቃቂ ወንዝ ማዶ ከሚገኘው ጫካ ውስጥ ሲገባ ፤ አንዱን ዛፍ ተደግፎ ቁና ቁና ተነፈሰና ተዝለፍልፎ ከሳሩ ላይ ወደቀ ። ረጋ ብሎ የሚነፍሰው እርጥብ ንፋስ በዛፎቹ መካከል ሽው ሽው ሲል ቅጠሎቹ ይንኮሻኮሻሉ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በልሁ ድንጋጤውና ድካሙ አልፎለት ከዛፉ ስር ጥላው ላይ በጀርባው ጋ ብሎ ተኝቶ የጠገበ ሆዱን እያሻሸ በትናንሽ አይኖቹ በዛፎቹ ቅርንጫፎች መካከል ሰርቃ የምታየውን ፀሃይ መልሶ እያየ ፈገግ ይል ነበር ።

ከዚያን ቀን በኋላ ግን በልሁ እዚያ መንደር ውስጥ አልታየም ። ወደ ከተማ ወጥቶ በየአውራ መንገዶቹ ላይ ሲዞር ፤ "ወዛደር! ወዛደር!" ብለው ሰዎች ሲጣሩ የሰማ እንደሆነ ወደዚያው ብር ብሎ እየሄደ ዘንቢሉንም አነስተኛ እቃውንም ሲሸከም. . .ከዚያ ደግሞ አንድ ሁለት ሶስት ቀን ከሻይ ቤት ውስጥ በአስተናጋጅነት ተቀጥሮ ሲሰራ ሰንባብቶ ነበር ። በመሃከሉም ያን እለት ዶክተር ማርኮ ማድ ቤት ውስጥ የሰራው ስራ ወሬው መንደሩ ውስጥ ተናኝቶ ነበር ።

ወደ ሰፈሩ የመጣ እለት እንደ ወትሮው ሁሉ ወደ ትንሿ ሱቅ ነበር የሄደው ። የመንደሩ ልጆች ከዚያ አይጠፉም ። ገና ከሩቅ ሲያዩት መሳቅ ጀመሩ ። በልሁ እንደ ማፈርም እያለው መሬት መሬቱን እየተመለከተ ፤ ደግሞ በነዚያ እንደ ቦና መሬት በተሰነጣጠቁት እግሮቹ ጣቶች መንገድ ላይ ያሉትን ጠጠሮች መታ መታ እያደረገ እንደ ምንም አጠገባቸው ደረሰ ።

ልጆቹ ገና ሲያዩት መሳቅ ጀመሩ ። በልሁ አጠገባቸው ደረሰና እሱም እየሳቀ ተመለከታቸው ።

"ብለህ ብለህ ደግሞ ሰው ቤት ገብተህ. . ." አለ አንዱ ልጅ ። ሁሉም እንደገና ሳቁ ።

"ምን አደረኩ?" አለ በልሁ ፣ ፈገግ ብሎ ።

"ለምን ሰው ቤት ገብተህ ሰርቀህ በላህ?"

"መቼ ሰረቅሁ? በላሁ እንጂ!. . ."

"ማን ፈቀደልህ? መቼ ሰረቅሁ ይላል እንዴ?"

"እማማ ሞተዋል. . .አባቴ የለም ፣ ራበኝ ፤ ምን ላድርግ ታዲያ?"

"አባትህ የት ነው ያለው?"

"እኔ እንጃ!"

ሁሉም በአንድነት ሳቁበት ።

"እሱም እንደ አባቱ ሌባ ነው የሚሆነው" አለ ሌላው ልጅ ።

"ምን ላድርግ. . .እማማኮ ሞተዋል!" አለ በልሁ እንደገና ።

"ታዲያ ቢሞቱስ. . .ሰርቀህ ብላ ብለውህ ፣ ነው የሞቱት?"

በልሁ አልመለሰላቸውም ። ፈገግ እንዳለ ፊቱን አዞረና በመጣበት መንገድ ቁልቁል መሄድ ጀመረ።

"ቆላ መጣልህ. . .ቺስታ!" አለ አንደኛው ልጅ ።

"የቱ ቆላ?" በልሁ ቆም አለና ፊቱን አዙሮ ጠየቀ ።

"ቆላ ዘበኛው ። የዶክተር ማርኮ ዘበኛ ። ካገኘሁት እገድለዋለሁ ብሏል!"

በልሁ እንደ ድኩላ ቸር ብሎ ወደፊት እየተምዘገዘገ ሮጠና ኮረኮንቹን መንገድ አልፎ ከመቅዐበት ከአውራ መንገዱ ገብቶ ተሰወረ ።

የዚያን ዘመን ክረምት ሃይለኛ ነበር ። ሌት ተቀን ይዘንባል ። ያቺ ቆሻሻ መንደር ይበልጥ ቆሸሸች ። በመንደሩ ግርጌ የምታልፈው ወንዝ ጢም ብላለች ። ያን እለት ከጠዋት ጀምሮ ሲጥል ያረፈደው ዝናም ሲያቆም ፀሃይ ግማሽ ጎኗን ብቻ ብቅ አድርጋ ትጣቀሳለች ። መረሬው አፈር ተላቁጧል ። የቆሻሻ ሽታ አካባቢው አየር ውስጥ ይዘዋወራል ።

በልሁ በድጡ ላይ ፏንጠር ፏንጠር እያለ መጣና ወንዙ ዳር ቆሞ ከበታቹ እያስገመገመ የሚያልፈውን ውሃ ተመለከተ ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ የወንዙ ውሃ ሲጎድል በልሁ እመር ብሎ በገደሉ ላይ ወረደና ከወንዙ ውስጥ እስከ ወገቡ ተንከረበተ ።

በልሁ አጎንብሶ በጣቶቹ ወንዙ ስር የተከማቸውን ደለል ይቧጥጥ ጀመር ። በመጀመሪያ በእጁ ሙሉ አሸዋውን ዘግኖ አወጣና ተመለከተው ። ከዚያም ተናዶ ወራጅ ውሃው ላይ መልሶ በተነውና ፍለጋውን ቀጠለ ። በሁለተኛው ሙከራው በጣቶቹ አንድ ነገር የያዘ መሰለው ። እጁን ቶሎ ብሎ ከውሃው ውስጥ አወጣውና የያዘውን ነገር ተመለከተው ። የዛገች የሻይ ማንኪያ ነበረች ። በልቡ ተስፋ አደረበትና ፍለጋውን ቀጠለ ። ደግሞ ደጋግሞ ሞከረ ። አሸዋ ፣ አሸዋ ፣ አሸዋ ብቻ . . . ተናደደ ። የመጨረሻ ሙከራው ነበር ። አንዲት የዛገች የድሮ አስር ሳንቲም ከአሸዋው ጋር አወጣ ። ተበሳጨና አስር ሳንቲሙንም አሸዋውንም መልሶ ውሃው ውስጥ ወረወረው . . .

በልሁ ወንዙ ውስጥ ዘሎ ሲገባ ያዩት የመንደሩ ልጆች አፋፍ ላይ እጅብ ብለው ቆመው ይመለከቱታል።

"ምንድነው የምትሰራው ፣ ቺስታ?"

በልሁ እስከ ወገቡ ወንዙ ውስጥ እንደ ተንከረ ቀና ብሎ አፋፉ ላይ የቆሙትን ልጆች አያቸው ።

"እፈልጋለሁ. . .ምናምን እፈልጋለሁ!"

ከዚያም እንደገና አጎንብሶ ስራውን ቀጠለ ።

"ምንድነው የምትፈልገው?"

"የተገኘውን. . .እቃ ምናምን ፣ ማን ያውቃል. . . ወንዙ ሲሞላ ብዙ እቃ ያመጣል!"

እውነትም በጣም የዘነበ እለት ትንሿ ወንዝ የማታመጣው ነገር አልነበረም ። ቃዲያ በልሁ ዝናቡ እስኪያቆም ይጠብቅና ውሃው ጎደል ሲል ዘሎ ይመሰግበታል ። በዚያን ሰሞን ለእሱ ከማንም በላይ የጠቀመችው ወንዟ ነበረች ። አሮጌ ቆርቆሮዎችና ብረታ ብረቶች ተጠራቅመው ፣ "ቆርቆሮ ያለሽ!" እያለ በየ እለቱ በመንደሩ ውስጥ እየጮኸ ለሚያልፈው ሰውዬ ይሸጣል ። ትናንሽ የመድሃኒት ብልቃጦችም ቢሆኑ የቁንጫ መድሃኒት ነጋዴው ይገዛቸዋል ። ቃዲያ ያን ሰሞን ሰማዩ ባስገመገመ ቁጥር የበልሁም ልብ በተስፋ ይዘል ነበር. . .

ከወንዙ ዳር የተሰራው የእትዬ ደብሪቱ ሽንት ቤት ፈራርሶ በዝናሙ ውሃ ጢም ብሎ ሞልቶ ነበር ። በጋውንም ቢሆን እንዲሁ አፉን ከፍቶ ስለነበር ከጎረቤቱ ሰዎች ጋር ሲያነታርካቸው ነበር የከረመው ። ህፃናት ልጆች ያላቸው እናቶች ፣ "ልጆቻችን ጉድጓዱ ውስጥ

የገቡ እንደሆን. . .›› እያሉ ሌት ተቀን ይጨቃጨቃሉ ። እየሰከሩ አምሽተው የሚመጡትም የመንደሩ አባወራዎች የሽንት ቤቱን ጉድጓድ ካላስደፈኑ እትዬ ደብሪቱን እንደሚከሷቸው ባለፉ ባገደሙ ቁጥር ያስጠነቅቋቸዋል ።

መጀመሪያ ግን ሽንት ቤቱን የሞላው ውሃ መዛቅ ነበረበት ። የቀን ሰራተኞችም ቢሆኑ የስራውን አስቸጋሪነት እያዩ ብዙ ገንዘብ እየጠየቋቸው አሻፈረኝ ብለው ነበር ። በልሁ ግን አላመነታም ። አሮጌ ባልዲው ላይ ገመድ አስሮ ውሃ ውን እየዛቀ ወስዶ ወደ ወንዙ ይደፋ ጀመር ። የጠየቃቸውም ገንዘብ ትንሽ ነበር ። አስር ብር ። ሌሎቹ ሰራተኞች ግን ከአርባ ብር በታች ንክች አናደርገውም ብለው እትዬ ደብሪቱም ተስፋ ቆርጠው ትተውት ነበር ።

አስር ብር ፡ ለዚያ አስልቺና አስቸጋሪ ስራ ። እትዬ ደብሪቱ በነፃ የተሰራላቸው ያህል ደስ ብሏቸው ነበር ፤ ከጉድጓዱ ራቅ ብለው የአፍንጫቸውን ቀዳዳዎች በባህር ዛፍ ቅጠል ወትፈው በልሁን እያዩ ለብቻቸው ይነጋገሩ የነበሩት ።

‹‹አይ ወንድ! አይ ጀግና!. . .አሁን ይሄ ልጅ ነው? የልጅ ጀግና!››

ትንሽ ቆይቶ ፀሃይዋ ወደ ምእራቡ ጀንበር ጋደል ስትል በልሁ የጉድጓዱን ውሃ ግማሹን ያህል ዝቋል ። ከወንዙ ወዲያ ማዶ ፡ ከአፋፉ ላይ የሚመጣ ድምፅ ሲሰማ ነበር ተሽብሮ ስራውን ያቆመው ።

‹‹በልሁ. . .በልሁ ቺስታ!›› ይላል ፣ ያው የሚያውቀው ድምፅ ደጋግሞ ፣ ‹‹በልሁ. . .ቶላ ዘበኛው መጣልህ!. . . ገደለህ! ቶሎ ጥፋ ፣ ገደለህ!››

በልሁ የሚገባበት ጠፋው ። ጉድጓዱ አፉ ላይ እንዳጎነበሰ ሲያዳምጥ ቆየና ባልዲውን ከነገመዱ እዚያው ጥሎ የተበጣጠሰችውን ካኔቴራውን ብቻ እንደ ለበሰ በዚያ በደንብ በማያውቀው መንደር ውስጥ እየተሹለከለከ እግሬ አውጪኝ አለ ። ወደዚያው ከትንሿ አቃቂ ወንዝ ማዶ ወዳለው ሜካ ነበር የገሰገሰው ። እትዬ ደብራቱ በበልሁ እንደዚያ ድንገት እንደ እብድ ሮጦ መጥፋት ቢገረሙም በስራው መጋመስና ሂሳቡን ሳይቀበል በመሄዱ ሳይደሰቱ አልቀሩም ነበር ።

በልሁ ሳሩ ላይ በደረቱ እጅዋ ብሎ እንደ ተኛ የደካምና የረሃብ እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ ። ብርዱ ነበር ከእንቅልፉ የቀሰቀሰው ። እንደዚያ አለት ድንግጦ አያውቅም ። ብንን ብሎ አይኖቹን ሲገልጣቸው ሜካው በጨለማ ተሸፍኗል ። ሰውነቱ ውስጥ የተረፈውን ሃይል ሁሉ ሰብስቦ እንዴት እዚያ ቦታ እንደ መጣ ለማስታወስ ሞከረ ። የሆነው ሁሉ እንደ ህልም በሃሳቡ ውስጥ ተሰማው ። አስታወሰ ። የእትዬ ደብራቱን ሽንት ቤት ጉድጓድ ፣ አጠገቡ ቆመው ያዩት የነበሩትን እትዬ ደብራቱን ፣ ከጉድጓዱ ዳር አጠልቆ አስቀምጦት የነበረውን አሮጌ ኮቱን ፣ “ቶሎ ዘበኛው መጣልህ! አምልጥ!” የሚለውን ድምፅ አስታወሰ ። ከዚያም ትዝ አለው ፣ አስሩ ብር ። ስራውን እንዳልጨረሰ ያውቀዋል ። ግን ከግማሽ በላይ ሰርቷል ። ምናልባት አምስት ብር ቢሰጡኝ ብሎ አሰበ ። እሱም ቢቀር አንድ ሶስት ብር ወይም ሁለት. . . አንድስ ቢሆን. . .ለእራት ይበቃዋል. . .

ብርዱ ጥርስ አውጥቶ ያኝከዋል ። የበልሁ ጥርሶች ይንቀጫቀጫሉ ። ሁለት እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ ፣ ብርዱ ዳንኪራ እያስረገጠው ፣ ጉቶውና ድንጋዩ እያደ

ናቅፈው በዚያች በደንብ በሚያውቃት መንገድ ላይ ወደ እትዬ ደብሪቱ ቤት አመራ ።

መንደሩ በድድቅ ጨለማ ታሽጓል ። የውሻ መንጋ እየተግተለተለ ለስሪያ በመንደሩ የጨቀዩ መንገዶች ላይ ይርሯሯጣል ። የእንቁራሪቶች ሲርሲርታ ከመንደሩ በላይ ያስተጋባል ። የመሸታ ቤቶች በሮች ተከፍተው ጭል ጭል በሚሉት መብራቶቻቸው አላፊ አግዳሚ ውን ይጠቅሳሉ ።

በልሁ ቁና ቁና ይተነፍሳል ። ትንፋሹ የጉም ቡጫቂ እየተመሰለ ከምሽቱ ቀዝቃዛ አየር ጋር ይደባ ለቃል ። የእትዬ ደብሪቱ ቤት ተዘግቷል ። በሩን አንኳኳ!

"ማነው?" አሉ እትዬ ደብሪቱ የበሩን መንኳኳት ሰምተው ።

በልሁ በበሩ ስንጥቅ አጮልቆ ወደ ውስጥ ተመለ ከተ ። ባለ ሃያ አምስት ሻማ አምፑል የደበዘዘ ብርሃኗን ቤቱ ውስጥ ፈንጥቃበታለች ። እትዬ ደብሪቱ ከጓዳ ወጡና በሩ አጠገብ ሲደርሱ ለማረጋገጥ እንደገና ጠየቁ ።

"ማነህ አንተ?"

"እኔ ነኝ . . እማማ ደብሬ!" አለ በልሁ ፣ ጥርሶቹ አላናግር እያሉት ።

"ማነህ አንተ? ስም የለህም?"

"በልሁ ነኝ!" እትዬ ደብሪቱ አውቀውታል ፤ ስሙን ሲሰሙ እባብ እንደ ነደፋቸው ሁሉ ወደ ኋላ ቸው ተፈናጠሩ ።

"በልሁ ማን?"

"በልሁ. . .በልሁ ቺስታ ነኝ ፣ እማማ ደብሬ ።"

"የቱ ነው በልሁ ፊሽካ ደግሞ?"

"ፊሽካ አይደለም እማማ ደብሬ ፣ ቺስታ ነው. . ."

"ምንድነው ቺስታ ደግሞ? ያባትህ ስም ሌላም አልነበር እንዴ? ለመሆኑ ቺስታ ብሎ ስም ምንድነው?"

"ልጆቹ ናቸው ቺስታ ብለው የሚጠሩኝ ፣ እማማ ደብሬ. . .ቺስታ ምንም የሌለው ፣ በቃ ጠብሽ የወገረው ማለት ነው. . ."

"በምን ቋንቋ መሆኑ ነው? መቼም የዛሬ ልጆች የማታመጡት ነገር የለም. . ."

"ልጆቹ ናቸው. . .እማማ ደብሬ ።"

"እሺ እሱስ ይሁንና አሁን ምን ፈለክ. . .አልመሸብህም? እንዲያው ጨለማውንም ፣ ተናካሽ ውሻንም አትፈራም ልጄ? እንዲያው ምን አይነት ልበ ድፍኑ ነህ በል? የወንዙንም ጋኔል ከምንም አልጣፍከው?"

"እማማኮ ሞተዋል ፣ አባቴም የለም ። የምበላው የለኝም እማማ ደብሬ ።"

"እሳቸውስ እንኳን ሞቱ ፣ ተገላገሉት ። ሰውም ምድሩም ሰልችቷቸው ነበር ። አባትህም ቢሆን በስራው ነው የታሰረው ። አንተም ብትሆን ትንደሱው ሳትሆን አትቀርም ። የማን ዘር ጎመን ዘር. . .ለመሆኑ እዚያ ቱጃሮች ቤት ምን ስትል ገብተህ ነው ማድ ቤት ገብ ተህ ድስቱን ከፍተህ. . ."

"እሺ ኮቴን ስጡኝ እማማ ደብሬ ፣ በርዶኛል" አለ በልሁ ፣ መንጋጋው ልክ ምስማሩ ተነቅሎ ነፋስ

እንደሚያንቀጨቅጨው የቤት ክዳን ቆርቆሮ ሽቅብና ቁልቁል እያለ አፉን አላስከደን ብሎት ።

"እንዲያው ምን ብትደፍር ነው በል ከማድቤታ ቸው ገብተህ ወጡን ገልብጠህ እንደዚያ ጉድ ያደረክ ቸው?"

"እርቦኝ ነው እማማ ደብሬ. . .እሺ ኮቴ የት ነው? ኮቴን. . .ብርዱ ገደለኝ!"

"ይብላኝ ለወለደህ. . .ባለጌን ከወለደ የገደለው ፀደቀ አሉ! ያውልህ ከዚያ በረንዳው ላይ ተሰቅሎልሃል!"

እርጌ ኮቱ ከበረንዳው አግዳሚ እንጨት ላይ እንደ ረጠበ ተንጠልጥሏል ። በዝናም በስብሶ ይከረፋል ። አውርዶ ለበሰው ። በልሁ ዝም ብሎ ቆየና እንደገና ቀጠለ ።

"ታዲያ ምንም አይሰጡኝም እማማ ደብሬ?"

"እስኪ እንዲያው የሰው ማድ ቤት ከመስበር አብሉኝ ብለህ ብትለምናቸው ምናለበት? ቱጃሮች ናቸው ። እንኳን ላንተ የሚሆን ቀርቶ. . .ይኸንን መን ደር በሙሉ ማብላት ይችላሉ. . .አይጨክኑብህም ነበር ።"

"የሰራሁብትን አይሰጡኝም እማማ ደብሬ? በጣም ርቦኛል!"

"ዘበኛቸውማ እንዲያው እጁ ይግባ እንጂ እሱን አያድርገኝ ይላል አሉ. . ."

"ማን?" አለ በልሁ ፤ ድንገት ቶላ በአይነ ህሊናው ታይቶት ።

"ያው ቶላ ነው ማንትስ የሚሉት ነዋ! ማ ይለኛል ደግሞ? ስራህን አጣኸውና ነው?"

"እሺ እርሶስ ግማሹን እንኳን አይሰጡኝም? በጣም ርቦኝ ነው. . ."

"ቢርብህ እኔ ምላርግህ? የወለዱህን ራበኝ በላቸው እንጂ ። አዳሜ ይፈለፍል ይፈለፍልና ለሰው ማስቸገሪያ. . .ድሮም እኔ ልጅና ረሃብ አልወድም ። እንኳን መሃን አደረገኝ. . .እንኳን ማህፀኔን ዘጋው. . ."

"እሺ ገንዘቡ ይቅርና. . .ቢቃ እንጀራ ስጡኝ ።"

"ጠዋት. . .ጠዋት ና ። አሁን አልከፍትም ። ሰአት አልፏል ።"

"እቤት አልገባም እሺ. . .በሩን ትንሽ ከፈት አድርጉና በቀዳዳ አቀብሉኝ ቢቃ. . ."

"አሁን አንድ ቀን ማደር አቅቶህ ነው እንደዚህ የምትሆነው? ነገ አልኩህ ነገ! እንግዲህ አታድርቀኝ!"

"ጠሚን እኮ ነው የዋልኩት እማማ ደብሬ. . ."

"ታዲያ ምን ላርግህ? እሳ! ምን እንዳበደ ሲያበር ወሰደህ? አሁን አልከፍትም አልኩህ አልከፍትም!. . . ለሌላ ነገር እንደሁ የመጣኸው ንገረኝ!. . ."

በልሁ ከዚያው ከበሩ ላይ ዝም ብሎ ቆመ ። ከዚያም ድንገት የሞቱት አሳዳጊው አሮጊት ትዝ አሉት ። ከየትም ከየትም ብለው አምጥተው ማታ ማታ የሚሰጡትን እንጀራ ሲያስታውስ አይኖቹ ለመጀመሪያ ጊዜ እንባ ቢጤ ቋጠሩ ።

ካልራበው በስተቀር ለምንም ለማንም ግድ የለውም ። እነዚያ አባትና እናት ያላቸው ፣ በሞቀ ቤት ውስጥ ጠግበው በልተው የሚኖሩት የሰፈሩ ልጆች ለምን እንደሚስቁበትና እንደሚሳለቁበት አስቦ እንኳን

አያውቅም ። ቶላ ዘበኛውም ቢሆን የቤቱ ባለቤቶች ዝም ሲሉ ለምን እሱ በሰው ቤት ሃላፊ ሆኖ እንደሚያላ ድደው ማንንም ጠይቆ አያውቅም ። እትዬ ደብሪቱም ቢሆኑ ቀን እንደዚያ ደስ እያላቸው ሲያስሩት ውለው፣ አሁን ሲመሽ ለምን እንደዚህ እንደ ተቀየሩ አላጤ ነውም ። እንዲት ዳቦ ትበቃው ነበር ፡ ለወስፋቱ ማስታ ገሻ ።

በልሁ አይኖቹን ጨመቅና ምንም ሳይናገር በመ ንደሩ አቋርጦ ወርዶ የእንጨት ድልድይዋን ተሻገረ ። ከእንጨት ድልድይዋ ስር ትንሿ ወንዝ እያንኀራኀረ ረች ቁልቁል ወደ አቃቂ ትወርዳለች ።

“ነገ . . . ነገ በጠዋት ተነስቼ ወንዟ ውስጥ ገብቼ እፈልጋለሁ . . . ሌሊት መዝነቡ አይቀርም ፤ እናም ወንዟ ብዙ እቃ ይዛ ሳትመጣ አትቀርም” አለና ከወንዟ ጋር የተግባቡ ይመስል ሆዱ ባዶም ቢሆን ፤ ልቡን ደስ አለው።

# መና የቀረ ህይወት

አውሮፕላኑ አዲስ አበባን ወደ ኋላው ትቶ ረጅም ጉዞውን ከጀመረ ቆይቷል ። ሸለብ አድርጎኝ ከነበረው እንቅልፍ ከነቃሁ በኋላ ትንሽ ጊዜ በመስኮት በኩል ውጪ ውጪውን ስመለከት ቆይቼ ፣ አጠገቤ የተቀመ ጠው ሰው ድንገት እንደ ብራቅ ሲጮህብኝ ነበር ቀልቤ ተገፎ አይኖቼን ወደ ውስጥ የመለስኩት ።

"ተመልከት እስኪ የእኔ ወንድም . . . እነዚህ እር ኩሶች የሚሰሩትን !" አለ ሰውዬው ፣ በእጁ የየያዘውን መፅሄት ገልጦ ከአንደኛው ገፅ ላይ ካለው ከአንድ ሰው ፎቶግራፍ ላይ አይኖቹን እያፈጠጠ ። "ድርጊቱ የተፈፀመው ኒው ዮርክ ውስጥ ነው ። አንዱ ፈረንጅ በባቡር ሲጓዝ ገና ለገና ሊዘርፈኝ ነው በማለት አን ዱን ጥቁር በሽጉጥ ተኩሶ ይገድለዋል ። እና ፣ ይኸ ዜና የሚለው ፣ ገዳዩ ፍርድ ቤት ከቀረበ በነፃ ሳይለቀቅ አይ ቀርም ነው ። አየህ ፣ እነሱ እንደሆኑ ለጥቁር ሞት ደንታ የላቸውም ። ነጩን ገዳይ ግን እንደ ጀግና ነው የሚ ያዩት ። አላባማ ወይም ሚሲሲፒ ቢሆን ኖሮ ወንጀሉ የተፈጸመው አይገርመኝም ነበር ። ይታይህ ግን ፣ ኒው ዮርክ ውስጥ እንደዚህ አይነት የዘረኝነት ተግባር ሲፈ ፀም . . . አንተ ራስህ አንብበው እስኪ ይኸንን ጉድ!" አለና ገልጦ የያዘውን መፅሄት እንዳነበው ሰጠኝ ።

በግምት አርባ አመት ይሆነዋል ። በደንብ የተ ገነባ ሰውነትና የቀይ ዳማ መልክ አለው ። ፀጉሩ ከግ

ንባሩ ገባ ያለ ፡ አይኖቹ ጉድጓዶቻቸው ውስጥ ወዲያና ወዲህ ብር ብር የሚሉ አይነት ናቸው ። እንቅስቃሴው ሁሉ ፈጣን ነው ። አሁን እግሮቹን ይዘረጋቸዋል ። እንደገና መልሶ ይሰበስባቸዋል ። እንደገና ያጣምራቸዋል ። ሲናገርም እጆቹን አስር ጊዜ ያጥፍና ይዘረጋቸዋል ። ጣቶቹን ያንቋቋና ፀጉሩን ወደ ኋላ በመዳፉ ያስተኛዋል ። ወዲያው ደግሞ አፍንጫው ስር ችርችም ብሎ የተስተካከለውን የሂሙን ጫፍ በረዶ በሚመስሉት ጥርሶቹ ይነካክሰዋል ።

“ለምንድነው የገደለው?” አልኩት ፡ ፊቱን ወደ ሰውየው አዙሬ ። ዝም አለኝ ብሎ እንዳይቀየመኝ ያህል ነበር የጠየኩት ። ደግሞም በዚያ ፈረንጆች በሚበዙበት በረራ ላይ ከሀገር ልጅ ጋር እየተጫወቱ መጓዙ ጥሩ አጋጣሚ መስሎ ተሰማኝ ። ባይሆን ብቸኝነቴን ይካፈልልኛል ብዬ አሰብኩና ሰውዬውን አዳመጥኩ ።

“ለምንድነው የገደለው ? . . . እሺ ጥሩ ጥያቄ ነው” አለ ሰውዬው ፡ እንደገና ሎሆ ። ከተቀመጠበት ሆኖ ይቁነጠነጣል ። “ማንበብ ካልፈለክ እኔው ልንገርህ ። መቼም እዚያ ሀገር ነገር ሁሉ በጥቁር ይገናል። ታዲያ ይኸ ነጭ ሲፈጥረውም እንዲያው እርብትብት ቢ ጤ ኖሯል . . . ደግሞም በዚያ ወንጀል በሚበዛበት የኒው ዮርክ የምድር ውስጥ ለውስጥ ባቡር ላይ ጥቁር ሰው ቢገድል ነገሩ ብዙም እንደማይከርበት ውስጠ ህሊናው ሳይገነዘበው አልቀረም ። ህጉ እንደሆነ በእነሱ ጎን እንደሚቆም የታወቀ ነው ። ታዲያ ሽጉጡን ያወጣና ኳ! ኳ! ኳ! ቡም! ቡም! ማድረግ ነዋ! ለጊዜው ይያዛል ። ሆኖም ይኸ ዕሁፍ እንደሚለው በነፃ መለቀቅ አለበት ። ምክንያቱም ራሱን ከወንጀለኞች ለመከላከል ብሎ ነው ግድያውን የፈፀመው ይላል ። እንዲያውም

ነጮቹ ወዲያው በነፃ እንዲለቀቅ ስልፍ ሁሉ አድር ገው ጠይቀዋል ። እንደ ጀግና ነው የሚያዩት ። ይታይህ እስኪ ፤ አንድ ያልታጠቀ ምስኪን ጥቁር ገደለና በቃ ጀብዱ መስራቱ ነው ። አብዶች ናቸው! የእብድ መጨ ረሻ !" አለና ፊቱን ድንገት ወደ መዕሄቱ መለሰው ።

የሰውዬው እንደዚያ መሆን ፡ ባነበበው ሁኔታ እን ደዚያ መቆርቆሩ ሳይገርመኝ አልቀረም ። እኔ ግን ከዚ ያም የበለጠ ወንጀል ስለ መፈፀሙ ባነብ ወይም ብሰማ፣ እራሴን ነቅንቄ ወይም ከንፈሬን መጥጬ ዝም ከማለት ሌላ ያን ያህል በነገሩ ልቤ የሚነካ አይመስለኝም ። የዚህ ሰውዬ ሁኔታ ግን የተለየ ነበር ። ወንጀሉ የተፈ ፀመበት ቦታ ተወልዶ ያደገበት ሀገሩ አይደለም ። የሞተውም ሰው ቢሆን የቅርብ ዘመዱ ወይንም ወገኑ አይደለም ። ግን እሱ እንደዚያ መቆርቆሩና በሁኔታው መናደዱ አስገረመኝና ደህና ሰው ሳይሆን እንደማይ ይቀር በመገመት ይበልጥ ላነጋግረው ፈለኩ ።

"ታዲያ . . . " አልኩት ፡ ፊቴን አዞሬ አይኖቹን ትኩር ብዬ እየተመለከትኩ ፡ "ታዲያ የሚቹ ወገኖች ይግባኝ ሊሉ አይችሉም እንዴ?"

ሰውዬው ድንገት እባብ እንደ ነደፈው ሁሉ ሰው ነቱን አወራጨና ወዲያና ወዲህ የሚመላለሱትን ትና ንሽ አይኖቹን ጉድጓዶቻቸው ውስጥ እያሽከረከረ ፤ "እዬዬ . . . የእኔ ወንድም ሞኝ ነህ ልበል? . . . ወይ ንስ ሀገሩን አታውቀውም? ነገርኩህ እኮ ፡ በምንቸ ገረኝነትና በትእቢት የተፈፀመ ወንጀል ነው ። በጥ ላቻ የተደረገ ነገር ነው ። ደግሞ ይኸ የመጀመሪያቸው ወይም የመጨረሻቸው ጊዜ አይደለም ። የዚያን ሀገር ታሪክ በደንብ አታውቀውም መሰለኝ ። ስንት መቶ አመት

ሙሉ ሲሰቅሉ ፣ ሲገድሉ ፣ ሲገርፉ ፣ እንደ ከብት ሲነዱ ነው የኖሩት—ጥቁሩን ህዝብ ። ታሪካቸው በፍርድ ገም ድል ድርጊቶች የተሞላ ነው ። ጥቁርን አሁንም ቢሆን በልባቸው እንደ ሰው አያዩትም ። እነዚህ ዘረኞች . . .እር ኩሶች ናቸው . . . 'ክሉ ክላኖች' ጥቁሩን በጠራራ ፀሃይ አልነበረም እንዴ በአደባባይ ሲሰቅሉት የኖሩት ?... አሁንስ በቅርቡ . . . ማልኮም ኤክስን ማን ገደለው ? ማርቲን ሉተር ኪንግን ማን ገደለው ? እነሱው ናቸው! አሁንም ቢሆን ያው ናቸው ፤ ለይስሙላ ነው እንጂ ብዙም አልተለወጡም ። በየቀኑ ስንት ጥቁር ይገደላል መሰለህ በግፍ ? ስንቱ ተስፋ እየቆረጠ ራሱን ይገድላል? ስርአቱ ስንቱን በቁሙ ይገድለዋል ? እውነት መሰለህ የነፃነት ሃገር የሚሉት ? ነጩና ሃብታሙ ነው ነፃ . . . በእር ግጥ ለይስሙላ አሁን አሁን አንዳንድ ጥቁሮችም ሃብ ታሞች ሆነዋል ፤ ግን አይምሰልህ . . . 'ናሙና' ነው ። ለይስሙላ ነው ። ከሰላሳ ሚሊዮን በላይ ጥቁር ህዝብ ባለበት ሃገር ስንት የጥቁር ሃብታም አለ ? በአንዱ እጅህ ጣቶች ላይ ትቆጥራቸዋለች ! . . . ሳውዝ ብሮንክስ ፣ ሃር ለም ፣ ዋሺንግተን . . . ሌላው ቦታ ስንት ምስኪን ጥቁር አለ? ቆጥረህ አትዘልቀውም . . . ''

''ዋሺንግተን ነው የምትኖረው ?'' አልኩት አቋ ርጬው ። እንደ ጦር የሚዋጉ አይኖቹን ጉድጓዶቻቸው ውስጥ እሽከረከረና መለሰልኝ ።

''አሁን እንኳን እዚያ አልኖርም ። ድሮ ተማሪ ሆኜ ግን በደንብ አውቀዋለሁ ። ከዚያም ወዲህ ብዙ ጊዜ ተመላልሼበታለሁ ። በነገራችን ላይ ትሁንም ወደ ዚያው ሃገር ነው የምሄደው ፣ ለስራ ጉዳይ ። ካይሮ ግን ትንሽ እቆያለሁ ። እና ፣ አብዛኛውን ሃገር አይቼ ዋለሁ ። ከምስራቅ እስከ ምእራቡ ክፍል ፣ ከፋውንም ደቡ

ንም አይቻለሁ ። ግን አይም ስልህ ፡ እነሱ እንደሚሉት አይደለም . . . . 'ዘ ላንድ ኦፍ ኦፖርቹኒቲ' ይሉታል— ሃገራቸውን ። ዕድል በሽበሽ የሆነበት ሃገር ማለት ነው። በእውነት እንነጋገር ካልን እድሉ ያለው ለነጩ ሃብ ታም ፡ ገንዘብ ላለው ወይንም እውቀት ላለው ብቻ ነው . . . ምክኒያቱም በእድሉ ይጠቀሙበታል ። ስንት ጥቁር ፡ ስንት ላቲኖ ፡ ስንት ባይታዋር ፍዳውን ያያል ። አየህ የእኔ ወንድም ፡ ነጮቹ . . . ማለቴ ሃብቱንና ፖለቲካ ውን የሚቆጣጠሩት ብልጦች ናቸው ። ያ ሁሉ አዱ ኛና ደስታ የተከማቸው በስንትና ስንት ትውልድ የባ ሪያ ጉልበት ፡ በስንት የመጤ እውቀት ነው ። ላባቸውንና ደማቸውን ያፈሰሱት ግን ከፍርፋሪ ሌላ አላገኙም ። ሃብታሙ የሚሰራ አይምሰልህ . . . በጣም ደልቃቆች ናቸው ። ከጥቂቶቹ በስተቀር በቃ ፡ መጠጥ ፡ ወሲብ ፡ ደስታ ማሳደድ ብቻ ነው . . . ፋብሪካውን ይገዛሉ ፤ እውቀቱን ይገዛሉ ፤ ያሰራሉ . . . እነሱ ብቻ ቁጭ ብለው በትርፉ መዝናናት ነው ።"

"ከውጪ ወደዚያ ሃገር የሚሄዱትስ እንዴት ይኖ ራሉ ?" እንደገና አቋርጬ ጠየኩት ፤ ምናልባት እንዲህ የሚመረረው በራሱ ላይ የደረሰ በደል ይኖራል ብዬ በመገመት ።

"እኔ እንኳን በስኮላርሺፕ ነበር የሄድኩት ። እን ደዚያ አይነት እድል ካገኘህ ይሻላል ። ረዳት ከሌለህ ግን እውነቱን ልንገርህ ፡ ፍዳህን ነው የምታየው ። ወይም ከመጠን በላይ ችሎታ እንዲኖርህ ያስፈልጋል፤ በማንኛውም መስክ ቢሆን ። ተሰጥኦ ካለህ ርግጥ ሌላው ቀርቶ ሌባና ነፍስ ገዳይ ብትሆን እንኳን ፡ እንደ ማፊ ያዎች ከብረህና ተከብረህ ትኖራለህ ። ተራ ሰው ከሆ ንክማ በቃ . . . እንደ ምንም ትበላለህ ትጠጣለህ ። በሮቶ

ግራፍ ሲያዩ ያማረብህ ፡ የደላህ ትመስል ይሆናል ። ደግ ነቱ ህሊናህን ገልጦ የሚያይ የለም እንጂ በስንት ነገር ትቆስላለህ መሰለህ ? በየቀኑ የሚደማውን ልብህን ለማን ታሳየዋለህ? ባይታወርነት ፡ በሰው ሃገር ጠብ ላይል ኑሮ ሌት ተቀን መዋተቱ ፡ የሀገር የለሽነት ስሜት ፡ በምፅዋት መኖሩ . . . ብዙ ችግር ይኖራል እርግጥ ሃብ ታም ሀገር ነው ። ለማመን የሚደንቅ ስልጣኔ አላቸው ። ግን በዚያ ሁሉ መሃል አንተ ምንም አይደለህም ። የእኔ የምትለው ነገር የለህም ። ውሎ አድሮ ለሃገሬ ፡ ለወገኔ ምን አደረኩለት የሚል ጥያቄ ይነዘንዝሃል ። እኛ አፍሪካውያን ዞረን ዞረን ያው ቤታችን ነው ትገ፤ የሚ ለን . . . ቢከፋም ቢለማም ያው የቀያችን ሽታ ፡ ቆሻ ሻውም ቢሆን ይናፍቀናል . . . ”

“አንተ ግን እዚያ የነበርከ ጊዜ የደረሰብህ ችግር ነበር? ማለቴ . . . ” ሰውየው እስከፌሬስ ድረስ አልጠ በቀኝም ። ከአፌ ላይ ነጠቀና ቀጠለ ።

“በእኔ ላይ ባይደርስስ ? ! የምታየውና የምትሰማው እንዴት እረፍት ይሰጥሃል ? መቼስ ሰው ነህ . . . ታዲያ የእኔ ወንድም ስንት አስነዋሪ ነገር አመለከት ነበር መሰለህ ። ታዲያ እንዳልኩህ እረፍት አይሰጥህም ፤ ያሰ ቃይሃል ። ገና ስታየው ያንገሸግሽሃል ፣የህ ፡ ይሄ የእኛ የአፍሪካውያን ባህርይ ነው ። ዌል ፡ ንንዳልኩህ ሃብታ ሞች ናቸው ። ይኸ ምንም ጥርጥር የለው ። ግን አየህ ከሃብቱ ጎን ስንት አሳፋሪ ነገር አለ መሰለህ ። እንዳል ኩህ ይኸ ዘረኝነታቸው ፡ ፍርደ ገምድልነታቸው ፡ ወንጀ ላቸው ፡ የተደበቀው የጥቁሮቹ ድህነት . . . እነሱ እንደ ሚሉት እንዳይመስልህ ። ገና ብዙ ይቀራቸዋል ።

“እኛ አፍሪካውያን በእርግጥ ድሆች ነን ። ግን ለሰው ክብር አለን ። ያው የምታውቀው መተዛዘን

አለ. . .እዚያ እኮ ብታይ ፡ ትን ቢልህ ውሃ የሚያቀብ ልህ የለም ። ሁሉም በየፊናው መሮጥ ፡ መሮጥ ፡ ነው ፡ መሽቶ እስኪነጋ መሮጥ ። መሮጥ ያልቻለው መንገድ ላይ ወድቆ ይቀራል ። የሚያነሳው ፡ አይዞህ የሚለው የለም ። እየዘለሉት ያልፋሉ ። ስለዚህ ህሊናህ ከመጠን በላይ ይወራጫል ። ሌት ተቀን ጭንቀት ነው ። ያው ዞሮ ዞሮ በልቶ ለማደር ፡ ለብሶ ለማጌጥ ነው ፤ ከከርስ ለማ ያልፍ ኑሮ. . .”

ሰውዬው ንግግሩን አቋርጦ ትንሽ ሲያስብ ቆየና እንደገና ቀጠለ ።

“እየህ ፡ እኛ አፍሪካውያን በዚህ የመተዛዘን ባህ ላችን ላይ ትንሽ ችግር ባይኖርብን ኖሮ. . .ምን ልበ ልህ ፡ ከእነሱ የተሻለ ህይወት ይኖረን ነበር ። ሙት እው ነቴን ነው ፤ መንፈሳችን እንደ እነሱ አልሻገተም ። ብል ጭልጭ ነገር የማምለክ በሽታ ገና ብዙ አልተጠናወ ተንም ። ዋናው ነገር ግን መተዛዘን ነው ። ለሰው ችግር ልብህ የማይደማ ከሆነ እኮ በቃ ሰው ነህ ማለት ያስ ቸግራል ። ርህራሄ ፡ ሰብአዊነት በሌለበት ህብረተሰብ ውስጥ መኖር በቃ ፡ በቁምህ ያሰቃይሃል ። ወይንም አንተ በገዛ እጅህ አለመኖርን ትመርጣለህ. . .ለዚህ እኮ ነው እዚያ ሃገር ሰው አማራጭ ሲያጣና ከሚችለው በላይ ሲሆንበት ከህንፃ ላይ እየዘለለ የሚሞተው ፡ ጥይት የሚጠጣው ፡ የመርዝ ኪኒን የሚውጠው. . .የቀረው ደግሞ በቁሙ ይሞታል ። ማለቴ አደንዛዥ እፅ ወን ጀል ፡ እስር ቤት ፡ የእእምሮ ህመም ፡ ሽርሙጥና. . . ስንቱ ስንቱ ይቆጠራል. . .እንዱ አንድ ጊዜ እንዴት እንደሞተ ታውቃለህ? ነገሩ የራስ ግድያ ነው ፤ ግን ከጀርባው ትልቅ ድራማ አለው ። የአሜሪካ መሪርና አሳዛኙ ህይወት ነው. . .” አለና የሰውዬው መልክ

በድንገተኛ ሃዘን ቅጭም አለ ። አይኖቹ እሩጫቸውን አቆሙና ድንገት ቅዝዝ አሉ ። ምራቁን አከታትሎ ዋጠ ።

"ማነው እሱ? ምን ሆኖ ሞተ?" አልኩት ፤ የሰውዬው ሁኔታ የማወቅ ፍላጎቴን እንደገና ቀስቅሶት ።

"ታሪኩ ትንሽ ቆየት ብሏል ። እዚያው ሃገር ተማሪ የነበርኩ ጊዜ የሆነ ነው ። ቢቆይም ቅሉ ከህሊና የሚጠፋ አይደለም" አለ በሻከረ ድምፅ ።

ሰውዬው እንደገና ዝም አለ ። እኔም ለማዳመጥ ጓጉቻለሁ ።

"በጣም ያሳዝንሃል" አለ እንደገና ትክዝ ብሎ ። "ያ ሃገር የስንቱን ህይወት ከንቱ አስቀረው?"

እንደገና ጥቂት ሴኮንዶች ያህል ዝም ብሎ ቆይቶ ቀጠለ ።

"ወጣት ሆኖ ነበር እዚያ ሃገር የመጣው—ለትምህርት" አለ ሰውዬው ፤ ረጋ ብሎ ሃሳቡን ለመሰብሰብ እየሞከረ ።

"ከየት ነበር የመጣው?" አልኩት ፤ ታሪኩን ለመስማት እየጓጓሁ ።

"ምን ያደርግልሃል ሃገሩ? በደፈናው አፍሪካዊ ነበር ፤ ጥቁር ነበር እንደ እኛ" አለ ሰውዬው ፤ ቀና ብሎ አይቶኝ እነዚያን እረፍት የለሽ አይኖቹን እንደገና ወዲህና ወዲያ እያንቀሳቀሰ ። እንደገና ዝም አለ ። አንድ የማይታይ ነገር ጉሮሮውን ፈጥርቆ የያዘው ይመስል ።

"እሺ. . . ከዚያስ?" አልኩት ፤ እንደገና እየጎተጎትኩት ።

"ታዲያ እዚያ ሃገር እንዲ መጣ. . .ምን ልበልህ ትንሽ ደመ ቁጡ ነበር ። መቼም እኛ አፍሪካውያን ስንባል በሄድንበት ሁሉ ይኸ የተፈጥሮ አትንኩኝ ባይ ነታችን አብሮን ይዞራል ። ታዲያ ፡ ያ ልጅ የመጣበት ዘመን እንደ አጋጣሚ መጥፎ ጊዜ ነበር. . .አቤት ጊዜው እንዴት ይሮጣል ። እንደ ቀልድ ሃያ አመት ሊሆነው ነው ። ጊዜው የሰው ልጅ መብት ንቅናቄ ዘመን ነበር ። ትግሉ ያየለበት ወቅት ነበር ። እነ ማልኮም ኤክስ ነበሩ ። እነ ጆርጅ ጃክሰን ፡ ጥቁር ፓንተሮች (የጥቁሮች የትግል ድርጅት አባላት) መቼም ስለነሱ ሳትሰማ አት ቀርም ። ነጮቹ ደግሞ ተርበድብደው ነበር ። ታዲያ ይኸ የምልህ ልጅ ለጥቁሮች መብት ለመታገል በነ በረው ፍላጎት በአፍላ ስሜቱ 'ፓንተሮችን' ይቀላቀ ላል ። ትንሽ ቆይቶ ድርጅቱ በአንድ ግዳጅ ላይ እንዲ ሳተፍ ያዘዋል ። ግዳጁ ይታቀዳል ። ምን ይመስልሃል እቅዳቸው?" አለና ቀና ብሎ በሚጠይቁ አይኖቹ ተመ ለከተኝ ።

"ምንድን ነበር?" አልኩት መልሼ እያየሁት ።

"አውሮፕላን መጥለፍ ነበር ፤ አንድ ቦይንግ አው ሮፕላን መጥለፍ ።"

"ለምን?" አልኩት ባልጠበኩት መልስ እየተገረ ምኩ ።

"በቃ በጊዜው ትክክል ቢሆንም ባይሆንም ፡ የት ግል ዘዴ ብለው የገመቱት ታክቲክ ነበር ። በቃ ፤ ሀል ውናቸውን ለማሳወቅና የነጭ ከበርቴዎች ንብረት የሆ ነውን ቦይንግ ጠልፈው ከወሰዱ በኋላ ለማቃጠል ነበር እቅዳቸው ።"

"የት ለመሄድ ነበር ያሰቡት?" ድንግጥ ብዬ ጠየ ኩት ። አውሮፕላን ውስጥ እያለሁ ስለ ጠለፋም ሆነ ስለ ቃጠሎ መስማቱ ሳያሳስበኝ አልቀረም ነበር ።

"ኪዩባ ። አውሮፕላን ጠልፈው ኪዩባ ለመሄድ ነበር ። እንደምታውቀው ኪዩባ ድሮም ቢሆን አሁን አሜሪካ ውስጥ ያሉት 'ታጋዮች' የሚወዱት ሃገር ነች ። በዚያን ጊዜ እነ ቼ ጉቬራ ፣ መቼም ምእራቡን አርበ ድብደውት ነበር ። ልብ በል. . . ቼ ጉቬራ በዚያኑ ዘመን ነበር ቦሊቪያ ውስጥ የተገደለው ።"

"እሺ ተሳካላቸው ወይንስ . . ."

"ቆይ እንጂ ፤ ምን ይሳካላቸዋል ፤ ጉድ ሊሆኑ ነው እንጂ ። ለእቅዳቸው ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጋቸ ውን ነገር ሁሉ አውሮፕላኑ ውስጥ ይዘው ይገባሉ ። ሽጉጥ ፣ የእጅ ቦምብ. . ."

"እንዴት ይዘው ገቡ?" አሁንም ደንግጬ ጠየ ኩት ፣ ስጋት እየተቀሰቀሰብኝ ።

"ቆይ እባክህ ፤ ብዙ ዘዴ ነበራቸው ። በሽፋን አውሮፕላን ማረፊያው ውስጥ የሚሰሩ ጓደኞቻቸው ይኖራሉ ። ጠራጊዎች ፣ መካኒኮች ፣ ፈታሾች ሆነው የሚ ሰሩ ። እሱ ቀላል ነው ። ይኸ አይደለም የሚያስገርመው። አውሮፕላኑ ውስጥ ገብተው እንደ ተቀመጡ ከነመሳሪያ ቸው እጅ ከፍንጅ ይያዛሉ ።"

"አውሮፕላኑ እየበረረ?" አልኩት ፣ እንደገና ደን ግጬ ።

"ማይ ጎድ! ምን ይበራል? ገና ከመሬት ሳይነሳ ነው እንጂ!"

"እንዴት ተያዙ?"

"እንዴት ተያዙ? አዎን ፡ ይኸ ነው ጥያቄው ። እስኪ ገምት ፡ እንዴት ሊያዙ ይችላሉ?" አለና ትክ ብሎ አየኝ ።

"እኔ እንጃ! ምናልባት አይተዋቸው ወይንም ሰው ጠቁሞባቸው ይሆናል!"

"ብራቦ! በጣም ጥሩ ነው ፤ መልሱን አግኝተኸ ዋል ። ሰው ጠቁሞባቸው ነበር ። ማን ይመስልሃል የጠ ቆመባቸው?"

"እኔ እንጃ!"

"የገዛ ጓደኛቸው! ከሃዲ ነው! አየህ ፡ እንዳልኩህ በዚያን ዘመን 'ጋንተሮችን' ለማጥፋት የማይፈነቅ ሉት ድንጋይ አልነበረም ። ለጠቋሚዎች ወፍራም ጉርሻ ይሰጡ ነበር ። መቼም የእነሱ አምላክ ዶላር ነው ። በዶ ላር ሃይል የማያደርጉት ነገር የለም ። ታዲያ የገዛ ጓደ ኛቸው ይከዳቸዋል ። 'ዳብል ክሮሲንግ' ይሉታል እን ደዚህ አይነቱን የክህደት ስራ. . .ታዲያ እሱስ ይቀናው መሰለህ?"

"ምን ሆነ?" አልኩት አቋርጨው ።

"አጅሬ ለካ ከዚህ በፊት በሌላ ወንጀል የሚፈ ለግ ሰው ነበር ። ከእነሱ ጋር መስራት ከመጀመሩ በፊት በባንክ መዝረፍ ወንጀል ተሳትፎ አምልጦ ነበር ። ታዲያ እንደ እሱ አስተሳሰብ የአውሮፕላኑን ጠለፋ አክሽፎ የአገልግሎቱን ዋጋ ከተቀበለ በኋላ በሰላም እያፏጨ ለመሄድ ነበር ። እራሱን ለማዳን ነበር ፡ ግን ከሃዲ መጨረሻው አያምርም ። ፈረንጆቹ ሁኔታውን

ያጣሩና ገንዘቡንም ሳይሰጡት በወንጀል ወደሚፈልግ በት ግዛት ይልኩትና እዚያው ወህኒ ይገባል ።"

"ያልከው ልጅስ እንዴት ሆነ?" አልኩት ፣ የታሪኩን መጨረሻ ለማወቅ እየቸኮልኩ ።

"እሱማ ጀግና ነው! ሌላ ምን ትለዋለህ? እስኪ ይታይህ ፣ ከሌላ ሀገር መጥቶ ፣ ሌላ ሀገር ለሚኖሩ ሰዎች ብሎ የመጣበትን የግል ጉዳይ ትቶ እሳት ውስጥ መግባት. . .እንደዚህ አይነት ድፍረትና ሰው መውደድ የሚገርም ነው ። ሆኖም ታዲያ ተይዞ ታሰረ ። ሊሰራው ያቀደውን ሁሉ አመነ ። በመጨረሻም አስር አመት ተፈርዶበት ወህኒ ወረደ ። ታዲያ ወህኒስ ወርዶ ሊተውት መሰለህ?"

"እንዴ ከተፈረደበት ደግሞ ምን ያደርጉታል?" ገርሞኝ ጠየኩት ። ሰውዬውም ትንሽ ተክዞ ቆየና ታሪኩን ቀጠለ ።

"እየህ ነገሩ ትንሽ የተወሳሰበ ነው ። ልጁ ከመያዙ በፊት አንዲት ፍቅረኛ ነበረችው ፤ ነጭ ነች ። አዎን ፣ አልፎ አልፎ በነጭና በጥቁር መሃከል እውነተኛ ፍቅር ይመሰረታል ። ሴቶች ከወደዱህ እስከ አለም ዳርቻ ተከትለውህ ይሄዳሉ ። የልጁ ፍቅረኛ አንድ ብረታ ብረት ፋብሪካ ውስጥ የሚሰራ ሰው ልጅ ነበረች ። ኮሌጅ ነበር የተዋወቃት ። በርክሌይ ውስጥ ። ካሊፎርኒያ ። ታዲያ ልጁ እንደ ተያዘ ብዙ ሳይቆይ የድርጅቱ መሪዎች ግማሾቹ ተያዙ ፣ ግማሾቹ ተገደሉ ፤ የቀሩት ደግሞ ስደት ሄዱ ። ድርጅቱም ፈረሰ ።

"ታዲያ ወህኒ ሆነውም አላረፉም ነበር ። የወህኒ ቤት ህይወት መቼም አሰቃቂ ነው ። በተለይ ለጥቁሮ

ችና ለፖለቲካ እስረኞች ። 'ሶል ኦን አይስ' የሚለውን መፅሃፍ አንብበሃል? እንደ ነገሩኝ ከሆነ ከጠዋት እስከ ማታ ፋብሪካ ውስጥ በነፃ ያሰሩሃል ። የወታደር ጫማና ልብስ ከሚሰራበት ፣ የጦር መሳሪያ ከሚሰራበት ቦታ. . . ማታ በድካም ውልቅልቅህ ሲወጣ ያንን ውሃ ውሃ የሚል ሾርባ ይሰጡህና መልሰው ክፍልህ ውስጥ ይወረውሩሃል ። ሲፈልጉ ደግሞ ሊጠፋ ሲሞክር ተመታ ብለው ከጀርባህ ተኩሰው ይገድሉሃል ። እንደ ጆርጅ ጃክሰን ማለት ነው ።"

የተሳፈርንበት አውሮፕላን መብረሩ እንኳን አይታወቅኝም ነበር ። አብዛኛዎቹ መንገደኞች ወንበራቸው ውስጥ ጋደም ጋደም ብለዋል ። ግማሹ ያነባል ። አንዳንዱ ያወራል ።

ሰውዬው አንድ አፍታ አይኖቹን አውሮፕላኑ ውስጥ አመላለሰና ሙልሶ እያየኝ ታሪኩን ቀጠለ ።

"በነገራችን ላይ የልጁ ስም ናካሳ ይባል ነበር ፣ ሮበርት ናካሳ. . .ታዲያ ሮበርት ሲታሰር ገና አፍላ ፍቅር ውስጥ ስለነበሩ ያቺም ልጅ በበኩሏ ትሰቃይ ጀመር ። አንዳንዶቹ እንደ ሮበርት ፍቅረኛ ያሉት ከወደዱ ወደዱ ነው ። በጣም ታማኞች ናቸው ። ከሮበርት ጋር አስር አመት ተለያይቶ መኖሩን ስታስበው እንኳን ያንገፈግፋት ነበር ። ይታይህ ፤ በአፍላ ፍቅር ላይ ያሉ ወጣቶች ሳይተያዩ አስር አመት መቆየት. . .ሊገናኙ አይችሉም ። ዕኑ እስራት ቦታ ውስጥ ነበር የታሰረው ። ዝንብ እንኳን አትወጣም ከዚያ እስር ቤት ። በደብዳቤ ብቻ ነበር የሚገናኙት ። ያውም በወር አንድ ጊዜ ሮበርት እንኳን እሱን እንድትረሳውና ሌላ ጓደኛ እንድትይዝ ደጋግሞ ለምኗት ነበር ። እንዲያውም እንዲህ ሲላት

ጊዜ ብሶባት አረፈው ። በፍቅር መቃጠል ሆነ ። የማያዩት ፡ የማያገኙት ፍቅረኛ ፡ ይታይህ እስኪ . . . በሌላ ሰው ልትተካው አልቻለችም ። ታዲያ ይኸንኑ ትፅፍለታለች ። በኋላም ሮበርት ሁኔታውን ተረድቶ ልቡን ወደሷው ይመልስና በበኩሉ መሰቃየት ይቀጥላል ። ግን እንዴት ያድርግ? ሊያመልጥና ሊወጣ አይችልም ። ቢሞክርም እንደሚገድሉት ያውቃል ።”

የምንጓዝበት አውሮፕላን ህዋውን በአፍንጫው እየቀደደ ወደ ካይሮ ይገሰግሳል ። በመሃሉም አስተናጋጅዋ ልዩ ልዩ አይነት መጠጥ የተደረደረበትን ጋሪ እየገፋች አጠገባችን ደረሰችና የምንወስደውን ጠየቀችን። ሁለታችንም ለስላሳ መጠጥ ወሰድን ።

“እሺ እባክህ?...” አልኩት ፣ በፕላስቲክ ኩባያ ውስጥ የያዝኩትን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ጨርሼ ። እሱ ግን አልጠጣውም ። ኩባያውን በግራ እጁ ይዞ በቀኝ እጁ አመልካች ጣት የኩባያውን ጠርዝ እያሻሸ መጠጡን ትኩር ብሎ ያየው ነበር ።

“ዌል...ከዚያማ በቃ ነገሩ ሁሉ ከአንዱ ትራጄዲ ወደ ሌላው በፍጥነት ይሸጋገር ጀመር ። ትንሽ ቆይታ ልጅቷ ምን ትለዋለች መሰለህ? እሷ ምን ታድርግ ፣ ፍቅረኛዋን ለማግኘት ያቀደችው ብልሃት ነበር ...‘እብድ ሆኛለሁ ብለህ ውሸትህን እንደ እብድ ሁን፣ ከዚያ በኋላ ዋጋ የለውም ብለው ይለቁሃል ’ ትለዋለች።

ከዚያ በፊት ብዙ ዘዴ ሞክሮ ነበር ። የሃገሩ ተወላጅ ስላልሆነ እንዲለቀቅና ቅጣቱን ሃገሩ ሄዶ እንዲፈፅም ጠይቆ ነበር ። ይሄ ሁሉ ግን ምንም አልረባውም ። እሱም መቼስ የወደደና ተስፋ የቆረጠ የማያደርገው የለምና እንዳለችው አብጃለሁ ይልና ነጋ

ጠባ መረበሽ ይጀምራል ። ልብሱን ይቀዳል ፣ ራቁቱን ይሆናል ፣ ፖሊሶቹን ልደብድብ ይላል ፡ መስሪያ ለመ ቀማት ይሞክራል…ምን ልንገርህ ፡ የማያደርገው ነገር አልነበረም አሉ ። በመጨረሻም እራሴን አጠፋለሁ እያለ ማስፈራራት ሲጀምር ምን አደረጉት መሰለህ… ያዙኑለት ይመስለሃል ? ይባስ ብለው ከክፍሉ እንዳይ ወጣ አድርገው ፣ የፀሀይ ብርሃን እንኳን እንዳያይ ተደ ርጎ ብቻውን አንድ ክፍል ውስጥ እንዲታሰር የወህኒ ቤቱ ሳይኪያትሪስት ይወስናል…"

"ከዚያስ አባክህ?" አልኩት ፡ የሮበርት ሁኔታ በአይነ ህሊናዬ እየታየኝ ።

"ከዚያማ … ምን ልበልህ … በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ እንኳን ሰውና ብረት እንኳን ይሰበራል ። የም ሩን አብዶ ቁጭ አለ ። ሲታመም እብዶች ሆስፒታል ውስጥ ጣሉት ። በኪኒንም ፣ በኤሌክትሪኩም አደንዝ ዘውት ትንሽ ሲሻለው ወደ መጣበት ሃገር እንዲመ ለስ ወሰኑበት ። እሱም ሁሉ ነገር በቅቶት ስለነበረ በዚያው ይስማማል ።"

"መጀመሪያ ለምን ወደ ሃገሩ አልመለሱትም?"

"እሱማ ያው ወንጀል ሰርቷል ስለ ተባለ በዚ ያው ሃገር ህግ ይቀጣል አሉ ። አውሮፕላን መጥለፍ ደግሞ ከሁሉም የሚጠሉት ወንጀል ነው ።"

"ከዚያስ ? ከሆስፒታል ከወጣ በኋላ እንዴት ሆነ?"

"ከዚያማ ሃገሩ እስኪመለስ ዋሺንግተን እኔ ከም ኖርበት ህንፃ ውስጥ አንድ ድሮ ከሚያውቀው የሃገሩ ልጅ ጋር ትንሽ ቀን ቆይቶ ነበር ። ይታይህ ፡ ወህኒ

ውስጥና ከዚያም ሆስፒታል አንድ ሁለት አመት ነበር ያሳለፈው ። ታሪኩን ሁሉ ያጫወተኝ እራሱ ነው ። አንድ ሰሞን ጥሩ ወዳጆች ሆነን ነበር ። ነፍሱን ይማረውና ፣ 'ሣገሬ ከተመለስኩ ደህና እሆናለሁ ። አዲስ ህይወት እጀምራለሁ...' እያለ ተስፋ ያደርግ ነበር ። በኋላ ግን ሃሳቡን ምን እንዳስለወጠው ይገርመኛል..."

"ያቺስ ፍቅረኛው እንዴት ሆነች?"

"እሷማ ምን ታድርግ ፣ የቻለችውን አደረገች ። ነገሩ ሁሉ እንደዚህ ይሆናል ብላ አላሰበችውም ነበር ። ደብዳቤውም ተቋረጠ ። በመሃሉም ታመመ ። አድራሻውን አታውቅም ነበር ። እሱም ከበሽታው በኋላ የድሮው ሮበርት አልነበረም ። በመሃሉ በቃ ፣ ተቆራርጠው ቀሩ ።"

አስተናጋጅዋ በድምፅ ማጉያው መልእክት ስትናገር ነበር ሰውዬው ታሪኩን ያቋረጠው ። ካይሮ አውሮፕላን ማረፊያ ለመድረስ ጥቂት ደቂቃዎች ቀርተውን ነበር ። ቀበቷችንን አጠባበቅንና ሲጋራችንን አጥፍተን ተቀመጥን ። አውሮፕላኑ ለመውረድ እየተዘጋጀ ነበር ።

"ወዴት ነው የምትሄደው የእኔ ወንድም?" አለ ጎኔ የተቀመጠው ሰውዬ ።

"አቴንስ ነው... እባክህን ታሪኩን ቶሎ ጨርስልኝ... እሺ ሮበርት በመጨረሻ እንዴት ሆነ?" በችኮላ ጠየኩት ።

"እንግዲያው እኔ ካይሮ ስለምወርድ እንዳልከው ቶሎ ልጨርስልህ ። እና...ምን ላይ ነበር ያቆምኩት? አዎን ፣ ከዚያ አፓርታማ ውስጥ እንዳለ አንድ ቀን

በመስኮት ከአስራ አንደኛው ፎቅ ላይ ዘሎ መሬት ላይ ተከስክሶ ሞተ! መጀመሪያ እነሱ በቁሙ ገደ ሉት ፣ ከዚያም እራሱን በራሱ ጨረሰ ። ትገዘ ይለ ኛል ፣ የሞተ እለት እኔም ህንፃው ውስጥ ነበርኩ ። ፖሊሶቹ አስራ አንደኛው ፎቅ ላይ ሲደርሱ የሮበ ርት ክፍል እንደ ተዘጋ ነበር ። ከውስጥ ነበር የተቆ ለፈው ። በተመሳሳይ ቁልፍ ከፍተውት ገቡ ። ትገዘ ይለኛል ፣ በተከፈተው መስኮት በኩል በረዶ የቀላቀለ የክረምት ንፋስ መጋረጃውን እያውለበለበ ይጫወት በት ነበር ። ክፍሉ ውስጥ የሚሸተው ከመኖሪያው ህንፃ አጠገብ ካለው የኬሚካል ፋብሪካ ንፋስ እየተ ሸከመ የሚመጣው አፍንጫ የሚሰነፍጥ ሽታ ነበር ። የቤቱ ሽታ እራሱ የሞት ያህል ይቀፋል ። በክፍሉ ውስጥ እቃው በስነ ስርአት እንደ ተቀመጠ ነበር ። አልጋው ላይ ብቻ ብርድ ልብሱ ተገልጦ አንሶላው መሬት ላይ ወድቋል ። ከመኝታው ተነስቶ እንደ ሞተ ግልፅ ነበር ።

"እኔም ሁኔታውን ስሰማ ዶንግጬ ወደዚያው ሄድኩ ። ታዲያ ነጭ ለባሹ ፖሊስ ወደ ተከፈተው መስኮት ተጠጋና አንገቱን እሰግጎ ወደ ውጪ ተመለ ከተ ። ከአስራ አንደኛው ፎቅ መስኮት ሆነው ቁል ቁል ሲመለከቱት የሮበርት ሬሳ ነጩ በረዶ ላይ ወድቆ ከመጠን በላይ ትንሽ ሆኖ ይታይ ነበር ።በፊት ለፊቱ ነበር የወደቀው ። እና ሁለት እጆቹን ወደፊት ዘርግቷቸዋል ። የወደቀበት ቦታ ጎድጉዶ ግማሽ ሰው ነቱን በረዶ ሸፍኖታል ..."

"ታዲያ ነጭ ለባሹ እሬሳውን ተመለከቱና ፣ 'በዚህ በኩል ነው የወደቀው ማለት ነው ፣ ከመኝታው ተነስቶ ነው የወደቀው. . .የፃፈው ማስታወሻ የለም...'

ሲል ሰማሁት ። ተመልትት እስኪ የእኔ ወንድም ፣ ጉድ አይፈሩም ፣ ደግሞ ማስታወሻ እንዲፅፍላቸው ይፈል ጋሉ . . . ከይሲዎች ናቸው . . . ሞተ ሞተ ፣ ገደሉት በቃ ። ደግሞ የምን ማስታወሻ ነው የሚፈልጉትገ 'እኔ ሞቻለሁ ፣ እናንተ ደህና ሁኑ . . .' እንዲላቸው ነውገ"

"ፎቶግራፍ ካነሱና ራሱን መግደሉን የሚያረጋግ ጡበትን ማስረጃዎች ከለቃቀሙ በኋላ ቤቱ እንዲታሸግ አዘው ሄዱ ። በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ እንባ አው ጥቼ ያለቀስኩት ያን እለት ነበር ። ከዚያ በኋላ እዚያ ህንፃ ውስጥ መኖር አልቻልኩም ፣ ለቅቂ ሄድኩ . . የልጁ ሁኔታ በቁሜም በህልሜም እየመጣብኝ አንድ ሰሞን እረፍት ነስቶኝ ነበር . . ."

"በእርግጥ በጣም በጣም ያሳዝናል" አልኩት በረ ጅሙ ተንፍሼ ፣ "ሬሳውን ግን ምን አደረጉት እባክህ?"

"በቃ ሁኔታው ከተጣራ በኋላ እንዴት መኪና ልከው ሬሳውን አስነሱ ። የልጁ ሞት እንደ እለት ወሬ እንኳን ሆኖ አልተሰማም ። ጥቁር ለእነሱ ሰው አይደ ለም . . . ከይሲዎች! ስለ ውሾቻቸውና ድመቶቻቸው እንኳን ብዙ ይጨነቃሉ . . ስለዚህ ነፍስ ጉዳይ እን ኳን ብዙ ያትታሉ . . . እንደዚህ አይነት ድርጊት ዘለ አለም ሲረብሽህ ይኖራል ። በዚች ደቂቃ ውስጥ እንኳን እዚያ ሃገር ስንት ግፍ ይፈፀም ይመስልሃል ? ልክ እንደ ሮበርት ፣ ልክ እንደዚህ ባቡር ላይ እንደ ተገደለው ጥቁር . . . የስንቱ ህይወት በከንቱ ውጪ ቀርቷል መሰለህ? እዚህ ባልወርድ ኖሮ ስለዚያ ሃገር ብዙ ጉድ አጫው ትህ ነበር ። ለማንኛውም ይኸን መፅሄት ጊዜ ስታገኝ በደንብ መርምረው እስኪ . . . አየህ ይኸን የመሰለ ግፍ ሲፈፀም ስታይና ስትሰማ የትም ይሁን የት ፣ ይረ ብሽሀል ። ደግሞም መረበሽ አለብህ ፣ ልብህ ማልቀስ

ኦሰበት . . . ታዲያ መጥፎ አይምሰልህ ፤ የሁላችንም ልብ የማይሰማ በድን ከሆነማ በአለም ላይ በየቀኑ የሚሰማውን የሰቆቃ ጩኸት ማን ያዳምጣል ብለህ ነው ? . . . '' አለና መፅሄቱን አቀብሎኝ እየተቻኮለ የእጅ ቦርሳውን አንስቶ ሰላምታ ሰጠኝና እንዳቀረቀረ ወደ መውጪያው በር አመራ ። ስሙን እንኳን አልጠየቅሁትም ። ታሪኩ ግን ዘወትር ህሊናን የሚከነክን አሻራውን ትቶብኛል ።

## በሽተኛው

በእርግጥ ወደ ሆስፒታሉ በየቀኑ ብዙ ህመምተኞች ይመጣሉ ። የበዛብህ ሁኔታ ግን ትንሽ የተለየ ነበር ። ግራ የሚያጋባ አይነት . . .

“ . . . ምን አድርግ ትሉኛላችሁ? እኔ አይደለሁም ገንዘቡን የበላሁት! ልብላው በቃ ፤ ምን አገባችሁ! ያ ማስረሻ ሌባው ነው የበላው! ማስረሻ ፤ አይ ማስረሻ . . . . አረፍ ሌባ ነሽ ግን ፤ በቃ አታለሺኝ ጠፋሽ ማለት ነው . . . ቆይ ብቻ እንገናኝ . . . አሳይሻለሁ ! ምን? ስራህ ተመለስ? እሺ ስራዬ እመለሳለሁ . . . ልቀቁኝ በቃ ልሂድ በቃ ፤ እኔ ከደሙ ንፁህ ነኝ ። ስራዬ ልሂድ ፤ ስአቱ ረፈደ፤ ስራ መግቢያው ። በቃ እሺ አልኩኝ እኮ . . . እሺ አስ ተማሪ ነኝ፤ ጎበዝ አስተማሪ ነኝ ። አይ አስተማሪ አይ ደለሁም በቃ ። ገንዘብ ያዥ ነኝ ። በቃ ገንዘቡን እንክት አድርጌ በልቼዋለሁ ፤ ምን ትሆኑ? ሁሉም ይበላ የለም? እናንተስ ትበሉ የለም? ማነው የማይበላው? ሌቦች ! እሺ በቃ አትዩኝ . . . ይኸው መጡ ፤ አይኖቹ መጡ ! ደግሞ ጆሮዬ ስር አታንሾካሽኩብኝ . . . አልሰማችሁም በቃ ! . . . ”ይላል በዛብህ ።

ጆሮዎቹን በሁለት እጆቹ ጥርቅም አድርጎ ይይዛቸዋል ። መለፍለፉን ግን አያቆምም ። ከእሱ በስተቀር ለማንም ከማይታየው አይኖችና ከሚሰማው ድምፅ ለመሸሽ ሲደነባበር ፤ ያው ከሰፈር ድረስ እየታገለ ያመጣው ሰውዬ ይዞ ያስቀረዋል ።

እንደገና በሁለት እጆቹ ፊቱን ይሸፍንና ይጮሃል ። "... መጡ! መጡ! አይኖቹ መጡ! ... ያዩኛል ፤ አሁንም ያዩኛል ። ብዙ አይኖች ያዩኛል!" ይኸንኑ ነበር ደጋግሞ እየጮኸ የሚናገረው ።

እናቱ ነበሩ ይዘውት የመጡት ። ከጎረቤትም አንድ ሁለት ሰዎች ተከትለዋቸዋል ። የሚጠጋው ግን ያው ከበደ ብቻ ነበረ ። በዛብህ ልሂድ ልብረር እያለ ሲታገል ፣ ሲጮህና ያየውን ሰው ሁሉ ሲሳደብ ያው ከበደ ነበር እየተቆጣም ፣ እያስፈራራም ፣ በጉልበትም ቢሆን የሚያስቀረው ።

እናቱ ግን ስራቸው ከምርመራው ክፍል ውስጥ ሆነው ማልቀስ ብቻ ነበር ። "ሰው እንዲህ ከመሬት ተነስቶ ብልሽትሽት ይላል? እመቤቴ ማሪያም ... አሁን ምን አልኩሽና በስተኋላ እንዲህ ያለ መከራ ታሳይኝ?"ይኸንን ብቻ ነበር እያማተቡ የሚያጉተመትሙት።

ታዲያ በዚህን ጊዜ በዛብህ ቀና ብሎ በነዚያ ሚጥሚጣ በሚመስሉት አስፈሪ አይኖቹ እናቱን ትኩር ብሎ ይመለከታቸውና ፣ "እማማ .... እውነቱን ልንገርሽ? በጣም እጠላሻለሁ! እኔ እንጂ ግን በጣም ነው የምጠላሽ ። እናቴ አይደለሽም ፤ ውጪ ከዚህ! ... ሂጂ ብዬሻለሁ.... ለምንድነው ጠበል የወሰድሺኝ? እኔ እስላም ነኝ አላልኩሽም? ስሜ መሃመድ ነው አላልኩሽም? ጫት ልቃም አላልኩም? ..." እያለ ይጮሃል ።

እናቱ ግን በአፋቸው ሳይሆን በእንባቸው ነበር የሚመልሱለት ። "ምን ያድርገው? ወዶን አይደለም... በሽታው ነው እንዲህ የሚያደርገው... ወትሮማ የእኔ ነገር መች ይሆንለት ነበር... እንዲያው ምን አይነት መድሃኒት ይሆን ያቀመሱብኝ... " ይላሉ ፣ በልባቸው።

‘ቪዞፍሬንያ’። ይሄንን ቃል ነበር ዶክተሩ መጀመሪያ የፃፈው፤ ካርዱ ላይ ። ከዚያም ሌሎች ብዙ ቃላት ፅፏል ። የበዛብህ እናትም በነዚያ ከማየት በስተቀር ምንም በማይለዩት አይኖቻቸው ካርዱ ላይ የተፃፈውን ነገር ዝም ብለው ይመለከታሉ ።

በዛብህ ከሃኪሙ ፊት ለፊት ፈንጠር ብሎ ከቆመው አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጦ አንዴ ዶክተሩን፤ አንዴ ሲስተር ትርሲትን ከዚያም እናቱን እሳት የሚተፉ በሚመስሉት አይኖቹ ይመለከትና እንደገና መርጮሁን፤ መዘባረቁን ይቀጥላል ።

ሲስተር ትርሲት ጎንበስ ብላ ጭኗ ላይ ካስደገፈችው ማስታወሻ ዴብተር ላይ ትፅፋለች ። ረጅሙ ፀጉሯ ወደፊቷ ከንበል ብሎ አይኖቿን ሲሸፍናት፤ ቀና ብላ በጣቶቿ ወደ ኋላ ትመልሰውና ነጩን መነፅሯን እፍንጫዋ ላይ በአመልካች ጣቷ ወደ ላይ ገፋ አድርጋ መፃፏን ትቀጥላለች ። ከህክምና ኮሌጅ ከመመረቋ በፊት አገልግሎት ለመስጠትና ልምድ ለማግኘት ከሆስፒታሉ ከመጣች ወር አልሆናትም ።

“መቼ ነው የጀመረው ለመሆኑ?” አለ ዶክተሩ፡ የሚፅፍበትን ብእር ካርዱ ላይ አስቀምጦ፤ ወንበሩ ላይ ከተደገፈ በኋላ የበዛብህን እናት እየተመለከታቸው ።

— “ኧ . . . ይኸው አሁንማ ሳምንቱ አለፈ . . . ” አሉ እንባ ባነቀው ድምፅ ።

“ታዲያ እስካሁን የት ነበር?”

“ጠበል . . . እንዲያው ይሻለው እንደሆን ብለን ጠበል ወስደነው ነበር . . . ”

“እሺ. . . ”

"ምን ያደርጋል ፤ እጣ ክፍሉ አልሆነም መሰለኝ እምቢ አለው ። እንዲያውም ብሶበት ቁጭ አለ ፤ ምንም አልፈየደለትም ። እጇ ላይ የነበረችውም ገንዘብ አለ ቀች ። ያለ ገንዘብ እንደሆነ ጠበሉ ቦታ አንድ ቀን እያሳድሩም ። ማደሪያው በኪራይ ነው ። ማስሪያው እግር ብረት እንኳን ሳይቀር በኪራይ ነው የሚገኝ ። ታዲያ ሰው ቃልቻ ቤት ውሰጂው ሲለኝ እኔ ዝም ብዬ እዚህ አመጣሁት ፤ ጥሩ ነው ሲሉኝ ጊዜ . . . እንዲያው ድሮም ቢሆን ቃልቻ አ ልወድም ።"

"እማማ . . . በቃ አልወድሽም ፡ ሂጂልኝ! ጫት ልቃም ብልሽ እምቢ አልሽ አይደል? እኔኮ እስላም ነኝ . . . ሼክ ሁሴን ውሰጁኝ . . . ድሬ ሼክ ሁሴን ! . . . ይኸው አይኖቹ መጡ ያዩኛል . . . መጡ ፡ ተጠጉ! መስ ኮቱን ዝጉት! አይኖቹ በመስኮት ሊገቡ ነው! "

በዛብህ ይስፈልፋል ። በዛብህ የሚያየው ነገር ሁሉ አይን ብቻ ሆኖ ነበር የሚታየው—ብዙ አይኖች ። ከፊቱ—ከኋላው—ከግራው—ከቀኙ—ከአየር ላይ እየተን ሳፈፉና ትየሮጡ ወደ ትሱ የሚመጡ ይመስለዋል ። ትናንሽ—ትላልቅ—ነጭ—ጥቁር — ቀይ . . . አይኖች ። ያፈጠጡ—ያላፈጠጡ—የሚታዘቡ— የሚቆጡ—የሚያ ፌዙ— የሚስቁ — የሚጠይቁ — የሚያሾፉ— የሚያሽሟ ጥጡ . . . አይኖች ።

"ምንድነው ስራው ?" ሃኪሙ እንደገና ጠየቀ ።

"ያዩኛል በቃ! ዝም ብለው ያዩኛል ። ይኸው አሁ ንም ያዩኛል ። መጡ! መጡ!" አለና በዛብህ ከተቀመጠ በት ተነስቶ ወደ ውጪ ሊሄድ ሲል ሲስተር ትርሲት ይዛ አስቀረችው ።

በዛብህ ቀና ብሎ ሲስተር ትርሲትን ተመለከታትና በፍርሃትና በሽብር ከተወጠረው ፊቱ ላይ ስስ ፈገግታ ቀስ በቀስ እየተስለከለከ ወጣና ከንፈሮቹ ተንቀጠቀጡ። "ሲ . . . ሲስተር እሽ, እቅመጣለሁ . . . አንቺ አታይኝም አይደል ? እነሱ ግን ያዩኛል . . . " ካለ በኋላ ፡ ሲያጠፋ እንደ ደረሱበት ልጅ አንገቱን ደፍቶ ሹክክ አለና ወደ ወንበሩ ተመለሰ ። ሃኪሙም ሆነ እናትየው ዝም ብለው ያዩታል ።

"ምን ነበር አሉ ስራው ? . . . " አለ ሃኪሙ እንደገና።

"ፊትማ አስተማሪ ነበር . . . " አሉ እናትየው ። "ባሌ ጎባ የሚባል ሃገር አስተማሪነት ተቀጥሮ ሄዶ ነበር ። ታዲያ ከዚያ ድንገት ሲመጣ ወትሮ ጠንቃቃ የነበረው ልጅ እንዲያው ሳይታሰብ ብልሽትሽት ብሎ አረፈው ። መጠጥ የሚባል ነገር ሲቀምስ ቀርቶ ስሙን እንኳን ሲሰማ የሚያንገሸግሸው ሰውዬ ዋናው ሰካራም ሆኖ ተመለሰ ። ትንባሆም ቢሆን የሰጠ አይመልስ ሰው ። ጫትም በቀን በቀን ይበላል ። እንደ መጣ እንኳን ሳላየው ተደብቆ ነበር የሚበላው ። ኋላማ በኮባ ጠቅልሎ እቤት ይዞ ከተፍ ማለት ጀመረ ። እኔማ እንዲያ ድንገት ፀባዩ ሲቀየርብኝ ጊዜ መድሃኒት አቀመሱብኝ ብዬ ያልረገጥኩት ቦታ የለም ።"

"ትንሽ ቆይቶም ከቤት መዋል ጀመረ ። ታዲያ ያ አጎቱ ይመካከርና ወስዶ ከሚሠራበት ከዚያ ከባንኩ ቤት ያስቀጥረዋል ። ደህና ሲሰራ ቆይቶ ፡ ሰውነቱም ተመልሶ ቀና ቀና ማለት ሲጀምር እንዲያው የነካውን ሳላውቀው እንደ ወትሮው እየተለዋወጠብኝ መጣ ። ድንገት ስራውን ተወና እቤት ተኝቶ መዋል ጀመረ ። ከዚያም ማንንም ሳያማክር አንድ ሰሞን ከቤት ወጥቶ

ውጪ ከረመ ። እኔም ይሻለዋል ብዬ የአቦን ጠበል እያ መጣሁ ላጠጣህ ብለው ጭራሹኑ እኔንም ጠሉኝ ቁጭ አለ ። እንዲያው ምን አድርጌው ይሆን እንዲህ የሚጠላኝ ጌታዬ? ይሁን ፡ በሽታው ነው ብዬ ተውኩት።"

"አንድ ቀን ይባስ ብሎ ሁለተኛ ጠበል የሄድሽ እን ደሆነ እናቴ አይደለሽም ብዬ እክድሻለሁ ፡ እስላም መሆኔን አታውቂም ? እምቢ ካልሽ የትም ብን ብዬ እጠፋለሁ አለኝ ። በጣም ደነገጥኩ ። ሌት ተቀን ፀሎት ባደርግም አልተሻለውም ። እንዲያው ሰው ቢገፋፋኝ ጊዜ ይሻለዋል ብዬ እዚህ አመጣሁት . . ." አሉና አይና ቸውን በነጠላቸው ጫፍ ጠራረጉት ።

"አዎን ፡ አሁንም ቢሆን እሄዳለሁ . . . እጠፋለሁ! ታዲያ እነሱ ለምንድነው የሚያዩኝ? ለምንድነው ጆሮዬ ስር የሚያንሾካሹኩብኝ ?" አለ በዛብህ ።

"ይኸው ሎሚ እንግዲህ ጌታዬ . . ." አሉ የበዛብህ እናት ፡ ፊታቸውን ወደ ሐኪሙ መልሰው ። "ይኸው እንዲህ ነው የሚያደርገው . . . እንዲያው በፈጠሮት ፤ ምን እየታየው ይሆን እንዲህ የሚሆነው ? ሰውማ የሚ ለው . . . ሴት ጋኔል ነች የተጠናወተችው . . . እውን ሴቷ ትሆን እንዲህ የምታደርገው ? ታዲያ ማርከሻው ምንድነው ይሉኛል ? እኔም እኮ በመሃሉ በስተርጅና ተንገላታሁ . . . "

ሃኪሙ የሚፅፍበትን ብእር እንደገና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና መነፅሩን አውልቆ ሲስተር ትርሲትን ተመለከታት ።

"ስሚ ትርሲት . . . ይኸም ቢሆን ባለፈው ጊዜ ከገጠመን የህመም አይነት ጋር ተመሳሳይ ነው ። እስኪ

ፍሩድ ስለ ቢዞፍሬኒያ የፃፈውን እንደገና ተመልከቺ ውና ከዚህ ሁኔታ ጋር አገናዝቢው . . . ሌላ ጊዜ እን ነጋገርበታለን . . . ለጊዜው በሽተኛው ይተኛ ። አሁን ጊዜ የለኝም ፤ ይኸውልሽ ይኸ ሁሉ ካርድ ይጠብቀኛል። መኝታ ቤት አድርሺውና ተመለሺ ። እግረ መንገድሽን ተረኛውን አስገቢልኝ” አለና የበዛብህን ካርድ አቀበላት።

ሲስተር ትርሲት ፡ ካርዱንና በዛብህ ስራ ስለሌለው በነፃ እንዲተኛ የተፈቀደበትን ወረቀት ፣ እንዲሁም በሽ ተኛውን ይዛ ወደ መኝታ ክፍል ሄደች ። እናትየዋም ተከትለዋል ።

“አይዞዎት እማማ ፣ ይሻለዋል ። እንዲተኛ ታዟል። አሁን ወደ ቤትዎ ይሂዱና ነገ መጥተው ሊጠይቁት ይችላሉ” አለች ሲስተር ትርሲት ፣ ወደ በዛብህ እናት ዞር ብላ ። አሮጊቷም ከቆሙበት ሆነው ሲስተሯና ልጃ ቸው እየራቁ ሲሄዱ ተመለከቱ ። ከዚያም አይኖቻቸ ውን ጨመቁና እያማተቡ ከግቢው ወጥተው ሄዱ ።

ቀለሙ በየቦታው ከተላላጠው ግራጫ የህሙማን መኝታ አዳራሽ ውስጥ ፣ ከሃያ የማያንሱ የሽቦ አልጋ ዎች ግራና ቀኝ ተደርድረዋል ። ህሙማኑ በሙሉ ራሳ ቸውን ተላጭተዋል ። ካለቅጥ የከሱ—ካለ ቅጥ የወ ፈሩ —የገረጡ — ቆዳቸው አሽቦ የሚመስል — የሚለ ፊልፉ —እንደ በድን ዝም ያሉ—የለበሱ—እርቃናቸውን የሆኑ—ብቻቸውን የሚነጋገሩ — የሚዘፍኑ . . . ህመምተ ኞች ። ከተከፈተው ሽንት ቤት የሚወጣው ሽታ ይተነ ፍጋል ። ያልታጠበ ገላ ጠረን ፣ የርካሽ ሲጋራ ጢስ ፣ የምግብ ትርፍራፊ ፣ የመድኃኒት ሽታ . . . ያንን የመኝታ አዳራሽ አውዶታል ።

በሶስተኛው ቀን ሲስተር ትርሲት በሽተኞች ክፍል ስትገባ በዛብህ ከረጅም የህመም እንቅልፉ ነቅቶ አልጋው ላይ ተቀምጦ ያጤስ ነበር ። በዘወትር ልብሱ ፋንታ ጥቁርና ነጭ ሸንተረር ያለበትን ፒጃማ ለብሷል ። ሲስተር ትርሲት ለህመምተኞቹ ሰላምታ እየሰጠች ከመግቢያው ጀምሮ የተደረደሩትን አልጋዎች አለፈችና በዛብህ አጠገብ ስትደርስ ቆመች ። በዛብህ ቀና ብሎ ተመለከታት ። እንደ ማፈርም ፡ እንደ መፍራትም ፡ እንደ መደሰትም አደረገውና ሰስ ፈገግታ ከንፈሮቹ ላይ ልምጣ ልቅር እያለ ፡ “ሲ. . . . ሲስተር” አለ ፡ ከአልጋው ላይ እየተነሳ ።

“ተቀመጥ . . . ተቀመጥ . . . ታዲያስ በሳ ሆንክ ፡ ተሻለህ ? እንዴት ነው አሁንስ . . . የሚታይህ ነገር ? ያስ በጆሮዬ ይንሾካሾካል የምትለው ፡ አሁን ምን ይሰማሃል ?” ሲስተር ትርሲት ጠየቀችው— ሳቅ እያለች ።

“እ . . . አሁን ይሻለኛል . . . ሁል ጊዜ አያዩኝም። አንዳንድ ጊዜ ግን በዚያ በኩል እየመጡ ያዩኛል” አለ በዛብህ ፡ ገርበብ ባለችው ትንሽ የብረት መስኮት በኩል ከግቢው ራቅ ብሎ ግማሽ ጎኑን የሚያሳየውን የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያንን ህንፃ በአመልካች ጣቱ እየጠቆመ ።

“መድሃኒቱን እየወሰድክ ነው ? . . . እንቅልፍስ እንዴት ነው ፡ ይወስድሃል?”

“አዎን እየወሰድኩ ነው . . . ግን አንዳንዴ ያዩኛል ። ብዙ አይኖች ናቸው ፡ እንቅልፍ ይወስደኛል ። ቢወስደኝም ግን እነሱ ያዩኛል. . . ሌሊትም ያዩኛል. . . በእንቅልፍ ልቤ ይታዩኛል. . . ”

"አይዞህ ይሻልሃል . . . መድሃኒቱን በደንብ ውሰድ አይዞህ . . ."

"ማን ሲስተር . . . እኔኮ ተሽሎኛል ፤ ከዚህ መውጣት እፈልጋለሁ . . . ወጥቼ ያንን ማስረሻን እፈልገዋለሁ ። እነም ጥፋቴን ተናግሬ ሰላም ማግኘት እፈልጋለሁ ። ከዚያ በኋላ ማንም አያየኝም በቃ! እና . . ." አለ በዛብህ ፡ በቀሉት አይኖቹ አጠገቡ የቆመችውን ሲስተር ትኩር ብሎ እያየ ። ከሲጋራው ጫፍ ላይ አመዱ ጉምድ ብሎ ብርድ ልብሱ ላይ ወደቀ ። ሲስተር ትርሲት በእጅዋ አራገፈችለትና አሊጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች ።

"ማነው እሱ ማስረሻ? እስኪ አጫውተኝ" አለች ሲስተር ፡ በዛብህ ሊነግራት የፈለገው በህሊናው ውስጥ የተደበቀ ምስጢር እንዳለ እየገመተች ።

"ማስረሻ!" አለ በዛብህ አይኖቹን አፍጥጦ ፡ "ማስረሻማ ያ ሌባ ነው!" ከዚያም ከሲጋራው ሳብ ሳብ አድርጎ በአፍንጫው ቀዳዳዎች ቡልቅ አደረገና ፍዝዝ ብሎ መሬት መሬቱን ይመለከት ጀመር ።

"ምን ሰረቀ ማስረሻ ?" አለች ሲስተር ፡ በዛብህን ለማናገር ዘዴ እየፈለገች ። ከዚያም ስለ ሰው አእምሮ የተማረችውን አስታወሰች ።

"ማስረሻ ምን ሰረቀ?" አለ በዛብህ እንደ መባነን ብሎ ። "ከዚህ በላይ ምን እንዲያደርግ ትፈልጊያለሽ ? ሲስተር . . . ታሪኩ ብዙ ነው . . . ቆይ እነግርሻለሁ ። አሁን የሚያዩኝ አይኖች የሉም አይደለም ? ልንገርሽ አይደል ? ምን መሰለሽ . . ." አለ በዛብህ አይኖቹን በጭንቀት አፍጥጦ ።

"እይዞህ ተናገር . . . ማንም እያይህም ። ከእኔ በስ ተቀር ማንም አይሰማህም" አለች ሲስተር ትርሲት፣ ኢያደፋፈረችው ።

"እሺ . . . አንቺ ብቻ አይደለሽ የምትሰሚው ? ለማንም አትናገሪም አይደል ? አዎን ፣ አንቺን እምንሻ ለሁ . . . እነግርሻለሁ . . ." አለ በዛብህ ፣ ሲፈራ ሲቸር።

"አዎን ፣ እኔ ብቻ ነኝ . . . ለማንም አልነግርም" አለች ሲስተር ትርሲት ።

"እሺ ምን መሰለሽ . . . ይኸ ማስረሻ ያልኩሽ ጓደኛዬ ነበር ። እና ፣ የዚያ የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ ሹም ነበር ። አይደለም ? እና ፣ አንድ ቀን እቤት መጣና ልጋ ብዝህ ብሎኝ አብረን ወጣን ። ታዲያ ስንጠጣ አመሸ ንና ሞቅ ሲለኝ አይቶ 'ስማ በዛብህ' አለኝ ፣ ያው ማስ ረሻ ያልኩሽ ሰው . . . በደንብ ስሚኝ ሲስተር . . . ማንም አያየኝም አይደል ? . . . አንቺ ብቻ አይደለሽ ?"

"ምንም አይሰማም ፤ ቀጥል" አለች ሲስተር ትርሲት።

"እና ፣ ምንድነው አልኩት ። 'አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ ። ለአንተም ለእኔም ጠቃሚ ነው' አለኝ ። እሺ ንገረኝ ልስማው አልኩት ። 'ይኸውልህ እዚያ አንተ ከምትሰራበት ቅርንጫፍ ባንክ በከፈት ነው ሂሳብ መስረት ሰሞኑን ሰላሳ ሺህ ብር አስገባ ለሁ. . .በፊት ሃያ ሺህ ብር አስገብቻለሁ ። በጠቅላላው ሃምሳ ሺህ ብር ይሆናል ማለት ነው' አለኝ ። አዎን ፣ አልኩት ። 'ታዲያ ዝም ብሎ ባንክ ውስጥ ከሚቀመጥ ለምን አውጥተን እንጠቀምበትም? ዘዴውን አንተ ታው ቀዋለህ ። ሁሉ ሰው የሚያደርገው ነው' አለኝ ። 'አንተ ገንዘቡ ባንክ ውስጥ እንዳለ የሚያስረዳ ሰነድ ሰርተህ

ትስጠኛለህ ። እኔ ገንዘቡን አወጣለሁ ። አለ አይደለም ፤ ዘዴውን ሳታውቀው አትቀርም ። ለምን ለነጋዴ አበድ ረን በትርፉ አንጠቀምም? ድንገት ቢታወቅም ገን ዘቡን አምጥተን እንተካለን ። ሰው ሁሉ በብዙ ዘዴ ሲጠ ቀም እኛ በሞኝነታችን ከሰው በታች ሆነን ቀረን ። ይኸ ደግሞ ወንጀል አይደለም ። ባንክ ከሚዘፈዘፍ አውጥተን ብንጠቀምበት ምን ክፋት አለው' አለኝ ። ትሰ ማኛለሽ አይደል ሲስተር? ማንም አያየኝም አይደል?''

''አይዞህ ቀጥል ፤ ማንም አይሰማም'' አለች ሲስ ተር ትርሲት ፤ የታሪኩን መጨረሻ ለማወቅና በዚያውም ለበሽታው መንስኤ ፍንጭ የሚሆን ነገር ለማግኘት እየጓጓች ።

''እና ፤ እኔም ሞቅ ብሎኝ ስለ ነበርና ደግሞም ያ በእስተማሪነት ያሳለፍኩት የችግር ጊዜ ሁሉ ታየኝና 'እኛ በሞኝነታችን ከሰው በታች ሆነን ቀረን' ያለኝ ቃል ልቤ ውስጥ ገባ ። ገንዘብ የማውጪያውን ዘዴ በእርግጥ አውቀዋለሁ ። እና፤ ከማስረሻ ጋር ተስማማሁ ። እነግርሻለሁ ከፈለግሽ. . . እና ፤ ገንዘቡም እንዳልኩሽ ወጣ'' አለ በዛብህ ፤ ዞር ዞር ብሎ አካባቢውን በአይኖቹ እየቃኘ ።

''ማንም አያይህም አይዞህ ቀጥል. . .'' አለች ሲስተር።

''እና ሲስተር ፤ አንቺን አምንሻለሁ. . .ጥሩ ሰው ነሽ. . .ለአንቺ ነው የምነግርሽ. . .እና ይኸውልሽ ሲስ ተር. . .ማስረሻ ገንዘቡን አወጣው. . .ማስረሻ ሌባው ፤ ማስረሻ ከሃዲው. . .እኔን ብቻ መሰለኝ የከዳኝ. . .ሚስቴ ንና ልጆቼን ሳይቀር ጥሎ ነው የጠፋው. . . አይደለም እንዴ ሲስተር?''

"ከዚያስ?" አለች ሲስተር ። "ገንዘቡን ካወጣ በኋላ እንዴት ሆነ?"

"ከዚያማ. . .ያንኑ እለት ከስራ ስወጣ በተቃጠር ነው መሰረት ማስረሻ ቤት ሄድኩ. . .ግን ምን እንደ ተፈጠረ ታውቂያለሽ ሲስተር?"

"እሺ ።"

"ማስረሻ ቤቱ የለም!"

"እሺ ።"

"ከዚያ በኋላማ ከቶማው አንድ አልቀረኝም ። ብፈልግ ባስፈልግ ከየት ላግኘው? ከስራ ቀርቼ ስፈልገው ሰነበትኩ ። አላገኘሁትም ። በሰው አስፈለኩት ። አልተገኘም ። በመጨረሻም የሆዴን በሆዴ ይዤ ተስፋ ቆርጬ ዝም አልኩ ። ነገሩ ግን እረፍት ነሳኝ ። ከአንድ ወር በኋላ ማስረሻ ከሃገር መውጣቱን ሰማሁ ። ገንዘቡን ይዞ ። ከዚያማ በኋላ ነርቭ ሆንኩ ። ወዲያውም ኦዲት ሲደረግ የገንዘቡ መጭበርበር ታወቀ ። ሰነዱ ላይ የፈረመበት ሰውዬ ተይዞ ወህኒ ወርዷል ። ነገሩን ያቀነባበርኩት እኔ ነበርኩ ። የሚለወጡትን ሰነዶች ለውጬ ፣ መጥፋት ያለበትን አጥፍቼ ፣ የሚደለዘውን ደልዤ. . .ምን ልበልሽ ፣ ዘዴውን አውቀዋለሁ. . . ታዲያ ውሎ አድሮ ያደረኩት ነገር ሰላም ይነሳኝ ጀመር። እንቅልፍ አሳጣኝ ። አንዳንዴ እራሴን ማጥፋት ይከጅለኝ ጀመር ። ግን በተፈጥሮዬ ፈሪ ስለሆንኩ አልቻልኩም. . .እና ፣ ከቤት መውጣት ያስፈራኝ ጀመር ። በኋላም እነዚያ አይኖች ያዩኝ ጀመር. . .ጆሮዬ ስር ደግሞ ይንሾካሾኩብኛል ። ማን እንደሚናገር ግን አላውቅም. . . ዝም ብሎ ድምፅ ብቻ ነው የሚሰማኝ. . ."

ሁኔታውን በማወቋ ሲስተር ትርሲት ደስ ሳይላት አልቀረም ነበር ። እርሷም ብትሆን ከአንድም ሁለት ጊዜ በሳይኮ አናሊሲስ ዘዴ ተጠቅማ ደህና ውጤት አግኝታበታለች ። በህቡእ ህሊና ውስጥ የተቀበረ ፀፀት . . . ማጭት ፣ ከማጭቱ የሚፈጠር የስብእና መመስቃቀልና የአእምሮ መቃወስ ።

"በጣም ጥሩ ነው እንግዲህ . . ." አለች ሲስተር ፣ የእጅ ሰአቷን መልከት አድርጋ ፣ "ነገ ደግሞ መጥቼ አይሃለሁ ። የተረፈውን ሁሉ ትነግረኛለህ አይደል?"

"ግን እኮ ሲስተር . . . መውጣት እፈልጋለሁ ፣ ተሽሎኛል ። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚያዩኝ ። እዚህ መኖር አልፈልግም ። እነዚህን ያበዱትን ሰዎች ሳይ እንደነሱ ሆኜ የምቀር ይመስለኛል ። በጣም እፈራለሁ ። ደህና ነኝ አይደል አሁን ? ነግሬሻለሁ አይደል ሁሉን ነገር? ነገ ደግሞ የቀረውን እነግርሻለሁ ፣ እሺ?"

ሲስተር ትርሲት ልትሄድ ተነሳች ።

"እሺ ፣ የቀረውን ነገ ትነግረኛለህ ።"

"አትሂጂ እባክሽ ሲስተር . . . ትንሽ ቆዪ ። አንቺን ብቻ ነው የማምነው ። አንቺ ስትኖሪ ደስ ይለኛል ። ስትሄጂ ግን በቃ ፣ እፈራለሁ ። አይኖቹ ይመጡብኛል ። የነገርኩሽን ታዲያ ለማንም እንዳትነግሪ እ? እና ፣ እንዳልኩሽ ማስረሻ ገንዘቡን ይዞ ቢጠፋም. . .ሁሉን ነገር ተናግሬ ወደ ስራዬ መመለስ እፈልጋለሁ. . .ስራ አስኪያጁን ያሳሳትኩት እኔ ነኝ ። በክንቱ ነው የታሰረው ። ይኸንንም መናገር እፈልጋለሁ ። ሌላም የምነግርሽ ነገር አለ ። ሁሉንም ልነግርሽ እፈልጋለሁ ። ያኔ ባሌ ጎባ አስተማሪ የነበርኩ ጊዜ. . .ትሰሚያለሽ ሲስተር?

የልማት ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ የነበርኩ ጊዜ ፣ ያንን ኀያለ የተባለውን ገንዘብ ያጠፋሁት እኮ እኔ ነኝ ። ጠጣሁ በት ። ስመዝ ስመዝ ጨረስኩት. . .ደግሞ ይኸ ብቻ አይደለም. . .ቀበሌ ስሰራም ቢሆን የሱቁን ሸቀጥ ባድ ብቅ ለነጋዴ እያሸጥኩ ትርፉን በስምምነት እንካፈለው ነበር ። ያን ጊዜ በየሳምንቱ መቶ ብር እቁብ የምጥለውም ገንዘብ ከየት ያመጣሁት መሰለሽ? ከዚያው ከትርፉ ነው! ይኸ ብቻ አይደለም ፡ ሲስተር . . .በየመጠጥ ቤቱ ሳልከፍል ነበር ብዙ ጊዜ የምጠጣው. . . ሞቅ ሲለኝ ፥ 'በቃ አልከፍልም ምን ትሆናላችሁ!' እላቸዋለሁ ። አይ ናገሩኝም ፡ ይፈሩኛል. . .ስንትና ስንት ውሽሞች ነበ ሩኝ. . .ምን ይሄ ብቻ ሲስተር፤ ሌላም ብዙ ነገር አለ. . . የዚያች የቡና ቤቷን ባለቤት ልጅ አስገድጄ ህጓን የወሰድኩት እኔ እኮ ነኝ. . .እናቷም ብትሆን ወዳጄ ነበረች. . .ምን ይኸ ብቻ ሲስተር ሌላም ብዙ ነገር አለ. . ."

በዛብህ ማቆም አልቻለም ። ውጪ ከወጣች በኋላ እንኳን ከሩቅ ድምፅ ይሰማት ነበር ። ተከትሏት ሊወጣ ሲል የክፍሉ ጠባቂ ነበር አስፈራርቶ ያስቀረው ።

በሚቀጥለውም ቀን አልቀረችም ነበር ፡ ሲስተር ትርሲት ። የገዛችለትን ብርቱካን ሰጠችውና አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች ።

"ዛሬስ ተሽሎሃል. . ." አለች ሲስተር ፡ መልኩን እያጠናች ። እውነትም ሰሞኑን ቀልተው የነበሩት አይ ኖቹ የበፊቱን ቀለማቸውን መያዝ ጀምረው ነበር ። ያበጠውም ፊቱ ጎድሎ ነበር ።

"እኔኮ እብድ አይደለሁም ሲስተር. . .ነኝ እንዴ? እኔ ለምን ከዚህ አልወጣሁም? ይልቁኑ እዚህ መቆየቱ

ነው የሚያሳምመኝ ። ጥፋቴን ተናግሬ የለም፣ ደግሞ እኔ ብቻ እኮ አይደለሁም ፡ እንደዚያ አይነት ነገር የሰራ ሁት. . .ስንትና ስንት ሰዎች አሉ ከዚህ የባሰ አጥፍ ተው ዝም ስላሉ ብቻ ሳይታወቁ የሚኖሩ? እነሱ ጤነ ኞች ናቸው ማለት ነው? እነሱ ናቸው በሽተኞች. . . ዝም ብለው የታመሙ. . .ያልታወቀባቸው በሽተኞች ብዙ አሉ ። እሺ እነዚያ ጉቦ የሚበሉት ፡ የሰው ሚስት የሚደፍሩ ፡ ሰው የሚያንገላቱት ፡ እንደ እስስት በቀን ውስጥ አስር ጊዜ ቀለማቸውን የሚቀያይሩት ፡ ለገን ዘብ ሙቶች ፡ ሳያውቁ አዋቂ መስለው የሚታዩት ፡ ሰውን ለማጥፋት በልባቸው ሴት ተቀን የሚዶልቱት ፡ የበታቾቻቸውን የሚያርበደብዱት ፡ ለበላዮቻቸው ደግሞ ንፋስ እንደ መታው የዛፍ ቅጠል የሚንቀጠቀጡት. . . ስንቶቹ ሲስተር ፡ ስንት በሽተኞች አሉ መሰለሽ! እነ ሱም ነገ ተነገ ወዲያ እዚህ ይመጣሉ ፡ እንደ እኔው ተይዘው ይመጣሉ! መድሃኒት ግን አይበቃችሁም ፡ ሲስተር ። ብዙ ናቸው ። አልጋም አይበቃም ። ለእነሱ የሚሆን መድሃኒትም ገና የተሰራ አይመስለኝም. . . አየሽ በሽታውን ስለማይናገሩ ጤነኛ ስለሚመስሉ. . . ቶሎ አይፈወሱም ። በሽታው ደግሞ ቆይቶባቸዋል. . . ብዙ አመታት ፤ ሃያ — ሰላሳ — አርባ — ሃምሳ — መቶ— ከመቶ አመታት በላይ ቆይቶባቸዋል. . .እና ሲስተር ፡ እኔ ስለ ተሻለኝ መውጣት አለብኝ. . .”

“አዎን ተሽሎሃል” አለች ሲስተር ትርሲት በመ ጨረሻ ፡ ብርቱካኑን ልጣ እየሰጠችው ። “ትናንት ማታ ከሃኪሙ ጋር ተነጋግረናል. . .ዛሬ ምንድነው ቅዳሜ አይደል? አዎን ፡ ነገ እሁድ ፡ ከነገ ወዲያ ሰኞ. . .ከዶክ ተሩ ጋር ተነጋግረን ሰኞ ትወጣለህ ። የታዘዘልህን መድሃኒት ትወስዳለህ ። ከዚያም በተመላላሽ ትታከማ ለህ?”

በዛብህ ብርቱካኑን ሲያኝክ ያዳምጣታል ። ልጣጩን ደግሞ በጣቶቹ እየበጣጠሰ መሬት ላይ ይጠረውረዋል ። ሲስተር ትርሲት ትንሽ ቆይታ ተሰናብታው ስትወጣም ምንም አልተናገረም ነበር ። ብቻ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ እየተከዘ አፉ ውስጥ ያደረገውን ብርቱካን ያላምጣል ። ግቢው ውስጥ የበሽተኞች ጩኸት አልፎ አልፎ ይሰማል ። ከዚያም ሰአቱ እየገፋ ቀኑ እየመሸ ሲሄድ የሆስፒታሉ ግቢ እንደገና በሚያስፈራ ፀጥታ መዋጥ ጀመረ ።

በመስኮት በኩል የሚታየው በእብኑ በረድ የተሰራው የቤተ ክርስቲያኑ ህንፃ የምትጠልቀውን ፀሃይ ፍንጣቂ ተቀብሎ ወደ ሆስፒታል ግቢ ያንፀባርቃል ። የበሽተኞቹ መኝታ አዳራሽ ግራጫ ግድግዳ ግን በቤቱ ውስጥ የሰፈነውን ሰቆቃ የሚያስተጋባ ይመስል ፍዝዝ ፣ ትክዝ እንዳለ ነው ።

ያን እለት እሁድም ቢሆን ተረኛ ነበረች ፡ ሲስተር ትርሲት ። ነጩን ካፖርቷን ከለበሰች በኋላ የመጀመሪያ ተግባሯ ሶስት ቁጥር መኝታ አዳራሽ ሄዳ በዛብህን ማየት ነበር ። የህመሙ መንስኤ ሲሆን የሚችለውን ፍንጭ ማግኘቷ አስደስቷታል ። ድሮም ቢሆን ችግሩ በሽተኞች የሚሰማቸውን በግልፅ አለመናገራቸው ነበር ።

ሰሞኑን ደግሞ ብዙ በሽተኞች አልጋ አጥተው ሲመለሱ ተመልክታ አዝናለች። ሻል ያላቸው በተመላላሽነት ሊታከሙ ይችላሉ ። በተለይ የበዛብህ ሁኔታ ካሁን ወዲያ አስቸጋሪ እንደማይሆን ሳትገምት አልቀረችም ። አስፈላጊው ምክርና የመድሃኒት እርዳታ ነበር የሚያስፈልገው ።

በዛብህ ቀን ቀን ከሌሎች ሻል ካላቸው በሽተኞች ጋር ግቢው ውስጥ ሲዘዋወርና ሲጫወት ይው-

ላል ። ማታ ማታ ደግሞ እራቱን በልቶ ሲያበቃ ቴሌ ቪዥን ሲመለከት ያመሽና መድሃኒቱን ከወሰደ በኋላ በሰላም ወደ መኝታው ይሄዳል ። እውነትም በጣም ፈጣን መሻሻል ነበር ያደረገው. . .

ያን እለትም ቢሆን ዶክተሩ የሚላትን ታሰላስል ነበር ። "አዎን ፡ በህቡእ ህሊና ውስጥ የታመቀ የመጥፎ ድርጊት ትዝታ በአእምሮ ውስጥ ግጭት ይፈጥርና ውሎ አድሮ ፀፀትን ያስከትላል. . . ቀስ በቀስም ህሊ ናን ገዝግዞ ዘልቆ ይወጣል. . .ስብእናንም ሊያናጋ ይች ላል ።"

እሁድ እሁድ ሁልጊዜ ሆስፒታሉ በጠያቂዎች ይጨናነቃል ። የበዛብህ እናትም ቢሆኑ በሶስት ቀን አንድ ቀን ያቺኑ ያገኟትን ምግብ ቋጥረው ልጃቸውን ሳይጠይቁ አይቀሩም ።

ሲስተር ትርሲት የበዛብህን እናት ያገኘቻቸው ከሴቶች ግቢ ወጥታ ወደ ቢሮዋ ልትሄድ ስትል ነበር ። የበዛብህ እናት ደግሞ የእቃ መያዣውን ላስቲክ እን ዳንጠለጠሉ ወደ ወንዶቹ ግቢ ሊገቡ ሲሉ በሩ ላይ ነው የተገናኙት ።

"እንዴት ነው ያ ልጅ. . . እንዲያው መቼ ይወጣ ይሆን?" ይሹ ነበር ጥያቄያቸው ።

"እንደምን ዋሉ እማማ? ደህና ነው ፡ ተሽሎታል. . . ነገ ከዶክተሩ ጋር ተነጋግረን ሰሞኑን ሳይወጣ አይቀ ርም. . .መጣሁ. . ." አለችና ሲስተር ትርሲት እየተቻ ኮለች ወደ ቢሮዋ መሄድ ጀመረች ።

ብዙም አልተራመደችም ። አንድ የተረበሸ ድምፅ ከወደታች በኩል ሲጠራት ሰማችና ፊቷን አዞረች ።

"ሲስተር ትርሲት!. . .ሲስተር ትርሲት!. . .ቶሎ ነይ እባክሽ. . .እስቸኳይ ነው!"

ሲስተር ገነት ነበረች ከወንዶች መኝታ አዳራሽ ወጥታ እየሮጠች የምትጣራው ።

"ትርሲት!. . .ትርሲት!. . .ያ. . .ያንቺ በሽተኛ!. . . በፍጥነት ሂጂ!. . ." አለችና ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ተመልሳ ቁልቁል ወደ አዳራሹ ሮጠች ። ሲስተር ትርሲትም ደንግጣ ተከተለቻት ።

ከሶስት ቁጥር አዳራሽ መግቢያ ላይ በዛብህ በሰዎች ታጅቦ ይጮሃል ።

"በቃ!" ይላል በዛብህ እየጮኸ ። "ካሁን ወዲያ ማንም አያየኝም!. . .በቃ ልቀቁኝ ድኛለሁ! ወደ ቤቴ ልሂድበት! ካሁን ወዲያ አያዩኝም! ካላየኋቸው አያዩ ኝም!"

የመኝታ አዳራሹ ሃላፊና ጥቂት ሰራተኞች ክንዶቹን ይዘው ወደ ውስጥ ይጎትቱታል ። ሲስተር ትር ሲት እየሮጠች በሩ ላይ ደረሰችና በዛብህን ቀና ብላ አየችው ። የቀኝ አይኑ ብረቱ ፊቶ ከጉድጓዱ ውስጥ ፈሳሽ ነገር ከደም ጋር ተቀላቅሎ ጉንጩ ላይ ይወር ዳል ። በዛብህ ባልተወጋው አይኑ ሲስተር ትርሲትን ትኩር ብሎ አየና ፣ "በቃ ካሁን ወዲያ አያዩኝም! ድኛ ለሁ አይደል? ነገ ትወጣለህ ብለሺኛል አይደል ሲስ ተር?" አለ ። ከዚያም በእጁ የያዘውን ሹካ መሬት ላይ ፣ ሲስተር ትርሲት እግር ስር ወረወረውና በሚያስፈራ ሁኔታ ከት ብሎ ሳቀ ።

"ከየት አገኘው ይኸንን!" ሲስተር ትርሲት ደን ግጣ ጮኸች ፣ እግሯ ስር ከወደቀው ሹካ ላይ አይኖቿን ተክላ ።

የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ግራ በተጋባ ሁኔታ አይኖቻቸው ተመለከቷት ።

"ከምግብ ቤት ይሆናል. . ." አለ ፡ ከተሰበሰቡት ሰዎች አንደኛው ።

"እሺ. . .ለጊዜው አስቸኳይ እርዳታ ይደረግለትና. . ቁስሉ ከታሸገ በኋላ የእንቅልፍ መርፌ ይሰጠውና ይተኛ. . .ተመልሼ እመጣለሁ!. . ." አለችና ሲስተር ትርሲት ድንጋጤው ሳይለቃት ተመልሳ ከግቢው ወጥታ ሄደች ።

"እራሱን መቅጣቱ ነው ማለት ነው?. . .በህቡእ ህሊናው ውስጥ የተቀበረውን ቁጣና ፀፀት ማስወጫ ሲያጣ ወደ እራሱ ዞረ ማለት ነው? ግራ የሚያጋባ ነገር ነው. . .ግራ የማያጋባ ሁኔታ. . .እስኪ ነገ ዶክተ ሩን እጠይቀዋለሁ. . ." አለችና ሲስተር ትርሲት ክን ዶቿን ደረቷ ላይ አጣምራ መሬት መሬቱን እየተመለ ከተች የግቢውን በር አለፈችና ወደ ቢሮዋ ሄደች ።

የብረቱን በር ካለፈች በኋላ የበዛብህ ጩኸት እንደ ተቆጣ የባህር ሞገድ በአየሩ ላይ እየተንሳፈፈ መጥቶ ጆሮዋ ውስጥ ይላተማል ።

"በሽተኛ አይደለሁም! ልቀቁኝ ልውጣ!. . .ከዚህ ግቢ ውጪ ብዙ በሽተኞች አሉ. . .እነሱ ይምጡና ይተኙ!"

ሲስተር ትርሲት ቆም አለችና አዳመጠች ።

"መጡ! መጡ! አይኖቹ መጡ! ያዩኛል! ብዙ አይኖች ያዩኛል! "

"አገረሸበት ማለት ነው?" አለችና ሲስተር ትር ሲት ራሷን እየነቀነቀች ወደ ቢሮዋ አመራች ።

## የሱራፌል እጣ

በዚያን ምሽት ሁለት ጊዜ እንደገና ተጠይቆ ለሶስተኛ ጊዜ ነበር ያንኑ ዘፈን የሚጫወተው ። አንድ እጮኛው በቅርብ ስለ ሞተችበት ፍቅረኛ ነበር የሚዘፍነው ። 'የመቃብር እጮኛዬ' ይላታል ። እሱም በቅርብ ቀን እንደሚከተላትና እስከዚያው ድረስ በትእግስት እንድትጠብቀው ይማፀናታል. . .

ሱራፌል የድምፅ ማጉያውን በሁለት እጆቹ ጨብጦ ፣ አንገቱን ወደ ኋላ ሰበር ፣ አይኖቹን ገርበብ አድርጎ በተመስጦ ሲጫወት ፣ እጮኛው የሞተችበት እሱው ራሱ እንጂ ፣ ሌላ ሰው ተመስሎ የሚዘፍን አይመስልም ነበር ።

ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ከተከፈተ ገና ወራት ለልተቆጠሩም ። ከምሽቱ አራት ሰአት ገደማ ይሆናል ። አዳራሹ ውስጥ የዳንስ ምሽቱ ቀልጧል ። ትሩፋት ብቻዋን ነበር የገባችው ። ከመድረኩ ፊት ለፊት በነጭ መጋረጃ ኪተሸፈነው ከትልቅ ባለመስታዉት መስኮት አጠገብ ተቀምጣለች ። ሱራፌልን ብቻ ነበር የምትለመከተው። እሱኑ ብላ ነበር የገባችው — ሲዘፍን ለማየት ። ሌላ የምትፈልገው ሰው እንኳን በውንዋ ፣ በህልምዋም አል ነበረም ።

አንድ ጊዜ አገጨን መዳፏ ላይ አስደግፋ ፣ ትከሻዋን አቋርጦ ጠቶቿ ላይ ያረፈውን የፀጉሯን ጫፍ በጣቶቿ እየቋጨች ትተክዛለች ። በሌላ ጊዜ ደግሞ አንገ

ቷን ወደ ጎን ሰበር ታደርግና እንደ ከር የቀጠነችውን የእንገት ሃብል እመልካች ጣቷ ላይ እየጠመጠመች ትፈታና በጥርሶቿ እየነካከሰች ትጫወትበታለች ። ትንሽ ትቆይና ደግሞ የፀጉሯን ነዶ ወደ ኋላዋ ወርወር፡ ረጃጅም ጣቶቿን ሰበር ሰበር አድርጋ ተራ በተራ ታንቋቋቸዋለች ።

አልፎ አልፎ ደግሞ ፡ ወንበሯ ላይ እንደ ተቀመ ጠች የሱራፌልን እንቅስቃሴ እየተከተለች ትቁነጠነጥ ነበር — ሳይታወቃት ። ወደ ዘፈኑ መጨረሻ ላይ የአዝ ማቹን ስንኝ ደጋገመው ።

የመቃብር ኢሎሜኛዬ ፡ ጠብቂኝ እመጣለሁ ፤

የቀረሁ እንዳይመስልሽ ፡ አደራ ብያለሁ ።

ትሩፋት ትክ ብላ ታየዋለች ። ተዋደው ሳይጋቡ ድንገት በሞት የተነጠቀችው ልጅ በአይን ህሊናዋ ታየቻት ። ከዚያም ረጃጅም ሽፋሎቿ ጫፍ ላይ እንደ ጤዛ ተንጠልጥለው የነበሩት የእንባ እንክብሎች ጉን ጮቿ ላይ ዱብ ዱብ አሉ ።

ሱራፌል ዘፍኖ ሲጨርስ አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ ። ከዚያም እረፍት ሆነና ሙዚቀኞቹ ወጡ ።

የሚያያት ሰው ይኑር አይኑር ልብ አላለችም — አላስቻላትም ። ሰው ምን ይለኛል ብላ አላሰበችም ። ተከትላው ወጣች ።

"ይ. . .ይቅርታ. . .አንድ ጊዜ" አለች ትሩፋት ፤ ሱራፌል አጠገብ እንደ ደረሰች ።

"ሰላም. . ." አለ ሱራፌል ፤ የቀይ ዳማ ፊቱን ድንገት አዙሮ ሳቅ እያለ ፡ ጥርሰ ፍንጭት ነው ። ያሳደ

ገው ዞማ ፀጉሩ ወደ ኋላው ተኝቷል ። ፊቱ በፈገግታ ሲበራ ላየው የቅድሙን ዘፈን የተጫወተው እሱ አይ መስልም ነበር ። ረጅምና ለግላጋ ቁመቱን ከወገቡ ሰበር አድርጎ ሰላምታ ሰጠ። አጅን ዘረጋና ጨበጣት ።

"እ. . .አንድ ጊዜ ላነጋግርህ ነበር. . ." አለች ትሩፋት ፣ እንደ ጨበጠችው ቀና ብላ አይን አይኑን በአድናቆት እየተመለከተች ።

"እሺ. . .ደስ ይለኛል" አለ ሱራፌል ፣ አንገቱን ሰበር አድርጎ ።

"እ. . .ምን መሰለህ. . .እ. . .በጣም በጣም ጥሩ ትጫወታለህ. . . እ. .በተለይ ቅድም ሶስት ጊዜ የተደ ገመውን ዘፈን. . .በጣም እወደዋለሁ ። 'የመቃብር አበ ባዬ' ነው አይደል? እ. . .እና ፣ ለሙዚቃ ከፍተኛ ስሜት አለኝ. . .እና ፣ ሙዚቀኛ ለመሆን ምን ልበልህ. . . በጣም እፈልጋለሁ. . .እና ፣ ምን ትመክረኛለህ? ማለቴ እንዴት ሙዚቀኛ መሆን ይቻላል? ማለቴ ጊዜ ቢኖር ህና ከልምድህ ብታካፍለኝ. . .እና ፣ አድራሻህን ባው ቀውና. . .ወይም ቆይ ፣ የእኔን አድራሻ ብሰጥህና ብት ደውልልኝ. . ." ለመናገር ያሰበችው ነገር ሁሉ ተደበላለ ቀባት ።

በመሃከሉ ሱራፌል ተጠራ ። ትሩፋት ትከሻዋ ላይ ካንጠለጠለችው ቦርሳ ውስጥ ቁራጭ ወረቀት በችኮላ አወጣችና ስሟንና የስልክ ቁጥሯን ፅፋ ሰጠ ችው ። ለማነጋገር ጊዜ አልነበረውም ።

ሱራፌል ወረቀቱን ተቀበለና ግማሽ ጎኑ ላይ ያደ ረሰውን ሲጋራ ባቅራቢያው ካገኘው መኮስተሪያ ላይ ጥሎ እየሮጠ ወደ አዳራሹ ገባ ። ትሩፋትም ተከትላው ገባችና ወንበሯ ላይ ተቀምጣ በረጅሙ ተነፈሰች ።

ስትወጣም ሆነ ስትመለስ ወሰንየለህ ተመልክ ቷት ነበር ። ሰሞኑን ሲከተላት ነበር የሰነበተው ። ከትሩፋት ማዶ ካለው ቦታ ለብቻው ፊንጠር ብሎ ተቀምጧል ። ጠባቂዎቹም ቢሆኑ ለጊዜው የት እንዳሉ ፣ እነማን እንደሆኑ አይለዩ እንጂ ከሰው ጋር ተደባልቀው ሰውን መስለው በየቦታው መሰግሰጋቸው የታወቀ ነበር ።

ወሰንየለህ ፊቱን አጠገቡ ወዳለው ጠባቂ አዞረና በአይኑ ጠቀሰው ። ሰውዬው ከመቀዕበት ከተቀመጠ በት ተነሳና ፣ በሁለት እርምጃ ወሰንየለህ ዘንድ ደርሶ ጎንበስ አለና ፣ "አቤት ጌታዬ!" አለ ።

"ያቻት እዚያ ጋ ትታይሃለች? ቀይዋ. . .ፀጉረ ረጅም. . .ጉንጯን በመዳፏ የደገፈችው. . .አሁን ከዘ ፋኝ ጋር ተከታትላ የገባችው. . .አይተሃታል አይደል?. . እሷን. . .ከአዳራሹ ውጪ ሰው ይፈልግሻል በልና አው ጥተህ ጠብቀኝ ፣ እ?"

ጠባቂው ጎንበስ ብሎ እጅ ነሳና ወደ ታዘዘበት ቦታ ሄደ ።

ትሩፋት አሁንም ቢሆን ነፍሷም ፣ ስጋዋም ፣ ልቧም ፣ መንፈሷም. . .ሁለመናዋ መድረኩ ላይ ነበር — ከሱራፌል ጋር ። ለስላሳ የፍቅር ዘፈን ነበር የሚዘፍ ነው ። መናገሪያውን በሁለት እጆቹ ይዞ ክሩን ክንዶቹ ላይ እየጠመጠመ ፣ ፊቱን ወደ ጣሪያው ቀና አድርጎ ፣ አይኖቹን እንደ መጨፈን ፣ ገርበብ እንደ ማድረግ እየቃጣው ፣ የድምፅ ማጉያውን አንዴ ወደ ልቡ ፣ አንዴ ደግሞ ወደ ሆዱ እየወሰደ. . .ያንጎራጉራል ። እና ፣ ከጣ ሪያው ላይ ቁልቁል የሚበራው ቀይ ደብዛዛ ብርሃን ፊቱ ላይ ቷ ብሎ ሲያበራ. . .በቃ አንድ አይነት ምት ሃታዊ መስህብ ነበረው ።

የትሩፋት አይኖች አሁንም ሱራፌል ላይ እንደ ሙጫ ተጣብቀዋል ። አሁን ደግሞ አንገቷን ዘንበል አድርጋ የትንሿን ጣቷን ጥፍር በጥርሶቿ ትንኳክሳለች ። አይኖቿ እንባ አጥልለዋል ። ወሰንየለህ አንገቱን ያስግ ግና በሰዎች መካከል አሻግሮ ይመለከታታል ። እንደ ገና አይኖቹን ወደ መድረኩ ይመልስና ሱራፌልን ያየዋል ። ከዚያም አንጀቱ በቅናት ኩምትር ሲል ከኩር ቫዜሩ ይደጋግምለታል ።

ወሰንየለህ ትሩፋትን ለማግኘት ከዚህ ቀደም ከም ትኖርበት ሰፈር ድረስ ሄዶ ሞክሮ ነበር ። በየሰፈሩ እየዞሩ ቆንጃጅት ልጆችን መርጠው የሚያመጡለት ጠባቂዎቹም ምንም ማድረግ አልቻሉም ። ይኸው አራ ተኛ ጊዜው ፡ እዚያ ሆቴል እየተከተላት ሲመጣ ። ብቻ ዋን እንደምትመጣ ተገንዝቧል ። ከመጣችም በኋላ ከማ ንም ጋር አትጫወትም ። ዳንስ ስትጋበዝም እሺ ብላ አትነሳም ። ብቻ ከተቀመጠችበት ሆና ሱራፌልን ብቻ ማየት ነው ። ወሰንየለህ በሱራፌል ቀንቷል ። በትሩፋት ሁኔታም በሽቆ ነበር ። አሁን ግን ብሽቀት ብቻ ሳይ ሆን እልህም ይዞታል ። ማንነቱን ሳያሳያት አያርፍም ።

“ይቅርታ የእኔ እህት. . .አንድ ጊዜ ታነጋግሪኛ ለሽ?” አለ የተላከው ሰውዬ ፡ የትሩፋትን ትከሻ በጣ ቶቹ ነካ ነካ አድርጎ ። አልሰማችውም ነበር ። ደጋግሞ ነካት ። ድንገት ዞር አለችና ቀና ብላ አየችው ። ሰውዬው አጠገቧ ቆሟል ።

“እ. . .አንድ ጊዜ. . .ከአዳራሹ ውጪ ሰው ይፈል ግሻል. . .” አላት ። አልመለሰችለትም ። ፊቷን ወደ መድረኩ አዞራ ሱራፌልን ታዳምጥ ጀመር ።

“ይቅርታ. . .ል. . .ልኡል ጌታዬ ናቸው የሚፈል ጉሽ. . .” አለ ሰውዬው ። ትሩፋት ዞር ብላ አየችው ።

"ይቅርታ. . .አድርግልኝ የእኔ ወንድም. . .እኔ እዚህ ማንንም ሰው ስለማላውቅ ማንም አይፈልገኝም ። ማንንም ማግኘት አልፈልግም ። ብቻዬን ተወኝ እባ ክህ. . .ሙዚቃ ለማዳመጥ ብቻ ነው የመጣሁት" አለች ትሩፋት ፣ አይኖቿን ከመድረኩ ሳትመልስ ።

"ሰው ማግኘት አልፈልግም ትላለች ጌታዬ. . . ጤነኛም አልመሰለችኝም . . . እ. . . ብቻዬን ልሁንበት፣ ሰው አልፈልግም አለችኝ . . . እ. . . ዞር ብላ እንኳን አላየችኝም . . . ሰ. . . ሰክራ ይሆናል ማን ያውቃል. . . እንደዚህ አይነቷ ብትቀርም . . ." አለ የተላከው ሰው ፣ ወደ ወሰንየለህ ተመልሶ ።

"ብትቀርም?! ብትቀርም አልክ? . . . ከመቼ ወዲህ ነው አንተ ወሳኝ የሆንከው ? አሁን ሂድና ሰማይ ወጥ ተህ ምድር ገብተህ ውጪ እንድታመጣት . . . እኔ የም ፈልገውን ከመቼ ወዲህ ነው የምትነግረኝ ፣ እ? ግዴ ለም ፣ ስለ ሁሉም በኋላ እንነጋገራለን . . . አሁን ግን ትእ ዛዝ ነው እ ? ይገባሃል ትእዛዝ ! ሂድ አሁን ፣ አሀያ!"

ጠባቂው ደንግጦ በሰዎቹ መሃል እየተሹለከለከ ሄዶና ትሩፋት ተቀምጣ ከነበረበት ወንበር ደረሰ ። ትሩ ፋት ግን ወንበሯ ላይ አልነበረችም ።

ወሰንየለህ ከአዳራሹ ወጥቶ ከሆቴሉ በራፍ ላይ ከምትጠብቀው ጥቁር ሜርሴዲስ መኪና አጠገብ ሲደ ርስ ሹፌሩ ከጋቢና ወጣና የኋላ በሩን ከከፈተለት በኋላ መልሶ ዘጋው ። ወሰንየለህ መላ ሰውነቱን ከኋላው ወን በር ላይ ወረወረውና በረጅሙ ተነፈሰ ።

"ኩርቫዚር የጠጣሁ እለት ምን እንደሆን አላው ቅም . . . አይቀናኝም ። አይሳካም ። ልክ እንደ ናፖሌዎን

ወተርሉ ላይ የተሸነፍኩ መስሎ ነው የሚሰማኝ ። በተ ለይ ዛሬ . . . ኩርቫዜር ፣ የናፖሌዎን ኮኛክ . . . ኢኪኪ. ኪኪኪ! . . . ያ አህያ ግን ሁለተኛ እንዳይከተለኝ ደደብ! . . . ድሃ ፣ የድሃ ልጅ ፣ አህያ ! እንዴት እሷን ማምጣት ያቅተዋል ? በማን ላይ ሆንሽ እግዜርን ታሚያለሽ አሉ አባቶቻችን ! የማን ሃገር ፣ የማን ግዛት ፣ የማን ሃብት ፣ የማን ሆቴል መሰለው ፣ እ? የእኛ ነው ! የእኛ ! የእኛ ! . . . ቆይ ልክ እንደዚያ አንጋች ነው የማባርረው ! ቆይ ይንጋ ብቻ . . . የበፊቱ አንጋች ምን እንዳደረገኝ ታው ቃለህ? አንድ ቀን ፣ እ? . . . አደን ሄደን አንዲት አጋ ዘን ሃያ ሜትር ከማይሞላ ርቀት ተኩሶ ሳታት . . . ከሃያ ሜትር አጋዘን የሳተ . . . ሰው ምታ ቢሉትማ ከአ ንድ ሜትር ይስተዋል ማለት ነው! . . . ታዲያ ያን ጊዜ በሽቁ እኔው እራሴ በጀርባው ልለቅበት ነበር። ዋጋ ቢስ ነው ! . . . እና ዛሬም ያ 'ብላዲ . . .' ማነው የሚባለው ? አንዲት የማትረባ ሴት ይዞ ማምጣት አቅ ቶት ለቀቃት ። አመለጠችው ። በጣም ያሳዝናል! . . . ካሁን ወዲያ አንድ እድል እሰጠዋለሁ . . . ከዚያ በኋላ በቃ ያንን ማእረጉን ገፍፌ ነው የሰው መሳቂያ የማ ደርገው ። እኔው እራሴ ነበርኩ የሾምኩት ፣ ሰው መስ ሎኝ . . ."

ወሰንየለህ ከትሩፋት ጋር ሊያሳልፍ አስቦት የነ በረው ሌሊት የውሃ ሽታ ሆኖ በመቅረቱ እንጀቱ ተቃ ጥሏል ።

ሹፌሩ የወሰን የለህን የስካር ቁጣ ቃል እያዳመጠ መኪናዋን አስነሳና በፍል ውሃ በኩል አድርጎ ሸቅብ ነጎደ ።

ሱራፌል ብዙ ሴቶች እንደሚወዱት ያውቃል ። ብዙዎቹ አፍ አውጥተው ነግረውታል ። ምን እንደሚ

ፈልጉ ይገባዋል ። በሙያው ምክንያት ከብዙ አይነት ሰዎች ጋር ተዋውቋል ። እቺኛዋ ግን የተለየች ነበረች ፤ ትሩፋት የተለየች ነበረች ። ሁሉም ይውደዱት ፤ ያድንቁት እንጂ ሙዚቀኛ ለመሆን እንደሚፈልጉ የነገሩት አልነበሩም ። በእውነት እቺኛዋ የተለየች መሆን አለባት ። ሊረዳት እንደሚገባው እያሰላሰለ ነበር ወደ ቀጠሮው የሄደው ።

በሚቀጥለው ቅዳሜ የተገናኙትም እዚያው ሆቴል ውስጥ ነበር ። ከቀጠሮው ሰአት ቀድማ ትጠብቀው ነበር ።

"እሺ. . .ለምን ሙዚቀኛ መሆን ፈለግሽ ታዲያ?" ሰላምታ ከሰጣት በኋላ የጠየቃት የመጀመሪያው ጥያቄ ነበር ።

"እንዲሁ ነው. . . እኔ እንጃ ፤ እንዲሁ ደስ ይለኛል ። ድሮም እንደዚሁ ነበርኩ ። የሚረዳኝ ግን አላገኘሁም ። አሁን ግን አየሁ ፤ በቃ . . . ሙዚቀኛ መሆን ካልቻልኩ. . . ደስተኛ የምሆን አይመስለኝም ። እንዴት ነው ሙዚቀኛ የሚኮነው እባክህ ?"

"ይኸውልሽ . . . እኔ እንኳን ዝም ብዬ ነው የጀመርኩት ። አንድ ሰሞን ስራ የለኝም ነበር ። ከትምህርት ቤት ከወጣሁ ቆይቼ ነበር ። በፊትም ቢሆን የቀለም ትምህርት አይሆነኝም ነበር ። በኋላም እንዲሁ ዝም ብዬ በየመጠጥ ቤቱ ስዘፍን የሰሙኝ ሰዎች ለምን ዘፋኝነት አትቀጠርም ? አሉኝ ። ሄጄ ተፈተንኩ ። ፈተናውን አለፍኩ ። ከዚያም በየናይት ክለቡ ስሰራ ቆይቼ ይኸው አሁን ደግሞ እዚህ ሆቴሉ ባንድ ውስጥ ተቀጠርኩ ። "

"እሺ. . . እኔ አሁን ሙዚቀኛ መሆን ብፈልግ . . . እንዴት ነው ? ምን አድርጊ ትለኛለህ ?"

"ጥሩ ስሜትና ጥሩ ድምፅ ካለሽ . . . ምናልባት ትችዪ ይሆናል ። ወይንም መሳሪያ መለማመድ ትቺያለሽ። ይኸ ያንቺ ምርጫ ነው . . . ዝንባሌው ካለሽ ማለቴ ነው ። ዋናው ግን ፍላጎቱ ነው እየሽ . . . ሃሳብሽ ግን የሚገርም ነው ። ምናልባትም አንቺ . . . የመጀመሪያዋ ሳትሆኚ አትቀሪም ። "

"ድምፄ ቆንጆ መሆኑን ማን ይነግረኛል ? እን ዴት ነው ቆንጆ ድምፅ የሚታወቀው ?"

"የሚቀጥሩት ሰዎች ይሰሙሻል ፣ ይፈትኑሻል። ድምፅሽን ከወደዱት . . . በቃ ይቀጥሩሻል ። "

"እሺ . . . ላስቸግርህና አንተ ብታዳምጥልኝስ ፤ ማለቴ ድምፄ ለዘፈን መሆን አለመሆኑን አዳምጠህ ብትነግረኝ . . . "

"የእኔ አስተያየት እንኳን አይበቃም . . . ግን ከፈ ለግሽ ልስማሽና ልገምት እችላለሁ ። "

"አስተያየትህን ትሰጠኛለህ ፤ እዚህ ነው ታዲያ? የት ነው የምታዳምጠኝ ?"

"አይ ሌላ ቦታ ፣ እዚህ እንኳን አይመችም ። "

"እሺ የት? መቼ ይመችሃል ?"

"አንቺ እንደ ተመቸሽ . . . እ . . . ቆይ እስኪ አስ ብበታለሁ ።"

"እሺ . . . እኔ ደውዬ እነግርሃለሁ . . . ቁጥርህን ልት ሰጠኝ ትችላለህ ?"

ሱራፌል ቁጥሩን ሰጣት ። ወዲያውም ምሽቱ ተጀመረ ። ሱራፌልም ወደ መድረኩ ሄደ ። እንደ ሰሞኑ ሁሉ እዚያው ወንበሯ ላይ ሆና ታዳምጠዋለች ። ወሰንየለህ ሙዚቃው ሲሟሟቅ መጣ ።

"ዛሬ እንግዲህ እንደ ነገርኩህ ነው. . . የመጨረሻ እድል ሰጥቼሃለሁ ። ሰማይ ወጥተህ ምድር ገብተህም ቢሆን ታመጣታለህ . . . ለዘፋኙም ደግሞ ንገረው ፤ እንዴ ምንም ብለህ . . . ብትቀርብህ ይሻልሃል በለው ። መኖር ከፈለክ እሷን ልጅ ተዋት በለው ! ማን እንደ ላከህ ደግሞ ንገረው ፣ ይገባሃል? አሁን መሄድ ትችላለህ . . ." ይኸንን ነበረ ጠባቂውን ያዘዘው ፣ ወሰንየለህ ።

ጠባቂው እጅ ነስቶ ከሄደ ቆይቷል ። ያን እለትም የሰጠቺው መልስ ያው ነበር ። ቢያስፈራራትም እሺ አላለችውም ። ማንንም ለማግኘት እንደማትፈልግ ነግራው ነበር ።

እረፍት ሲሆን ነበር ጠባቂው ሱራፌልን ያገኘው። ውጪ ካስጠራው በኋላ የታዘዘውን የማስጠንቀቂያ ቃል ነግሮታል ። ማን እንዳዘዘውም በተዘዋዋሪ ጠቆም ሳያደርግ አልቀረም ነበር ። ለመልእክቱም ማጠናከሪያ ይሆነው ዘንድ ኮቱን ገለጥ አድርጎ ብብቱ ስር የታጠቀውን ነገር አሳይቶታል ።

ታዲያ ነገሩ ሱራፌልን ሳይከነክነው አልቀረም ። በማያውቃት ልጅ ፣ የማያውቃቸው ሰዎች እንዴት ያስፈራሩታል ? እሷ ነች ድምፃዊ መሆን እፈልጋለሁ ብላ የተዋወቀችው . . . ታዲያ እሱ ምን ያድርግ? ያን እለት ድምፅዋን ለመስማት እቤቱ ይዟት ሲሄድም ይኸንኑ ነበር የሚያስላስለው ። እምቢ ሊላት አልፈለገም ። ቤቱ ከወሰዳት በኋላ ነበር ሁሉን ነገር የተረዳው . . .

ሶስት ክፍል ቤት ፣ አንድ አልጋ ፣ ጥቂት ፎቴ ወን በሮች ፣ ትልቅ የሸክላ ማዘፈኛ ፣ ብዙ ሸክላዎች . . . ከሞላ ጎደል እነዚህ ነበሩ ቤቱ ውስጥ የነበሩት እቃዎች ።

ወደ ቤት እንደ ገቡ ማዘፈኛውን ነበር የከፈተው ። የራሱ ምርጫ የሆነውን ሙዚቃ እንድታዳምጥ ጋበዛት ።

"ይቅርታ . . . ሌላ ምን ላጫውትልሽ ?"

ነገረችው ። ሸክላው ማዘፈኛው ላይ ይሽከረከራል። አንደኛው ገፅ ሲያልቅ ገለበጠው ። ያም አለቀ እንደገና ሌላ ሸክላ . . .

"እሺ . . . ያንቺን ድምፅ ደግሞ እንስማዋ . . ." አለ ሱራፌል ፣ ማዘፈኛውን እያጠፋ ። ክፍሉ በፀጥታ ተዋጠ ። ለጥቂት ሴኮንዶች እሷም ዝም አለች ።

"የእኔን ድምፅ መስማት ትፈልጋለህ አይደል?" ድንገት ፀጥታውን ሰብራ ጠየቀችው ።

"እ . . . አዎን ፣ ለእሱ አይደለም እንዴ የመጣነው?"

"የእኔን ድምፅ ለመስማት?" አለች ትሩፋት በረ ጅሙ እየሳቀች ። "እውነቱን ልንገርህ? እኔ ምንም ድምፅ የለኝም . . . ማለቴ ዘፋኝ መሆን እንደማልችል አውቀዋለሁ . . . ሙዚቃ ግን . . . እውነቴን ነው ፣ በጣም እወዳለሁ ። እና ፣ ሙዚቀኛ መሆን ባልችልም . . ."

ሱራፌል ክው ብሎ ቀረ ።

"ታ . . . ታዲያ ለምን . . ." አለ ሱራፌል ድን ጋጤው መለስ እንዳለለት ።

"ቤትህ መምጣቴን አልፈለከውም ማለት ነው ?"

"እንደሱ ማለቴ ሳይሆን . . ."

"በቃ ድምፄን ለመስማት ካልሆነ ያመጣኸኝ ለምን እንደሆነ ማወቁ የአንተ ፋንታ ነው!!" አለች ትሩፋት ፣ ድንገት ጥንክር ብላ ። የቅድሟን ትሩፋት አት መስልም ነበር ።

"አልገባኝም . . . በእውነት አልገባኝም" ሱራፌል ትኩር ብሎ እያያት አንገቱን ነቀነቀ ።

"ሊገባህ ያስፈልጋል እ? . . . ለምን ይመስልሃል በሳምንት ሁለት ጊዜ እዚያ ሆቴል እየመጣሁ አፌን ከፍቼ አንተን ሳዳምጥ የማመሸው ፣ እ? ከአንድ ሰው ጋር ስጫወት አይተኸኝ ታውቃለህ ፣ እ? ከሌላ ወንድ ጋር የማልሄደው ለምን ይመስልሃል ? እስኪ አስበው . . . ደግሞስ ባለፈው ምሽት ፣ ከዚያም በፊት . . . ከተ ቀመጥኩበት እየመጡ ከመሬት ተነስተው ሲያስፈራ ሩኝ እምቢ የምለው ለማን ብዬ ይመስልሃል ? እስኪ መልስልኝ ፣ እ ? . . . "

ትሩፋት አፈጠጠችበት ። ሱራፌል ደንግጦ ያያ ታል ። ዱብ እዳ ነበር የሆነበት ።

"ማ . . . ማነው የሚያስፈራራሽ ? ለምን?" ደን ግጦ ጠየቃት ።

"እኔ ምን አውቃለሁ . . . አንድ የሆነ ሰው ነው . . . እየመጣ ሰው ይፈልግሻል ይለኛል ። እምቢ ስለው በቃ . . . ማስፈራራት ጀመረ ። ትልቅ ሰው ነው የሚፈ ልግሽ ይለኛል ። እኔ ትሩፋት . . . ለምን ንጉስ አይሆ ንም ። አልፈልግም አልፈልግም! ብቻ እሱን እርሳው... ኬር የለኝም . . . "

"ለመሆኑ ምን አለሽ?" እንደገና ጠየቃት ።

"እሱን እርሳው በቃ አልኩህ! ልማዳቸው ነው። ከእሱ ጋር ሁለተኛ የታየሽ እንደሆነ . . . ምናምን ይሉኛል ። በማስፈራራት የሚወደዱ ይመስላቸዋል ።"

"ከማን ጋር ነው እንዳትታዩ የሚሉሽ?" ሱራፌል አቋርጦ ጠየቃት ።

"ከአንተ ጋር ነዋ ! ሌላ ከማን ጋር አዩኝ?" ሱራፌል ደነገጠ ።

"ለምን ?"

"እኔ ምን አውቅላቸዋለሁ . . . . አንድ ቀን ደግሞ ምን እንዳሉኝ ታውቃለህ ?"

"እ?"

"በቅርብ ቀን ይሄ የምትኮራበት መልክሽ እንዳል ነበረ ይሆናል ፤ በሃዘን ይጨራመታል አሉኝ ። ምን ማለታቸው እንደሆነ አልገባኝም ። ለምንድነው የማዝነው? ለምንድነው መልኬ በሃዘን የሚጨራመተው ? ምን ማለታቸው ነው ? የፈለጉትን ያድርጉኝ እንጂ እኔ ትሩፋት አልፈልግም ብያለሁ አልፈልግም! እሱን እርሳውና ሱራፌል . . . ግን ወደፊት አዲስ ዘፈን ትዘፍናለህ? 'የመቃብር እጮኛዬ' ን በጣም ነው የምወዳት . . . ግን ሌላ መዝፈን አለብህ. . . ሌላ የሚያሳዝን ሳይሆን የሚያስደስት . . . የደስታ ዘፈን ።"

"ለምሳሌ . . · ስለምን ልዝፈን ? እስኪ ሃሳብ ስጪኝ" አለ ሱራፌል ።

ትሩፋት ትንሽ ስታስብ ቆየች ። ከዚያም ፈገግ ብላ እያየችውና ነገረችው ።

"ለምሳሌ . . . ለምሳሌ የአይን ፍቅር ስለ ያዛት ምስኪን ሴት . . . ዘፋኝ አይታ ስለወወደች ሴት . . .እና እሷ ወዳው እሱ ሳያውቅላት ስለምትሰቃይ ሴት . . . ይገ ባሃል አይደል ?"

"እሺ ጥሩ ሃሳብ ነው . . . . በመጨረሻስ እንዴት ይሆናሉ?" ሳቅ ብሎ ጠየቃት ። ትሩፋት ትንሽ አሰበ ችና ቀጠለች ።

"መጨረሻው ግን ያምራል . . . እንደ 'የመቃብር እጮኛዬ ' አይደለም ። ሴትየዋ ብዙ ከተሰቃየች በኋላ በመጨረሻ ማፍቀሯን ትነግረዋለች ። እሱም ያውቅ ላታል ። ከዚያ በኋላ በቃ . . . ጥሩ ፍቅረኞች ሆነው ብዙ ጊዜ አብረው ይኖራሉ ግን አይጋቡም ።"

"ጥሩ . . . ደህና ሃሳብ ነው ። ለመሆኑ ግጥም ትፅ ፊያለሽ ? ብትረጂኝ ደስ ይለኛል ። አየሽ ፣ ወደፊት ብዙ ሙዚቃ ለመድረስ አላማ አለኝ . . . የፍቅር ብቻ ሳይ ሆን ሌላም ሌላም . . . ስለ ተፈጥሮ ውበት ፣ ስለ ደግ ነት ፣ ስለ ፍቅርም ቢሆን እንደዚሁ በጠባቡ ሳይሆን . . . በስፋት በእናትና ልጅ ፣ በሰውና በተፈጥሮ ፣ በእንስሳት፣ በቤተሰብ . . . መካከል ስላለው ፍቅር . . . ስለ ክፋትና ደግነት ፣ ስለ ህይወትና ሞት ሁሉ መዝፈን እፈልጋ ለሁ . . . ስለ ክፉውም ስለ ደጉም . . . እና የሙዚቃ መሳሪያ ለማጥናትም አላማ አለኝ . . . ከዚያ በኋላ የራ ሴን የሙዚቃ ባንድ እመሰርታለሁ . . . እና ፣ ሙዚቃ ለመድረስ በቂ ጊዜ ይኖረኛል ። ነፃ ሰው እሆናለሁ . . ." አለ ሱራፌል በህልም አይነት ፣ አይኖቹን ትሩፋት ላይ ተክሎ ።

"ታዲያ እኔንም አዲሱ የሙዚቃ ባንድህ ውስጥ ታስራኛለህ ?" አለች ትሩፋት ።

"ከልብሽ ከሆነ . . . በጣም ደስ ይለኛል . . . ግን ፣ ቆይ እስኪ ማን ይመስልሻል እየተከተለ የሚያስፈራ ራሽ ?" ሱራፌል ጠየቃት ፣ እንደገና ።

"እኔ እንጃልህ! እሱን ሌላ ቀን ትጠይቃቸዋለህ . . . የእኔ ጉዳይ አይደለም . . . የእነሱ ማስፈራራት እዚያ ቦታ ከመምጣት ፣ አንተን ከማየት አያስቀረኝም . . . እንኳን በመኪና ቤቴ ድረስ እየመጡና . . . ከዚህም የበለጠ የፈለጉትን ቢያደርጉ አልቀርም . . . እሱን ተወ ውና እባክህ ስለሌላ ደስ ደስ ስለሚል ነገር አጫው ተኝ . . . እሺ የሙዚቃ ባንዱን ካቋቋምክ በኋላስ?"

"ማናቸው እነሱ?" አለ ሱራፌል ፣ ፊቱን ከስክሶ ፤ "ቤትሽም ይመጣሉ ?"

"አላውቅም አልኩህ ፣ ምናባክ! . . . ግን እኔ አን ቶን ብዬ ስለ መጣሁ አይደለም የሚያስፈራሩኝ ፣ እ? ሱራፌል . . . አዎን ፣ ምን ልበልህ . . . እምኖርበት ሰፈር ድረስ ይመጡና ሰው ልከው ያስጠሩኛል ። ማነው ስላ ቸው ፣ ጥቁር ማርቼዲስ መኪና ነው ። ይሉኛል . . . እኔ እፈራቸዋለሁ ። ማን እንደሆኑ አላውቅም ። ግን በቃ፣ እፈራቸዋለሁ . . . እኔ አልፈልግም ነው የምላቸው ። ሱራፌል ሙት እኔ ሌላ አልፈልግም . . . ምናባክ እንዴሱ ታየኛለህ? አትናገርም እንዴ ፣ እ?"

ሱራፌል ሲነሳ ሲል እጁን ጎትታ አስቀረችው ።

"ንገረኝ እንጂ ምን ይዘጋሃል ? ተደፈርኩ ብለህ መኩራትህ ነው እንዴ ? አውቃለሁ ፣ ዘፋኝ ይጠየቃል እንጂ አይጠይቅም . . . ተናገር እንጂ !" አለች እጁን የያዙትን ጣቶቿን እያላላች ።

ቀና ብላ አይኖቿን ገርበብ አድርጋ ታየዋለች ። ትኩር ብሎ አያት ። አንገቷን ወደ ጎን ሰበር አድርጋዋለች ። በግራ እጅዋ ጣቶች ፣ ከትካሻዋ አልፎ ቁልቁል የተንዘረፈፈውን የፀጉሯን ጫፍ ትቋጫለች ። እንደ ብርቱካን እምቡጥ የተፈነካከቱት ከንፈሮቿ ተሳቀው አፏ ገርበብ ብሏል ። ድንገት ሁለመናዋ ልውጥውጥ አለና . . . በቃ ፣ የውበት ጣኦት መስላ ቁጭ አለች ። ትሩፋት እንደዚያ በምትሆንበት ወቅት ማንም ወንድ ቢሆን ወኔው ፀሃይ እንደ ነካው የበረዶ እንክብል ነበር የሚሆነው ።

"በመጨረሻ . . . ተገኘህ አይደለም ?" አለች ትሩፋት ፣ እቅፉ ውስጥ ሆና ። "ታዲያ ስለዚያች ሴት መቼ ነው የምትዘፍነው ?"

"ስለየቷ?"

"በአይን ፍቅር ስለ ተሰቃየችው ሴት ።"

"ማንች እሷ ?"

"ካሁኑ ረሳሃት ? . . . ያቺ ዘፋኝ የወደደችው ሴት?"

"ሂጂ! ደረቅ! በጣም ትገርሚያለሽ ። ደረቅ ነሽ . . . ለካ የራስሽን ታሪክ ነበር . . . ደግሞ ተንኮለኛ ነሽ . . ."

"ማፍቀር ተንኮል ነው እንዴ ?"

"አይ . . . ዘዴሽን ማለቴ ነው . . . ሃሳብሽ ግን ለጥሩ የዘፈን ግጥም መንደርደሪያ ይሆናል ።"

"ሁሏም ሴት እኮ የምትፈልገውን ወንድ አፍ አውጥታ ለመጠየቅ ይከጅላታል ። ስለምትፈራ ነው እንጂ . . . ይኸኔ ስንቶቹ በልባቸው ተመኝተውህ ይሆን ? እኔ ግን ቀደምኳቸው! ብዙ ሴቶች ያስቸግሩሃል መሰለኝ ?"

"እንደሱ ሳይሆን . . . እኔ ደግሞ እውነትም አዲስ የሙዚቃ ሰው ፣ ያውም ሴት ..አገኘሁ ብዬ . . . "

"መውደድ እራሱ ሙዚቃ አይደለም እንዴ?" አለች ትሩፋት አቋርጣው ።

"ነው . . . ግን እንዳንቺ እስከዛሬ ሙዚቃ እወዳ ለሁ ፣ ሙዚቀኛ መሆን እፈልጋለሁ ብሎ የቀረበኝ ስላልገጠመኝ ነው ።"

"በቃ እኔ የመጀመሪያዋ ልሁና!"

"ግን ማን ይመስልሻል የሚያስፈራራሽ ፣ እ?"

"በቃ እሱን ተወው ፤ እርሳው አልኩህ እኮ! . . . ውሸቴን ነው በቃ ፣ እንዳልከው ለዘዴ ያደረኩትንነው። አንተን ለማግኘት ። ነገ ፕሮግራም አላችሁ አይደል? እመጣለሁ ። ምናባክ ! ነገ ከአንተ ጋር ነው የምደን ሰው ። በቃ ይወቁት ። ይለይላቸው ። እንዳታሳፍረኝ ግን እሺ ?"

"ግዴለም ከሌላ ሰውም ጋር ቢሆን ትጫወቻለሽ ።

"ለምን ? አብረን እንደሰትም ማለት ነው? እሁ ንም አልገባህም?"

"እኛ እኮ ሰውን ማስደሰት እንጂ የራሳችንን የግል ህይወት መድረክ ላይ አንኖርም . . . ችግር ነው ።"

"ለመጀመሪያ ጊዜ ከእኔ ጋር ትደንሳለህ ፣ በቃ! ከዚያም በኋላ የሚሆኑትን አያለሁ ። ምን አስፈራህ ? ያበጠው ይፈንዳ !"

ከሳምንት በኋላ ያን እለትም ወደ ሆቴሉ ስትገባ በር ላይ የጠበቃት ያው ሰውዬ ነበር ። አሁንም እንደ

ጥላዋ ይከተላታል ። በአጠገቡ ስታልፍ ክንዷን ያዛት። እሷ ግን ክንዷን በሃይል መንጭቃ አስለቀቀችና ጥላው ወደ ውስጥ ገባች ። ሃሳቧ ሁሉ ከመድረኩ ላይ ነበር— ሱራፌል ጋ ።

መድረኩ ጭር ብሏል ሙብራቶቹ ሁሉ ጠፍተዋል። አዳራሹ ውስጥ የተሰበሰበው ሰው የፕሮግራሙ ስአት መድረሱን ለማስታወስ ያጉረመርማል ። ትንሽ ቆይ ቶም የእለቱ ፕሮግራም መሰረዙ ተገለፀና ሰው ተበተነ።

የትሩፋት ልብ ብዙ ነገር ጠረጠረ ። ፕሮግራሙ ቢሰረዝስ ለምን ሱራፌል መጥቶ እንዳማያነጋግራት ፣ ለምን ቁጭ ብለው እንደማይጫወቱ ራሷን በራሷ ጠየ ቀች ። ለምን ፕሮግራሙ እንዴ ቀረ ለመጠየቅ በአይኗ ሰው ትፈልግ ጀመር ። ማንንም አላገኘችም ። በመጨረ ሻም አዳራሹ መውጫ ላይ ወዳለው የመጠጥ መሸ ጫያ ባንኮኒ ተጠጋችና አንዱን አሳላፊ ጠየቀችው— ለምን የዳንስ ምሽቱ እንደተሰረዘ . . .

"ስማ እንጂ . . ." አለ አንደኛው አሳላፊ ወደ ጓደኛው ዞር ብሎ ፤ "በሱራፌል ምክንያት ነው አይደ ለም ? የዛሬው ፕሮግራም የተሰረዘው ?"

"ሱ . . . ሱራፌል ምን ሆነ ?!" ትሩፋት ድንገት ጮኸች ። ሁለተኛው አሳላፊ ቀና ብሎ አያት ። አጭር ወፍራምና መላጣ ነው ። ትላልቅ አይኖቹን ትሩፋት ላይ ተክሎ ለጓደኛው መለሰለት ።

"ያ ሰውዬ ነው እሱ እንዲህ ያደረገው . . . ምን አይነት ጨካኝ ነው እባክህ . . . "

"ሱ . . . ሱራፌል ምን ሆነ?!" ትሩፋት እንደገና ጮሃ ጠየቀች ። የመጀመሪያው አሳላፊ ቀና ብሎ ተመ

ለከታትና ቀጠለ ። ቀጭን ረጅምና መነፅር ያደረገ ሰው ነው ።

"ማነው እሱ እባክህ ?"

"ዝም በል ፤ ስሙ አይጠራም ። ጣሪያና ግድግዳው ሁሉ ጆሮ አለው" አለ ወፍራሙ ሰውዬ ።

"ማነው እሱ እባክህ? ንገረኝ ማንም አይሰማም" አለ ባለመነፅሩ ሰውዬ ፤ ዞር ዞር ብሎ አካባቢውን በአይኖቹ እየቃኘ ።

"ል . . . ልኡሉ ነው እሱ" አለ ወፍራሙ ሰውዬ ።

"እረ ተው! ለምንድነው እባክህ?" ረጅሙ ሰውዬ ድንግጦ ጠየቀ ።

"በሴት ነው አሉ . . ." አለ መላጣው ሰውዬ ፤ በእጁ የያዘውን ብርጭቆ መደርደሪያው ላይ መልሶ እያስቀመጠ ።

"በፊት ጠብ ነበራቸው?" ባለመነፅሩ እንደገና ጠየቀ ።

"ያው በሴት ይሆናላ! ሌላ ምን ያገናኛቸዋል!"

"ልኡል ድሮም ዘፋኝ ሲባል አይወድም ነበር አሉ እባክህ ።"

"ታዲያ ለምን እዚህ እየመጣ ያመሻል?"

"ሙዚቃማ ይወዳል ። ዘፋኝ ነው የማይወደው ። ደግሞም ሴት ፍለጋ ነው ።"

"ዘፋኝ ምን አደረገው እባክህ?"

ትሩፋት ባንኮኒውን ተደግፋ እንደ በድን ቆማለች። ሁለቱ ሰዎች የሚያወሩት እሷ ስለምታውቀው ሱራፌል ሳይሆን ፣ ስለ ሌላ በስም ሞክሼ ስለሆነ ሰው ይመስል የሁለቱ ሰዎች ድምፅ ከሩቅ እንደሚመጣ የገደል ማሚቶ ሆኖ ተራ በተራ ይሰማታል ።

"እራሱ ሙዚቀኛ መሆን ይፈልግ ነበር አሉ ። ፈረንጅ ሃገር ድረስ ሄዶ ለመማር ሞክሮ ነበር አሉ ። ሙዚቀኛ ከሆነ በቃ ዝነኛ የሚሆን ፣ ሁሉ የሚወደው ይመስለው ነበር. . . ግን አልሆነለትም ። ከዚያም በቃ ዘፋኝ ይጠላ ጀመር" አለ ቀጭኑ አሳላፊ ፣ በክንዱ ባንኮኒው ላይ ተደግፎ ።

"በሽታ ነው ይኸ" አለ ወፍራሙ ሰውዬ ፣ ሌላ ብርጭቆ በደረቅ ጨርቅ እየወለወለ ።

"አዎን ትልቅ በሽታ ነው ።"

"ምን እሱ እንደሆነ ካለ ተሰጥኦ አይሆን አሉ..."

"አዎን . . . ግን እነሱ ካልሆኑላቸው ፣ በቃ ሌላው እንዲሳካለት አይፈልጉም ፤ ጠባያቸው ነው ። ተሰጥኦ ያለው ሰው አይወዱም ፣ ያጠፉታል ።"

"አዎን ፣ በምቀኝነት ብዙ ተሰጥኦ የነበራቸው ሰዎች ተበላሽተው ቀርተዋል ። የሱራፌልም እጣ ያው ሆኖ ነው . . . ምስኪን ።"

"አዎን ፣ በዚህኛው ጉዳይ ግን ሴትም አለች በት አሉ !"

"አዎን ፣ ሴቶች ዘፋኝ ይወዳሉ ። ቅንቶ ይሆናል እንዲህ ያደረገው ።"

"እውነቱን ማን ያውቃል . . . ሌላም ነገር ሊኖር በት ይችላል . . ."

"ምናልባት ነገሩ ተጣርቶ በጋዜጣ ይወጣ ይሆናል ።"

"በጋዜጣ አይወጣም ።"

"ለምን ?"

"እንደዚህ አይነቱ ነገር በጋዜጣ አይወጣም።"

"አዎን ልጄ . . . እውነትህን ነው ። ረስቼው ነው። አይወጣም ። እንዲሰማ አይፈለግም ።"

"እንዲሰማባቸው አይፈልጉም ።"

"እውነት ከሆነ ማን . . . ልኡሉ እብድ ነው ማለት ነው!"

"ድሮም እሱ ወፈፌ ቢጤ ነው አሉ ። በተለይ በሴት ለመጣ ነገር ምንም ከማድረግ አይመለስም ይላሉ። እብድ ነው . . . ብዙ ሰው ሳያበላሽ አይቀርም ።"

"ሁሉም ያው ናቸው . . . ዘራቸው በሙሉ ያው ነው . . . ከመሃላቸው አንድ ጤነኛ የለም !"

"እነሱስ እንደ ፍጥርጥራቸው . . . ይህ ምስኪን ምን አደረጋቸው ? በጣም ያሳዝናል !"

"በእውነት ያሳዝናል . . . ያልፍልኛል ብሎ ሌት ተቀን ሲሮጥ . . ."

"ከዚህ የበለጠ ምን የሚያሳዝን ነገር አለ ? ቆመውም አያምርባቸው . . . ሲሞቱም ይኸው እንዲዚህ ነው . . . እነሱ እንዲያው ለራሳቸው ሳይሆን ለሌላ ሰው የተፈጠሩ ነው የሚመስሉት ፣ ምስኪኖች ናቸው . . ."

"ለመሆኑ እንዴት ነው እሱ የሞተው ?"

"ማን አየው ብለህ ነው . . . ግማሹ በሽጉጥ ነው ይላል . . . ግማሹ እንቀውት ነው ይላል . . . ሌላው ደግሞ በመርዝ ነው ነው የሚለው ።"

"ያም ሆነ ይህ ገደሉት . . ."

"አዎን ፣ ሞተ ። ግን ጥይት ቢሆን ይሻላል ። ቶሎ ይገላግላል ። አያሰቃይም" አለ ቀጭኑ አሳላፊ ፣ ድንገት ፊቱን ወደ ጓደኛው አዙሮ ።

"መታነቅም ቢሆን ያው ነው ፣ ጊዜ አይፈጅም አንድ ደቂቃ ነች . . . ፈርገጥ ፈርገጥ . . . በቃ!" አለ ወፍራሙ ሰውዬ ፣ ጓደኛውን አንጋጦ እያየው ።

"መርዝ መጥፎ ነው" አለ ባለመነፅሩ ።

"በጣም መጥፎ ነው . . . ሳያሰቃይ አይቀርም" አለ ወፍራሙ ፣ ፊቱን ከስክሶ ።

"አዎን ፣ ያሰቃያል . . . በጣም ያሰቃያል እንጂ ፣ ምን ማለትህ ነው ?"

"ዘፋኞችን ለምንድነው የሚመርዟቸው ?"

"እኔ እንጃ! ምናልባት እንዲሰቃዩ ስለሚፈልጉ ይሆናል ።"

"አዎን ፣ እንዲሰቃዩ ይፈልጋሉ ።"

"በመጀመሪያ በቁማቸው እንዲሞቱ ነው የሚፈልጉት ።"

"ልክ ነህ . . . መጀመሪያ በቁማቸው ነው የሚገሏቸው ።"

"ለዚህ እኮ ነው ደህና ሰው እድሜ የሌለው።"

"አዎን ፤ ለዚሁ ነው . . . ደህና ሰው እድሜ የለ ውም ። ደህና ሰው አይወጣም ። ቢወጣም በእጭሩ ይቀጫል . . . በጣም ያሳዝናል ።"

"ለመሆኑ እሬሳው የት ይሆን ?" ቀጭኑ አሳላፊ ጠየቀ ።

"ያው ሆስፒታል ይሆናላ . . . ለምርመራ . . . ምናልባት ሬሳውን እንኳን ሰላም ቢሰጡት?" አለ ወፍ ራሙ አሳላፊ ። ከዚያም ሁሉቱም ዝም አሉ ።

ትንሽ ቆይቶ ቀጭኑ አሳላፊ ተደግፎ የቆመበትን ባንኮኒ ለቆ ወደ ውጪ ሄደ ። ስለ ጊዜው መምሸት ፡ ስለ ሱራፌልና አንድ ቀን እሱም እንዴት እንደሚሞት ያሰላስል ነበር ። . . .

ትሩፋት በድን የሆነውን ሰውነቷን እንደ ምንም እን ቀሳቀሰችና ወዴት እንደምትሄድ ሳታውቀው እንደ እብድ እየሮጠች ወደ ውጪ ወጣች ።

ምሽቱ በጨረቃ ብርሃን ቢታጀብም መንገዱ ዳር የተተከሉት የዘንባባ ዛፎች ጥላቸውን አካባቢው ላይ አጥልተውበት ነበር ።

ትሩፋት ሆቴሉ በር ላይ ቆመችና ግራና ቀኝ ተመ ለከተች ። አካባቢው ጭር ብሏል ። ከዚያም ድንገት ሳታ ስበው ጮኸች ፤ "ገደሉት ? ሱራፌልን ገደሉት? ሞተ ? በቃ ሞተ ማለት ነው ? እንደ ቀልድ ሞተ ማለት ነው? ለምን? ለምን ? . . ."

ድምፅዋ በአካባቢው ደጋግሞ አስተጋባ ። መልስ የሰጣት ሰው ግን አልነበረም ።

## የመጀመሪያው መሰናክል

"ስሚ . . . ዝናሽ ነው ስምሽ አይደል ? . . . አዎን፣ እንደ ጊዜው መሆን ነው ፤ እ? ጥሩ ነገር ፈልጎ ደግሞ አይናፋር ሆኖ አይሆንም ። ከሁለት አንዱን መምረጥ የግድ ነው . . . ደግሞም ባንቺ አልተጀመረም . . . የከተማ ልጅ አይደለሽም እንዴ ፣ እ? እንደዚህ መሆን ጥሩ አይደለም ። ለመሆኑ የት ነው የተማርሽው ፣ እ? ሚሲዮን ትምህርት ቤት ነው እንዴ ? . . ." ሳቅ ኮስተር፣ እንደገና ፈገግ፣ እንደገና ኮስተር እያለ ጠየቃት ።

አልመለሰችለትም ። ብቻ አንገቷን ሰብራ አውራ ጣቷን በጣቶቿ ትፈትጋለች ። ውስጥ እጅዋን አልፀ.ታል ።

"ስንት አመትሽ ነው ለመሆኑ ?"

"ሃያ አንድ" አለች ፣ በሰለለ ድምፅ ።

ስትፈራ ስትቸር ቀና ብላ አየችው ። በጨረፍታ እንኳን ስታየው ያስፈራታል ። ተመችቶት ያደገ ዱባ የሚመስለው መላጣ ጭንቅላቱ ፣ ዘወትር ከጉድጓዶቻቸው አፋፍ ላይ ብቅ ብለው የሚንከባለሉት ደም የጎረሱ አይኖቹ ፣ እንደ ቅሪላ የተነፋው ሆዱ ፣ ሁሉም ያስፈሯታል ። እንደገና አቀረቀረች ።

"ሃያ አንድ! ሃያ አንድ! ታዲያ ምን እስክትሆኚ ነው የምትጠብቂው? የአሥራ አምስትና የአስራ ስድስት አመት ልጆች ስንት ነገር በሚሰሩበት ዘመን . . . አንቺ በሃያ አንድ ሃፍረትሽን እንኳን ገና አላሸነፍሽም ልበል?

ሚሲዮኖች ጋ ነው እንዴ ያደግሽው ?” አለና ትኩር ብሎ ተመለከታት ።

አዎ አታየውም ። እንደገና ቀጠለ ።

“ስሚ አንቺ . . . እኔኮ ያቺ ማነች? ጓደኛሽ ነች ዘመድሽ ? አዎን ፣ አጥብቃ ስለለመነችኝ እና እንደ እኔ አድርገህ እያት ስላለችኝ ነው . . . በሌላ ሰው ቦታ አን ቺን እ . . . ያስገባሁት ። ምን ማለት እንደሆነ ይገባሻል፣ እ? ይኸን ደግሞ ለዘመድሽ እንዳትነግሪያት ። ስንቱ ሲለ ምነኝ እምቢ ብዬ ነው ፣ እ?”

ዝም ብላ ታዳምጠዋለች—እንዳቀረቀረች ።

“እየሽ አንቺ ገና ልጅ ነሽ ። መስሪያሽ ፣ መደሰቻሽ አሁን ነው ። እንኳን አንቺ እኛ እንኳን ገና ነን እንላ ለን ። መቼም እድሜ የአስተሳሰብ ጉዳይ ነው ፣ ፈረን ጆቹ እንደሚሉት ። እና ፣ ዋናው ነገር ደስታ ነው ። የምት ኖሪው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ሁለት ህይወት የለሽም። አዎ ፣ የዛሬ ልጆች አታገቡም እንጂ . . . አንድ ፈላስፋ አንድ ጊዜ ምን እንዳለ ታውቂያለሽ ? . . . የህይወት አላማ ሁለት ነው ። አንደኛው የምትፈልጊውን ማግ ኘት ፣ ከዚያ በኋላ መደሰት ። ግን ይላል ፈላስፋው ፣ ይቅ ርታ ስሙን ለጊዜው ዘንጋሁት . . . ግን ፣ ብልህ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው ባገኙት መደሰት የሚችሉት ።”

ብብቷንና ጆሮ ግንዷን ፣ ሁለመናዋን አልቧታል ።

ቸርነት ድንገት ወንበሩ ላይ ተሽከርክሮ ጠረጴዛው ላይ ያለውን ስልክ መናገሪያ አንስቶ ደወለ ። ከዚያም በጀርባው ወንበሩ መደገፊያ ላይ ተለጠጠ ። አይኖቹን ዝናሽ ላይ ያጉረጠርጣል ። ይኸው ነው ቸርነት ። አይቶ አይቶ አይጠግብም— ሴት ። መጀመሪያ በአይኖቹ ነው የሚልጣቸው ። ከዚያ በኋላ ሌላው ይከተላል ።

ክፍሉ ፀጥ ብሏል ። ልቧ ደረቷ ስር ሲዘል ለጆሮዋ የሚሰማት መሰላት ።

"ሃሎ ፡ ፍቅርተ ነሽ? ስሚ ፍቅርተ . . . እኛ ፡ ዘመዴ ነኝ አደራህን ብለሽ የላክሻት ልጅ . . . ምን አይነት . . . እ . . . ምን አይነት ዝምተኛ ልጅ ነች እባክሽ? ፀባይዋ ነው ወይንስ ምንድነው? ፎርማሊቲውን እን ድታሟላና . . . ስለ ስራው ሁኔታ ላነጋግራት እዚህ ቢሮዬ ነው ያለችው . . . ግን ምን ልንገርሽ? ወይ ፍን ክች ያባ ቢላዋ ልጅ . . . "

"ምን መሰለህ? ገና ልጅ ነች ፤ እና . . . "አለች ፍቅ ርተ ፡ ከወዲያኛው ጫፍ ።

"ልጅ? . . . የምን ልጅ እባክሽ ?" አለ ቸርነት ፡ ከአፏ ነጥቆ ። "የሃያ አንድ አመት ህፃን እኔ አላየሁም። ሰምቼም አላውቅ ። በዚያ ላይ የከተማ ልጅ . . ."

"ስማ እንጂ ፡ እድሜዋን ሳይሆን . . . ደግሞ ከተ ማው ገና ያልዳሰሳቸው ስንት ንፁሃን በየቤቱ አሉ መሰለህ . . . ቀልዱስ ቀልድ ነው ፡ ግን እሷ አሁን ምን ይሁን ነው የምትለው ?"

"አፋ! እሱን ተዪው እባክሽ ! . . . ፈንጣጣና ምን . . . ከሃገር ከወጣ ቆይቷል አሉ ፡ እሱን ለጊዜው ተዪ ውና . . . ለመሆን ወይንም ላለመሆን የምትፈልገውንስ ነገር መቼ ተናግራ !"

ዝናሽ ይበልጥ አላባት ። ነገሩ ሁሉ ተምታታባት ።

"እስኪ ለማንኛውም ላነጋግራት" አለች ፍቅርተ ።

ቸርነት ፊቱን ወደ ዝናሽ መለሰና ፡ “እንጋግሪኝ ትልሻለች” አለ ።

ከዚያም የስልኩን መነጋገሪያ ለዝናሽ አቀበላትና ወንበሩ መደገፊያ ላይ ተለጥጦ ትኩር ብሎ ይመለከ ታት ጀመር ።

“ሃሎ!” አለች ዝናሽ ፡ ጉሮሮዋን እያጣራች ።

“ሃሎ . . . ፍቅርተ ነኝ . . . አንቺ ዝናሽ ፡ ለመ ሆኑ ምን መሆንሽ ነው? ምን ነበር ያልኩሽ ፡ እ? ነግሬሻለሁ ፡ በገዛ እጅሽ እንጀራሽን አትዝጊው! . . . የተባልሺውን ማድረግ ነው ። የምን እንደዚህ ግግም ማለት ነው ? ይኸን የመሰለ እድል አንዴ ካመለጠሽ ሁለተኛ በእግርሽ ቀርቶ በእጅሽ ጭምር ብትሄጂ አታገኚውም ። በኋላ ፍቅርተ ምን ብላኝ ነበር እንዳትዪ፤ እ . . . ነገርኩሽ!”

“ምንድነው የምትዪኝ ? እሺ ምን ላድርግ ? ምን ድነው የሚደረገው ? የምትሉት እኮ አልገባኝም!” አለች ዝናሽ ፊቷን ከስክሳ ።

በቅድሙ የፍርሃት ላብ ፋንታ አሁን ደግሞ የን ዴት ወበቅ ተሰማት ።

“አይ የኛ ጨጨ! አጉል ፋራ አትሁኚ እባክሽ ። ለምን እንደዚህ እንደምትሆኚ ገብቶኛል . . . እሱ ግን አያዋጣሽም ። ይልቁኑ እንጀራሽን ብታበስይ ይሻ ልሽ ነበር ። ዳንኤል እንጀራ ሆኖ አይበላም ። በባዶ ሆድ ፍቅር አንቺ ታውቂያለሽ . . . በይ ለማንኛውም ማታ ቤት ብቅ በይና እንነጋገርበታለን ። እኔ ነግሬሻ ለሁ ፣ ብታስቢበት ይሻላል !” ፍቅርተ መልስ ሳትጠ

ብቅ ስልኩን ዘጋችው ። ዝናሽ መናገሪያውን አስቀምጣ ወደ ወንበሯ ተመለሰች ።

"ተነጋገራችሁ ? ነገረችሽ አይደል ? እሺ ፣ ለማን ኛውም ነገ በአራት ሰአት ተመልሰሽ ትመጪያለሽ ። ስለ ፎርማሊቲውም ሆነ ስለ ማንኛውም ጉዳይ እንነ ጋገራለን ። አስቢበት ታዲያ ፣ እ? ፍቅርተ ስላንቺ ብዙ ነገር ስላጫወተቺኝ ነው እንጂ እውነቱን ነው የም ልሽ . . . ስንት አስቀጥረን እያሉ የሚያስቸግሩኝ ሰዎች አሉ መሰለሽ ። አስቢበት ፣ እ? "አለና ቸርነት ከወንበሩ ተነስቶ ሳቅ ብሎ እጇን ዘረጋ ። በጥንቃቄ የተጠበቁት ጥርሶቹ አሞጭ ይመስላሉ ። መልኩ ጥርሱ ብቻ ነው ። ታዲያ እሱም በየአጋጣሚው ፈገግ ብሎ ጥርሶቹን ማሳ የት ያስደስተዋል ።

ቸርነት እንደ ቆመ ጨበጣት ። ለስላሳው የእጁ መዳፍ እንደ ሙጫ ያጣብቃል ። ቀና ብላ ሳታየው የቢ ሮውን በር ከፍታ ወጣች ።

"ጨረስሽ ? አለቀልሽ?" አለች የቸርነት ፀሃፊ ፈገግ ብላ ። እንደ ላስቲክ ይሳባል ፈገግታዋ ። ከፀሃፊነት ትምህርቷ ጋር የፈገግታ ኮርስ አብራ የወሰደች ትመ ስላለች ። ሰው ባየች ቁጥር ጎራዳ ፊቷ ላይ ፈገግታዋ ብርግድ ይላል ።

"ገና ነው ፤ ነገ ተመለሺ ብለውኛል ።" ይኸን ብቻ ነበር የመለሰችላት—ዝናሽ ።

ከመቼው ከህንፃው እንደ ወጣች አላወቀችውም። ነገሩን በልቧ ታብሰለስላለች ። ፀሃይዋ ደግሞ ሰማዩ ላይ ለብቻዋ ድብብቆሽ የምትጫወት ነው የምትመስለው ። አንድ ጊዜ ብልጭ ትልና ብዙም ሳትቆይ ሊወድቅ የደረሰ ቋጥኝ ከሚመስለው ጉም ጉያ ውስጥ ገብታ ትሰ

ወራለች ። ጉሙ በንፋስ እየተንሸመ ሽቅብ ሲሮጥ ፀሃይዋ እንደገና ታጮልቃለች ።

በመንገዱ ላይ ሁሉ ነገር ይተራመሳል ። ሳር ቅጠሉ፣ የወረቀት ቁርጥራጩና ቆሻሻው ፣ በመንገዱ ግራና ቀኝ የተተከሉት የጥድ ዛፎች . . . ሁሉም ድንገት ነፍስ ዘር ተው በየአቅጣጫው መሄድ የፈለጉ ይመስል ካሉበት ሆነው ይወናጨፋሉ ። በየሽቦዎች ላይ ታጥበው የተሰ ቀሉት እርጥብ ልብሶች ሳይቀሩ ክንፍ አውጥተው እንደ አሞራ ወደ ሰማይ ለመብረር ያሰቡ ይመስል ይውለበለባሉ ። ዝናሽም ተረብሻ ነበር ።

በንፋሱ የተመሰቃቀለውን ፀጉሯን በእጇዋ እያስተ ካከለች ቶሎ ቶሎ ትራመዳለች ። ፍቅርተ በስልክ ያለ ቻትን ነገር ደጋግማ ታስባለች ። ". . . ዳንኤል እንጀራ ሆኖ አይበላም . . . " ያለቻትን ። ከዚያም ስለ ቸርነት ታስባለች ። "ያስፈራራል . . . ምንድነው የሚፈልገው . . . " ልቧ ከአንጠንጧ ጡቷ ስር ሆኖ ከድሮ ይበልጥ የሚመታ ይመስላታል ። ትንሽ ተራመደችና የልቧን አካባቢ በመዳፏ ጥምስቅ አድርጋ ያዘችው ። ይበልጥ ሲነዝር ተሰማት ። ለቀቅ አደረገችውና ተነፈሰች ። መጀመሪያ በረጅሙ ፣ ከዚያም በአጭር በአጭሩ . . .

"ምን ነካኝ ዛሬ ? . . ." አለች እየተራመደች ። ከዚያም እንዴ ቀሚሷን ለመግለብ ፣ እንዴ ደግሞ አን ገቷ ላይ ሸብ ያደረገችውን ሻሽ ለማውለቅ ከሚከጅ ለው ቀዝቃዛ ነፋስ ጋር እየታገለች የመንገዱን ጠርዝ ይዛ ፣ መጣሁ ቀረሁ እያለ የሚያስፈራራውን ዝናብ እን ኳን ከቁም ነገር ሳትጥፍ እንጉብሳ ነገሩን እያሰላሰለች መራመዷን ቀጠለች ።

ዝናሽ ታስባለች ። "እንደዚህ ነው እንዴ ሰው ሁሉ ስራ የሚቀጠረው ወይንስ እኔ ብቻ ነኝ ? ምንድነው

ቀጣሪው የሚፈልገው ? ሁሉም የተቀጠረው እንደዚህ ይሆን? እኔ ምን አውቃለሁ ? ብቻ ሰውዬው በጣም ያስ ፈራል! በጣም ትልቅ ነው ። አባቴ አይሆንም ? በደንብ ይሆናል . . . ደግሞ እድሜዬን ለምን ጠየቀኝ ? የአስራ አምስት አመት ልጆች ምንድነው የሚሰሩት ?”

ከዚያም ስለ ፍቅርተ አስታወሰች ። “ፍቅርተ ደግሞ ምን ማለቷ ነው ? ለሰውየው ምን ብላ ነግራው ይሆን? ‘ዳንኤል እንጀራ ሆኖ አይበላም’ አለችኝ አይደል ? ሆሆ ፣ ዳንኤል አሁን እዚህ ውስጥ ምን አድርግ ብላ ታነሳዋለች? ምን አደረጋት ዳንኤል ? እሷም ስራ ያገኘ ችው እንደዚህ ይሆን ? ማን ያውቃል ? እኔ ግን . . . እኔ ግን የመጣው ይምጣ እንጂ ዳንኤልን በሌላ አለ ውጠውም . . . ደግሞ ሰውየው ምን እንደሚለኝ ነገ ይታያል . . . ነገሩ ግራ የሚያጋባ ነው ። ፍቅርተ ግን ለምን እንደዚህ ተቆጣቺኝ ? እሱንም ቢሆን ማታ እቤቷ ሄጄ አጣራለሁ ። አዎን ፣ ሁሉንም ነገር ማወቅ አለ ብኝ ።”

ወደ ማታ ነበር ዝናሽ ፍቅርተ ቤት የሄደችው ።

“ስሚ አንቺ ! ቅድም በስልክ ምን ለማለት ፈል ገሽ ነበር እንደዚያ የምትሆኚው እባክሽ? ዘለአለም ዳር ዳር ስትይ ከሰው በታች ሆነሽ መቅረትሽን አላወ ቅሺውም ? የድሃ ቀብራራ አንቺን አየሁ! ደግሞ ይኸ ዛሬ የምትገደረደሪበት መልክሽ ነገ ጠዋት ይጠፋና ሲቆጭሽ ይኖራል ። በጊዜ ካልሰሩበት ምን ያረጋል ? ስንቷ የዝናሽን መልክ በሰጠኝ ኖሮ ትላለች ። አንቺ ግን በእጅ የያዙት ወርቅ ሆነና በቃ . . . ኩራት ኩራት አለሽ ። እኛ እንኳን በዚችው ባለችን ስንት ሰርተንባ ታል ! እራሳችን ተጠቅመንበት ሌላውንም ጠቅመናል”

አለች ፍቅርተ ፣ ዝናሽ ገና የቤቱን ደፍ አለፍ ብላ ወደ ቤት ከመግባቷ ።

ዝናሽ ደንግጣ ከቆመችበት እንደ ምንም ተንቀሳ ቀሰችና በሩ አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠች ።

"አንቺ ምን ቸገረሽ ፤ እነዚህ የፈረደባቸው ወላጆ ችሽ ላይ ያለ ሃሳብ ተቀምጠሽ ። ስሚ ልንገርሽ ፣ እነሱም ቢሆኑ ያው አፍ አውጥተው አይናገሩሽም እንጂ እንደ ሰለቸሻቸው የታወቀ ነው ። የወለደ ሆድ ሆኖባ ቸው ነው ዝም ያሉሽ ። አሳደጉ ፣ አስተማሩ . . . . አሁን ደግሞ አንቺ የትም የትም ብለሽ እነሱን መርዳት እንጂ የምን ጉራ መቸርቸር ነው ? ምን እንደዚህ ያንቀባርር ሻል ? ነግሬሻለሁ በኋላ ይቆጭሻል ። ነገ ጠዋት እንደ በምትከሽ ትገባበትና የእግር ውስጥ እሳት ይሆንብ ሻል ። ሲያንገበግብሽ ነው የሚኖረው!" ሰላምታ እን ኳን አልሰጠቻትም—ፍቅርተ ። ዝም ብላ ወረደችባት ።

"መጀመሪያ ነገር ሰላምታ የሚቀድም መሰለኝ ። ደግሞ እኔ ቀንጆ ነኝ አላልኩም ። ድህነቴንም ቢሆን አንቺም ባትነግሪኝ አውቀዋለሁ ። ጉረኛ የሆንኩም አይ መስለኝም ። ምነካሽ ፍቅርተ? ምን አደረኩሽና እንደዚህ ትወርጂብኛለሽ ?" አለች ዝናሽ ፣ በፍቅርተ ሁኔታ እየተ ገረመች ።

"እባክሽን ዝም በይ! ቀኑን ሙሉ ስበሽቅ ነው የዋልኩት ፣ ባንቺ ሁኔታ!" አለች ፍቅርተ ፣ ሊፈርስ የደ ረሰ ጎታ የሚመስለውን ሰውነቷን ግራና ቀኝ እያወ ራጨች ። በመቃ የተነፋ የሚመስለውን እግሯን አነባ በረችና ፣ ክንዶቿን የሰንን እንቁላል ከሚያካክሉት ጡቶቿ ላይ ካጣመረቻቸው በኋላ በትናንሽ አይኖቿ ዝናሽን ትክ ብላ ተመለከተቻት ።

"ምንድነው የሚያበሽቅሽ ፍቅርተ? እኔኮ የምትሉት ነገር ሁሉ አልገባኝም ! እስኪ ግልጥልጥ አድርገሽ ንገሪኝ" አለች ዝናሽ ፡ ወንበሩ ላይ ተስተካክላ እየተቀመጠች ።

"ምኑን ነው የምነግርሽ ? አማሽውና ነው ? ተይ እባክሽ ዝናሽ" አለች ፍቅርተ ፡ የለበጣ ሳቅ እየሳቀች።

"አልገባኝም እኮ ነው የምልሽ ። ምናልባት ብታስረጂኝና ብሰማው"አለች ዝናሽ ፡ ተኮሳትራ ።

"እሺ፣ ስራ ትፈልጊያለሽ አትፈልጊም ?"

"ምን ትጠይቂኛለሽ ፍቅርተ?"

"እሺ፣ ጥሩ ፤ ስራ አግኝተሻል አላገኘሽም ?" ፍቅርተ አቋርጣ ጠየቀቻት ።

"ያገኘሁ መስሎኛል" አለች ዝናሽ ።

"እሺ፣ ስራው እንዴት እንዴ ተገኘ ታውቂያለሽ?"

"የው . . . አንቺ ነሻ ያገኘሽልኝ . . . ግን እንዴት እንዳገኘሽው አልነገርሽኝም ። "

"ጥሩ ፤ እንዴት እንዳገኘሁልሽ ብታውቂ ኖሮ ምናልባት እንደዚህ አትሆኚም ነበር ። ይኸውልሽ ፡ የሰው የው ፀሃፊ ጓደኛዬ ነች ። እና ፡ እንዴት ያለ ጥሩ ሰው እንደሆን ዘወትር ታጫውተኛለች ። እሷ እንደ ነገረችኝ ከሆነ ለተቸገረ የሚያዝን ፡ ለተጠጉት ሁሉ የሚጠቅም አይነት ነው ። ትርሲት እንዳለችኝማ በቃ ፡ ለወደደው ሰው ሌላው ቀርቶ በገዛ ፈቃዱ የደመወዝ ጭማሪ ይጠይቅላቸዋል ። መስሪያ ቤቱ ውስጥ ብዙ ተቀናቃኞች ስላሉት በቃ ፡ የሱን ስም በደግ ለ ሚያነሱ ፡ ምን ልበ

ልሽ ፣ በእሱ ወገን ለሚቆሙ ሁሉ ውለታቸውን እንደ ሚከፍል ነግራኛለች ። ታዲያ አየሽ ፣ እንደዚህ አይነት ሰው ሲገኝ መጠቀም ጥሩ ነው ። እናም ፣ በነገር ነገር ስለ ስራ ማጣት ከትርሲት ጋር ስንጫወት እግረ መን ገዴን ስለ አንቺ ነገርኳት ። እንዳጋጣሚ እሷም ልክ እንዳንቺው በፊት ስራ አጥታ የተቸገረች ስለነበረች ፣ 'ቆይ እስኪ አለቃዬ ይኸን ሰሞን ለማምጃ ቤት ሰው እንቀጥራለን ሲል ሰምቼዋለሁ ። ጠይቄ እነግርሻለሁ' አለችኝ ። እንዳለችውም ስራው ተገኘ ። ዛሬ የሄድሽው ልዮት እስኪ ትምጣ ብሏል ስለ ተባለ ነበር ። ሰውዬው ሁኔታሽን አይቶ አዝኖልሽ ፣ በማእረግ ቢሮው ውስጥ አስቀምጦ ሲያነጋግርሽ አንቺ ምን ይዘጋሻል ? ስንት አመት እንኳን የሰሩት ያንቺን እድል አላገኙም ። ዳሩ ምን ታደርጊ ፣ ምን አይነት ሰው እንደሆነ አታውቂ ውም ። ”

“መቼ ዝም አልኩት? ለጠየቀኝ ጥያቄ መልስ ሰጥቻለሁ ። በተቀር ፈርቼ ነው ። በጣም አስፈራኝ ። የመጀመሪያ ጊዜዬ ሆኖ ይሆናል ። ግን እኔ እንጃ በጣም ፈራሁት ።”

“ሰው አይደለም? ምኑ ነው የሚያስፈራው? ከስ ራው እንጂ አንቺ ከእሱ ምን አለሽ? 'የትም ፍጨውዱቄቱን አምጪው' አሉ ። ሁሉን ነገር ነግሮኛል ። አንቺ ከሄድሽ በኋላ ደውሎልኝ ነበር ። ትርሲትም ደውላልኛለች ። እና ፣ በፈጠረሽ ፣ ልጅቷን አታሳፍሪያት ። የገዛ እንጀራሽንም አትገዢ ። ወላጆችሽንም በሃሳብ አትግደያቸው ።”

“እሺ ምን አድርጊ ነው የምትዪኝ? አሁንም እኮ ግልፅ አይደለም!”

"የሚልሽን እሺ በይው ።"

"ምኑን ነው እሺ የምለው?"

"ታውቂዋለሽ!"

"አላውቀውም!"

"ለማንኛውም እሱ ይነግርሻል ። ነገ በቀጠረሽ ሰአት እንድትሄጂ ።"

"አልሄድም በቃ!"

"አትሄጂም?"

"አዎን ፣ አልሄድም!" ዝናሽ ከመቀመጫዋ ተነስታ ቆመች ።

"ለምን አትሄጂም? ቆይ ቁጭ በይ ፣ ምን አስቸኮለሽ?"

"ገብቶኛል! የሚፈልገው ገብቶኛል! እኔ ደግሞ አልፈልግም! ታውቂያለሽ. . .ዳንኤል አለ ። እሱ ባያየኝ አምላኩ ያየኛል ። እና ፣ አልችልም! ቢሆንም ባይሆንም ኮርሱን ጨርሶ እስኪመጣ መጠበቅ አለብኝ ።"

"እፉ! ምን አይነት የማይገባሽ ልጅ ነሽ? አሁን ስለ ዳንኤል ማን ጠየቀሽ? ዳንኤል ምን ይሁን አልኩሽ? 'ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ' አሉ! እኔ የምልሽ እንጀራሽን ማብሰል ትፈልጊ እንደሆነ ቀጣሪው የሚልሽን እሺ በይ ነው ። ያንቺን ዳንኤል እዚያው እንዳሻሽ አድርጊው ። የሆነ ሆኖ ቀጠሮው ቦታ እንዳትቀሪና እኔንም ቅሌት ውስጥ እንዳትጨምሪኝ ። መቆራረጫችን ነው የሚሆነው ። ሁለተኛ አይንሽን አላየውም ። ለእናትሽ መጥቼ የምነግራቸውም ይኸንኑ ነው ።"

ዝናሽ አልቆየችም ። ከቤት ወጥታ ሄደች ። ስት ወጣ ሰላምታ እንኳን አልሰጠቻትም — ለፍቅርተ ። ውጪ ስትወጣ ጨልሞ ነበር ። የመንገዱ መብራቶች በርተዋል ። አካፍቶ ነበር ። አስፋልቱ በዘይት የተወለ ወለ ይመስል ያብለጨልጫል ። የመኪናዎች መብራቶች አስፋልቱ ላይ እንደ መስታወት ተንፀባርቀዋል ። እቤቷ እስከምትደርስ ድረስ ብዙ ሃሳብ ተፈራርቆባት ነበር ።

"ልሂድ ወይንስ ልቅር?" ትላለች ዝናሽ—ሃሳቧ ለሁለት ተከፍሎ ። "ብሄድ ምን ያደርገኛል? ሄጄ የሚ ለኝን እሰማለሁ ። ምናልባት እኮ እሷ እንዳለችው ጥሩ ሰው ይሆን ይሆናል ፤ ማን ያውቃል? እንዳለችው ስለ ስራው ሊያነጋግረኝ ይሆናል ። ወይኔ! ዳንኤል እዚህ ቢሆን ኖሮ ለእሱ ነግሬው የሚሆነውን ይነግረኝ ነበር ። የሆነ ሆኖ ነገ ሄጄ የሚለኝን እሰማለሁ ። ግን ሁሉም ስራ ያገኙት እንደዚህ ይሆን? ፍቅርተም ፤ ትርሲትም ፤ ሌሎቹም? አልቀርም ። ነገ በቀጠሮው ሰአት ሄጄ የሚሆ ነውን አያለሁ ። ፍቅርተ ከፉ ነገር እንድሰራ ለምን ትገፋፋኛለች? ዳንኤል ቢሰማ ምን ይለኛል? ምስኪን ዳንኤል! እሱ ባያየኝም እኮ ሀሊናዬ እሺ አይለኝም። ቢሆንም ነገ ሄጄ ሰውዬው የሚለኝን እሰማለሁ ።"

ቤቷ እስከምትደርስ ድረስ ታስብ ነበር ። እንዴት እንደ ደረሰች አላወቀችም ። መምሸቱንም ቢሆን ልብ አላለችም ። የውጪውን የቆርቆሮ በር አንኳኳች ። ግቢው ውስጥ የታሰረው ውሻ ጮኸ ። "ማነው?" አለ አንድ ድምፅ ከቤት ውስጥ ። አባቷ ነበሩ ። የውጪው መብ ራት በራ ። ዝናሽ ደነገጠች ።

ባሻ ዘለቀ አሮጌውን የወታደር ጫማቸውን አጠ ለቁና ቤት ከመግባታቸው በፊት እግረ መንገዳቸውን

ፉት ያሏት አራት ብርሌ ጠጅ እያንሜነሜቸው ወደ ውጪ ወጡ ። "ማነው?" አሉ እንደገና በሩ ላይ ቆመው። ዝናሽ እኔ ነኝ ማለቱን እንኳን ፈርታለች ።

"ማነው እሱ?" አሉ ባሻ ዘለቀ እንደገና ። 'ችሎ ማደር' የሚሉት ውሻቸው አለቃቀሰና 'ቡፍ! ቡፍ!' አለ ፤ ጭራውን እየቆላ ። ዝናሽን በጠረኗ አውቋታል ።

"እኔ ነኝ አባዬ" አለች ዝናሽ በለሆሳስ ።

"የኔው ጉድ ነሽ? ታዲያ አፍሽን ምን ለጎመው?" አሉ አባቷ ። ዝናሽ አልመለሰችላቸውም ። በተከፈተው በር አልፋ ወደ ቤት አመራች ። አባቷ የግቢውን በር መልሰው ዘግተው ድንጋዩ እያደናቀፋቸው ወደ ቤት ገቡና የውጪውን መብራት አጠፉት ። 'ችሎ ማደርም' ወደ መኝታው ተመለሰ ።

"እሺ, የኛ ጎረምሳ ፤ ብለሽ ብለሽ ደግሞ በውድ ቅት መግባት ጀመርሽ? እንደኛሽን እዚያው አታድ ሪም ነበር ፤ ለምን መጣሽ?" አሉ አባቷ ፤ ቤቱ መሃል ምሰሶ መስለው እንደ ቆሙ ።

"ጓደኛዋ ጋ ነው ያመሸችው ፤ የት ሄዳች ብለሁ ነው? ቅድም ጠይቀሁኝ ጎረቤት ነች አላልኩትም?" አሉ እመት ይመኙሻል ። እናቷ ናቸው ። ባሻ ሲቆጡ ሁልጊዜ አስቀድመው የሚከላከሉላት እናቷ ናቸው ።

ልጃቸው የት እንደ ቆየች ባያውቁም ዘወትር ይደጋግፏታል ። "ምን አድርጊ ነው የምትሏት ? ወጣ ብላ ንፋስ እንኳን አትቀበልም እንዴ? ከጓደኞቿ ጋር አትጫወትም?" ይሸንኑ ነበር የሚሉት ።

"የዘንድሮ ጓደኛ ምን ሊያደርግላት ጓደኛ ጓደኛ ትያ ለሽ! አርፋ ቤቷ አትቀመጥም? ምን አጣችና ነው በየ

ቤቱ የምትዞረው? ያገኘነውን ተካፍለን እናድራለን ፤ አይነ ጥላዋ እስኪገለጥላት ። የምን መንቀዥቀዥ ነው!"

"ይስለቻል ፡ እንኳን ለእሷ ለእኔም ቤት መቀመጡ ይሰለቸኛል ፤ የምሄድበት የለኝም እንጂ እኔም አልቀመጥ ነበር ።"

"አብራችሁ ዞሩዋ! እሱው ነበር የቀራችሁ ።"

"እንሄዳለን! ወትሮስ እናትና ልጅ ለምን ይለያያል?"

"አብራችሁ አይደል የምትውሉት? እንዲህ ተደጋገፉ እንጂ ።"

"እንዋሳ! ምናለበት ብንውል? ለሳም ቀንደ አይከብዳትም!"

"በርቱ እንግዲህ ፤ እሷም ዶህና እንጀራዋን ዘግቶባታል ። አብራችሁ ጡረታ ትወጣላችሁ ። ኤድያ! እኔ ባሻ ዘለቀ መርሻ! እንኳን በአንድ ቀረሁ ። የምን ሴት ልጅ አባካችሁ! ከፋም ለማም ያው ወንድ ልጅ ይሻላል!"

"ጊዜያቸው ነው ። ሁሉም በጊዜው ይጫወታል ፡ ምን አድርጊ ነው የምትሏት?"

"እንቺ ደግሞ በመደጋገፋም አላወቅሽበትም ። ቀንድ እስኪታወጣልሽ ድረስ ቀሚስሽ ውስጥ አስቀምጫታ! ይኸው ነው የቀረሽ ። ስራ እንደሆነ ዘግቶባታል ። ባሉም አልተገኘም ። ወላጅ ያስተምራል ፡ ያሳድጋል እንጂ ስራና ባል አይፈልግ ።"

"ነሳ ይመኘኛል! ዛሬ ምን ከላይ ከላይ ያናግራችዋል? ምናምን ቀማምሰው ነው የመጡት መሰለኝ ። ምን እድ

ርጉ ይሉናል? ስራ መፍታት በእኔ ልጅ አልተጀመረም ። ስንቱ በየቤቱ ስራ ፈትቶ ተቀምጧል ። ደግሞም እግዜር ያለላት ቀን ትገባለች ። የገባች ጊዜ ትግባ ። አንድ ልጅ ጌጥ ነው ። የበላነውን በልታ ትኖራለች ። እንዲያውም የማታ እንጀራ ነው ጥሩ ። ባሉም እንደሆን እዚያው ቅርቅር ብሎ ይቅር!”

እናትዋ ይህን ሁሉ የሚናገሩት እንዳይከፋት ብለው እንደሆን ይገባታል ። እንደ እውነቱ ከሆን ግን የእሷን እርዳታ ይፈልጋሉ ። የባሻ ጡረታ አበል ለሶስት ሰው እንዴት ይበቃል? አልበቃ ቢላቸው አይደል ከዚያ ጋራጅ ዘበኝነት የተቀጠሩት? ለእለት ባይቸግራቸውም ገቢያቸው አስተማማኝ አይደለም ። ደግሞስ ያ ሁሉ ለወላጆቿ ተስፋ. . .ተምራ ስትጨርስ አልፎላት ታሳልፍልናለች ሲሉ የኖሩት. . .አስራ ሁለት አመት ሙሉ በተስፋ. . .አስራ ሶስተኛው አመት ላይ ንፋስ ያየው አመድ ሆኖ ሲቀር ።

ተኝታም ቢሆን ይኸንኑ ስታሰላስል ነበር በመጨረሻ እንቅልፍ የገላገላት ። እንዴት ልጅ ፣ የደከሙ ወላጆች ፣ እሩቅ ያለ ፍቅረኛ ። ስራ ተገኘ ተባለ ። ፍቅርተ ሌላ ታሪክ ታወራለች ። ቸርነትም ነገሩን በይደር አንጠልጥሎ ትቶታል ። ነገ ቀጠሮው ቦታ ትሂድ ትቅር? ለመሄድ ወስና ነበር የተኛችው ።

ዝናሽ ከቢሮው ስትደርስ ቸርነት ከሰው ጋር ነበር ። እንግዳው እስከሚወጣ ፀሃፊው ቢሮ ውስጥ ተቀመጠች ።

“እ ፣ መጣሽ? እንዴት ነው ታዲያ ፣ ዛሬ ነው ቀጠሮሽ አይደል?” አለች ትርሲት ፣ ፊገግታዋ ከንፈሮቿ ላይ እየደነሰ ።

"አዎን ፣ ዛሬ ነይ ብለውኛል" አለች ዝናሽ ።

"አዎን ፣ አየሽ አንቺ ደግሞ ዝም አትበይ ፣ አነጋግሪያቸው ። ለሚጠይቁሽ ጥያቄ በጎ በጎውን መልሺላቸው ። ቆይ እራስሽ ታይዋለሽ ። እንዴት ያሉ ጥሩ ሰው መሰሉሽ? ትንደ አለቃ አይደሉም ። ከተጠጓቸው ብዙ ይረዳሉ ። እኔ ልንገርሽ ፣ ፀባይ ካለሽ ወደፊት ትልቅ ቦታ ትደርሺያለሽ ። ትርሲት ምን ብላኝ ነበር ትያለሽ በኋላ! ደግሞ አየሽ ፣ አንቺ ገና ልጅ ነሽ ። በዚያ ላይ እውነቴን ነው ፤ መልክሽም ቢሆን ከማንም ቢበልጥ እንጂ አያንስም ። እና ፣ ተጠቀሚበት ነው የምልሽ ። በተረፈ ፍቅርተ ሁሉን ነገር ሳትነግርሽ አትቀርም ። እንግዳው ወጥተዋል ፤ በይ ግቢ ።"

ስልክ ተደወለ ። ፍቅርተ ነበረች የደወለችው ።

"ሃሎ ፣ ፍቅርተ ነሽ? ይኸው አሁን ስላንቺ ስናወራ ነው የደወልሽው ። ሲያሙ ከተፍ ። ከዚያች ልጅ ጋር ፣ ከዝናሽ ጋር እያወራን ነበር ።"

"መጣች?" አለች ፍቅርተ ። "እሱኑ ለማጣራት ነበር የደወልኩት ።"

"መጥታለች ። ልክ አሁን አንቺ ስትደውዪ እንግዳው ወጣና እሷ ገባች ።"

"ምክሪያት እባክሽ ትርሲት ፤ በኔ ሞት ምክሪያት ። እኔንማ ጠቼም እምቢ ብላኛለች ። ይኸውልሽ ማታ እቤት መጥታ ነበር ። ታዲያ ለራሷ ብዬ የሚሆን የሚሆነውን ብነግራት ደህና እደሪ እንኳን ሳትለኝ ተቆጥታ ጥላኝ ሄደች ። እንግዲያውስ ከመጣች የራሷ ጉዳይ! እኔስ ስንቱን ነገር ቀባጥሬ ፣ 'ፕሮሚስ' ገብቼለት ቀርታ ታሳፍረኛለች ብዬ ነበር የፈራሁት ። ቸርነት ካሁን ካሁን

ደውሎ ይወቅሰኛል እያልኩ ይኸው ቢሮ ከገባሁ እስካሁን ልቤ አላረፈም ። ወቀሳውንስ እችለዋለሁ ። ያቺን በዚያን ሰሞን አንድ እርከን ወደ ላይ ከፍ ትያለሽ ያለኝ ነበር ያሳሰበኝ ። እሱ እንደሆነ ፀባዩን ታውቂዋለሽ አይደል? ትንሽ ነው የሚበቃው ። ቂም ይይዛል ። የፈለገውን ካላገኘ ፍንክች አይልም ።''

''ከዚህ በላይ ምንም ማድረግ አትቺይም ። 'ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም ። ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ፤ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል' ትላለች እማዬ ስትቶርት ። እንግዲህ ፈረሱም ይኸው ፤ ሜዳውም ይኸው ። እና ፤ ቸርነት እንዳልኩሽ እኔንም ቢሆን መቆሚያ መቀመጫ ነው ያሳጣኝ ። አንቺ እንኳን ትንሽ ራቅ ትያለሽ ፤ እኔ እዚህ አጠገቡ ነኝ ። በቃ፥ ሲወጣ ሲገባ ካለሱ አይጠይቀኝም ። አሁንስ ጭንቅ ነው ያለኝ ። ካልሆነ አንዱ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት እንዳንቺው እቀየራለሁ ።''

''ምናለሽ በእኔ ሞት?''

''እሺ አስብይልኝና የማደርግልሽን አታውቂም ይለኛል ። ገና ሲያያት እብድ ነው ያለው ። አንቺ ደግሞ ምንድነው ያልሺው በኔ ሞት?''

''እ . . .እኔማ ሲያቀብጠኝ እ . . . 'ገርል' ነች ብዬ ምዬ ተገዝቼ ነገርኩት!''

''ምን ማለትሽ ነው ፍቅርተ? አንቺ ነሻ ያሳበድሽው ፤ እሱ ምን ያድርግ ታዲያ? በቃ ሰውዬው ተረብሿል ማለት ነው ። የሱን ፀባይ አውቀዋለሁ ።''

''እንግዲህ ከሆነ ሆነ ፡ ካልሆነም. . .''

"ካልሆነም ዛሬ ቁርጡ ይታወቃል ። እውነት ግን እ…እውነት 'ገርል' ነች? አለፈላት በይኛ!"

"ልጅቷን ብታያት ግግም ያለች ናት ። መንቻካ ። ወንድ በአይኔ አልይ ነው የምትለው ። እኔ እንኳን መቼም አላየኋት ፤ ያው በግምት ነው ። አንድ ዳንኤል የሚባል የሷን ቢጤ ወዳ ሌላው ወንድ ስራ የታጠቀ አይመስላትም ። ብትሞት እሺ አትልም ። ደግሞ ከቤት እግሯ ውልፍት አይልም ። ከዚህ የበለጠ ምን ማስረጃ ትፈልጊያለሽ?"

"የት ነው ያለው እሱ ፣ ልጁ?"

"አዋሳ ነው ። መምህራን ማሰልጠኛ ። ይኸውልሽ እሱ ገና ለገና አስተማሪ ሆኖ ያሳልፍልኛል ብላ ትጃ ጃልልሻለች ።"

"እንኳን እሱ እዚህ አልሆነ! ሌላውን ቸርነት ያውቅበታል ። ማግባባት እንደሆን የተካነበት ሙያው ነው ። እሷም ብትሆን ከአንገት በላይ ነው ። የኛን የቤቶ ችን ፀባይ ታውቂው የለም? በመጀመሪያ እሺ ላለማ ለት እንግደረደራለን ። በኋላ ግን ለምን አልተጠየቅ ንም ፣ ችላ ተባልን ብለን ውስጥ ውስጡን እንናደዳለን ። ከእኔ ጀምሮ ሴት ልብ የላትም እባክሽ ።"

"እቺ እንኳን ጋግርታም ቢጤ ናት ። ፈርቻታለሁ ።"

"ነገርኩሽ እኮ ፣ ከልኩ አታልፍም ። ሴት ምንጊ ዜም ሴት ናት!"

"ቻዎ በይ ለማንኛውም በኋላ እደውላለሁ ።"

"ለውጤቱ ።"

"አዎን ፣ ለውጤቱ ። 'ብራምባር' ለማለት ሂሂሂሂ ሂ!"

"ይቅናት እስኪ!" አለች ፍቅርተ ።

"ይቅናው በይ እንጂ!" አለች ትርሲት ።

"ያው ነው ። ኢሷን ከቀናት እሱንም ቀናው ማለት ነው ። አይደለም እንዴ?"

"ቻዎ በይ ትርሲት!"

"ቻዎ ፍቅርተ ፥ በኋላ እንደዋወል ።" ትርሲት መናገሪያውን ስልኩ ላይ አስቀመጠችውና ያንን ፈገግ ታዋን ብልጭ ድርግም ካደረገች በኋላ ፊቷን አጠገቧ ወዳለው ታይፕ አዞረች ።

ዝናሽ ፈረስ የሚያስጋልበውን የቸርነትን ቢሮ አቋርጣ ጠረጴዛው አጠገብ እስክትደርስ እግሮቿ እየ ተማቱባት አስቸግሯት ነበር ። ቸርነት ወንበሩ ውስጥ በጀርባው ተለጥጦ በነዚያ ዘወትር ረሃብተኛ በሆኑት አይኖቹ ከእግር እስከ እራሷ እንደገና ከእራስ እስከ እግሯ ያያታል ።

አጠገቡ ስትደርስ ከወንበሩ ተነስቶ ጨበጣት ። እጅዋ ይሞቃል። ረጃጅም ፥ ቀጫጭንና ለስላሳ ናቸው— ጣቶቿ ። ቸርነት እንደ ጨበጣት አንድ ሁለት ደቂቃ ዎች ቢቆይ ፈቃዱ ነበር ።

"ታዲያስ ፤ ደህና አደርሽ? እ…ምን ይምጣልሽ? ቡና ፥ ሻይ ፥ ለስላሳ ፥ ምናምን?" አይኖቹ አፍ ቢኖራቸው ከጉድጓዶቻቸው ወጥተው በዋጧት ነበር ።

"ደ. . .ደህና ነኝ. . .አልጠጣም ። አሁን ጠጥቻ ለሁ" አለች ዝናሽ ፥ ቀና ብላ አይታው ።

"እንቺ ደግሞ ሁሉን እምቢ ብለሽ. . .ተይ እንደ ዚህ አትሁኚ እንጂ ፥ እ? ትናንት ሁሉን ነገር ነግሬሻ ለሁ ። አይዞሽ ፥ ዘና በይ ። ምን እንዲህ ያስጨንቅሻል?"

ከዚያም ስልኩን አንስቶ ለትርሲት ደወለላት ።

"ስሚ ትርሲት . . .አንድ ቡና በወተት ፣ አንድ ኬክ . . .ለእኔ ደግሞ ቡና እዘገርልኝ ። በአስቸኳይ እ?"

እንደገና ፊቱን ወደ ዝናሽ አዞረ ።

"እና ፣ ምን ላይ ነበር ያቆምኩት? አዎን ፣ አትጨነቂ ። በህይወት ውስጥ ትልቁ ነገር የምትችይውን ያህል ደስታ ማግኘት ነው ። በየሰአቱ ፣ በየደቂቃው ፣ ቢቻልም በየሴኮንዱ ። መደሰት ከተቻለ ምናለበት? እና ፣ ዛሬ የምትሞዪው ፎርም አለ ፤ የቅጥር ፎርም ። ፎቶግራፎች ደግሞ ያስፈልጉሻል ፣ ዛሬውኑ ። እሱ እንኳን ቀላል ነው ፤ አንድ ቦታ አለ ፒያሳ ፣ በአምስት ደቂቃ ያደርሱልሻል ። ባይሆን በገንዘቡ እንረዳዳለን ። አዎን ፣ በኋላ ምሳ አብረን እንበላና ፎቶውን ትነሺያለሽ ። አዲስ ቅጥሮች ችግር እንዳለባችሁ አውቃለሁ ። ባይሆን ብድሩን ወር ላይ ትከፍያለሽ ።"

ዝናሽ በግማሽ ልቧ ነበር የምታዳምጠው ። ግማሽ ልቧ ሌላ ቦታ ነው ያለው ።

"ምሳ አብረን እንበላለን. . .አብረን ሄደን ፎቶግራፍ ትነሺያለሽ. . .ገንዘቡን እኔ እሰጥሻለሁ. . ." እነዚፀ ቃላት ነበሩ የሃሳቧን በር እያንኳኩ የሚፈታተኗት ።

"እኔ ብቻ ነኝ ወይንስ ሁሉም ሲቀጠሩ ምሳ ይጋበዛሉ? ፎቶግራፍ መነሻውንስ ገንዘብ ፣ ቀጣሪው ነው የሚሰጠው? ለምንስ አብረን እንሂድ አለኝ? ሌሎቹስ ሲቀጠሩ አብረውት ይሄዳሉ? በጣም ያስፈራሉ — አይኖቹ ። አይኖቹ በጣም ያስፈራሉ ። ለምን ደግሞ አሁንም አሁንም ያለ ምክንያት ፈገግ ፈገግ ይላል? ቅድም

ደግሞ ለምን እንደዚያ በሃይል ጨበጠኝ? ማንም ሰው እንደዚያ ጨብጦኝ አያውቅም ።”

ከዚያም ቀና ብላ አየችው ። ትኩር ብሎ እያያት የሆነ ነገር ይናገር ነበር ። እሷ ግን ምን እንደሚል በቅጡ አልሰማችውም ። አይኖቹን ለመሸሽ ያህል ብቻ በተከፈተው መስኮት ወደ ውጪ ትመለከት ጀመር ። ከተማው ከሩቅ ተንጣሎ ይታያል ። ከዚያም አረንጓዴ ሜዳ ፣ ከሜዳው ጀርባ ደግሞ በጭጋግ የተሸፈነው ተራራ ይታያል ። ሃሳቧ ከሩቅ የሚታየውን አድማስ አልፎ ሄደ ። ዳንኤል ከአድማሱ ጀርባ ሆኖ በትዝብት አይኑ የሚያያት መሰላት ። በሃሳቧም ዳንኤል ጣቱን ቀስሮ ፣ ‘ፍይ አይቼሻለሁ! ከማን ጋር ነው ቁጭ ያልሺው? ከማን ጋር ነው ምሳ የምትበዪው? ማነው ለፎቶ ግራፍ መነሻ ገንዘብ የሚከፍልልሽ? ለምን? ምን ተባብለን ነበር? ሁሉም ነገር እኔ ከመጣሁ በኋላ ይሆናል ብዬሽ አልነበረም? ስድስት ወር . .ስድስት ወር መጠበቅ አቃተሽ? አይ ዝናሽ ፣ ለካስ እንደዚህ ደካማ ልጅ ነሽ?’ የሚላት መሰላት ። ዳንኤል ሲያዝንባት በአይነ ህሊናዋ ታያት ።

ቸርነትም በበኩሉ ያስባል ። በሃሳቡ ምሳ ሊጋብዛት ይወስዳታል ። ሆቴል አይደለም ፤ በመኪናው ወደ ቤቱ ይወስዳታል ። ብቻውን ነው የሚኖረው ።

ምሳ ከበሉ በኋላ እንደ ምንም ብሎ ቢራ እንድትጠጣ ያደርጋታል ። እምቢ ካለችም ያንን ለዚሁ ብሎ ያስቀመጠውን ፣ ንሁልል ፣ ዝልፍልፍ አድርጎ ሳይታወቅ እንቅልፍ የሚያስወስደውን ኪኒን ኮካ ኮላ ውስጥ ጨምሮ ይሰጣታል ። በዚህ ዘዴው ስንቷን እምቢተኛ አሸንፏል? ይህም ካልሆነ ያስገድዳታል ፤ በቃ ። እንዴ

ያውም ማስገደዱን ይወደዋል ። ያን እለትም ባይሆን ሌላ ቀን ቀስ ብሎ ያደርገዋል ።

ታግሎ ጥሎ ፣ በጥፊ መትቶ ፣ እሱም ቢሆን ደረቱና ክንዱ በሴት ጥፍር ተቦጫጭሮ ፣ ሴቶቹም በመጨረሻ ተሸንፈው ፀጉራቸው ትራሱ ላይ ብትን ብሎ ቁና ቁና ሲተነፍሱ ፣ የሴትነት ጠረናቸው ከላባቸውና ከተቀቡት ሽቶ ጋር ተደባልቆ ሲሸተውና እያለቀሱ ሲለምኑት. . . እንደዚህ ነው ተፈጥሮው የሚወደው ።

"ቸርነት ሙት 'ገርል' ነች!" የፍቅርተ ድምፅ ጆሮው ውስጥ ደወለበት ። እናም ፣ በሃሳቡ ቀይ ነገር ታየው ። ከዚያም ፣ "ወይኔ ተበላሸሁ!" የሚል የሴት ድምፅ ጆሮው ውስጥ ደወለበት ። ከዚያም ለቅሶ. . .ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ።

"አይዞሽ ። በቃ አላወቅሁም ነበር ፤ አይዞሽ እረዳ ሻለሁ ፤ እስከ መጨረሻው አልክድሽም ፣ ፈቃድሽ ከሆ ነም በቃ. . .አገባሻለሁ. . ." ሌላም ነገር እያለ የተለ መደውን መሃላ ሲደረድር. . .ከዚያ በኋላ ቀዝቃዛ ሻወር ይወስድና ለጣለው ግዳይ መታሰቢያ ሙሉ የውስኪ ጠርሙስ ይከፍታል ።

ስልኩ ሲደውል ነበር ከቁም ራእዩ የነቃው ። መናገሪያውን መንጭቆ አንሳና ፊቱን አጨማደደ ። "ምንድነው እሱ ፣ እ? ምንድነው አሁንም አሁንም መደወል? ትናንት ፊርማ የለም? ስንት ጊዜ ነው የሚ ፈረመው?. . .አዎን ... ታዟል በቃ! መቼም ከፊርማ ጋር የእድሜ ልክ ፍቅር ነው የያዛችሁ. . .ከእንግዳ ጋር ነኝ. . .ማንም እንዳይደውል ካሁን በኋላ. . . ስራ ላይ ነው በላቸው!. . .አንተ ደግሞ ዘላለም አዲስ ትሆና ለህ!. . .ሃሎ!. . .ትርሲት. . . ከእንግዳ ጋር ነው አትያ

ቸውም እንደ፣ ምንካሽ? በቃ መልእክቱን ብቻ ተቀ በዬልኝ!"

ቸርነት መናገሪያውን ስልኩ ላይ መልሶ ወረወረ ውና ፊቱን በመዳፉ አባበሰው ።

ዝናሽ አይኖቿን ከውጪ ብትመልስም የዳንኤል ነገር ከሃሳቧ አልወጣ ብሏት ነበር ። የህሊናዋ አይኖች እፍጥጠው ያዩታል ፤ የዳንኤል ምስልም አይኖቹን እፍ ጥጦ ያያታል ።

"የምን ግብግቦ ነው ፣ እ? ከማን ጋር ነው የተቀ መጥሽው? ለምን? ምንድነው ያለሽ ቅድም? ምንድነው የሚፈልገው? የሚፈልገውን ታውቂዋለሽ? በቃ ይኸው ነው ማለት ነው ያንቺ ነገር? ምን ነበር የተባባልነው? ለስድስት ወር. . .አንቺም እንደነሱ ደካማ ነሽ ለካ!" የሚላት መሰላት—በሃሳቧ የሚታያት የዳንኤል ምስል ።

ቸርነት ያዘዘው ሁሉ መጥቶ ጠረጴዛው ላይ ተቀ ምጧል ። የቡናውን ስኒ አንስቶ ፉት አለለትና ፣ "በዶ. . . ዝናሽ. . .ጠጪ. . .ኬኩንም ብዬ ። ይቅርታ ግን ምን አይነት እንደምትፈልጊ አልጠየኩሽም" አለ ፣ ፈገግ ፈገግ እያለ ።

ዝናሽ አልመለሰችለትም ። ከፊቷ የተቀመጠውን ወተትና ኬክ ትኩር ብላ አየችውና አቅለሸለሻት ። ከዚያም ቀና ብላ ቸርነትን አየችው ። እንደገና በአይነ ህሊናዋ ዳንኤል ታያት — እንዳፈጠጠባት ።

"በ. . . በቃኝ! እ. . . አልበላም በቃኝ!. . . ል. . . ልሂድ በቃ!" አለች ፤ ድንገት እንደ አበደ ሰው ከተ ቀመጠችበት ብድግ ብላ ። ሰውነቷ ሁሉ ተለዋውጧል ። ቸርነት ደንግጦ ያያታል ። ጤነኛ አልመሰለችውም ።

"ም. . .ምነው? . . . ቁ . . . ቁጭ በይ እንጂ! . . . ም. . . ምንካሽ. . . እ?" አለና ቸርነትም ሳያስበው ከመቀ መጫው ተነስቶ ቆመ ።

ዝናሽ ሰፊውን ቢሮ እየተንደረደረች አቋረጠችና በሩን በርግዳ ከወጣች በኋላ የፀሃፊዋን ጠረጴዛ አልፋ በኮሪደሩ ላይ በፍጥነት እየተራመደች ሄደችና ከህን ፃው ወጣች ።

ከግቢው ወጥታ ስትሄድ ቸርነት በመስኮት ይመ ለከታታል ። ከዚያም እራሱን ነቅንቆ ፣ "ሜርድ! ምን አይነቷ ጋግርታም ነች? እሉ እንደዚች አይነቶች ። አልፎ አልፎ ያጋጥማል ፤ ሁልጊዜ አይሳካም ። 'ሴላቪ!' ኤእ!" በማለት እያጉተመተመ ውስጥ ውስጡን ሃፍረ ትና ብሽቀት እየተሰማው ወደ ጠረጴዛው ተመልሶ ግማሽ አካሉን ወንበሩ ውስጥ ክትት አደረገ ።

ዝናሽ የግቢውን በር አልፋ ስትሄድ ሁለመናዋን ቀለል ሲላት ተሰማት ። ዳንኤል እስኪመጣ ድረስ ትንሽ ጊዜ እንደምትቸገር ሳታውቀው አልቀረችም ። ባሻ ዘለቀም ምናምን የቀማመሱ እለት በነገር ወረፍ ወረፍ እንደሚያደርጓት ታውቀዋለች ። ቢሆንም እዳው ገብስ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ እናቷ እሉላት ። ደገፍ ደገፍ ያደርጓታል ። ዋናው ነገር ታማኝ እንደ ሆነች መቆየቷ ነበር ። የመጀመሪያውን መሰናክል አልፋለች ። ማን ያውቃል ፣ ዳንኤል ከመጣ በኋላ ህይ ወት ወደ ተሻለ አቅጣጫ ትመራ ይሆናል ። ማን ያውቃል?

መቤቴ ጌታ ትጉደኛ ፤ ከዋርካ ሥር ወደ [illegible]
ቶሎ—ድብልቅ [illegible] ያለ [illegible] ነው
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ነው ።

ዋጋው ብር 3.50